# አለም አቀፍ ከግድያ ነፃ የፖለቲካ ሳይንስ

ግሌን ዲ. ፔጅ

አለምአቀፋዊ አለመግደል ማእከል/ Center for Global Nonkilling

creative commons

ክርኤቲቭ ኮመንስ ፈቃድ/CREATIVE COMMONS LICENCE
Attribution-Noncommercial-No Derivative Works 3.0

ይህንን ስራ ለማካፈል፣ ለማባዛት፣ለማከፋፈል እናም ለማስተላለፍ ይቻላል
በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት፡

- መጥቀስ፡፡ በደራሲው ወይም በፈቃድ ሰጪው በተጠቀሰው መሰረት ይህንን ስራ መጥቀስ ይኖርቦታል (ነገር ግን የአንተን ወይም የአንተን ስራ እርዳታ በማያመላክት መልኩ መሆን ይኖርበታል)
- ለንግድ የማይውል፡፡ ይህንን ስራ ለገበያ ማዋል አይቻልም
- ከዚህ የተመረኮዘ ስራ አይቻልም፡፡ ይህን ስራ መቀየር፣ማሻሻል ወይም መሰረት አድርጎ ሌላ መፃፍ አይቻልም፡፡

* ለማንኛዉም እንደገና መጠቀም ወይም ማከፋፈል፣ የስራውን ፈቃድ መስፈርት ግልፅ ማድረግ ይገባዎታል፡፡
* ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ከባለ ኮፒ ራይት ባለቤቶቹ ፈቃድ ከተገኘ መጣስ ይችላል

ይህ ፈቃድ የፀኃፊውን የሞራል እና የህግ መብት አይነካም ወይንም አይወስንም፡፡

የዚህ ስራ አንድ እትም የወጣው በGFDL (ጂኤፍዲኤል) እና Creative Commons Attribution (ክሬቲቭ ኮመንስ አትሪቢውሽንስ) 3.0 እንደ የዊኪቨርስቲ ስኩል ኦፈ ነንኪሊንግ ስተዲስ ክፍል ይካፈላሉ፡፡(http://en.wikiversity.org/wiki/School:Nonkilling_studies)

© ግሌን ደ. ፔጅ፣ 2009
© ሴንተር ፎር ግሎባል ነን ኪሊንግ፣ 2009(ለዚህ እትም)

ISBN-13: 978-1490483931
ISBN-10: 1490483934
Printed by CreateSpace in June 2013

የትርጉሞች ዝርዝር የሚገኙት በ http://www.nonkilling.org

ካታሎጊንግ የህትመት ዳታ

Paige, Glenn D.
Nonkilling Global Political Science / Glenn D. Paige.
ISBN 978-0-9822983-0-5
1. Political science – Moral and ethical aspects.
2. Nonkilling. 3. Pacifism – Nonviolence. 4. Peace.
1. Title. II. Paige, Glenn D.

በተጨማሪም የኮንግረስ ላይብረሪ ውስጥ የካታሎግ መዝገቡ ይገኛል

Center for Global Nonkilling
3653 Tantalus Drive
Honolulu, Hawaii 96822-5033
United States of America
Email: info@nonkilling.org

ሪቻርድ ሲ. ስናይደር
1916-1997

ኤች. ሂውበርት ዊልሰን
1909-1977

የፖለቲካ ተመራማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ጓደኞች

መጀመርያ ያገኙትን ለመርሳት የሚጠራጠር ሳይንስ
እንደጠፋ ይቆጠራል።

አልፍሬድ ኖርዝ ዋይትሄድ

**ማውጫ**


| | |
|---|---|
| ማውጫ | 5 |
| መግቢያ | 6 |
| ምስጋናዎች | 8 |
| **ምዕራፍ 1** | |
| ከግድያ ነፃ ማኅበረሰብን መፍጠር ይቻላልን? | 11 |
| **ምዕራፍ 2** | |
| ከግድያ ነፃ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያሉ ብቃቶች | 24 |
| **ምዕራፍ 3** | |
| ፒለቲካ ሳይንስን የሚያመላክቱ ነገሮች | 49 |
| **ምዕራፍ 4** | |
| ችግርን መፍታት የሚያመላክታቸው ነገሮች | 66 |
| **ምእራፍ 5** | |
| ተቋማዊ ምልከታ | 82 |
| **መዕራፍ 6** | |
| ያለመግደል ዓለም አቀፍ የስነ ፖለቲካ ሳይንስ | *94* |
| ዋቢ ሰነድ 1 | 104 |
| ዋቢ ሰነድ 2 | 106 |
| ዋቢ ሰነድ 3 | 108 |
| ዋቢ ሰነድ 4 | 11 |
| ማስታወሻ | 117 |
| ማጣቀሻ | 120 |
| ማውጫ | 137 |

## መግቢያ

ይህ መጽሀፍ፣ በአለም ዙሪያ ያሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን፣ ከተማሪዎች ጀምሮ እስከ ጡረተኛ ፕሮፌሰሮች ድረስ፣ እንዲመረምሩት እና ጥልቅ አስተያየት እንዲሰጡበት የቀረበ ነው:: ግድያን ልናመልጠው የማንችለው የሰብአዊ ፍጡር ሁኔታ እንደሆነ፣ ፖለቲካዊ መላምቶች /ቲዎሪዎች/ እና ተግባሮች ሊቀበሉት ይገባል የሚለው አስተሳሰብ ላይ እድሜም ሆነ ትምህርት ለውጥ እያመጣ አይደለም:: ይሄንን አስተሳሰብ አንባቢዎች በጥያቄ ውስጥ እንደሚያስገቡት እና ግድያ ላይ የማያተኩር አለምን ለሚያጠናክር እይታ እና ድርጊት አስተዋፅኦ እያደረጉ እንደሚሄዱ ደራሲው ተስፋ ይደረጋል::

ይህ መፅሀፍ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ጊዜ በአርስቱ ውስጥ የማይገድል "Nonkilling" የሚለውን ቃል የያዘ መፅሀፍ ሊሆን ይችላል:: ቃሉ የተለመደ አይደለም:: ይህ ቃል ከ "ሰላም" እና "ጥቃትን ከማስቀረት" የበለጠ በማተኮር የሰውን ልጅ ህይወት ማጥፋት ላይ ትኩረትን ለማነጣጠር ይፈልጋል:: የአብዛኞች የመጀመሪያ ምላሽ የሚሆነው፣ ምናልባትም አለመግደል ላይ ማተኮር በጣም አሉታዊነት ያለው፣ የጠበበ እና የተሻለ ጠቀሜታ ያላቸው ነገሮች ላይ አትኩሮትን የሚቀንስ ሁኔታ እንደሆነ ሊሆን ይችላል:: እነርሱም ጋንዲ ያቀረበውን ሀሳብ፤ ማለትም - አለመግደል ላይ ያለ ትኩረት፣ ጥቃትን መቀነስ ላይ የሚኖረው አስተዋፅኦ ውስን ይሆናል የሚለውን ሀሳብ ይቀበሉ ይሆናል:: ጋንዲ «አሂምሳን» ወይም ጥቃት የለሽነትን ሲተረጉም በሀሳብ፣ በቃላትና በተግባር አለመጉዳት ብሎ ነው ያስቀምጠው::

ሆኖም ግን፣ ጋንዲም እንደ አንባቢ ተመልሶ ቢያስበው ፤ መግደል ላይ ማተኮር ሌሎች የጥቃት አይነቶችን ለማስወገድ እንደሚረዳ እና አለመግደል ላይ ለሚሰራ የፖለቲካዊ ሳይንስ ወደፊት የሚያስኬድ እርምጃ እንደሆነ ሊያምን ይችላል:: እናም ህይወትን ከሚያጠፉ ፖለቲካ፣ ህይወትን ወደ ሚያረጋግጥ ፖለቲካ መሄድ ይቻላል::

የዚህ መፅሀፍ ትኩረት አለመግደል ላይ የሚያተኩር አለምአቀፋዊ ህብረተሰብ ሊኖር እንደሚችል እና፤ ይህንንም ለማምጣት በፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት እና በማህበረሰብ ውስጥ ያለ አስተሳሰብ እና ሚና ላይ ለውጦች አስፈላጊ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው:: መግደል የማይቀር የሰው ልጅ ባህሪ ስለሆነ በፖለቲካዊ ጥናትና ተግባር ውስጥ ይሄንን መቀበል አለብን የሚለውን አስተያየት፣ ይህ መጽሀፍ ጥያቄ ውስጥ ያስገባል:: በመጀመሪያ ደረጃ እንደሚታወቀው የሰው ልጆች በተፈጥሮአቸው ወይም በተደጋጋሚ በሚማሩት ነገር ለመግደልም ሆነ ላለመግደል ብቁ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ የታየው ነገር ቢኖር፤ ምንም እንኳን የመግደል አቅም ቢኖራቸውም አብዛኛዎቹ የሰው ልጆች ነፍሰገዳዮች አይደሉም:: በሶስተኛ ደረጃ፣ ያለመግደል ችሎታዎች በተለያዩ ማህበረሰባዊ ድርጅቶች ውስጥ በአዲስ ሁኔታ ከተዋሀዱ እና ከተገሩ፣ የማይገድል ማህበረሰብን ለማምጣት የሚሰራ ስራ ላይ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ:: አራተኛ፣ አሁን ያሉ እና ወደፊት ይኖራሉ ተብለው የሚጠበቁ ነፍስ የማጥፋትን፣ ያለማጥፋትን፣ እና በመግደልና አለመግደል መሀከል ያሉ ተፈጥሮአዊ፣ ሳይኮሎጂያዊ፣ እና ማህበረሰባዊ ምክንያቶችን የሚያጠኑ ሳይንሳዊ እድገቶች፣ የማይገድልንና ለውጥን የሚያመጣ እርምጃን ለመፍጠር ይችላሉ:: አምስተኛ፣ የተነሱት ነጥቦች እንዳሉ ሆነው የሰው ልጅን የነፍሰ ገዳይነት ተፈጥሮ እንድንቀበል በፓለቲካዊ ሳይንስ እና ፖለቲካ ውስጥ መቀመጡ ሳይንሱ ከመሰረቱ ስህተት እንዳለው ያሳያል:: በስድስተኛ ደረጃ፣ ሁሉም ወደሚፈልገው በአካባቢም ሆነ አለምአቀፋዊ ህይወት ውስጥ ያለ ግድያን የማቆም ሁኔታ ላይ ለመድረስ፣ ይህንን ሀሳብ የሚቃወሙና የሰው ልጅ ግድያ ወደሌለበት ማህበረሰባዊ ለውጥ ላይ ሊደርስ አይችልም የሚሉ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች ሀሳቡን ወስደው የሚጨመሩና የሚቀነሱ ሁኔታዎችን እንዲመረምሩ ይጋብዛቸዋል:: ይህንን ሀሳብ የሚደግፉም ሆነ ሂስ የሚሰጡ ግለሰቦች የትምህርቱ እድገት ላይ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ:: የኒኩሊየር ማቆምን የሚደግፉም የሚቃወሙም ግለሰቦች የኒኩሊየር ጦርነት በአካባቢም ሆነ አለምአቀፋዊ ተጽእኖዎቹ ላይ ምርመራ እንዳደረጉ ሁሉ፣ መግደልን የሚቃወሙም ሆነ ጥቃትን የሚደግፉ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች ተባብረው ገንቢ በሆነ መልኩ ግድያ የሌለበትን አለማቀፋዊ ኑሮ ለማምጣት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን፣ ሂደቶችን እና የውሳኔዎች ውጤቶችን ሊመረምሩ ይችላሉ::

ይህ መጽሀፍ በመጀመሪያ ደረጃ ፖለቲካዊ ሳይንስን ለሚያጠኑና ለሚተገብሩ ግለሰቦች የተዘጋጀ ቢሆንም፣ የተለያዩ ሳይንሶች እና ትምህርቶች አስተዋፅኦ ካላደረጉ ግድያ የሌለበትን ማህበረሰብ እውነታ

ሆኖ ማግኘት እንደማይቻል የታወቀ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የሀርቫርድ ሶሲዎሎጂስት የሆነው ፒትሪም.ኤ.ሶሮኪን በ «ዘ ዌይስ» እና «ፓወር ኦፍ ላቭ» (1954) ስራው ራስን የማይጠቅም ፍቅር ላይ ያቀረበው መሰረት ፈንጣቂ የሆነ ሀሳብ ነው። ሌላው የደብሊው ኤች ኦ «ወርልድ ሪፖርት ኦን ቫዮለንስ ኤንድ ሄልዝ» (2002) ሲሆን፣ ይህም የሰው ልጅ ጥቃት «ልንከላከለው የምንችለው በሽታ» ነው ብሎ አስቀምጦታል። እኛ የማይገድል ተፈጥሮአዊ ሳይንስ፣ የማይገድል ማህበራዊ ሳይንስ፣ የማይገድሉ ሰብአናዎች፣ የማይገድሉ ሙያዎች፣ እና ከተለያየ የህይወት ጎዳና የመጡ የማይገድሉ ሰዎች ያስፈልጉናል። በተጨማሪም፣ አሁን ያሉም ሆነ ቀድሞ የነበሩ፣ የሰው ልጅ ችሎታዎችን ለመረዳት በተለያዩ ባህሎችና አካባቢዎች ያሉ እውቀቶችንና ልምዶች መካፈል ይኖርብናል። የሌሎችን ስሜቶች ለመረዳት፣ ተገንዝቦ እርግጠኛ ለመሆን እና ለመተግበር፣ መግደል ላይ ያላተኮረ ፖለቲካዊ ሳይንስ በሀሳብም ሆነ በተሳትፎ ደረጃ አለም አቀፋዊ መሆን አለበት።

በ 2002 ከታተመ ጀምሮ የዚህ መፅሀፍ «አለመግደል» ላይ ያተኮረ ይዘት በተለያዩ አንባቢዎች ላይ አስደናቂ የሆኑ ስሜቶችን ፈጥሯል። ለምሳሌም ሩሲያዊዉ ፖለቲካዊ ሳይንቲስት ፕሮፌሰር ዊሊያም ስመርኖቭ እንዳለው «የዚህ ልዮ መፅሀፍ መሰረታዊ ሀሳብ በ21ኛ ክፍለ ዘመን ላይ ላለው ሰብአዊ ፍጡር ተቀባይነት ያለው ሆኖ፣ እውነታቸውንም የሚቀርፅ ሊሆን ይገባል። ይችላልም።» የበፊቱ የህንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር አይ.ኬ.ጉጅራል እንዳለውም «ይህ መፅሀፍ በሁሉም የፖለቲካዊ ሳይንስ ዲፓርትመንቶች ውስጥ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሊነበብ ይገባል።»

የአንባቢዎች አስተያየትና ከሰላሳ በላይ የሆኑት የዚህ መፅሀፍ ትርጉሞች እንደሚያሳዩት፣ /15 የታተሙ ሲሆን/ አለመግደል ላይ የሚያተኩር አለምአቀፋዊ እይታ ወደፊት ሊመጣ እንደሚችል ነው።

# ምስጋናዎች

ምንም እንኳን በበቂ ሁኔታ ሊገለፅ ባይችልም፣ አሁን ያሉና በፊት የነበሩ፣ እያወቁም ሆነ ሳያውቁ አስተዋፅኦ ያደረጉ ሰዎች፣ ይህንን መጽሀፍ እውን አድርገውታል፡፡ ይሄንንም ከዚህ በታች እና በቢብሊዮግራፊው ላይ በጨረፍታ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህንን የመማር ጉዞ በጉልበታቸው ላገዙት የሀዋይ ህብረተሰቦች ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ምስጋናውም ከተለያዩ አካባቢዎች እጃቸውን በማያያዝ «ጥቃታዊ ያልሆኑ የፓለቲካ አማራጮች» ላይ የምረቃና ድህረምረቃ ትምህርቶችንና ሴሚናሮችን ከ 1978-1992 ድረስ የሰሩ የሀዋይ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና እና የዶክትሬት ጥናታቸውንም የገፉበት እንደ ፍራንሲን ብሉም፣ ቼዋት ሳታ-አናንድ፣ እና ማካፓዶ ኤ.ሙስሊም ያሉ ሰዎችን ይጨምራል፡፡

ይህንን መጽሀፍ በማቀርብበት ጊዜ የሁለት ታላላቅ የፕሪንስተን ፖለቲካ መምህራን ማለትም ሪቻርድ ሲ.ስናይደር እና ኤች.ሁበርት.ዊልሰን አስተዋፅኦ ይሰማኛል፡፡ ስናይደር ክብር የሚገባው ለሳይንስ ባለው አክብሮቱ፣ የተለያዩ ትምህርቶችን በማካተቱ፣ ፓለቲካ የተለያዩ አማራጮችን ማየት እንደሚኖርበት በመገንዘቡ፣ ትምህርት በሁሉም ደረጃ እንደሚያስፈልግ በማመኑ፣ እና የተለያየ እምነት ያላቸው ሰዎች መግባት ጠቀሜታ አንድ እምነት ቢኖራቸው ኖሮ ሊያዩት የማይችሉትን ነገር እንዳሳያቸው ማመኑ ነው፡፡ ለዊልሰን እና በሁዋላም ለጋንዲ ምስጋና የሚያስፈልገው ነፃ እና ፍትሀዊ ለሆነ ማህበረሰብ ምሳሌ ስለሆኑ፣ ስለተማሩና፣ እውነታን እንደሚያዩት አድርገው ሀሳባቸውን ለመግለፅ ዝግጁ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ፣ አንዳንድ ጊዜ ለብቻ መቆምን ሊፈጥር ይችላል፡፡

እንደሁሉም ምሁራን ሁሉ፤ ከሌሎች ምሁራን፣ ከተለያዩ የማህበረሰቡ አካባቢዎችና፣ ምንጮች ትምህርትንና መነቃቃትን አግኝቻለሁ፡፡ ከመንፈሳዊ መሪዎች ውስጥ በይበልጥ ውለታ ያደረጉልኝ አቻርያስ ቱልሲ እና ማህርጂያ፣ ራባይ ጄ ቤንትሌይ፣ ዳይሳኩ ኢኬዳ፣ ላማ ዶቡም ቱልኩ፣ ጆርጅ ዛቤልካ እና አብዱራህማን ዋህድ ይገኙበታል፡፡ ከተፈጥሮ ባዮሎጂ እና ማህበራዊ ሳይንቲስቶች መሀል ለአን ቹንግ ሲ፣ ቹንግ ዩን-ጄ፣ ጄምስ ኤ. ዴቶር፣ ጆሀን ጉልታንግ፣ ፒየሮ ጂዮርጂ፣ ሆንግ ሱንግ-ቺክ፣ ሊ ጃይ-ቦንግ፣ ብራያን ማርቲን፣ ሮናልድ ኤም.ማካርቲ፣ ብሩስ ኢ.ሞርተን፣ ኪንህይድ ሚሻኮጂ፣ ኤርሜይ ፓርኖቭ፣ ኢልያ ፕሪጎጂን፣ ኤል ቶማስ ራምሴ፣ ሪ ዩንግ-ፒል፣ ሂሮሀሩ ሴኪ፣ ዊሊያም ስመርኖቭ፣ ሌስሊ ኢ. ስፓንሴል፣ ጂን ሻርፕ፣ ራልፍ ሳሚ እና ጆን ትሬንት ይገኙበታል፡፡ ከሰብአዊ ጉዳዮች ምሁራን መካከል ኤ.ኤል ኸርማን፣ ሪቻርድ ኤል ጆንሰን፣ ቻማን ናህል፣ ጆርጅ ሳይመን፣ ታቲያና ያኩሽኩና እና ማይክል ትሩ ይገኙበታል፡፡ ከላይብረሪያን መካከል ሩት ቢንዝ እና ብሩስ ዲ. ቦናታ፤ ከፖለቲካዊ እና ማህበራዊ መሪዎች መካከል ኤም አራም፣ ኤ.ቲ.አሪያራትኔ፣ ዳኒሎ ዶልቺ፣ ግዌንፎር ኢቫንስ፣ ዋንግ ጃንግ-ዮፕ፣ ፔትራ ኬ.ኬሊ፣ ጃን ሳዳኮ ኪንግ፣ ማይሪድ ኮሪካን ማጉዋየር፣ እብዱል ሰላም አል-ማጃሊ፣ ሮናልድ ማሎን፣ ኡርሱላ ማሎን፣ አንድሬ ፔስትራና፣ ኢቫ ኩዊስትሮፕ፣ ሻይ-ጉ፣ ኢክራም ራባኒ ራና፣ ሱላክ ሲቫራስካ እና ቲ.ኬ.ኤን ኡኒታን ይገኛሉ፡፡ ከመምህራን መካከል ሆዜ ቪ አቡዬቫ፣ ኤን.ራድሀክሪሽናን፣ ጂ. ራማቻንድራን፣ ጆአኪን ኡሪያ እና ሪታ ዋልስትሮም አሉ፡፡ «አለመግደል» ላይ ስልጠና ከሚሰጡ ግለሰቦች መሀል ዳርማንዳ፣ ቻርልስ ኤል.አልፊን፣ በርናንድ ላፋዬት ጂኒየር ይገኛሉ፡፡ ከሰውነትና የመንፈስ ህክምና ባለሙያዎች መካከል ቲዬንግ. ኤች. ካም፣ ጆን አር.ሊዱክ፣ ራሞን ሎፔዝ ሬይስ፣ ሪ ዳንጊሽክ፣ ሮህ ዜንግ-ዉ እና ዌስሊ ዎንግ፡፡ ፈጠራን ከሚደግፉ ግለሰቦች መሀል ቪጃይ ኬ.ባህርዋጅ፣ ካረን ክሮስ፣ ላሪ አር.ክሮስ፣ ቫንስ ኤንግልማን፣ ሴ.ኤል ጋንዲ፣ ሉ አን ሀአሂዎ ጉዋንሰን፣ ማንፍሬድ ሄንግሰን፣ ቲዎዶር ኤል.ኸርማን፣ ዜ.ሂያን ሊዎንግ፣ አንቶኒ ጄ.ማርሴላ፣ ሪቻርድ ሞርስ፣ ሮምላ ሞርስ፣ ስኮት ማቬይ፣ ጂዶንግ ቦገስ ኦካ፣ ጃአን ታቺባና፣ ቮልዴማር ቶማስክ እና አላቫሮ ቫርጋስ ይገኙበታል፡፡

የዚህ መፅሀፍ የመጀመሪያ ድራፍትን በበጎ ፈቃደኝነት በማየትና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ አንባቢዎች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ አን ቹንግ ሲ፣ ኤ.ቲ.አራያትኔ፣ ጄምስ ማክግሬገር በርንስ፣ ቴ ሼዋት ሳታ አናንድ፣ ቫንስ ኤንግልማን፣ ጆሀን ጋልታንግ፣ ሉዊ ዣቪየር ቦቴሮ፣ አማዲዮ ኮቲኖ፣ ኤሊሳቢታ ፎርኒ፣ ሉ አን ሀአሂዎ ጉዋንሰን፣ ኬ. ኸርበርት፣ ቲዎዶር ኤል. ኸርማን፣ ሆንግ ሱንግ ቺክ፣ ኤድዋርድ ኤ.ኮሎድዚጅ፣ ሬመን ሎፔዝ ሬይስ፣ ካይክሲያ ሉ፣ ማይሬድ ኮሪጋን ማጓየር፣ ብራያን ማርቲን፣ ሜሊሳ ማሽበርን፣ ጆን ዲ. ሞንቶጎመሪ፣ ብሩስ ኢ. ሞርተን፣ ሙኒ ማሂንድራ ኩማር፣ ቪንሰንት ኬ. ፖላርድ፣ ኢልያ ፕሪጎጂን፣ ኤን. ራድሀክሪሽናን፣ ፍሬድ ደብሊው. ሪግስ፣ ጄምስ ኤ.ሮቢንሰን፣ በርተን ኤም. ሳፒን፣ ናምራታ ሻርማ፣ ጆርጅ ሲምሰን፣ ጄ.ዴቪድ ሲንገር፣ ሻንዙ ሶንግ፣

ራልፍ ሳሚ፣ ኮንስታንቲን ቲውሶቭ፣ ቮልዴማር ቶሙስክ፣ ማይክል ትሩ፣ ኤስ. ፒ. ኡዲያኩማር፣ ቲ.ኬ.ኤን ኡኒታን፣ አልቫሮ ቫርጋስ እና ቦክሱ ዛኦ ይገኙበታል። የነዚህ ግለሰቦች አስተያየቶች፣ የመፅሀፌን ፍሬ ሀሳብ ለማዳበርና፣ መፅሃፉን ወደ እውነት ለማምጣት የሚኖሩትን መደናቅፎች ለመለየት አስችሎኛል። ለእነዚህ ግለሰቦች እውቀት በቂ ምላሽ ካልተሰጠ ተጠያቂ የምሆነው እኔ ነኝ።

በፌብሩዋሪ 1999 መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ላነበበው ለጀምስ ኤ ሮቢንሰን ጥልቅ ምስጋና አቀርባለሁ። ለመጽሐፉ መግቢያ ለማዘጋጀት በጎ ፈቃደኝነቱን ላቀረበው ሪቻርድ ሲ.ስናይደር እና በዚህ የ2009 ዕትም ላይ አርታአዊ አስተያየት ላቀረቡት ለጆአም ኢቫንስ ፒም ጥልቅ ምስጋና አቀርባሁ።

ለባለቤቴ ግሌንዳ ሀትሱኮ ናይቶ ፔጅ፣ ይህንን መፅሀፍና ሌሎች ጽሑፎቼን ከ25 ዓመት በላይ በመተየብ፣ የእኔን የ"አለመግደል" እውቀት ግኝት ሂደት ከባሊ፣ ባንኮክ፣ ቤጂንግ፣ በርሊን፣ ብሪባን፣ ሂሮሽማ፣ ካራቺ፣ ለንደን፣ ሞስኮ፣ ሂውዴልሂ፣ ኒው ዮርክ (ዩኤን)፣ ፓሪስ፣ ፕሪስንስታውን፣ ፒዮንግያንግ፣ ሲኦል፣ ቶኪዮ፣ እና ኡላን ባቶር ድረስ አስተዳዳሪያዊ እና የሙያዊ ድጋፍ በማድረግ በመካፈሏ ሁሌም ምስጋና አቀርባለሁ።

የጆን ደብሊው በርገስን የ1934 «ሬሚኒሴንስስ ኦፍ አን አሜሪካን ስኮላር» ውስጥ የተወሰኑ ክፍሎችን ለማተም ፍቃድ ለሰጠኝ ለኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ምስጋና አቀርባለሁ። በኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ፈቃድ የታተመ።

# ምዕራፍ 1

## ከግድያ ነፃ ማኅበረሰብን መፍጠር ይቻላል?

*ፊሎሶፊ የሚጀምረው አንድ ሰው አጠቃላይ ጥያቄን ሲጠይቅ ነው። ሳይንስም እንደዛው።*
*በርትራንድ ራሴል*

*አንድ አገር የሚያቀርበው ጥያቄዎች የሀገሩን ፖለቲካዊ እድገት የሚያሳዩ ናቸው። ብዙ ጊዜ የአንድ ሀገር ውድቀት የሚፈጠረው ያ ሀገር ለራሱ ትክክለኛዎቹን ጥያቄዎች በማያቀረብበት ጊዜ ነው*
*ጀዋሀርላል ኔህሩ*

### አለመግደልን የሚችል ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል? ካልሆነ ለምን? ከሆነስ ለምን?

ነገር ግን "አለመግደል የሚችል ማኅበረሰብ" ስንል ምን ማለታችን ነው? ይሄ ማለት የሰብአዊ ማህበረሰብ የሆነ፣ ትልቅም ሆነ ትንሽ፣ በአንድ አካባቢ የተወሰነ፣ ወይም ዓለምአቀፍ የሆነ፣ ማንንም ግለሰብ ባለመግደል ወይም በግድያ ማስፈራራት የሌለበት፣ ምንም ግለሰቦችን ለመግደል የሚጠቅሙ ወይም መግደልን የሚደግፉ መሳሪያዎች የሌሉበት፣ እና ምንም የሚገድል ኃይልን ለለውጥና ቅያሪ የማይጠቀሙ፣ ወይም መጠቀም የማያስፈልጋቸው ሁኔታዎች ላይ ጥገኛ ያልሆኑ ማኅበረሰቦች ናቸው።

ሰዎችን መግደልም ሆነ በመግደል የማስፈራራት ሁኔታ የለም። ይህ እንስሳንና ሌሎች ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ሊጨምር ቢችልም፤ የመጨረሻ ዝቅተኛ መስፈርቱ የሰው ልጆችን አለመግደል ነው። ለመግደል ማስፈራራት የለም። እና ያለመግደሉ ሁኔታም የተፈጠረው ፍርሃትን በመፍጠር አይደለም።

ህይወትን ለመውሰድ በቂ ምክንቶችና በተጨማሪም የመግደያ መሳሪያዎች አይኖሩም። (ማለትም የሰው ልጅን ደም መፈሰስ ከሚመዘግቡ ሚውዚያምች በስተቀር)። እርግጥ ግድያን ለመፈፀም ምንም መሳሪያዎች አያስፈልጉም። እጅችና እግሮች በቂ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ይህንን ችሎታ ለመጠቀምም ሆነ ለቴክኖሎጂያዊ መንገድ ለማሳደግ ፍላጎት አይኖርም። ሃይማኖቶች መግደልን የተባረከ ተግባር አያደርጉትም። ግደሉ የሚሉ ትዕዛዞችም የሉም። መንግሥታት ሕጋዊ አያደርጉትም። ጀግንነትም መግደልን አይፈልግም። አብዮተኞችም አያዙትም። ምሁራን ለመግደል ምክንያትን አይደረድሩም። ወይም ስለመግደል ይቅርታን አይጠይቁም። አርቲስቶችም አያሞካሹትም። የሕዝብ እውቀትም አያስፋፋውም። ጠቅላላ እውቀትም ቢሆን አያመሰግነውም። በኮምፒዩተር ዘመን ቋንቋ ቢገለጽ፤ ማኅበረሰብ ለግድያ ሀርድዌሩንም ሆነ ሶፍተዌሩን አያቀርብም።

የማኅበረሰብ መዋቅር መግደል ላይ የተመረኮዘ አይደለም። ራሳቸውን ለማቆየትም ሆነ ለመቀየር መግደልንም ሆነ በግድያ ዛቻ ማስፈራራትን የሚጠይቁ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች የሉም። የመብለጥም ሆነ የማግለል ግንኙነቶች ለድጋፍም ሆነ ሌላን ለመፈተን ብለው ግድያን አይፈልጉም። ለምሳሌ፡- በገደብ፣ የመንግስት ዓይነት፣ ንብረት፣ ስርዓተ ፆታ፣ ዝርያ፣ ብሔር፣ መደብ ወይም መንፈሳዊ እና ዓለማዊ የእምነት ሥርዓቶችን። ይህ ማለት እንደዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ ውስንና ግጭት የለውም ማለት ሳይሆን፤ መዋቅሩና ሂደቶቹ መግደል ላይ የተመሰረቱ ወይም የተመረኮዙ አይደሉም ማለት ነው።

ምንም ዓይነት ሕጋዊም ሆነ ሕገወጥ የሆነ የመግደል አላማ ያላቸው ሙያዎች የሉም። ስለሆነም የማይገድል ማኅበረሰብ ውስጥ የሕይወት ባህሪ የሚታየው በሰው ልጅ አለመግደል ወይም በመግደል አለማስፈራራት ሲሆን፤ ለመግደል ምክንያቶችም ሆነ የመግደል ቴክኖሎጂዎች አይኖሩም። ማስፈራራት እና የመግደል ችሎታ ያለው ኃይል መጠቀምን የያዙ ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎችም አይኖሩም።

## ከግድያ ነፃ ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል?

*የኛን መልሶች፣ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች የሌሎችን ባህሪዎች ሊያብራሩባቸው የሚሞክሯቸው ሁኔታዎች፤ ማለትም የግል ልምድ፣ የሙያ ስልጠና፣ ባህልና ሁኔታ ይወስኑታል፡፡ ከነዚህ ተፅዕኖዎች እኛም የተላቀቅን አይደለንም*

*ለነጭራሹ ሊታሰብ የሚችል አይደለም!*

ይህ የሀያ አሜሪካዊ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች፣ በ1979 እ.ኤ.አ በናሽናል ኢንዶውምንት ፎር ዘ ሂውማኒቲስ ድጋፍ በተደረገ ሴሚናር ላይ፣ በኮሌጅ ትምህርት ውስጥ የክላሲክ ዌስተርን ፖለቲካዊ እይታን እንዲገመግሙ በተጠየቁ ጊዜ የመለሱት ምላሽ ነበር፡፡ ያኔ የተጠየቀው ጥያቄ «ኃይልና ጥቃት ያልተሞላበት ፖለቲካና ፖለቲካዊ ሳይንስ ሊኖር ይችላል?» የሚል ነበር፡፡ የዚህ ሴሚናር ላይ አራት ዋና የአሜሪካ ፖለቲካ ሳይንስ ጥናቶች እኩል ተወክለው ነበር፡፡ እነሱም የፖለቲካ ንድፈ ሃሳብ፣ የአሜሪካ አስተዳደር፣ ንፅፅራዊ ፖለቲካ እና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶች ነበሩ፡፡ ከአንዷ በስተቀር ሁሉም ምሁራን ወንዶች ነበሩ፡፡ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች የሴሚናሩን ጥያቄ በዚህ ጊዜ መልሰውታል፡፡ መጀመሪያ ደረጃ፣ የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ግድያ ፈፃሚዎች ናቸው፡፡ ሁሌ ለመግደል ዝግጁ የሆኑ አደገኛ ማኅበረሰባዊ እንስሳዎች ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ በቂ ያልሆነ ሀብት በመኖሩ ሁልጊዜም ውድድር፣ ግጭት እና ግድያ ይኖራል፡፡ ሦስተኛ፣ ሁሌም የአስገድዶ መድፈር መኖር፣ ለተደፈሩ ሴቶቹ የሚዛመዱት ወንዶች የበቀል ግድያ እንዲፈፅሙ ያደርጋቸዋል፡፡ (ተነፃፃሪ የሆነው የአሜሪካዊቷ ሴት ምላሽ አልተሰማም፡፡ "ማንም በልጄ ሕይወት ቢመጣብኝ እገለዋለሁ"፡፡ በተጨማሪም ስለማይገድል ፖለቲካ መኖር ያሉ ሀሳቦችን ዝም ያሰኘ የተለመደው የምላሽ ጥያቄ ያለመጠየቁም ነው፡፡ "ሂትለርንና ሆሎኮስትን ባለመግደል መንገድ እንዴት አድርጋችሁ ልታቆሟቸው ትችላላችሁ?") የሰው ልጆች መሠረታዊ ተፈጥሮ፣ የሀብት እጥረት፣ እና ፆታዊ ጥቃት፣ «የማይገድል ፖለቲካዊ ሳይንስ እና ተግባር ሊኖር ይችላል» የሚለውን ሀሳብ ውድቅ አደረገው፡፡ በቅርብ ወደታየው ክላሲካል ዌስተርን ፖለቲካዊ ሃሳብ መመልከትም አላስፈላጊ ነበር፡፡ ቅጣት ላይ እንደሚያተኩሩት የቻይና ሕጋዊ ባህል እና የህንድ ዘጼያዊ ኮቲሊያን ባህል ወደዛ ድምዳሜ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል፡፡ አንድን ጥሩ ማኅበረሰብ ለመፍጠርና ደህንነቱን ለመጠበቅ በቀጥታም ሆነ ውስጥ ለውስጥ ለመግደል ዝግጁ መሆን እንደአስፈላጊ ተወስዷል፡፡

በፕሌቶ (427-347 ም.ዓ) ፍፁም «ሪፐብሊክ»፣ ከተዋጊ ክፍል የተመረጡ መሪዎች ወይም ጠባቂዎች አምራቾችንና ባህሪዎችን በማስፈራራትና ኃይል ይገዛሉ፡፡ በተጨማሪም ሊዮን ሀሮልድ ክሬግ እንደሚለው "ባንድ ጎን ያላዳላ ተመልካች የፕሌቶ ሪፐብሊክ ውስጥ በሚያይበት ጊዜ፣ ጦርነት የፖለቲካዊ እና፣ የሁሉም ሕይወት አውነታ እንደሆነ እና ሁሉም ውሳኔዎች ያንን አውነታ ታሳቢ በማድረግ እንደሚፈፅሙ ማመኑ አይቀርም፡፡" (ክሬግ 1994፡17፣ ሲ.ኤፍ ሳገን 1979 ዓ.ም) በአሪስቶትል (384-322 ም.ዓ) «ፖለቲክስ»፣ ተመራጭ በሆኑ በአንድ፣ በጥቂት ወይም በብዙ ግለሰቦች በሚመሩ ግዛቶች ውስጥ፣ የሀብት ባለቤቶች መሳሪያ ሊኖራቸው ሲገባ፣ ባሪያዎችን ገዝቶ ለማቆየትና በጠላት እጅ ስር በባርነት ላለመውደቅ ጦሮች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ፕሌቶም ሆነ አሪስቶታል የሚሊታሪን ገዳይ አስፈላጊነት ከጥያቄ ውስጥ አያስገቡትም፡፡

በብዙሀን ተደናቂ የሆነው ማኪያቬሊ (1469-1527 እ.ኤ.አ) «ዘ ፕሪንስ» በሚለው ሥራው፣ መሪዎች ስልጠናዎችን ጠብቆ ለመቆየትና የክልላቸውን ክብርና እውቅና ለማስከበር መግደል እንደሚኖርባቸው ያብራራል፡፡ እንደ ቀበሮ ብልጥ ሆኖ በዘዴ መምራት የሚመረጥ ቢሆንም፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መሪዎች እንደ አንበሳ በድፍረት ለመግደል ከመሞከር መሸሽ የለባቸውም፡፡ በዚህም የሕዝብ ሚሊሻዎች የሪፐብሊካዊ ክፍሉን ጠብቆ ለማቆየት እንዲኖሩ ይመክራል፡፡ ቶማስ ሆብስ (1588-1679 እ.ኤ.አ) «ሌቪያታን» በሚለው ስራው፣ መንግስታት ማኅበረሰባዊ ሥርዓትን ለመጠበቅና በጦርነት ውስጥ አሸናፊነታቸውን ለማረጋገጥ መግደል እንደሚያስፈልጋቸው ያብራራል፡፡ ሰብአዊ ፍጡራን ነፍሰ ገዳዮች በመሆናቸው ሥርዓት የሌለው ተፈጥሯዊ ኑሮ የግድያ ቀውጢን ይፈጥራል፡፡ ነገር ግን ሰብአዊ ፍጡርን በሕይወት ለማቆየት ስለሚፈልጉ፣ አንድ ማዕከላዊ የሆነ ኃይልና ለነሱ ደኅንነት ሲባል ግድያን

ሊፈፅም የሚቻል ኃይልን ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን አለባቸው። ይህ ራሳቸውን ከጥቃት ለመከለከል ሲሉ ሊፈፅሙ የሚችሉትን ነፍስ ማጥፋት አይከለክላቸውም። ሆብስ በመሳሪያ የሚደረግ አመፅን ከመደገፍ ትንሽ ነው የራቀው።

ይህ የተደረገው በጆን ሎክ (1632-1704 እ.ኤ.አ) «ቱ ትሪቲስ ኦፍ ጋቨርመንት» በሚለው ስራው ነው። ሎክነ ፖለቲካዊ አመራር ለመግደል ዝግጁ መሆንን እንደሚጠይቅ ከኘሎቶ፣አሪስቶትል፣ ማኪያቬሊ እና ሆብስ ጋር ይስማማል። እሱ ግን በተጨማሪ የአብዬታዊ ግድያን አስፈላጊነት ያብራራል። በስልጣን ላይ ያለው ሀይል አምባገነን ሲሆንና የሰዎችን ሀብት ማግኘት፣ ነፃነት እና የህይወት ሲጥስ፣ የተጨቆኑ ዜጐች ያንን ስልጣን የማጥፋት መብትና ሀላፊነት አለባቸው። አንድ ነፍስ ገዳይ እንዲገደል እንደሚገባው ሁሉ የሲቪል ማህበረሰብ ዜጐች አምባገነናዊ መሪን ማውደም ይችላሉ።

ሆብስና ሎክ በገዢና ተገዢ መሀከል ሊኖር ስለሚገባው የመግደል ሁኔታ እንዳብራሩት፤ ካርል ማርክስ (1818-1883 እ.ኤ.አ) እና ፍሬድሪክ ኤንግልስ (1820-1895 እ.ኤ.አ) «ዘ ኮሚዉኒስት ማኒፌስቶ» ላይ ወደ ኢኮሚያዊ የመደብ ጦርነት ገፍተውበታል። ሀብት ያላቸው የማህበረሰብ መደቦች፣ ፍላጎታቸውን፣ ሊገድል የሚችል ሀይል በመጠቀም ሊጠብቁና ሊያስፋፉ ይችላሉ። ነገር ግን የቁሳቁስና የማህበረሰባዊ ግንኙነቶች አስጊ ደረጃዎች ላይ ሲደርሱ፣ የተጨቆኑ የማህበረሰብ መደቦች የማህበረሰቡን ኢኮሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስርዐት ለመቀየር በሀይል ሊነሱ ይችላሉ። ጥቂት ዘመናዊ የምርጫ ዲሞክራሲ ባለባቸው ጊዜዎች፣ ሰላማዊ ለውጥም ሊደረግ ይችላል። አንድ ጊዜ ወደፊት፣ የኢኮኖሚ ብዝበዛ ሲቆም በመደብ ላይ የተመሰረተው ገዳይ የሆነነው ክልል ይጠፋል። ነገር ግን በሽግግር ዘመን ውስጥ የኢኮኖሚ ምክንያቶች ወደግድያ ሊከቱ ይችላሉ።

ሆብስን በማስተጋባትና በሎክና ማርክስ ዘመን መሀከል በመፃፍ፣ ጃን ጃክ ሩሶ (1712-1778እ.ኤ.አ) የማህበረሰብ ውል መላምትን «ሶሻል ኮንትራክት» በሚለው ስራው በማቅረብ፣ የክልሎች ፖለቲካዊ ድርጅት መሰረት እንደሆነ ያብራራል። ዜጐች የክልሉን ህዝብ እና ሉአላዊ ግዛት ያሳያሉ። "ከአብዛኛው ፍላጎት" የወጡ ህጐችን ለሚያወጣና ለሚያስተዳድር ገዢ አካል ዜጐች ራሳቸውን ተገዢ ያደርጋሉ። በኮንትራቱ ስር ክልሉ ጦርነት የማድረግ መብቱን ያሳውቃል። አገር ከሀዲዎች እና ወንጀለኞች ሊገደሉ ይችላሉ። የገዢው አካል ዜጐች ለክልሉ ሲሉ የራሳቸውን ህይወት መስዋዕት እንዲያደርጉ ሊጠይቅ ይችላል።

> Quand le prince lui à dit: Il est expedient à l'État
> que tu mueres, il doit mourir; puisque. . . sa vie
> n'est plus seulement un bienfait de la nature,
> mais un don conditionnel de l'État.
> *Du contrat social*
> Livre II, chapitre v.

> */ገዢው ሀይል ለዜጋው ለክልሉ ብለህ መሞት አለብህ
> ሲለው መሞት አለበት ምክንያቱም... ህይወቱ ተፈጥሮ
> የለገሰቸው ብቻ ሳይሆን መንግስት ከቅድመ ሁኔታ
> ጋር የሚሰጠው ስጦታ ነው።/
> /ሶሻል ኮንትራት መፅሀፍ 11 ምዕራፍ 5/*

በመጨረሻ የሩሶ ዲሞክራሲያዊ የማህበረሰብ ኮንትራት ከግድያ ጋር የተያያዘ ነው። በ20ኛው ክፍለዘመን ማክስ ዌበር /1864-1920እ.ኤ.አ/ የተባለው ታዋቂ የጀርመን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስት እና የሶሲዎሎጂ ንድፈ ሃሳብ አውጪ በመጀመሪያ በ1918 በሙኒክ ዩኒቨርስቲ ያደረገውንና በኋላ «ፖለቲክስ አስ ቮኬሽን» ብሎ በሰየመው ስራው፣ ፖለቲካ ከአለመግደል ጋር የተያያዘ ሙያ ሊሆን ይችላል የሚለውን ሀሳብ ያጣጥላል። ለዌበር "ለፖለቲካ ወሳኙ መንገድ የሀይል ጥቃት ነው።" በታሪክ እንደታየው የበላይነት የነበራቸው ፖለቲካዊ ድርጅቶች ለስልጣን ሲሉ ከከባድ የሀይል ትግሎች ተነስተዋል። በመሆኑም ዌበር ዘመናዊ መንግስትን ወይም ክልልን ሲገልፀው "የሰብአውያን ማህበረሰብ ሆኖ *ህጋዊ የሀይል ጉልበትን በአንድ ክልል ወስጥ ለብቻው መጠቀም እንደሚችል ያወጀ*" ብሎታል።

/አፅንኦቱ በመጀመሪያው እትም የሚገኝ/ ስለዚህ "የራሱንና የሌሎችን ነፍስን ለማዳን የሚሞክር ሰው፣ በፖለቲካ ጉዳና ውስጥ ያንን መፈለግ እንደሌለበትና የተለያዩ የፖለቲካዊ ስራዎች መፍትሄ የሚያገኙ ብት ብቸኛ መንገድ በሀይል ጥቃት እንደሆነ ነው።" /አፅንኦት የተጨመረ/ /ዌበር 1958:121, 78, 126/

ስለዚህ፣ በዌበሪያን ባህል እና የፍልስፍና ተከታዬቹ የሰለጠኑ ኘሮፌሰሮች፣ አለመግደልን መሰረት ያደረገ ፖለቲካና ፖለቲካዊ ሳይንስ "መታሰብ አይችልም" ቢሉ መረዳት አይከብድም። የዚህ መሰረት የሆነው አስተያየት አንድ ብዙ ልምድ ባለው አሜሪካዊ ፖለቲካዊ ሳይንቲስት ለአንድ ወጣት ምሁር በ1950ዎቹ ውስጥ የ"ፖለቲካ" ትርጉም ብሉ ባቀረበለት መልስ በአጭሩ ይታያል። ፒፓዉን እየማገ የመለስለት"እኔ የማጠናው ከሞት ጋር የሚገናኘውን የመንግስትን ሀይል ነው።"

በተጨማሪም ገዳይ የሆነው የፍልስፍና ባህል ጥቃትን በሚቀበል ሀይማኖት ተደግፎ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲካዊ ታሪክ እና ባህል ውስጥ እያስተጋባ፣ የዜጐችና ምሁሮችን አለመግደል የሚችል ማህበረሰብ እንደሌለ ያላቸውን እምነት ያጠናክራል። እነዚህ የሚሰሙት፣ የአሜሪካን አብዬት በቀሰቀሱት በሌክሲንግተን የተሰጡ የጠመንጃ ጩኸቶች፣ ለዲክላሬሽን ኦፍ ኢንዲፔንደንስ ያነሳሱት የሚደውሉ ሎኪያን ማብራሪያዎች፣ እና በኒው ሀምኘሻየር ለተሰማው ተቋውማዊ ጩኸት "በነፃነት መኖር ወይም መሞት!" በሚሉት ነው። "ከሪፐብሊኩ የጦርነት መዝሙር" ተሰምተዋል። ይህም ዩኒየኑ የኮንፌደሬት ተቋዋሚዎችን እንዲያሸንፉ አነሳስቷል።

በተጨማሪም"በዲክሲ" የቆየ የተቃውሞ ዘፈን፣ እና የሩቅ የመሬትና የባህር ላይ ጦርነቶቹን የሚያወድስ "የሜይን ዘፈን" ላይ ተሰምተዋል።ኘሬዚደንቱ መሪ ተብሎ ሲሰየም በሚያስተጋቡት ሀያ አንድ የመድፍ ጩኸቶች፣ የአገሪቱን ጦርነት የተሞላበት ታሪክና ያለውን የጦር ሀይል በማስታወስ ያስተጋባል። በህይወት ዘመን ውስጥ በተለያዩ አከባበሮች ማለትም በባንዲራ፣ የብሔራዊ መዝሙር፣ በመሳሪያ በማጀብ፣ የግድያና ራስን የመሰዋት ስሜቶችን በመፍጠር፣ እና ኘሬዚደንቱ በሚናገረው "እግዚአብሔር አሜሪካን ይባርክ" በሚለው አባባል የተቀደሰ ተደርጐ ይቀርባል። /ትዌይን 1970/[1]

መግደል ለዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ መመስረት፣ ግዛትን ማስፋፋት፣ ብሔራዊ ጥንካሬ፣ እና አለምአቀፋዊ ደረጃ ሀይል ማሳየት ላይ አስተዋፅኦ አድርጓል። በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ፣ ከተራው ሕዝብም ሆነ ጦር ሰራዊት ውስጥ የሞቱትና የቆሰሉት አይታወቁም፤ ወይም ምናልባት መደመር አይችሉም። ነገር ግን የአሜሪካ መንግስት ከሞት ጋር መያያዝ አጠያያቂ አይደለም። በሌሎች አገሮች ያሉ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶችም፣ የራሳቸው ፖለቲካዊ ማንነት ላይ፣ ብዙ ወይም አነስተኛ የግድያ መጠን ያለውን አስተዋፅኦ እንዲያደጠኑ ይጋበዛሉ።

አዲሱ አገር ከቅኝ አገዛዛዊ የዘውድ አገዛዝ ላይ በነበረው የሪፐብሊካኖች የመሳሪያ ጦርነት የጀመረ ሲሆን፣ ባሪያዎችን ግን በጭቆና ስር አቆይቷል። ከነፃነት አርማ ስር የአገሩን የመጀመሪያ ነዋሪዎች በደም መፋሰስ እያስለቀቀ፣ በደቡብና ሰሜን ጐረቤቶቹን በጉልበት እየገፋ እና፣ ከመዋጋት ይልቅ መሸጥ ከመረጡት እየገዛ አህጉራዊ መጠኑን አስፍቷል። መንግስቱ የሀገራዊ አንድነትን ያረጋገጠው በሲቪል ጦርነቱ ጊዜ 74,542 የኮንፌደሬት ወታደሮችንና ከገደለና 140, 414 የዩኒየኑን መስዋዕት ካደረገ በኋላ ነው።

ራሱን ወደ ባህር ማዶ በመዘርጋት፣ የአሜሪን መንግስት የሚከተሉትን አካባቢዎች ተቆጣጥሯል። ሀዋይ /1898/፣ ፖርቶ ሪኮ፣ ጉዋም እና ፊሊፒንስ /1898/ ፣ ምስራቃዊ ሳሞዋ /1899/፣ የፖሲፊክ ደሴት ይዞታዎች /1945/። ፊሊፒንስ ውስጥ የነበረውን የቅኝ አገዛዝን ተቃውሞ ከ1898-1902 ያፈነ ሲሆን፣ መቀላቀልን የተቃወሙ መስሊም ሞሮስ ከ1901-13 ተገድለዋል። ተነጥሎ የነበረውን ጃፖንንም በባህር ሀይል በማስፈራራት ለውጭ ንግድ አስገድዶታል /1853-54/።

በጦርነትና በሚወስዳቸው ርምጃዎች እየተነሳ የነበረው ሀገር ፍላጐቱን ወደሌሎች የማድረስና የመጠበቅ ስራ ስርቷል። ከተዋጋቸው ጦርነቶች ውስጥ ከብሪታኒያ ጋር /1812-14/፣ሜክሲኮ /1846-48/፣ስፔን /1898/፣ ጀርመን፣ ኦስትሪያና ሀንጋሪ፣ ቱርክ እና ቡልጋሪያ /1916-18/፣ ጃፖን፣ ጀርመንና ጣሊያን /1941-45/፣ ደቡብ ኮሪያና ቻይና /1950-53/፣ ሰሜን ቬትናም /1961-75/፣ አፍጋኒስታን /2001- / እና በኢራቅ /1991, 2003/። የትጥቅ እርምጃዎች ከተወሰደባቸው አካባቢዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ። ፒኪንግ /1900/፣ ፓናማ /1903/፣ ሩሲያ /1918-19/፣ኒካራጉዋ /1912-25/፣ ሄይቲ /1915-35/፣ ሊባኖስ /1958/፣ ዶሚኒካን ሪፐብሊክ /1965-66/ እና ሶማሊያ /1992/። በወረራ፣ የአሜሪካ መንግስት

በሚከተሉት አገሮች ውስጥ መንግስታትን ከስልጣን አወርዷል:: ግሬናዳ /1983/ ፓናማ /1989/ እና በወረራ በማስፈራራት በሄይቲ /1992/:: በወረራ እና ጥቃቶች እገዳዎችን ለማድረግ በካምቦዲያ /1970/ እና ላኦስ /1971 የሞከረ ሲሆን ለመበቀል ደግሞ በሊቢያ /1986/፣ አፍጋኒስታን /1998/ እና ሱዳን /1998/:: ስትራቴጂያዊ ፍላጐቶችን ለማስፋፋትም በኢራቅ /1993/፣ በቦስኒያ /1995/ እና ዩጐዝላቪያ /1999/ ሞክሯል::

ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኃላ በነበረው ግማሽ ምዕተ አመት፣ ዩናይትድ ስቴትስ የግድያ ችሎታዋን በአለም አቀፍ ደረጃ በማስፋት፣ ከነበራት ካፒታሊስት አገሮችን ከሚቃወሙ መንግስታት፣አብዬተኞች፣ እና ሌሎች ጠላቶችን ውጊያ ውስጥ ተሳትፋለች:: በአብዮታዊው ዘመን ከ 1000 ያንሱ የነበሩት የሀገሪቱ የታጠቁ ሀይሎች በ1990ዎቹ ወደ 1.5 ሚሊዬን ወንድና ሴት ያደጉ ሲሆን ፣ ይህም በ23,000 የፔንታጐን እቅድ አውጪዎች፣ በሳይንሱ አለም ተለቅ ያሉ የፈጠራ ችሎታ ባላቸው ግለሰቦች፣ እና በአለም በጣም ያደገው በመሳሪያ ኢንዱስትሪው የተደገፈ ነው:: ይሄ ሁሉ መደረግ የተቻለው ኮንግረስ እና ኘሬዚደንቱ ባፀደቀው ቢያንስ የትሬሊየን አንድ አራተኛ በሚሆን የታክስ ከፋዩ ዶላር ነው:: በመጠኑ በሚሰላበት ጊዜ የሀገሩ የኒኩሊየር መሣሪያ ኘሮግራም ከ1940-96 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ የሀገሩን 5.821 ትሪሊየን ዶላር እንደወጣበት ይታሰባል:: /ሽዋርትዝ 1998/ ከማንኛውም ሀገር የበለጠ ዩናይትድ ስቴትስ የባህርማዶ የጦር ሰፈሮች፣ ውጭ የተላኩ የጦር ሀይሎችና የጦር ንብረቶች አሉት:: በተጨማሪም ዩናይትድ ስቴትስ ከማንም የበለጠ የውጭ ሀይሎችን አሰልጥና መሳሪያ አስታጥቋል:: /ጠላቱን የሚገሉ፣ አንዳንዴ ጓደኞቹን፣ አንዳንዴ የራሱን ህዝቦች/:: በመያያዝም በአለም ውስጥ ባለው ውድድር የበዛበትና ትርፋማ የመሳሪያ ገበያ ውስጥ፣ አሜሪካ ከሚመሩት የመሳሪያ አቅራቢዎች መሀከል ሆናለች:: በቴክሎጂ ደረጃ አሜሪካ በመሬትና በውሀም ሆነ በአየር ላይ ገዳይ የሆነ ሀይል፣ በሰው ልጅ የመግደል እውቀት በተሰሩ በጣም አጥፊ በሆኑ መሳሪያዎች የማድረግ ሀይል አላት::

በ1990ዎቹ በጦርነት የተወለደችው ዩናይትድ ስቴትስ በ1776 ነፃነቷን ከማወጅ ተነስታ ራሷን "የአለም ብቸኛ የጦር ልዩ ሀይል እና የአለም ኢኮኖሚ መሪ" ብላ ሰይማለች /ኘሬዚደንት ዊሊያም ጄ ክሊንተን, ስቴት ኦፍ ዘ ዩኒየን ንግግር ላይ፣ ፌብሩዋሪ 19, 1993 እ.ኤ.አ/ የህብረት ቺፍ ኦፍ ስታፍ ሊቀመንበር የጦር ጀነራል ጆን ሻንስቪሊ እንደተናገረው፣ አሜሪካ"አለም አቀፍ ሀገር" እና "አለማቀፋዊ ፍላጐቶች" ያሏት ሆናለች:: በ1995 ጃፓን ላይ የተደረገው ሀምሳኛው የአቶሚክ ጦርነት ድል በሚከበርበት ጊዜ የሀዋይ ኘሬዚደንት ለተሰበሰቡት ጦሮች ቃል የገባው "በአለም ውስጥ ሁሌም ከሁለም የተሻለ የሰለጠናችሁና መሳሪያ የታጠቃችሁ ጦር ትሆናላችሁ" ብሎ ነው:: እንዳለውም " በዘመናችን ውስጥ ያሉትን የጨለማ ሀይሎች ለማሸነፍ በአለም ከሁለም ጠንካራ የሆነው ሀገር መሆን አለብን" ነው:: ይህ ቆራጥነት በ1996 ቺፍ ኦፍ ስታፍ ጀነራል ሮናልድ ፎግልማን ስለ አየር ሀይሉ ስትራቴጂ ባብራራበት ወቅት ታይቷል:: እንዳለውም "አላማችን በአለም ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ማንኛውንም ነገር ለማግኘት፣ ለማስተካከል፣ ለመከተል እና አለም ለማግኘት ነው::" በተጨማሪ እንደገለፀው "አሁን ልናደርገው እንችላለን:: ነገር ግን ቀጥታ እየተደረገ አይደለም" /በተደረገበት ሰዓት አይደለም/ /በሄሪቴጅ ፋውንዴሽን የተደረገ ንግግር ዋሽንግተን ዲሲ፣ ዲሴምበር 13, 1996 እ.ኤ.አ/

ሀያኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ በሚደርስበት ጊዜ የአሜሪካ መሪዎች ዘመኑን "የአሜሪካ ክፍለ ዘመን" ብለው ለመሰየምና የሶስተኛው ሚሊኒየም የመጀመሪያውን ክፍለ ዘመን "ሁለተኛው የአሜሪካ ክፍለ ዘመን" ለማስባል ፈልገው ነበር:: የጥቃት ሀይልን ጥንካሬ በሚያደንቅ እንደዚህ አይነት ባህል ውስጥ ስለ የማይገድል ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ማውራት የማይታሰብ ነው:: መግደልና በመግደል ማስፈራራት የሀገርን ሉአላዊነት ፈጠሩ፣ ባርነትን አስወገዱ፣ ናዚና ፋሽዝምን አሸነፉ፣ሆሎኮስቱን አቆሙ፣ በአቶም ቦምብ በተመታችው ጃፓን ህይወታችን አተረፉ፣ አለም አቀፍ የኮሚውኒዝምን መስፋፋት አስወገዱ፣ የሶቪየት ግዛት እንዲፈርስ አደረጉ፣ እና አሁን በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የዲሞክራሲያዊ ነፃነትን እና ካፒታሊስት ኢኮሚን የምታስፋፋ መሪ አገር እንድትሆን አስቻለ::

ፖለቲካዊ ሳይንስን ለሚያጠኑ ብዙ ልምድ ያላቸው ባለሞያዎችም ሆነ ጀማሪ ተማሪዎች፣ የማይገድል ህብረተሰብ ሊኖር እንደማይችል ለማሳመን የፍልስፍና ሆነ ሀገራዊ የፖለቲካ ባህልን መጥቀስ አያስፈልግም::

በየአመቱ ከአስራአምስት ሺህ በላይ አሜሪካኖች በሌሎች አሜሪካኖች ይገደላሉ:: / 18209 በ1997፣ ከ100, 000 ሰው ውስጥ 6.8 ወደ 1.2 በ1990 እና 5.7 በ1945/ ሪፖርት የተደረጉት ግድያዎች "ምክንያት ያላቸው ግድያዎችን" ማለትም በፖሊስ ወይም የግል ዜጐች የተደረጉን አይጨምርም /353 እና 268 በ1997/:: ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ጀምሮ የነበሩት የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎች /ወደ 750, 000 የሚገመቱ/ በአጠቃላይ በሀገሪቷ ከኖሯት የጦርነት ሞቶች /650, 053/ ይበልጣሉ:: የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎች ላይ "የተባባሱ ጥቃቶች"/1, 022,492/ በ1997፣ ማለትም 382 በ100, 000/ ሊጨመሩ ይችላሉ:: እነዚህም ሞትን ወይም ለሞት የሚያደርስ ጉዳትን ሊፈጥሩ በሚችሉ መሣሪያዎች የሚደረጉ ጥቃቶችን ይጨምራል:: / ፌደራል ኢንቨስትጌሽን ቢሮ በ1998 15, 22, 33/:: በአሜሪካ ማህበረሰብ ወስጥ ራስን ማጥፋት ከነፍስ ማጥፋት ወንጀሎት በላይ ሞቶችን ይፈጥራል:: /31, 284 በ1995፣ 11.9 በየ 100, 000/:: የራስን ነፍስ የማጥፋት ሙከራዎች ሀያ አምስት እጅ ይተልቃሉ:: በአመት የሚደረጉ ውርጃዎች በ1,000 , 000 በላይ ናቸው::

አሜሪካኖች በብዛት የሚገድሉት በድብደባ፣ ጭንቅላትን በመቁረት፣ በቦምብ፣ በማቃጠል፣ በማስመጥ፣ በመስቀል፣ በመግፋት፣ በመመረዝ፣ በመወጋት፣ በማፈን፣ በማነቅ እንዲሁም በብዛት በተኩስ ነው /67.8% በ1997/:: ግድያዎች ቀድመው የታቀዱ፣ ያልታቀዱ፣ በባለሙያዎች የሚደረጉ ወጭ ድንገተኛ ሊሆኑ ይችላሉ:: የትዳር አጋርን ከማጥቃት፣ የህፃናት ጥቃት፣ የአረጋዊን ጥቃት፣ ጥሎች፣ የስካር ጠቦች፣ አደንዛዥ እፅን ከማዘዋወር፣ የቡድን ጥሎች፣ ቁማር፣ ቅናት፣ የልጅ ጠለፋ፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ አስገድዶ መድፈር፣ ዝርፊያ፣ የመሽፋፈን ስራዎች፣ እና "መንፈሳዊ" ወይም "ሰይጣናዊ" ትዕዛዛዊ ጋር ይያያዛሉ:: የትኛውም ቦታ ሙሉ ለሙሉ ደህንነትን ሊጠብቅ የሚችል አይደለም:: ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንገዶች፣ ጉዳናዎች፣ የስራና የእምነት ቦታዎች፣ እስር ቤቶች ፣ ፖርኮች፣ ትንንሽና ትልልቅ ከተሞች፣ ጫካዎች፣ እና የሀገሩ ዋና ከተማ:: ተጠቂዎች ሊገደሉ የሚችሉት ብቻቸውን፣ በተከታታይ ነፍስ በሚያጠፋ ሰው፣ በብዛት ወይም በአጋጣሚ ሊሆን ይችላል:: በብዛትም ወንዶች ናቸው:: /77% በ1997/ ከ1976 - 85 በተገደሉት የትዳር አጋሮች ውስጥ ሚስቶች /9,480/ ከባሎች /7,115/ በቁጥር ይበልጣሉ /ሜርሲ እና ሳልዝማን 1989/:: ገዳዮች ግለሰቦች፣ ጥንዶች፣ ቡድኖች፣ አንድ የሀይማት ወገን፣ ማህበሮች፣ አሸባሪዎች፣ እና ህግ አስከባሪ የመንግስት አገልጋዬች ሊሆኑ ይችላሉ:: የታወቁ ገዳዩች በብዛት ወንዶች ናቸው:: /11, 177 ወንዶች ከ1, 229 ሴቶች ጋር በ1997 ሲነፃፀሩ/:: በተጨማሪም የወጣቶቹ ቁጥር እየጨመረ ነው:: በ1980 እንደተገመተው "እያንዳንዱ አሜሪካዊ በህይወት ዘመኑ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ተጠቂ የመሆን አንድ ከ240 እድል ለነጮች ሲኖር፣ አንድ ከ47 ደግሞ ለጥቁሮችና ሌሎች አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሔረሰቦች ነው::" /ሮዘንበርግ እና ሜርሲ 1986:376/:: ኘሬዚደንት ክሊንተን በስቴት ኦፍ ዘ ዩኒየን ላይ ጄንዋሪ 27, 1998 እ.ኤ.አ ላቀረበው ንግግር ምላሽ የሰጠው የሴኔት አብላጫ መሪ ሪፐብሊካን ትሬንት ሎት በቴሌቭዥን እንደገለፀው "ሀይለኛ ጥቃትን የፈጠረ ወንጀል አገራችንን ከነፃነት ምድር ወደ አስፈሪ ምድር እየቀየረው ነው::"

የዜና ሚዲያዎች በየቀኑ አሜሪካንን ለህይወት አስጊነት ይመሰክራሉ:: ሴት ልጅ የእናቷን ጭንቅላት ቆርጣ ተገኘች፣ ከዛም በፖሊስ ጣቢያ በኩል እየነዳች አልፋ መንገዱ ዳር ጣለችው:: አንድ እናት ሁለት ልጆቿን አሰመጠች:: ሁለት ወንድ ልጆች ወላጆቻቸውን ገደሉ:: ሰዎችን በተከታታይ የሚገድል ግለሰብ ሴተኛ አዳሪዎችን ገደለ:: አንድ ግብረሰዶማዊ ወጣቶችን በመማረክ ገደላቸው፣ ሰዉነታቸውን ቆራረጠ፣ ፍሪጅ ውስጥ ከተተና ስጋቸውን በላ:: አንድ አልሞ ተኳሽ በዩኒቨርስቲ ውስጥ አስራ አምስት ሰዎችን ተኩሶ ገደለ:: ሁለት ጠመንጃ የያዙ ወንድ ተማሪዎች በገጠር አንደኛ ደረጃ ት/ት ቤት ውስጥ አራት የክፍላቸውን ሴት ተማሪዎች እና አስተማሪ ገድለው፣ አንድ ሌላ አስተማሪ እና ዘጠኝ የክፍላቸውን ልጆች አቆሰሉ:: ሁለት በከባዱ የታጠቁ፣ በሊትልተን ኮለራዶ ኮሎምቢን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ወንድ ተማሪዎች ፣ አስራ ሶስት የክፍላቸውን ልጆች ከገደሉ በኃላ 28 አቁስለው የራሳቸውን ሕይወት አጠፉ:: ከ1996-99 ድረስ ከ11-18 አመት የሚሆናቸው የትምህርት ቤት ተማሪዎች 27 መሰል ተማሪዎችን፣ ሁለት አስተማሪዎችን እና ሶስት ወላጆችን ገድለው 65 ሌሎችን አቆሳሉ:: የአውቶማቲክ የጦር መሳሪያ የያዘ አንድ ግለሰብ በአንድ የከተማ ትምህርት ቤት መጫወቻ

ውስጥ የነበሩ ልጆችን ገደለ፡፡ በቬትናም ጦርነት የተዋጋ ግለሰብ በማሺን መሳሪያ የቤተሰብ ሬስቶራንት ውስጥ የነበሩ 20 ተገልጋዮችን ገድሎ 13 አቆሰለ፡፡ የጦር ውጊያ ልብሶችን የለበሰ አንድ ግለሰብ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞችን "ከዚህ በፊት ሺዎችን ገድያለሁ፡፡ አሁንም ተጨማሪ ሺዎችን እገላለሁ" እያለ እየጮኸ ገደለ፡፡

ዜጐች በደረደሩት የሆቤሲያን የጥቃት ፍራቻዎች እና በሎኪያን የዌበርን መንግስት ያለማመን ሁኔታ መሐከል፣ ወደ ሁለት መቶ ሚሊዩን መሳሪያዎች ያሏቸው የታጠቁ ግለሰቦች አሉ፡፡ ቢያንስ 70 ሚሊዩን አፈሙዝ፣ 65 ሚሊዬን የእጅ ሽጉጦች፣ 49 ሚሊዩን ጠመንጃዎች እና ሌሎች 8 ሚሊዩን ረጅም ሽጉጦች /ኩክ እና ሉድዊግ 1997/፡፡ የመሳሪያ ንግዱ ምርት፣ ሽያጭ፣ አምጪና ላኪ፣ ትልቅ ቢዝነስ ሆኖ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ህጋዊና ህገወጥ አሻሻጮች አሉት፡፡ በ44 ሚሊዩን ጐልማሶች ስር ያሉ የጦር መሳሪያዎች ቢያንስ በአንድ ሦስተኛው የአሜሪካ ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ወላጆች ባይመስላቸውም ብዙ ልጆች እነዚህን መሣሪያዎች እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ፡፡ የልጆችን ጥበቃ ፈንድ መሠረት በማድረግ የሀገሪቷ የመጀመሪያ እመቤት ሂላሪ ክሊንተን፣ 135 ልጆች ሽጉጦችንና ሌሎች መሣሪያዎችን በየቀኑ ወደ ት/ቤት እንደሚወስዱ ገልፀዋል፡፡ /በናሽዋ፣ ኒው ሀምፕሻየር በፌብሩዋሪ 22, 1996 እ.ኤ.አ ባቀረቡት ንግግር የተገለፀ/፡፡ ለዜጐች የመሣሪያ ባለቤትነት በብዛት የሚሠጡበት ምክንያቶች፡- ራስን ከጥቃት ለመከላከል፣ ለአደን ፣ ለመዝናኛ እና በ1971 ሁለተኛ በዩናይትድ ስቴትስ ሕገ መንግስት ማሻሻያ እንደተሰጠው፤ ግለሰቦች ራሳቸው ከመንግስት ጭቆና ማውጣት እንዲችሉ በተሰጣቸው መብት "በደንብ የተስተካከለ የጦር ሀይል ለነፃ ሀገር ደህንነት አስፈላጊ በመሆኑ የግለሰቦች መሳሪያ የመያዝ መብት መጣስ የለበትም፡፡"

የሀገር ውስጥ የግድያ አደጋን ለመጋፈጥ የአሜሪካ የታጠቁ ፖሊሶች አሉ፡፡ እነዚህን ፌደራል የሕግ አስፈፃሚ አካላቶችንና የሀገርና የክልል ፖሊሶችን ይጨምራል፡፡ /618, 127 ፖሊሶች በ1997፣ 250 በየ100, 000 ግለሰቦች/ ስልሳ አምስት በ1997 ተገድለዋል፡፡ /ፌደራል ምርመራ ቢሮ በ1998 286/ በናሽናል ጋርድ የመንግስት አንድ ቡድን እና የዩናይትድ ስቴትስ ፌደራል የትጥቅ ሀይሎች በሚፈለጉበት ጊዜ እነዚህ ይጠናከራሉ፡፡ በተለያዩ ወንጀሎች የተፈረደባቸው ከ 1.7 ሚሊዩን በላይ እስረኞችና በ1996 3219 የሞት እርምጃ የሚጠብቀው እስረኞች በእስር ቤት ጠባቂዎች ይጠበቃሉ፡፡ /የፍትህ ቢሮ በ1997፣ 1998/፡፡ ከ50 ክልሎች ውስጥ በሰላሳ ስምንቱ ውስጥ የሞት ብይን የፊደራል ጥፋቶች ተፈፃሚ ነው፡፡ ከ1977–96 ባለው ጊዜ ውስጥ 358 የሞት ቅጣቶች ተካሂደዋል፡፡ ሀያኛው ክፍለ ዘመን ሲያልቅና የጥቃት ቁጥር መጨመር ፍርሐት በፈጠረበት ጊዜ ውስጥ የሞት ፍርድን ለማስፋትና መልሶ ለማስፈፀም የፍርሃት ጥሪዎች እየቀረቡ ነው፡፡ እነዚህም ብዙ ፖሊሶችን መንገዶች ላይ እንዲገኙ፣ የበለጠ ረጅም የእስር ቅጣቶች እንዲጠየቁ፣ እና ተጨማሪ እስር ቤቶች እንዲገነቡ እየጠየቁ ነው፡፡

በአሜሪካ ውስጥ የሀይል ጥቃት ማለት፣ ከማህበረሰቡ የሚማሩት ነገርና በባህል የተጠናከረ ነው፡፡ መደበኛ በሆነና ባልሆነ፣ ህጋዊ ወይም ህገወጥ መንገድ ሰዎች እንዴት መግደል እንዳለባቸው ይማራሉ፡፡ ወደ ሀያ አምስት ሚሊዩን የሚጠጉ የቀድሞ ወታደሮች ስለመግደል ሙያዊ ስልጠና አግኝተዋል /25 551 000 ሰዎች በ1997/፡፡ ብዙ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የመጀመሪያ የመዘጋጃ የውጊያ ስልጠና ያቀርባሉ፡፡ ንግዶች ራስን ከጥቃት ለመከላከል እንዴት መግደል እንደሚቻል ያስተምራሉ፡፡ የግል ጦሮች ለውጊያ ይሰለጥናሉ፡፡ የጐዳና አሸባሪ ቡድኖች ለውጊያ ብለው ይግባባሉ፡፡ እስር ቤቶችም እንደ ጥፋት ኮሌጆች ያገለግላሉ፡፡ መፅሔቶች የውጊያ ስልትን ለወንጀለኞች ያስተምራሉ፣ መሣሪያ ይሸጣሉ እና በገንዘብ የሚሰሩ ገዳዬችን ያስተዋውቃሉ፡፡

የቪዲዮና የኮምፒውተር "ጌሞች" ወጣት ተጫዋቾችን ከመንገድ ግድያ ጀምሮ እስከ መሬት ከመንገድ ግድያ ጀምሮ እስከ መሬት፣ አየር ውሀ እና የህዋ ዉጊያ ድረስ ያለማምዳሉ፡፡ "ልክ እንደእውነታ የሆነ" ጨዋታ «መግደል ወይም መገደል» በሚል ስም በመዝናኛዎች ውስጥ "አድሬናል የመስጠት ስሜቶች አለው፡፡ ለጊዜው የኮሌጅ ኮምፓሶች ውስጥ የተለመደው ተንኮል ደግሞ "የግድያ" ጨዋታ፣ አብረዉ የሚማሩ ልጆች ላይ የሚደረግ ነው፡፡ የህፃናት ልጆች በአሻንጉሊት ሽጉጥ የሚያደርጉት ጨዋታም፣ የእውነተኛ ወይም የማስመሰል ግድያ ተፈጥሮአዊ ቅጥያ ይመስላል፡፡

*የሌላውን ስቃይ የማያይ የግድያ ስልጠና፣ እና የሰውን ልጅ የህይወት ዋጋ አለመስጠት በብዙሀን መገናኛዎች ይቀርባሉ:: የካርቶን ፊልሞች፣ የቴሌቭዥንና ሬድዩ ኘሮግራሞች፣ መዝሙሮች፣ መፅሀፎች መፅሄቶች እና ማስታወቂያዎች አስተማሪዎች ናቸው:: ከልጅነት እስከ እውቀት በአእምሮአችን ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ በጥቃት የተሞሉ ስዕሎች ይታተማሉ:: ይሄም በጀግናዎችና ወንጀለኞች ምን ያህል ሰዎች ንብረት፣ እንስሳትና ተፈጥሮ በሚገርም መልክ ሊወድም እንደሚችል ያሳያሉ:: የደም መፍሰስና ጭካኔያዊ ስዕሎች በመቀያየር ያታዊ መስህብነት ጋር ከሚያሳዩ ስዕሎች ጋር ይፈራረቃሉ:: በተለይም ሀብትን የሚያሳዩ ፊልሞችና ማስታወቂያዎች ላይ በመታየትና ለገዳይነትን ልዩ ማራኪ ባህሪን ይሰጣሉ::*

*በታሪክ ውስጥ እንደ አሁኑ ብዙ ከግድያ ጋር የተያያዙ ስዕሎች በሰዎች ጭንቅላቶች ውስጥ ተቀርፀው ቀርተው አያውቁም። የጦር ሰራዊቶች መግደልን እንዳይፈሩ ወይም እንዳይሸሹ ሚሊተሪ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ አስፈሪ አረመኔያዊ ድርጊቶችን ሰልጣኞቹ እንዲያዩ ማስገደድ ነው። ለምሳሌ ጭንቅላት ተፈጥርቆ ተይዞ አይን ፈጦ የሚታይበት ሁኔታ /ዋትሰን 1978: 248 -51/። ለህይወት ያለውን አክብሮት ትቶ ዓለም ሁሉ ስሜት የሌለው በመሆኑ፣ ግድያን እየተቀበለ ያለ ይመስላል። ዳኞች እንደገለጹት፣ መረጃ የሚሳየው ወጣት ገዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሰው ልጅ ሕይወት የሚሰጡት ዋጋ እየቀነሰ እንደሄደ ነው። ለተራው የማኅበረሰብ አባል ይሄ ጎጂ ቢሆንም፤ የሃገር ፍቅር ያለው የሰለጠነ ገዳይ ለሚፈልግ ሀገር፣ ጥቃት የተሞላ ሚዲያና የሚያስተምረው ትምህርት ጠቃሚ ነው። ምሳሌ ተደርጎ የሚገለፀው በቴሌቭዥን በሚታየው የአሜሪካ ሱፐር ቦል ፋትቦል ጨዋታ ጊዜ ሚላዮን ዶላር ተከፍሎበት የሚታየው የጦር ምልመላ ማስታወቂያ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠር ተመልካቾች፣ ሰይፍ የመዘዘ የጥንት ዘመን ተዋጊ ከቪዲዮ ጦርነት “ጨዋታ” ተቀይሮ ወደ ዘመናዊ ጎራዴ ይዞ ሰላምታ የሚሰጥ የዩናይትድስቴትስ የባህር ኃይል ተዋጊ ሲቀየር ያያሉ።*

*ቋንቋ ግድያን ያንፀባርቃል እና ያጠናክራል። ይሄም የሚሆነው ‹ተፈጥሯዊ ነው› የሚል እና ‹ልናመልጠው አንችልም› የሚል ስሜት በመፍጠር ነው። የአሜሪካ ኢኮኖሚ የተመሰረተው ነፃ የኢንተርፕራይዝ ካፒታሊዝም ላይ ነው። አሜሪካዎች ሲናገሩ “እክሲዮን ገበያ ውስጥ ግድያ ፈፅሜአለሁ” ይላሉ። አንድ የዎል ስትሪት አባባልም አለ “መግዛት የሚመረጠው ጎደናዎች ላይ ደም ሲኖር ነው”። ቢዝነሶች ሲወጣጠሩ “የዋጋ ጦርነት” ይላሉ። የአሜሪካ ፖለቲካ የተመሰረተው ነፃ የምርጫ ዲሞክራሲ ላይ ነው። የምርጫ ቀስቃሾች “ወታደሮች” ወይም “ የእግር ተዋጊዎች” ተብለው ሲታወቁ፣ በሕግ ውስጥ የሕግ ማሻሻያዎች “ተገደሉ” ነው የሚባለው። በተጨማሪም ሀገሪቷ በደኅነት፣ በወንጀል፣ አደንዛዥ ዕፅ እና ሌሎች ችግሮች ላይ “ጦርነት ታዉጃለች” ይላሉ። የአገሪቷ ዋና ስፖርት ቤዝቦል ነው። የተበሳጩ የጨዋታው ተመልካቾች የሚሉት “ዳኛውን ግደሉ!” ነው። የስፖርት ዘገባዎች ጎበዝ የፉትቦል ቡድኖችን “ገዳዮች” ሲሏቸው፣ ተጫዋቾች “መሳሪያዎች” ይባላሉ። ኳስ ማስተላለፍ “ረጅም ቦምብ” ሲባል፣ የአሸናፊ ቡድኖች «የገዳይ ደመነፍስ ያላቸው» ተብሎ ይታሰባል። የሃይማኖት ነፃነታቸውን ተጠቀመው የክርስቲያን የመስቀል ተዋጊዎችንና ለውጥ ፈላጊዎችን መንፈስ እያንፀባረቁ “የያቆብን መሰላል” እንደ “መስቀሉ ወታደሮች” በመዝሙር ይወጡታል። ስራ የማይሰራበት እና ህይወት ሚቀጥልበትን ጊዜ “ጊዜን መግደል” ብለው ይጠሩታል።*

*የዘር እና ፆታ መድልኦን የሚያሳይ ቋንቋዎች ስላላቸው ጎጂ ውጤት ያለው እውቀት እያደገ ቢመጣም፣ የግድያን ቋንቋ አሜሪካዊያኖች ያለምንም ሃሳብ በመናገር ቀጥለዋል። የአሜሪካ እንግሊዘኛ የቋንቋ “ጥሩር” በታሪክ የሚታወቁ መሳሪያዎችን፣ አጠቃቀማቸውንና፣ ውጤታቸውን የሚያንፀባርቁ ቃላቶችን ይጠቀማል። ክህደት “ከጀርባ መውጋት”፣ በጀቶች “በመጥረቢያ ይቆርጣሉ”፣ ሙከራ “ለመተኮስ መሞከር”፣ ሀሳቦች “ይወነጨፋሉ”፣ ተቃዋሚ የሚታወቀው “ፀረ አውሮፕላን ጠመንጃ” ተብሎ እና የተግባሮች ውጤት የሚታወቁት “ጥል” ተብለው ነው። ጠበቃዎች “የተቀጠሩ ሽጉጦች” ናቸው። ቆንጆ የፊልም ተዋናይነት የምትታወቀው “ቆንጆ የቦምብ ሼል” ተብላ ነው። በሌላ ጎኑ ቀጥተኛ ያልሆኑ ቃላት አብዛኛው ጊዜ እውነተና ግድያን ይሸፍናሉ። “ትንሹ ልጅ” ተብሎ የሚታወቀው ሂሮሺማ ላይ የተጣለው የዓለም የመጀመሪያው አቶሚክ ቦንብ ከB-29 የቦምብ ጣይ ላይ ተጥሏል። B-29ኙ የተሰየመው በፓይለቱ የእናት ስም “ኢኖላ ጌይ” ተብሎ ነው። በመቀጠል የፕሉቶንየም ቦምብ “ወፍራሙ ሰውዮ” ናጋሳኪ ላይ የተጣለው በ”ቦክ መኪና” ነው። ብዙ የከተማ ህዝቦችን መግደል የሚችሉ፣ አህጉር አቋራጭ ሚሳይሎች “ሰላም ፈጣሪ” በሚል ስም ይታወቃሉ። ለስፖርቶች የሚጠቀሙትን ቋንቋ በማገላበጥ፣ የሚሊተሪ ሊግድያ ሲዘጋጅ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች “ጨዋታ” በመባል ይታወቃሉ። የሰላማዊውን ኅብረተሰብ ወይም የራሱ ጦር አባልን መግደል “ብዙ የማይጎዳ ጥፋት” ተብሎ ይጠራል።*

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን እንዳሉት “በዘመናዊ ታሪክ ውስጥ አሜሪካ ከሁሉም ያነሰ ጦርነት ያለባት የምትመስል እና ሰላማዊ ሀገር ናት” (ፒቢኤስ 1993).

በተወሰነ ጊዜ በአሜሪካ ውስጥ ያሉ የግድያ ሁኔታዎች፣ በዜጎች መሀከል ያለ የኃይል ጥቃትና በዜጎች በመንግሥት አካሎች መካከል ያሉ ጥቃቶችን ያደባልቃሉ። በ1992፣ 52 ሰዎች ተገድለው 2,000 የአካል ጉዳት ደርሶባቸው እና 8,000 ታስረው ነበር። ይህ የሆነው ፖሊሶች አንድ ጥቁር ዜጋ ላይ ያደረሱትን ጥቃትና በሕግ ነፃ መደረጋቸውን አስመልክቶ በሎስ አንጀለስ በተደረገ ተኩስ፣ ዘረፋ እና የንብረት ማቃጠል ነው። በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ፣ በአካባቢው ያሉ ፍርሃት ያደረባቸው ግለሰቦች ወደ 70,000 የሚጠጉ ሽጉጦችን ገዝተው ነበር። ያ የደም መፍሰስ ከዛ በፊት የተደረጉ ተመሳሳይ እልቂትን ያስታውሳል። በዋትስ (34 በ1965)፣ ኒውዮርክ (26 በ1967)፣ ዲትሮይት (47 በ1967)፣ እና በ18ኛው 19ኛው ክፍለ ዘመን የባርነት ተቃውሞዎች ጊዜ የጠፉ ሕይወቶችን። በ1967 ዲትሮይት ውስጥ ስርዓትን መልሶ ለማስፈን 4,700 የአየር ሀይል ወታደሮች፣ 1,600 ዘብ ጠባቂዎች፣ እና 630 የሚሺጋን ስቴት ጦር አስፈልጓል። (ሎክ 1969)

የሆቤሲያን-ዌበሪያንን መንግሥት እና ከሎኪያን ሀለተኛ የማሻሻያ ነጥብ ውርስ ውጤት የሚታየው ለምሳሌ በዋኮ ቴክሳስ በ1993 ዓ.ም የታየው ግድያ ነው። በተጨማሪም በ1995 በኦክላሆማ ሲቲ በታየው ግድያ። በዋኮ፣ የመንግሥቱ የታጠቁ ኃይሎች፣ የታጠቁ የኃይማኖት ቡድኖች ላይ ሕግን ለማስከበር ጥረት ሲያደርጉ አራት ፌዴራል ሰራተኞች ተገለው፣ 12 የቆሰሉ ሲሆን፤ 89 የሃይማኖት ቡድኑ አባላት ሴቶችና ልጆችን ጨምረው ሞተዋል። የዚህ አሳዛኝ አጋጣሚ ሁለተኛ ዓመት ዋዜማ ላይ ተቃዋሚዎች ብቀላ ለማድረግ በኦክላሆማ ሲቲ የፌዴራል ቢሮ ህንፃ በመኪና ቦምብ ያጋዩ ሲሆን፤ 168 ሰዎች፣ ሴቶንና ልጆችን ጨምረው ተገለዋል።

ከራሳቸው ክልል አልፈውም ሌሎችን ሲያዩ፤ አሜሪካውያኖች መግደል የማይችል ኅብረተሰብ ሊኖር እንደማይችል በቂ መረጃ ያያሉ። በሰው ልጅ ታሪክ ብዙ ደም መፍሰስ የነበረው ዘመን በመሆን፤ ሃያኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅን ታላቅ የመግደል ችሎታ አሳይቷል። በሩዶልፍ ጄ ሩሜል የተሰራ ጥናት፣ ደም መፍሰሱን በታሪክና አለማቀፋዊ እይታ ያስቀምጣል። በተመዘገበ ታሪክ ውስጥ ያለውን ግድያ፣ ሩሜል በሰንጠረዥ 1 ላይ አስቀምጦታል። ይሄንን “ዴሞሳይድ” (ማለትም መንግሥት የራሱን ሕዝብ በዘር ማጥፋት፣ የግድያ ቅጣት፣ በብዛት በመግደል፣ እና በሰው ሰራሽ ረሃብ መግደል)፤ እና በጦርነት ጊዜ የደረሱ ሞቶች (ማለትም በዓለም ደረጃ ፣ በአካባቢ፣ በተራው ኅብረተሰብ፣ በአብዮትና፣ ሽምቅ ውጊያ) ብሎ ይለያያቸዋል።

**ሰንጠረዥ 1፡ “በዴሞሳይድ” እና ጦርነት የደረሱ ሞቶች እስከ 1987**

| | ከ1900 በፊት | 1900-1987 | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|
| ዴሞሳይድ | 133,147,000 | 169,198,000 | 302,345,000 |
| ጦርነት | 40,457,000 | 34,021,000 | 74,478,000 |
| ድምር | 173,604,000 | 203-219,000 | 376,823,000 |

ምንጭ ሩሜል 1994 ለሰንጠረዥ 1-66, 66-71

በመሆኑም በግለሰቦች የተደረጉ ነፍሰ ግድያዎችን ሳይጨምር፣ ምናልባትም ወደ አራት መቶ ሚሊዮን አካባቢ ሰዎች በታሪክ ውስጥ የፖለቲካዊ ግድያ ተጠቂዎች ሆነው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ሩሜል አብዛኛውን “ዴሞሳይድ” ከኮሚዮኒስት ገዢዎች ጋር ሲያያዝ፣ በመቀጠልም አምባገነናውያን መሪዎች ይመጣሉ። ከሁሉም መጨረሻ ላይ ዲሞክራሲያዉን ይገኛሉ። በአሜሪካውያኖች ትዝታ ውስጥ አሁንም ቅርብ ሆኖ የሚታወሰው የሂትለር ሆሎኮስት፣ የስታሊን “የማፅዳት ስራ”፣ የጃፓኖች የኃይል ጥቃት፣ እና የማኦውያን ግድያዎች ናቸው።

ዊሊያም ጀ ኤከርት እና ተከታዮቹ እንዳሰሉት፤ በ1900 እና 1995 መካከል ከጦርነት ጋር የተያያዙ የሃያኛ ክፍለ ዘመን ሞቶች ሲገመቱ ቢያንስ 106,114,000 ሰዎችን፤ ማለትም 62,194,000 ሰላማዊ ኅብረተሰብና 43,920,000 የጦር ተጎጂዎችን ይጨምራል (ሲቫርድ 1996 ፡ 19)። "በሰላማዊው" የ "ቀዝቃዛ ጦርነት" ዘመንም የቀጠለው እልቂት፤ ከ1945 እስከ 1992 ወደ 22,057,000 ሰዎችን በ149 በጦርነቶች ገድሏል ተብሎ ሲገመት፤ ከነዚህ ውስጥ 14,505,000 ሰላማዊ ግለሰቦች፣ እና 7,552,000 ተዋጊዎች ናቸው ተብሎ ይታሰባል (ሲቫርድ 1993፡20-1)። በ1996 ብቻ ቢያንስ ሰላሳ ጦርነቶች በሂደት ላይ ነበሩ።

በዓለም ሁሉ ያሉ የቴሌቭዥን መስኮቶች የደም መፋሰሶችን በተደጋጋሚ የሚያሳዩ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ የድሮ ጥል ላይ የተመሰረቱ እና በቅርብ ቅራኔዎች የተባባሱ እና ፍላጎትን ማሟላት ካለመቻል ጋር የተያያዙ ናቸው። አንድ አሰቃቂ ትእይንት በሌላው እየተተካ ሲሄድ፣ ሚዲያም ለተወሰነ ጊዜ አንዱ ላይ ያተኩርና ወደሚቀጥለው ያልፋል። ደም መፍሰሱ የተለያየ ገፅታ የሚይዝ ሲሆን፣ ሁሉም ለመግደል ዝግጁ መሆን ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ ዓለማቀፍ ጦርነቶች፣ የሕዝብ ጦርነቶች፣ አብዮቶች፣ የመገንጠል ጦርነቶች፣ የሽብርተኞች ጥቃት፣ የክልል ጥሎች፣ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች፣ ዘር ማጥፋት፤ የዘር፣ ኃይማኖት እና ብሔር ማጥፋት፣ የቅጥር ግድያዎች፣ የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት እና ከመግደል ጋር የተያያዙ እልቂቶችና እጥረቶች ናቸው። አንዳንዴ ከሌሎች አገሮች ጋር ያሉ ግጭቶች፣ አገር ውስጥ ያሉ አሜሪካውያንን ሕይወት ይሰልባሉ። ለምሳሌ በ1993 ዓ.ም የነበረው የኒውዮርክ የወርልድ ትሬድ ሴንተር ቦምብ ፍንዳታ የተከሰተው፣ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል መንግሥትን መደገፏን በሚቃወሙ ግለሰቦች ሲሆን፤ ስድስት ሰዎች ሞተው አንድ ሺህ ተጎድተዋል። በተጨማሪም በ1998 ዓ.ም በናይሮቢ እና በዳሬሰላም የሚገኙ የአሜሪካ ኤምባሲዎች ላይ የተደረጉት የመኪና ቦምብ ጥቃቶች፣ 12 አሜሪካውያን እና 300 አፍሪካውያንን የገደሉ ሲሆን ወደ 5,000 ተጎድተዋል።

በሴፕቴምበር 11, 2001፣ አስራ ዘጠኝ የአልቃይዳ አባላት አራት የጉዞ አውሮፕላኖችን ጠልፈው እንደመሳሪያ በመጠቀም በኒውዮርክ የሚገኙት መንታ የወርልድ ትሬድ ሴንተር ህንፃዎች እና ዋሽንግተን በሚገኘው ፔንታገን ላይ አጥፍቶ የመጥፋት ጥቃት ያደረጉ ሲሆን፤ ካፒቶሉ ጋር ባይደርሱም 2,986 ሰዎችን ገድለዋል። ዩናይትድ ስቴትስ ለዚህ ምላሽ ብላ አልቃይዳ መሠረት ያደረገውን አፍጋኒስታንን ከኦክቶበር 2001 ዓ.ም ጀምሮ የወረረች ሲሆን፤ ከዛም በኋላ፣ ቀድሞ የማጥቃት ጦርነት ኢራቅ ላይ ከማርች 2003 ዓ.ም ጀምሮ አድርጋለች።

እያለፈ ያለውን ሃያኛው ክፍለ ዘመን የአሜሪካ መሪዎች በሚያዩበት ጊዜ፣ ሆብሰንን እያስተጋቡ ሊሉ የሚችሉት፡- «እዛ ያለው ጫካ ነው!» ብለው ይሆናል። በተጨማሪም የሞተው የሮማን አገዛዝን፡- "ሰላምን ከፈለክ፣ ለመዋጋት ዝግጁ ሁን" የሚለውን አባባል ሊደግፉ ይችላሉ። (*si vis pacem para bellum*)

እዚህ መሠረታዊ እምነቶች፣ የፍልስፍና ውርሶች፣ ስለአገር ወደድነት ያሉ ትምህርቶች፣ ሚዲያ የሚሰራው የማጠናከሪያ ስራ፣ የባህል እምነት፣ እና ዓለም አቀፍ ደም መፋሰስ ባሉበት ሁኔታ፤ የአሜሪካ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች እና ተማሪዎቻቸው አለመግደል ያለበት ማኅበረሰብ ሊኖር አይችልም ብለው ቢያልፉ አይገርምም።

በዩኒቨርስቲ ውስጥ ላሉ ተማሪዎች የመጀመሪያ የመግቢያ የድህረምረቃ ሴሚናር ኮርስ ላይ ይሄ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፤ በተለምዶ የቀረቡት ምላሾች፡- የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባህሪ፣ የሀብት እጥረት፣ እና ራሱን ከዖታዊና ከሌሎች ጥቃቶች ለመከላከል ያለው ሁኔታ፣ ይህንን እንደማይፈቅድ ነው። ምንም እንኳን ምላሾች የተመሳሰለ ሁኔታ ቢኖራቸውም፣ ልዩነቶችና የምላሾቹ አካሄዶች የማያልቁ ናቸው። ሁልጊዜ ጥያቄው በተነሳ ቁጥር አንድ አዲስ ነገር ይጠበቃል። የሰው ልጆች ኃይል ፈላጊ ናቸው። ራስ ወደድ፣ ቅናተኛ፣ ጨካኝ እና እብድ። ራስን ለመከላከል ብሎ መግደል በተፈጥሮ የመጣ እና የሰው ልጅ የተሰጠው ልንቃወመው የማንችለው መብት ነው። ሰዎች ለሀብት ስግብግብ እና ተፎካካሪ ናቸው።

የማኅበረሰብ ልዩነቶችና የፍላጎቶች መለያየት፣ መግደል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከመግደል የባሱ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ስነ-ልቦናዊ ጥቃትና፣ የሀብት እጦት፡፡ መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ በአንድ መሪ ስር በአምባገነንነት የተያዘ ይሆናል፣ ነፃነትም ይጠፋል፡፡ በተጨማሪም ከውጭ በሚመጡ ጠላቶች ሊጠቃና ሊገዛ ይችላል፡፡ አለመግደልን እንደ ፖለቲካዊ መርሆ ሰንወስደው ግብረገባዊ ያልሆነ ተግባር ነው፡፡ ለጥቃት የሚጋለጡ ሰዎችን ለማዳን ተብሎ የሚደረግ ግድያ ፍትህ የተሞላ ነው፡፡ ወንጀለኞችን ለመቅጣትና ለማቆም ብሎ መግደል ማኅበረሰብን ይጠቅማል፡፡ መሳሪያዎች አንዴ ተፈጥረዋል፤ ያንን ወደኋላ መመለስ አይቻልም፡፡ የግድያ ቴክኖሎጂ ሁልጊዜም ይኖራል፡፡ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ በታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም፤ ሊታሰብም አይችልም፡፡

ይሄ ማለት አንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ሁሉ ተስማምተዋል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ አሜሪካዊ ተማሪዎች፣ የሰው ልጆች የፈጠራና ለሰው የማዘን ችሎታ ስላላቸው መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ በትምህርት ሊፈጠር እንደሚችል ያምናሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ በትንንሽ ማህበረሰቦች ውስጥ ሊሳካ እንደሚችል፤ ነገር ግን በትልልቅ ማህበረሰቦችና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደማይሆን ይናገራሉ፡፡ ይሄ ማለት፣ የአሜሪካውያን አስተያየት በሌሎች አገሮች ካሉ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰሮች እና ተማሪዎች የበለጠ በጥቃት የተሞላ ነው ለማለት አይደለም፡፡ ይሄንን ለማወቅ ዜዴያዊ የንፅፅር ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ግን በአሁኑ የፖለቲካ ሳይንስ ሙያ ዓለም ውስጥ፣ አሉታዊ አስተያየት እንደሚያመዝን ይታሰባል፡፡

“መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል?” የሚለው ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ሌሎች የፖለቲካ ባህሎች ለየት ያሉ ምላሾችን በሚያስገርም ሁኔታ ሰጥተዋል፡፡

*ስለዚህ ጥያቄ በፍፁም አስቤ አላውቅም…*

ይህን ምላሽ አንድ ስዊድናዊ የሙያ አጋር፣ በ1980 በስዊድናዊ ፊውቸሪስት ስብሰባ ላይ ስራ ጥቃት ስለሌለው ፖለቲካዊ ሳይንስ ወይይት ሲነሳ የመለሰው ነው፡፡ “ስለዚህ ጥያቄ በፍፁም አስቤ አላውቅም፡፡ ይሄንን ለማሰብ ትንሽ ጊዜ እፈልጋለሁ፡፡” በሚገርም ሁኔታ በአንድ ጊዜ ይሄንን ሃሳብ የመቀበልም ሆነ ውድቅ የማድረግ ሁኔታ አልነበረም፡፡” ጥያቄው ወደፊት ተጨማሪ እይታ እና ሃሳብ እንደሚያስፈልገው ነው የተወሰደው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በ1977 በሲዖል አለማቀፋዊ የሲስተም ሳይንቲስቶች ባደረጉት ስብሰባ ላይ፣ በኬምስትሪ የኖቤል አሸናፊ የሆኑ ግለሰብ የመለሱት “አላውቅም” ብለው ነው፡፡ ይህ፣ በቂ የሆነ ሳይንሳዊ መሰረት የሌላቸው ጥያቄዎች ሲያጋጥሟቸው በተለምዶ የሚያቀርቡት ምላሽ ነው፡፡ በመቀጠልም ሳይንስ እና እድገት እየተሻሻሉ የሚሄዱት የማይቻል የሚመስለውን በመጠየቅ ስለሆነ፣ የስብሰባው ተሳታፊዎች ለጥያቄው ተገቢ አትኩሮት እንዲሰጡ ጠይቀዋል፡፡

*ሊታሰብ ይችላል ግን …*

ሞስኮ ውስጥ በ1979 በተካሄደው 11ኛው የኢንተርናሽናል ፖለቲካ ሳይንስ አሶሴዩሽን ወርልድ ኮንፈረንስ ላይ፤ ሁለት ሩሲያዊ ምሁራን «ጥቃት የሌለበት ፖለቲካዊ ሳይንስ» የሚል ፅሁፍ ላይ፣ ብቃት ያለው ትንተና ለማድረግ ፍላጎት አሳይተዋል፡፡ ሁለቱም በሚገርም ሁኔታ የመለሱት፤ ‹የፖለቲካዊ ሳይንስ እና የፖለቲካ ግብ፣ ጥቃት የሌለበትን ማኅበረሰብ እውን ማድረግ ነው› ብለው ነው፡፡ ነገር ግን አንዱ የጠየቀው፣ «ጥቃት የሌለበት ፓለቲካና ፖለቲካዊ ሳይንስ ኢኮኖሚያዊ መሠረቱ ምንድን ነው?» ብሎ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ «አንዳንድ አሳዛኝ ነገሮች ሲያገጥሙን እንዴት አድርገን እንወጣወለን?» ብሏል፡፡ ለምሳሌ በቺሊ (በዴሞክራሲ የተመረጠውን ሶሻሊስት መንግስት በሚሊተሪ መፈንቅለ መንግሥት ሲያወርደው)፣ በኒካራጉዋ (ጥቃት የተሞላበት አፈና እና አብዮት የታየበት)፣ እና ካምፑቺያ (ከአንድ ሚሊዮን በላይ ህዝብ በአብዮታዊ የከተማ መደብ ማጥፋት ሂደት ውስጥ የሞተበት)፡፡

እውነትም ምን አይነት ኢኮኖሚ በግድያ ላይ ላይመረኮዝና ላይደግፍ ይችላል? - እንደ “ካፒታሊዝም” እና “ኮሚዩኒዝም” ዘመናዊ ቅርፆች፡፡ መግደል የሌለበት ፖለቲካ፣ እንዴት አድርጎ ገዳይ የሆኑና አረመኔያዊ ድርጊቶችን ቀጣይ ውጤት ሊያስወግድ ወይም ሊያቆም ይችላል? ይህ ጥቃት የለሽ ሁኔታ በሚታሰብበት ጊዜ፣ ጠንከር ያለ ሳይንሳዊ ጥናቶችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡

*የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ጥቃት አድራጊዎች እንዳልሆኑ እናውቃለን ግን ...*

በጆርዳን ዩኒቨርሲቲ፣ በ1981 ለአረብ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች እና የህዝብ አስተዳደር ምሁሮች ስለ ጥቃት የሌለው ፖለቲካዊ ሳይንስ ለቀረበ ጥያቄ ሁሉም የተስማሙት እና አንድ ፕሮፌሰር ያስቀመጠው፤ "የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ጥቃት አድራጊዎች እንዳልሆኑ እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ራሳችንን ከጥቃት ለመከላከል እንጣላለን" ብሎ ነው፡፡ ‹የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው ጥቃት አድራጊ ናቸው› የሚለው አስተሳሰብ በጥያቄ ውስጥ ከገባ፣ ማንም ሰው የመግደል ተግባር ውስጥ የማይገባበት ሁኔታ ልናጠና እንደምንችል ያሳያል፡፡

*ይቻላል ግን ...*

በሄሮሽማ ዩኒቨርስቲ ኢንስቲቲውት ኦፍ ፒስ በ1985 በተደረገ 10ኛ ዓመት ሴሚናር፣ ጃፓናዊ ተሳታፊዎች እኩል ወደሚስማሙና ወደማይስማሙ ቡድኖች የተከፈሉ ሲሆን፤ የትምህርት ዘርፍ ፕሮፌሰር የሆነ ግለሰብ እንደመለሰው "ሊሆን አይችልም፡፡ ግን እንዲሆን ማድረግ ይቻላል" ብሎ ነው፡፡ መግደል የሌለበትን ማኅበረሰብ በፍጥነት ማግኘት ባይቻልም፤ ወደፊት ሊሆን የመቻሉ ሁኔታ ግን አልተተወም፡፡ በመቀጠልም የጠየቀው "ጥቃት የሌለበት ማኅበረሰብ ለመፍጠር ምን አይነት ትምህርት ያስፈልጋል?" ብሎ ነው፡፡ ገንቢ የሆነ እና ፈጠራዊ የችግር መፍቻን መንገድ የመገበዝ ሁኔታ-

*ሙሉ ለሙሉ ይቻላል*

ኮሪያዊ የፍልስፍና ፕሮፌሰርና፣ የኮሪያ ሶሻል ሳይንቲስቶች አሶሴሽን ፕሬዚዳንት የሆኑ የፒዮንግያንግ ፓለቲካዊ መሪ፣ በዲሴምበር 1987 በአስገራሚ ሁኔታ ያለመጠራጠር የመለሱት "ሙሉ ለሙሉ ይቻላል" ብለው ነው፡፡ ለምን? አንደኛ ደረጃ፣ የሰው ልጆች በተፈጥሮ የመግደል ፍላጎት የላቸውም፡፡ "ስነልቦና"፣ "ማመዛዘን"፣ እና የፈጠራ ችሎታ" ስላላቸው መግደልን እንዲተው ያደረጉዋቸዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ የሀብት እጥረት ለመግደል ምክንያት ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡ ሰዎች የቁሳቁስ ባሪያዎች አይደሉም፡፡ እጦትን «በፈጠራ ችሎታ»፣ በ"ምርታማነት"፣ እና በሁሉም በበለጠ "በእኩል ክፍፍል ልንወጣው እንችላለን፡፡ ሦስተኛ ደረጃ፣ «አስገድዶ መድፈር እስካለ ድረስ የማይገድል ማኅበረሰብ ሊኖር አይችልም» ብለን ማስቀመጥ የለብንም፡፡ አስገድዶ መድፈር በ"ትምህርት" እና "ተገቢ የሆነ ማህበረሰባዊ ሁኔታን" በመፍጠር ሊጠፉ ይችላል፡፡

በፌብሩዋሪ 2000 ዓ.ም በማኒዛሌስ ኮሎምቢያ፣ ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ የማህበረሰብ መሪዎች ባሉበት ስበሰባ «መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል?» የሚለው ጥያቄ ሲጠየቅ፤ በሚገርም ሁኔታ አንድም ሰው እጁን አንስቶ አይችልም አላለም፡፡ በመቀጠልም ሁሉም እጃቸውን አንስተው «አዎ» ብለው መልሰዋል፡፡

እዚህ በኮሪያና በኮሎምቢያ የታዩት አዎንታዊ ምላሾች፣ በአካባቢያቸው ካለው የኃይል ጥቃት ጋር ሲነፃፀር አስገራሚ ነበር፡፡ በህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኮሪያ ሪፐብሊክ ውስጥ ያለው ኃይል የተሞላ የፖለቲካ ባህል ሲታይ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ውስጥ ካለው ጋር ትይዩ ነው፡፡ የትጥቅ ፀረ ቅኝ ግዛት አብዮት፣ የአንድ ለመሆን የተደረገ የሕዝብ ጦርነት፣ እና ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ጠላቶች ጋር የተደረገ ራስን የመከላከልና የማጥቃት ስራን ይጨምራል፡፡ ለአስርት ዓመታት የኮሎምቢያ ህብረተሰብ የማይመለስ በሚመስለው የሚሊተሪ ፖሊስ፣ መደበኛ ያልሆነ ጦር፣ ሽምቅ እና የወንጀለኞች ግድያዎች ወረርሽኝ ተጠቅቶ ነበር፡፡

*የተለያዩ የማህበረሰብ ምላሾች*

«መግደል የሌለበት ማህበረሰብ ሊኖር ይችላል?» የሚለው ጥያቄ በተለያዩ ቡድኖች፣ አገሮች፣ ባህሎች እና የማህበረሰባዊ ዝንባሌዎች ውስጥ ያለቅድመ ውይይት በሚነሳበት ጊዜ፤ በቡድኖች ውስጥ የመስማማት ወይም ያለመስማማት የተለያዩ ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ ጥናት አስፈላጊነት ግልፅ ሆኗል፡፡

በቪሊነስ ሊቱኒያ ዉስጥ፣ ሜይ 1998 ዓ.ም በተደረገ የአቻ ጥናት ሴሚናር ላይ በነበረ ስለ «አዲስ ፖለቲካዊ ሳይንስ» ውይይት ውስጥ፣ የቀድሞ ሶቪየት አካባቢ አገሮች ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች የተገኙ ሲሆን፤ እዚህ በኦፐን ሶሳይቲ ኢንስቲቲውት ድጋፍ በተደረገ ሴሚናር ላይ ስምንቱ አይ ሲሉ፣ አንዱ አዎ ብሏል። በሴኦል ናሽናል ዩኒቨርስቲ፣ በማርች 1999 ዓ.ም በተደረገ የመጀመሪያ የመግቢያ ፖለቲካዊ ሳይንስ ሴሚናር ላይ ከነበሩ ምሩቅ ተማሪዎች ውስጥ፣ አስራሁለቱ አይ፣ አምስቱ አዎ እና ሁለቱ አዎ እና አይ ብለው መልሰዋል። በሆኖሉሉ ሀዋይ ውስጥ፣ ፌብሩዋሪ 1998 ዓ.ም ላይ፣ ‹በፓሲፊክ የፓርላማ አባላት በጃፓን የተመሠረተ እና ዩናይትድ ኔሽንስን የሚረዳ ድርጅት› እርዳታ በተደረገ ፎረም ላይ፣ ስድስት ሰዎች አዎ፣ አምስት አይ እና ሁለት ደግሞ አዎ እና አይ ብለው መልሰዋል። ከጃፓን ከመጡ ተመልካች የሴቶች ቡድን ውስጥ፣ አስራሁለቱ አይ፣ አስራአንዱ አዎ እና አንዷ አዎ እና አይ ብለው መልሰዋል።”

በሜደሊን ኮሎምቢያ፣ በኖቬምበር 1998 ዓ.ም በተደረገ “የትምህርት የወደፊት ሁኔታ” የሚል አገር አቀፍ የመምህራን ኮንፈረንስ ላይ፣ 275 አዎ ሲሉ 25 ደግሞ አይ ብለዋል። የሜደሊን የቤተሰብ ማኅበረሰብ ሰራተኞች ቡድን ውስጥ፣ ሠላሳው አዎ፣ እና አስራ ስድስት አይ ብለዋል። በቡድን የተደራጁ «ትንንሽ ቢላዎች» ከሚባሉ በቅጥር የሚገድሉ ገዳዮችና ወጣት ጥፋተኞች መካከል፣ አስራስድስቱ አይ ሲሉ ስድስቱ አዎ ብለዋል። ለምላሻቸው ምክንያቱን በተጠየቁ ጊዜ አንድ ገዳይ እንደመለሰው፣ “ሁለት ሴት ልጆቼን ለመንከባከብ ብዬ መግደል አለብኝ። ምንም ስራ የለም” ብሎ ሲሆን፤ ሌላው ሲያብራራ “በሀብታምና ድሃ መካከል ያለው ክፍተት ሲሞላ እኛ መግደል አይኖርብንም» ብሏል።

ኤድመንተን ካናዳ ውስጥ፣ በኦክቶበር 1997 ዓ.ም «እምነቶችና 21ኛው ክፍለ ዘመን» በሚል ‹በማሀተመ ጋንዲ የካናዳ ለዓለም ሰላም ፋውንዴሽን› የተደገፈ፣ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በተደረገ ሴሚናር ላይ፣ አርባ ስምንቱ አይ ብለው ሃያ አምስቱ አዎ ብለዋል። በጆርጂያ አትላንታ፣ በኤፕሪል 1999 ‹በማርቲን ሉተርኪንግ ሴንተር ፎር ነን ቫዮለንት ሶሻል ቼንጅ› በተደገፉ “ዓለምአቀፍ ኢ-የኃይል ጥቃት ኮንፈረንስ” ላይ፣ አርባ ሰዎች አዎ ሲሉ ሦስት አይ ብለው መልሰዋል። በኦምስክ ሩሲያ፣ ፌብሩዋሪ 2000 ላይ ከእድሜያቸው ከአስራ ሰባት እስከ ሃያ አንድ ከሚሆኑ ስነ-ጽሑፍ ተማሪዎች ጋር በተደረገ ጥናት፣ 121 አይ ሲሉ፣ 34 አዎ እና 3 ደግሞ አዎና አይ ብለው መልሰዋል።

መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል? አሁን በኃይል በተሞላው ሃያኛ ክፍለ ዘመን ካሉት፣ ብዙ አለማቀፋዊ ግድያዎች እና ለመግደል ማስፈራራቶች አንፃር ሲታይ፣ ፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች እና ተማሪዎቻቸው፣ ‹ይሄ ሊታሰብ አይችልም› ብለው እንዲደመዱሙ በቂ መሠረት አላቸው። ነገር ግን፣ ይሄንን ጥያቄ በጥልቅ ለማየት የፈቃደኝነት ሁኔታዎችም ይታያሉ። ሊታሰብ ይችላል። ምናልባትም ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ከሚታሰበው በላይ የሰው ልጅ ሕይወት ላይ ብዙ የሚያስጉ ነገሮች ቢኖሩም፣ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ዓለማቀፋዊ የመንፈሳዊ ሀብቶች፣ ሳይንስ፣ ድርጅቶች እና ልምዶች ስላሉ፣ ይሄንን ሙሉ ለሙሉ እንዲቻል ያደርጉታል።

# ምዕራፍ 2

## ከግድያ ነፃ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያሉ ብቃቶች

*አማራጭ መንገዶችን ለመፈለግ ከወሰንን፣ የሰው ልጅ የኃይል ጥቃት የተሞላበት ዘመኑን መዝጋት እንደሚያስፈልገው በደንብ እናውቃለን ማለት ነው።*
*ዴቪድ ኤን ዳንኤልስ እና ማርሻል ኤፍ ጊሉላ*
*ሳይኪያትሪ ዲፓርትመንት፣ ስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ፣ 1970 ዓ.ም*

መግደል የሌለበት ማህበረሰብ ሊኖር ይችላል ለማለት ምን በቂ መሰረት አለ? የሰው ልጆች በሙሉ ለህይወት አክብሮት ሊሰጡ ይችላሉ ብሎ ለማሰብ እንዴት ይቻላል?

### የሰው ልጅ ያለመግደል ተፈጥሬሮ

በመንፈሳዊ መሠረት መጀመር እንኳን ብንችልም፣ በቅድሚያ አለማዊ እውነታዎችን እንይ። ብዙዎቹ የሰው ልጆች አይገድሉም። አሁን በሕይወት ካሉ እና ከዚህ በፊትም በምድር ላይ ከነበሩት ውስጥ፣ በጣም ጥቂቶቹ ግለሰቦች ናቸው ገዳይ የነበሩት። ለዚህም፣ የማንኛውንም ማህበረሰብ የግድያ መረጃ ማየት ይቻላል።

በጦርነት ወስጥ ያሉ ግድያዎችን እንመልከት። የዓለም የሚሊተሪ እና ኤትኖግራፊ ሚውዚየሞች፣ የዓለም ህዝብ ግማሽ የሆኑት ሴቶችን፣ የውጊያ ገዳዮች አድርገው ለማሳየት የሚጠቀሙበት መረጃ በጣም ጥቂት ነው። ምንም እንኳን ሴቶችም ግድያ ቢፈፅሙም፣ አንዳንዶቹ ጦርነቶችና አብዮቶች ውስጥ የተሰለፉ ቢሆንም፣ አንዳንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ለመንፈሳዊ ሥርዓቶች ተብለው የሚደረጉ የአካል ስቃይ እና የተሸነፉ ወታደሮችን ግድያ ቢያደርጉም፣ እና በብዙ ዘመናዊ ሰራዊቶች ውስጥ ለግድያ እየተመለመሉ ቢሆንም። ከዚህ ላይ፣ የወንዶችን በጣም ውስን የሆነ የመግደል ሚና ጨምሩበት። በምድር ላይ በአጠቃላይ ካሉት ወንዶች ውስጥ፣ ጦርነት ላይ የሚዋጉት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ደግሞ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው የመግደል ሚና የሚኖራቸው። አብዛኞቹ ግድያ የሚፈፅሙት ሳይፈልጉ ሲሆን፣ ቆይቶም በሰሩት ስራ የማዘን ስሜት ይኖራቸዋል። ምናልባትም ሳይከፋቸው በተደጋጋሚ መግደል የሚችሉት፣ ቢበዛ ሁለት ፐርሰንት ቢሆኑ ነው። ሌተናንት ኮለኔል ዴቭ ግሮስማን፣ ወንዶች በጦርነት ውስጥ መግደል ስላለመፈለጋቸው በተደረገ ዋና ጥናት ላይ ሲያብራሩ "ጦርነት ማለት፦ ለምንም ያህል ጊዜ በውስጡ የተሳተፉ ግለሰቦች ውስጥ 98 ፐርሰንቱ ላይ የሥነ-ልቦና ችግር የሚፈጥር ሁኔታ ነው። በጦርነቱ ምክንያት ወደ እብደት ያላመሩት ሁለት ፐርሰንት ደግሞ፣ ጦርነቱ ውስጥ ከመግባታቸውም በፊት ያበዱ ወይም አደገኛ የሥነ-ልቦና ችግር ያለባቸው ናቸው (ግሮስማን 1995-50)። ስለዚህም፣ «ሰዎች በተፈጥሮ ገዳይ ናቸው» ከሚለው ከተለመደው የፖለቲካዊ ሳይንስ አስተሳሰብ በተቃራኒ፣ የጦርነት ስልጠና የሚያተኩረው «የግለሰቦችን ጥብቅ የሆነ ያለመግደልን ፍላጎትን ማንሳት ላይ ነው»። (295)

የሰው ልጅ ቤተሰብ፣ መግደል ያለመቻል ሁኔታዎችንም ያሳያል። የሰው ልጆች በተፈጥሮ ገዳዮች ቢሆኑ ኖሮ፣ ወይም ግማሹ የሰው ልጅ ፍጡር እንኳን የገዳይነት ዝንባሌ ቢኖረው ኖሮ፣ ቤተሰብ በተለያየ ቅርጽ ሊኖር አይችልም ነበር። አባቶች እናቶችን ይገድሉ ነበር፤ እናቶች አባቶችን፣ ወላጆች ልጆችን፣ እና ልጆች ወላጆችን። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ያጋጥማሉ። ነገር ግን ይሄ ማለት፣ የሰው ልጅን ዕጣ የሚወስን የተፈጥሮ የገዳይነት ሕግን ያሳያሉ ማለት አይደለም። ቢሆን ኖሮ፣ የዓለም ሕዝብ ከረጅም ጊዜ በፊት ይጠፋ ነበር። በተቃራኒው፣ ምንም እንኳን ከባድ የቁሳቁስ እጥረትና ጥቃት ቢኖርም፣ የሰው ልጅ ቤተሰብ በማይገመት ደረጃ ሕይወትን እየፈጠረና እያቆየ ይገኛል።

ተደጋጋሚ የመፍትሄ መንገዶችን የሚሸት፣ የዓለም አቀፍ አለመግደል እንቅቅልሽ ሊፈታ የሚችለው፣ ምን ያህል ሰዎች በዚህ ምድር ላይ እንደኖሩ እና፣ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ ምን ያህሉ ገዳይ እንዳልሆኑ በማስላት ነው። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ብዛትን የሚያሳየው አንድ ግምት፣ ከ1 ሚሊዮን ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 2,000 ዓመተ ምህረት ድረስ የተሰላ ሲሆን፤ ይሄም

91,100,000,000 ሰዎች በምድር ላይ ኖረዋል ብሎ ይገምታል (ኬይፊትዝ 1966 ከዊክስ 1966፡ 37 ጋር ተደባልቆ በራምሴ 1999 ድጋሚ ሲሰላ)፡፡ ሩሜል ያቀረበውን የጦርና "ዴሞሳይድ" ሞቶች፣ ወደ ግማሽ ቢሊየን አሳድገን ብናየው፣ እና ትክክል ባልሆነ መንገድ «አንድ ሰው የተገደለው በአንድ ሰው ነው» ብለን ብናስብ፤ እና ይሄንን በሚያጠያይቅ መልኩ በስድስት አባዝተን፣ የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎችንም ከግምት ብናስገባ፤ ከ1,000 ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት ወደ 3,000,000,000 ገዳዮች ነበሩ ብለን ልንገምት እንችላለን፡፡ (ከ1 ቢሊየን ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት ያሉ ቁጥሮች አልተገኙም)፡፡ ነገር ግን፣ ይህም ግምታዊና የተጋነነ የግድያ ቁጥር ቢወስድ እንኳን፣ ከዓለም ሕዝብ ውስጥ ቢያንስ ዘጠና አምስት ፐርሰንቱ እንዳልገደለ ያሳያል፡፡ በቅርብ የተሰራ፣ የዩናትድ ስቴትስ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ስሌት የሚያሳየው፣ 10 ሰው ከ100,000 እንደሆነ ሲሆን፤ ይሄም በዓመት .01 ፐርሰንቱ ሕዝብ ግድያ እንደሚፈጽሙ ያሳያል፡፡ ከባድ የአካል ጥቃቶችም እንደ ነፍስ ማጥፋት ሙከራ ቢወሰዱ፣ (382 ከ 100,000 በ1997 ዓ.ም) 382 ፐርሰንት ከአጠቃላዩ ዩናይትድ ስቴትስ ሕዝብ ላይ .392 ፐርሰንት በመጨመር፣ የፈጸሙ ወይም ሙከራ ያደረጉ ገዳዮችን ያሳያል፡፡ በተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ያሉ የገዳዮች ፐርሰንቴጅ፣ እንደ አካባቢው ባህልና፣ ዘመን፣ በጣም ሊለያይ ይችላል (ኬሊ 1996)፡፡ ሆኖም ግን፣ የሰው ልጅ ደኅንነትና እየተባዛ መሄድ፣ የሰው ልጅ ባህሪ ውስጥ ካለው የመገዳደል ስሜት ይልቅ አብሮ የመኖር ስሜት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡

***መንፈሳዊ ስሮች***

በሰው ልጅ መንፈሳዊ ባህሎች ውስጥ ያሉ መረጃዎች፣ ግድያ የሌለበት ማኅበረሰብ ሊኖር እንደሚችል ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን ሃይማኖቶች፣ ዘግናኝ የዘር ማጥፋትን፣ የሰው መስዋዕትን፣ እና የአቶሚክ ግድያዎችን ለማብራራት እንደ ምክንያት የቀረቡ ቢሆንም፤ (ቶምሰን 1988 ዓ.ም) ነገር ግን የፈጣሪ፣ የታላቁ መንፈስ የእግዚአብሄር ዋና መልእክት፣ በምንም መልኩ «ኦ የሰው ልጅ ቃሌን ስማ! ሂድ ፈልግና ሌላ የሰው ልጅ ግደል!» አይደለም፡፡ በተቃራኒው መልእክቱ፣ "ሕይወትን አክብር! አትግደል!" ነው፡፡ በዓለም ያሉ ኃይማኖቶች በሙሉ ‹አትግደል› የሚል ትዕዛዝን ይዘው ይገኛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ማክስ ዌበር ‹መንፈሳዊነትና መንፈሳዊ ግጼታ ከፖለቲካዊ የመግደል ፍላጎት ጋር አይጣጣምም› ብሎ አስቀምጧል፡፡ ጄኒዝም እና የሂንዱ ሃይማኖት፣ *‹አሂምሳ ፓራም ዳርማ›* (አለመግደል የህይወት ተቀዳሚው ህግ ነው) የሚለውን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ የመጀመሪያው የቡዲዝም እምነት ቃል ኪዳን፣ "ሕይወትን ከመቅጠፍ መቆጠብ" የሚለው ነው፡፡ ቡዲዝም፣ የክርስትና እምነትና፣ እስልምና፣ "መግደል የለብህም" (ኤክስደስ 30፡13) የሚለውን መለኮታዊ ትዕዛዝ ይጋራሉ፡፡ ከጥንት የአይሁድ እምነት ትምህርቶች መካከል አንዱ፣ "የማንንም ሕይወት የጠበቀ አንድ ሰው ብዛት ያላቸውን ሰዎች እንዳዳነ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን የአንድን ሰው ሕይወት ያጠፋ ሰው፣ ዓለምን እንዳጠፋ ነው የሚቆጠረው" ይላል (አይሴንድራዝ 144)፡፡ የዚህ ትምህርት ፍሬ ሃሳብ፣ አንዳንድ መመሪያዎችን ጨምሮ፣ በእስልምና ኃይማኖት ውስጥም ይታያል፡፡ ማንኛውንም የሰው ልጅ፣ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል የፈፀመ ወይም በምድር ላይ ጥፋትን ያመጣ ከሆነ፣ የሰው ልጆችን በሙሉ እንደገደለ ይቆጠራል፡፡ እና፣ የማንንም ሕይወትን ያዳነ ሰው ደግሞ፣ መላው የሰው ዘርን እንዳዳነ ይቆጠራል (አል ቁራን 5፡32)፡፡ የአይሁድን፣ ክርስትናን፣ እና እስልምና ሃይማኖቶችን በሚያካትተው የባህይ እምነት እንደሚለው፤ «ፈጣሪን ፍሩ፣ ኦ ሰዎች፣ እና የማንንም ደም ከማፍሰስ ተቆጠቡ" (ባህኡላ 1983፡ 277)

ሰብአዊ ባህሎችም መግደል የሌለበት ማኅበረሰብን ተፈላጊነትና፣ መገኘት ያምናሉ፡፡ በኮንፊውሽን እምነት መሰረትም፣ በመሪዎች መካከል ቀናነት በሚኖር ጊዜ፣ ምንም የሞት ቅጣት አያስፈልግም (ፊንግ 1952፡ 60) በታኦይዝም የሰው ልጆች በቀላልና ተራ ሁኔታ እና ከተፈጥሮ ጋር በተስማማ መንገድ ሲኖሩ "ምንም እንኳን የጦርነት መሳሪያዎች ቢኖሩም ማንም ሰው በነሱ አይለማመድም" (ፉንግ 1952፡190)፡፡ በዘመናዊ ሶሻሊዝም አስተሳሰብ፣ ሰራተኞች እርስ በእርሳቸው መገዳደልን መደገፍ ሲያቆሙ፣ ጦርነቶች ይቆማሉ፡፡ ፀረ የዓለም ሁለተኛ ጦርነት መግለጫ እንዳወጀው፡፡

> ስለመደብ የተገነዘቡ የዓለም ኢንዱስትሪያል ሰራተኞች በሙሉ ሕሊናቸው የሰው ልጅ ደም መፍሰስን የሚቃወም ሲሆን፤ ይሄም እንደ ክዌከር ወይም "ጓደኛዊ ማህበረሰቦች" ለሃይማኖታዊ ምክንያት ሳይሆን፣ ‹ሁሉም አገር ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ፍላጎትና

ደኅንነት አንድ ዓይነት ናቸው› ብለን ስለምናምን ነው፡፡ የጀርመንን ኢምፔሪያሊስት ካፒታሊስት መንግሥት በከፍተኛ ሁኔታ የምንቃወም ቢሆንም፣ የማንኛውም አገር ሰራተኞችን ግድያና አካል ጉዳት እንቃወማለን፡፡ (ትሩ 1995፡ 49 ድፍረት ለተሞላበት ምሳሌ ባክስተር 2000ን ተመልከቱ)

በሁሉም ማኅበረሰብ ውስጥ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ይከለከላል፡፡ ለሰው ልጅ ያለ አክብሮትና፣ ለሕይወት ያለ ሃይማኖታዊ አክብሮት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በዓለም ውስጥ ባሉ መንፈሳዊ እና ሰብዓዊ ባህሎች ውስጥ ያለው የሰው ነፍስን ያለማጥፋት ሁኔታ፣ ግድያ የሌላባቸው ማኅበረሰቦችን እውን ለማድረግ ምን አስተዋፅኦ አለው? በአንድ እጅ፣ በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ለሰው ሕይወት ከፍተኛ አክብሮትን ለመትከል ያለውን የተቀደሰ ፍላጎት ያሳያል፡፡ በሌላ ጎኑ፣ የሰው ልጅ እንደዛ ያለ መርሆን ለመቀበል፣ ምላሽ ለመስጠት፣ ወይም ለመፍጠር ያለውን ችሎታ ያሳያል፡፡ የሰው ልጆች በማይቀየር መልኩ በተፈጥሮአቸው ገዳይ ቢሆኑ ኖሮ ምንም አይነት መርሆን መቀበል፣ ማስተካከል ወይም መፍጠር አይቻልም ነበር፡፡ ጨቋኞች ተጨቋኞችን ለማድከም፣ ገዳዮች ቅጣትን ለማምለጥ፣ እና አብዮትን ለማጥፋት ተብሎ መግደል የሌለበት መንፈሳዊ ሥርዓት ከበላይ ባሉት አካሎች ቢፈጠር እንኳን፤ ለነሱ ተብሎ የተፈጠረላቸው ሰዎች ሃሳቡን በአዎንታዊ መልኩ መቀበል እንደሚችሉ ነው፡፡

የአለመግደል መንፈስ፣ በታሪክ በተፈጠሩ አሰቃቂ ደም መፈሰሶች ጊዜ፣ ከነሱ በፊትና፣ በኋላ ተነስቷል፡፡ የዚህ አገላለፅ፣ በገዳዮች በጎ ፈቃደኝነት የተሰጠ ስጦታ ብቻ አይደለም፡፡ ወደ ዘመናዊው ዘመን ሳይታፈን በማለፍ፣ ከግድያ ነፃ የመውጣትን ፍላቶች እያነሳሳ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከመስቀል ታዋጊዎች በኋላ የነበረው ክርስትና፣ ከወረራ በኋላ የነበረው እስልምና፣ ከሆሎኮስት በኋላ የነበረው የአይሁድ እምነት፣ ከወታደራዊ ዘመን በኋላ የነበረው ቡዲዝም፣ እና ከቅኝ ግዛት ባህል በኋላ የነበሩ የአሜሪካ አካባቢ አገሬ ኗሪዎች ፡፡ ብዙ ደም መፍሰስ በነበረበት ሃያኛው ክፍለ ዘመን የሚታየው፣ ለዓለምአቀፋዊ ለውጥ ቆመው በነበሩት ደፋር አስተዋፅኦዎች ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ክርስቲያን የሆኑት ቶልስቶይ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ ሂንዱ የሆነው ጋንዲ፣ ሙስሊሙ ጃፋር ካን፣ አይሁዱ ጆሴፍ አቤሊያ፣ ቡዲስቱ ደላይ ላማ፣ ግሪን ፔትራ ኬሊ እና ሌሎች ብዙ ያልተቆጠሩና ያልተነገሩ፡፡

በሁሉም ሃይማኖቶች የሚታየው ያለመግደል መንፈስ፣ እና በመርሆ የተቀመጡ የተግባር ምሳሌዎች፣ በመቶ ሚልየን አማኞች የመነሳሳትና፣ የመረጋገጥ እድሉን ይከፍታሉ፡፡ በአለመግደል ምርጫ፣ እና ለመግደል ባለ ኃላፊነት መካከል ያለው ውጥረት እና የሱ ጤናማ ያልሆነ ውጤት፣ አለመግደል ላይ ያተኮረ የግል እና ማኅበሰረባዊ ለውጥን ለማምጣት ያነሳሳል፡፡ የአለመግደል ስሮች፣ በሁሉም ባህል ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ የሰው ዘር መንፈሳዊ ቅርስ በአጠቃላይ የባንያን ዛፍን ሕይወት እንደሚደግፍ፣ ባለብዙ የስር መስመር ነው፡፡ መነቃቃትና በሕይወት መቆየት፣ ከሙሉ የስሩ መረብ ወይም ከአንዱ ክፍል ሊወሰድ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የሕይወትን ኃይል ይወስዳሉ፡፡ በሃይማኖታዊ እና ሰብአዊ እምነቶች ውስጥ ያለው ለሕይወት የሚሰጥ ክብር፣ መግደል የሌለበት ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል ለሚለው አስተሳሰብ ጠንካራ መንፈሳዊ መሠረት ይሰጣል፡፡

**ሳይንሳዊ መሰረቶች (ስሮች)**

"ወደ ጥቃት የሌለው ሁኔታ፣ በሃይማኖት ብቻ መድረስ አንችልም፡፡" ይህ ምክር፣ የህንድ ተቀዳሚ የሃይማኖት መሪ የሆነው አቻር ማህፐራጂያ ሲሆን፤ እሱም የጄን ባህል የሆነው *አሂምሳ* (ጥቃት የለሽነት) ፈጣራዊ ወራሽ ነው፡፡ በጄን አስተሳሰብ ውስጥ፣ "አሂምሳ የሁሉም የሕይወት ደረጃዎች ልብ ሲሆን የሁሉም የተቀደሱ ፅሁፎች ፍሬ ነገር፣ ድምር … ዋና ነገር … የሁሉም ቃል ኪዳኖችና ጥንካሬዎች ነው፡፡" (ጄን እና ቫርኒ 1993 ፡139) ለአቻር ማህፐራጂያ፣ ጥቃት የሌለበትን ማኅበረሰብ እውነታ ማድረግ የሚቻለው፣ ግለሰቦች በራሳቸው ውስጥ ጥቃት እንደሌለ እንዲውቁ በማስቻል እና፣ ዘመናዊ ‹ኒውሮሳይንስና› መንፈሳዊ እውነታዎችን በማቀላቀል በማኅበረሰብ ውስጥ እንደገልፁት በማስቻል ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ እንደገለፀው፣ ጥቃት የሚፈጠረው በኢንዶክሪን ግላንድ

የሲሚፓቴቲክ እና ፓራሲምፓቴቲክ ነርቨስ ሲስተምን በመንካት በሚፈጥሩት ስሜት ሲሆን፣ ከምንመገበው ነገር ጋር የተገናኘ ነው። በተጨማሪም፣ ሳይንሳዊ ኒውሮሎጂካል ሲስተማችን ውስጥ ያለውን እውቀታችን በመጠቀም፣ አእምሯችን ቀለል ያሉ የሜዲቴሽን እንቅስቃሴዎችን እንዲሰራ በማድረግ በውስጣችን ያሉ ኢ-ጥቃታዊ ስሜቶችን ማሳደግና፣ ራሳችን ግድያ ለሌለበት ማህበራዊ ኑሮ ለማቆም እንድንፀና ማድረግ እንችላለን (ማሀፐራጅና [sic] 1987 እና 1994፣ ዛቤሪ እና ኩማር 1992)

ግድያ የሌለበት የሰው ልጅ ችሎታ እንዳለ ለመተማመን፣ ያሉን ሳይንሳዊ መሠረቶች ምንድን ናቸው? ሳይንስ በሰፊው ሲብራራ፣ በጥያቄና ሙከራ (ማለትም እውነታዎች፣ መላምቶች፣ እና እውነታንና አስተማማኝነትን በመለኪያ ዘዴዎች) ተጠቅሞ የተገኘ የእውቀት አይነትን በሙሉ ይጨምራል። የሣይንሳዊ አብዮት መምጣት አመላካች የሚባለው፣ ፈላስፎች የተወሰኑ ሰው የተቀበሏቸውን አስተሳሰቦች በጥያቄ ውስጥ ማስገባት ሲጀምሩ ነው።

ከአለመግደል ጋር ተያይዞ ይህ የተደረገው፣ በኤ.ሪቻርድ ኮንራድ (1974) ሲሆን፤ እሱም ‹ከአስገድዶ መድፈር እስከ ሆሎኮስት ያሉ ጥቃቶችን ማለፍ የሚቻለው በመግደል ነው› የሚለውን የተለመደ አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ አስገብቷል። ኮንራድ እንደሚለው፣ አንድ ጥቃት ላይ የተመረኮዘ የችግር መፍቻ መንገድ፣ ሦስት ሀሳቦችን ይንተራሳል። አንደኛ፣ ሁሉም ግድያ የሌለባቸው አመራጮች ተለይተው እንደታወቁ፤ ከዛ ሁሉም እንደተሞከሩ፤ እና ሁሉም እንዳልተሳኩ። ነገር ግን፣ እነዚህ አስተሳሰቦች እርግጥ ሊሆኑ አይችሉም። ግድያ የሌለባቸው የችግር መፍቻ አማራጮች ተቆጥረው ሊያልቁ አይችም። የታወቁትን አማራጮት እንኳን ስራ ላይ ለማዋል የጊዜ፣ ሀብት፣ እና ሌሎች እክሎች ይኖራሉ። በመሆኑም አንድ ጥቃት የተሞላበት አማራጭ ብቻ ውጤታማ ነው ብሎ በእርግጠኝነት መደምደም አይቻልም። ስለዚህ፣ ኮንራድ ጥቃትን ከሚቀበል ፊለዞፊያዊ አስተያየት፣ ወደ ግድያ የሌለባቸው አማራጮችን ለማግኘትና የሚሞክር አስተያየት መለወጥ እንደሚገባ ያብራራል። እንደዘህ አይነት መንገድ፣ የሰው ልጅን ጥያቄ የሌለው የግድያ ችሎታ ወደሚቃረኑ ሳይንሳዊ ግኝቶች ሊመራ ይችላል። (በተጨማሪም ዮደር 1983 ይመልከቱ)

‹የሰው ልጆች በእንስሳዊ ተፈጥሯቸው ምክንያት ገዳይ ናችው› የሚለው አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። የቱሌን ዩኒቨርስቲ ሳይኮሎጂስት የሆኑት ሎህ ሴንግ ሳይ (1963) እንዳሳት፣ አይጥ ገዳይ የሆነ ድመትና፣ የቱቦ ውስጥ አይጥ ከአንድ ሰሃን በሰላማዊ መንግድ እንዲመገቡ ማስተማር ይቻላል። የተጠቀሙት ዘዴ፣ በማድረግ የማስተማርና የማኅበራዊ ትምህርት ቅልቅል ነው። በመስታወት መከፋፈያ ተለይተው የተቀመጡት ሁለቱ እንስሳት፣ በመጀመሪያ የተማሩት፣ ወደ አንድ የመመገቢያ ሰሀን ምግባቸውን ለመጣል ሁለቱምም ተራ በተራ የሚጫኑት ነገር እንዳለ ነው። ከሰባት መቶ ሙከራዎች በኋላ መለያየው ተነስቶ ምንም የደም መፋሰስ ሳይከሰት ቀርቷል። ሳይ እንደደመደሙት፣
በሳይንስ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጠቃሚ ሙከራዎች በኋላ የተፈጥሮ ጠላቶች የሚባሉት ድመትና አይጥ ሊተባበሩ እንደሚችሉ እናም እንደቻሉ አሳይተናል። እንደዚህ ዓይነት ግኝት፣ ‹የእንስሳ ባህሪ ውስጥ ሊጠፋ የማይችል፣ ጦርነትንና ውጊያን እንዲኖሩ የሚያደርግ፣ ጠበኝነት አለ› የሚለውን የቀድሞ ሳይኮሎጂ እምነት ያፈርሰዋል። (1963፡ 4)

ሳይ «ለዓለም ሰላም መላምታዊ መሠረት ሊሆን የሚችል የተፈጥሮ መሠረት፣ እኛ በሰራነው ጥናት ተጥሏል ብለው ያምናሉ» ካሉ በኋላ "በመተባበር በሕይወት መቆየት" የሚል ሳይንስን መሠረት ያደረገ ፍልስፍና እንደኖርና፣ ‹ውድድር የተሞላበት የማናመልጠው የግድያ ሁኔታ አለ› የሚለው አስተሳሰብ እንዳይቀጥል ጥሪ ያቀርባሉ። በፍፁም ከዚህ በተለየ ትምህርት፣ የፊዚክስና የሳይንስን ታሪክ አጥኚ የሆነው አንቶኒዮ ድራጎ፣ የካንቶኒያን እና ኒውቶኒያን የግጭት መፍቻ ዘዴ ሜካኒክስን ውጤቶች በማነጻጸር፣ ተማሳሳይ የሆነ እና ላቅ ያለ መተባበርን ወደሚደግፍ፣ ሳይንስን መሰረት ያደረገ ምክር ያቀርባል (ድራጎ 1994)። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሳይኮቴራፒስቱ ጀሮም ዲ ፍራንክ ሁሉንም የሚጠቅም የጋራ ግብ ላይ ለመድረግና ገዳይ የሆኑ መቃረኖችን ለማስወገድ ትብብርን መፍትሄ አድርጎ ያቀርባል። (ፍራንክ 1960፡ 261-2, 1993 ዓ.ም 204-5)

የሰው ልጅ ገዳይ ባህሪ የኖረው ከ"ገዳይ ጦጣዎች"፣ ሂደታዊ እድገት በመምጣቱ ነው የሚለውን አስተሳሰብ፣ ሌላ በማዕከላዊ አፍሪካ ውስጥ ከሚገኝ ገዳይ ካልሆነ ‹ቦኖቦ› ከሚባል ተመሳሳይ ዝርያ ካለው የዝንጀሮ ዓይነት በመነሳት የተሰራ ጥናት፣ ተቃርኖውን ያቀርባል (ካኖ 1990)፡፡ በኮንጎ ውስጥ ያሉ ማንጋንዱ የሚባሉ፣ ጫካውን ከነዚህ ቦኖቦ ከሚባሉ ዝንጀሮዎች ጋር የሚጋሩ ኅብረተሰቦች፣ የቦኖቦችን ግድያ አጥብቀው ይቃወማሉ፡፡ ይሄም በጥንቱ ጊዜ የነበሩ አያቶቻቸውና ቦኖቦዎች እንደዘመድ አንድ ላይ ይኖሩ ነበር ከሚል እምነት በተነሳ ነው፡፡ (ካኖ 1990፡ 62) ከጎሪላዎች ቺምፓንዚዎች እና ሌሎች የጦጣ ዝርያዎች በተለየ ቦኖቦዎች እርስ በርሳቸው ሲገዳደሉ ታይተው አይታወቅም፡፡ (*ራንግሀም እና ፒተርስን 1990 ዋል 1997*)፡፡ በተጨማሪም በቅርብ የተደረጉ «ሰላምን መፍጠርና»፣ «እርስ በርስ የመጠቃቀም ሁኔታ" የማይገዳደሉ በጦጣ መሰል ዝርያዎች ላይ ምን እንደሚመስል ያጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በእንስሳት ውስጥ የመግደል ብቻ ሳይሆን ወደሰው ልጅ የጊዜ ለውጥ ሲደረስ ያለመገደል ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያመላክታሉ፡፡ ( ዋል 1989; 1996) የእንስሳት ሰላማዊ ተፈጥሮ ያለ ሲሆንነ ክሮፖትኪን ( 1914 ) ፣ ሶርኪን ( 1954 ) እና አልፊ ኮን ( 1990 ) እንዳሳዩት የሰው ልጅ ተፈጥሮ የትብብር፣ የመጠቃቀም እና "ብሩህ ጐኖች" እንዳሉት ነው፡፡

በሰው ልጆች እና በእንስሳት መካከል ያለውን የግልፍተኝነት ሁኔታ በማፃፀር ያጠናው ኢቶሎጂስትና አንትሮፖሎጂስት የሆነው ኢሬየስ ኢብል ኢብላፈልድት እንዳገኘው፣ መንፈሳዊ ለሆነው ያለመግደል ፍላጐት ተፈጥሮአዊም የሆነ መሰረት አለው፡፡ " በብዙ የእንስሳት ዝርያዎች ውስጥ ያለው የውስጥ ጥል የራሱን ስርዐት የተከተለ በመሆኑ የአካል ጉዳት አያስከትልም" ብሎ ያስተዋለ ሲሆን ፣ የሰው ልጅም ደም መፋሰስን ለማስቀረት የሚጠቀማቸው መንገዶች እንዳሉ አግኝቷል፡፡ "በተወሰነ መንገድ ተፈጥሮአዊ የማጣራት መንገድ 'መግደል የለብህም' የሚለውን ትዕዛዝ ያስቀምጣል፡፡" ነገር ግን በባህል፣ አንዳንዶችን እንደ ሙሉ ሰዉ ባለመቁጠርና፣ ሊገደሉ ይችላሉ ብሎ በማሰብ፤ የሰው ልጅ ተፈጥሮ መግደል የለብህም ብሎ ያስቀመጠለትን ትዕዛዝ አልፎ ይገኛል፡፡ በጦርነት ጊዜ "የእምነቶች መጋጨት የሚታይ ሲሆን፣ አንድ ሰው ጠላቱን ምርኮኛ አድርጐ እንደሰው በተጋፈጠው ጊዜ በሚሰማው የህሊና ፀፀት ይታያል፡፡" ሌላ ይሕ የሚታይበት መንገድ፣ ከጦርነት የተመለሰ ተዋጊ፣ የማህበረሰብን አቀባበል ለማግኘት ብሎ በሚያደርገው የመንፃት ሂደት ነው፡፡

የኢብል አብሰፈልድትን መላምት ግሮስማን በመደገፍ እንደሚያቀርበው፣ "በታሪክ ውስጥ በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ ጦርነት ውስጥ ያሉ ወንዶች ጠላትን ለመግደል አይሞክሩም፡፡ የራሳቸውንም ሆነ የጓደኞቻቸውን ህይወት እንኳን ለማዳን ሲሉ፡፡" ( ግሮስማን 1995፡ 4) ግሮስማን እንደጠቆመው በቀጥታ የግድያ ተግባር የፈፀሙ ወታደሮች ምንም ግድያ ካላደረጉት የበለጠ የስነልቦና ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ የወታደሮች ሳይኮሎጂስቱ እና ኢቶሎጂስትና አንትሮፖሎጂስት የሆኑት ሁለቱ ምሁሮች የሚለያዩት ባቀረቡት የፖሊሲ ውጤት ነው፡፡ የመጀመሪያው ያቀረበው፣ ያለመግደል ፍላጐትን ለማጥፋት መያዊ ስልጠና ሊሰጣቸው እንደሚገባ ነው፡፡ ሁለተኛው እንዳለው፣ ችግሩ ባህልንናነ ያለመግደል የሰው ልጅን ተፈጥሮአዊ ስሜት አንድ ላይ እንዲጣጣሙ ማድረግ ላይ ነው፡፡ ኢብል - ኢቢስፈልድት እንዳለው፣ አለም አቀፍ የሰላም ፍላጐት ስር የሚገኘው በባህላዊና ተፈጥሮአዊ አስተሳሰቦች ግጭት ውስጥ ሲሆን፣ ይህም ሰዎች የተፈጥሮአዊና ባህላዊ አስተሳሰባቸውን ወደ መስማማት የሚያመጣ የሀሳብ ማንገዋለልን ይፈጥራል፡፡ ህሊናችን ያለን ተስፋችን ነው፡፡ በዚህ ላይ መመስረት፣ በሚመዛዘን የተሞላ ሂደታዊ ለውጥ ሰላም ሊያመራ ይችላል፡፡ ይህ፣ ጦርነት በሌሎች ደም መፋሰስ በሌለባቸው መንገዶች መካሄድ አለበት የሚለወን ግንዛቤ ፣ ቀድሞ ይገምታል፡፡ (1979: 241)

የአእምሮ ሳይንስ፣ መግደል የሌለበት የሰው ልጅ ችሎታ ይኖራል የሚለውን ሀሳብ የሚደግፍ መላምት ያቀርባል፡፡ ፈር ቀዳጅ የሆነው ብሩስ ኢ.ሞርተን ( 2000 ) " ኒውሮሪያሊዝም " ብሎ በሰየመው ስራው "ዱዋል ኩዋድብሬን ሞዴል ኦፍ ቢሄቭየራል ላተራሊቲ" የሚል ሀሳቡን የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ለመግደልና ላለመግደል የሚቀርቡ የኒውሮ እና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶችን ያሳያል፡፡ የሞዴሉ አራቱ ክፍሎች " በአንድ ቴድራቲክ ስርዐት ስር ያሉ ሁለት ቅርፆችን ይዞ ይንቀሳቀሳል፡፡" እነሱም የአእምሮ መሰረታዊ ስርዐት ( ደመነፍስ ) ፣ ተቀጥያ ስርዐት ( ስሜቶች) ፣ የቀኝና ግራ ክፍያ ስርዐቶች ( ምናብና እውቀት ) ፣ እና ኒዎሴሬብራል ስርዐት ( በደመነፍስ የማወቅ ችሎታ) ናቸው፡፡ ሞርተን፣ ከፍተኛ የሆኑ መንፈሳዊና ማህበረሰባዊ እውቀቶችን በኒዎ ሴሬብራል በደመነፍስ ማወቅ ችሎታ ውስጥ ይከትል፡፡ ይህ " ከፍተኛ ምንጭ እወተኛ፣የፈጣሪ ችሎታ ያለው፣ ራስን የሚገዛ፣ለሌሎች ማሰብን፣ መተባበርን፣

አዛኝነትንና፣ ጥቃት መሆንን ይይዛል" ። የቡድኑን የረዝም ጊዜ ቆይታ የሚረዳ ሲሆን በአእምሮ ላይ ብቻ የሚገኝና ለሁሉም ያለ ሁኔታ ነው። የ" ምንጨ " ወደ እውቀት መምጣት፣ ስልታዊ ነገሮችን ይጠይቃል። ለሞት ሊያደርስ የነበረ አደጋ፣ የተወሰኑ ስሜትን የሚቀይሩ እፆች፣ እና ከሁሉም በላይ ጥልቅ የሆነ መረጋጋትና ማሰብ። በሁሉም ቀን ማህበረሰባዊ ኑሮ ውስጥ " ምንጨ" በደመነፍስ ወደ "ጥቃት የሌለበት ማህበረሰብ" መምጣት ይመራል። በህይወት ለመቆየት የሚያዳግቱ ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳል፣ ከነሱም ይጠቀማል።

በመሆኑም ኒውሮሪያሊስት የአእምሮ ሳይንስ፣ በራስ ለሚፈጠር ያለመግደል ቃል ኪዳን እና ማህበረሰባዊ ለውጥ መሰረት ሲሆን ፣ ይህ ማህበረሰባዊ ለውጥ ያለመግደል መንፈሳዊ ስሜትና የተፈጥሮ ፍላጎት አለመኖር ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ይህም ከሂንዱ ቪቬንናቶ ካለው እይታ ጋር ይመሳሰላል። ማለትም የትልልቅ ሀይማትና አባቶች ሀላፊነት አምላክን ከውጭ ማምጣት ሳይሆን ፣ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለውን አምላካዊነት ማውጣት ነው። ይህ ከክርስቲያኑ ቶልስቶይ አባባል " የእግዚአብሔር ግዛት በውስጣችሁ ነው" ካለው ጋር ይመሳሰላል ( ቶልስቶይ 1974 [ 1893 ] ) ። ይህንን ፣ በአስራምስተኛው ክፍለ ዘመን አምላክን በፀሎት ለመገናኘት ይሞክር ከነበረው ካቢር ጋር ያስተያዩ።

> በሁለቱ አይኖች መካከል ጌታ አለ
> የአምላክ መልእክተኛ፣
> በሰውነታችሁ ውስጥ አምላካችሁ አለ።
> ስለዚህ እሱን ለማየት ለምን የውጭኛውን አይናችሁን መክፈት ያስፈልጋል?
> ( ሴቲ 1984: 56-7)

ነገር ግን ተፈጥሮን መሰረት ያደረገ የአእምሮ በትክክል አለመስራት፣ አንዳንድ ግለሰቦችን ግልፍተኛ ገዳይ ሊያደርጋቸው ይችላል? ይህ የገዳይ ስሜት በተፈጥሮ የተመራ በባህል እና ትምህርት ያልተፈጠረ እንኳን ቢሆን ፣ ሳይንሳዊ ግኝት ተፈጥሮአዊ ገዳዬችን ከገዳይነት ስሜታቸው ነፃ ለመውጣት ቃል ይገባል። ይህንን የሚያደርገው ሌሎች የሰብአዊነት ባህሪያቸውን ሳይገል እንደሆነ ያስቀምጣል። ዘመናዊ ኒውሮሳይንስ፣ ጄኔቲክስ ( ስነ ባህሪይ ) ፣ እና ሌሎች ባዮሳይንሶች በተነሱበት ዘመን ውስጥ የሰው ልጅ ሊያመልጠው የማይችል የገዳይነት ባህሪ ምንም ከተፈጥሮአዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ እንኳን ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም።

ፈር ቀዳጅ የሆነ ምሳሌ በመሰረታዊ እና ተግባራዊ ጥናቶች የተሰጠ ሲሆን ፣ ከዚህ ውስጥም ኒውሮሳይኮሎጂስት የሆነው ጂምስ ደብሊው ኘሬስኮት እና ኒውሮሳይኪያትሪስት የሆነው ሮበርት ጂ ሂዝ ( ሬስታክ 1979: 118-133 ) ይጠቀሳሉ። እነሱ የሚያቀርቡት መላምት፣ በአንዳንድ ግለሰቦች (" የደስታ መንገዶች" ) ላይ የሚፈጠር ችግር እንዳለ ሲሆን ፣ እነዚህ ስሜትን የሚቆጣጠር የአእምሮን ክፍል ከሰውነት እንቅስቃሴ ( ሴሬብለም ) ጋር የሚያያይዙ ናቸው። በመቀጠልም የሚያቀርቡት መላምት የነዚህ መስመሮች መዳበር ወይም መበላሸት በልጅነት እድገት ጊዜ ያለ የሰውነት እንቅስቃሴ መጠን ጋር የተያያዘ ሲሆን ፣ ይህንንም ለማረጋገጥ በተደረገ ሙከራ የቺምፖንዚ ልጆችን ጭንቅላት እንደማይነቃነቅ አድርጐ አጥብቆ በመያዝ፣ ወይም በሚሽከረከር ወንበር እያሽከረከሯቸው በመሞከር ታጠንቷል። በጥናቱም፣ ተይዘው የተቀመጡት ቺምፖንዚዎች የበለጠ ለጠብ የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ የሚንቀሳቀሱት ማህበራዊ ሆነው ተገኝተዋል። ይሄንን ወደ ድርጅታዊ ገዳዬችና ሰዎች በመተርጐም፣ ትንሽ በእጅ በሚያዝ መቆጣጠሪያ ሊሰራ የሚችል ኤሌክትሮድ፣ የግድያ ፍላጐት ያለው አንድ ሰው የኋላ የአእምሮ አካል ላይ ገጠሙ። ይሄ "ሴራብላር ስቲሙሌተር " ወይም " ሴራብለር ፔስሜከር " በመባል ይታወቃል። የመግደል ስሜት በሚነሳበት ጊዜ አንድ ሰው የደስታ መተላለፊያ መንገዶቹን እንዲሰሩ በማድረግ ስሜቱን ያጠፋል። አንዳንድ " ወንጀል መፈፀም ደረጃ የደረሱ እብደት ያለባቸው" ተብለው የተመደቡ ሰዎች ከብዙ ዘመናት ብቸኝነትና እስር በኋላ ይሄንን ሲጠቀሙ ወዲያው እረፍት ተሰምቷቸዋል። ሌሎቹ ደሞ፣ ቀስ በቀስ የግድያ እና የራሳቸውን ነፍስ የማጥፋት ፍላጐታቸው እየጠፋ ሄዷል። ሌሎችም ያልተሳካ አሉ። አንድ ጊዜ ሴሌቤለር መስመሩ ተበጥሶ፣ አንድ ታካሚ መቀስ በመጠቀም ነርሷን ገድሏል። ሆም ግን ፣ የዚህ ፈር ቀዳጅ ሂደት ውጤታማነት፣ ቴክኖሎጂያዊና መላምታዊ ፈጠራዎች፣ ግድያ ተፈጥሮአዊ ባህሪ አለው ከሚለው አሉታዊ አስተሳሰብ እንዲላቀቅ እየጠየቀ ነው።

ሌሎች አዎንታዊ የሆኑ አለመግደል እንደሚቻል የሚያሳዩ መረጃዎች ከፖለቲካዊ ሳይንስ አሉታዊ አስተሳሰብ በመቃረን ተገኝተዋል። አንዱ፣ በሀያ ሶስት የስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ ሳይኪያትሪስቶች

የተደረሰ መደምደሚያ ሲሆን ፣ እነዚህም ኮሚቴን በመፍጠር የማርቲን ሊተር ኪንግ ጁኒየር፣ የሴኔተር ሮበርት ኤፍ ኬኔዲን መገደል መሰረት በማድረግ በዩናይትድ ስቴትስ ውጥስ ያለውን “ የሀይል ጥቃት ቀውስ” አጥንተዋል:: (ዳንኤልስ፣ ጊሉላ እና አችበርግ 1970) :: የሀይል ጥቃትን እና ፀበኝነትን ከባዬሎጂ፣ ሳይኮዳይናሚክስ፣ የአካባቢ ጥናት፣ ንዴት፣ በቡድን ውስጥ ያለ ግጭት፣ መገናኛ ብዙሀን፣ የጦር መሳሪያዎች፣ የአእምሮ ህመም፣ የእፅ አጠቃቀም፣ እና ሌሎች ጉዳዬች ጋር ካጠኑት በኃላ፣ ዳንኤልስ እና ጊሉላ እንደደመደሙት፣ “ *ስለለው ልጅ በበቂ ሁኔታ እውቀት ስለለን የሀይል ጥቃት ዘመኑን ለመጨረስ ሌሎች አማራጨችን መከተል ይችላል::*” [አፅንኦት የተጨመ] ( 441)

ከጆርጅ ኤፍ ሰለሞን ( 1970 ) የቀረቡ የግድያ ጉዳይ ጥናቶች ግድያን ልንረዳውና ልናቆመው የምንችል ሁኔታ እንደሆነና “ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪ” እንዳልሆነ እንድንረዳ አድርገዋል:: በአንድ ጥናት ላይ ስሜት የሌላቸው የሚመስሉ፣ ዝም ብለው አነጣጥረው ሴቶችን የሚገድሉ ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ልምድ ሲታይ፣ በቁማርተኛ አባት የተተወ ልጅ፣ በመጠጥ ሱስ እጅ በተለከፈች እና ሱሰኛ በሆነች እናቱ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰበት፣ ለመሳሪያ ልዩ ፍቅር ያለው፣ እና በቤተሰብ አባል ጋር የተደረገ ግንኙነትን ላለማሰብ ተብሎ የሚደረግ የእፅ አጠቃቀም ይገኙበታል:: በሌላ ጥናት፣ የፈታትን ማለቱን አዲስ-ባል የገደለ ግለሰብ የቀድሞ ታሪክ ሲጠና:- ድህነት፣ አባቱ እናቱ ላይ ለሚፈፅመው ጥቃት ጥላቻ፣ አባቱ ጭንቅላቱ ላይ ከደበደበው በኃላ የተፈጠረ የመንቀጥቀጥ ችግር፣ የእናቱ ማጣጣል እና ማንጓጠጥ፣ በእህቶቹ የመደብደብ፣ በመርከብ ውስጥ ሰርጀንት ሆኖ የመቀጠር፣ በቡና ቤት ውስጥ ያገኛትን ሴተኛ አዳሪ የማግባት፣ ሁለት ልጆችን ከሷ የመውለድ፣ እሷ ላይ አካላዊ ጥቃት የማድረስ፣ ለመርከበኛነት ስራው በተጓዙበት ወቅት በማመንዘሯ እጇ ላይ በስለት ቆርጦ ራሱን ሊያጠፋ መሞከር፣ በ .38 ካሊበር የእጅ ሽጉጥ እሷ ያደረገችበት ማስፈራራት፣ የእጅ ሽጉጥ መያዙ፣ ከዛም እሷን ሳይሆን አዲስ ያገባችውን ሰው በቤት ውስጥ ሶስቱ በተሳተፋበት፣ ከልጆች ድጋፍና የጥየቃ መብት ጋር የተያያዘ ጭቅጭቅ ተነስቶ መግደል ይገኝበታል::

ሰለሞን እንደደመደመው

> እንደ ሳይኪያትሪስት የሰው ልጅ ባህሪ ሊሻሻል ይችላል የሚል ጥብቅ አቋም አለኝ:: የመከላከል እና ማዳን ላይ ያሉ የኛ ድክመቶች ካለማወቅ የመጡ ሲሆን ፣ ይሄም ቀጣይ ጥናቶችን በማድረግ ሊሻሻል ይችላል:: ይህ የሚደረገው:- ተቀባይነት ያላቸው ግን ተግባራዊ ያልሆኑ መርሆወች ላይ፣ አዲስ ፈጠራን ለማድረግ ያለ ፍራቻ፣ ከማህበረሰብ ማፈንገጥ ላይ ያለው ጥላቻ፣ ሌሎች ሊድኑ አይችሉም ተብለው ከሚታሰቡ አስተሳሰቦች ነው:: የሰው ልጅ የማደልና የመዳን ችሎታ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም ለሀይል ጥቃት ያለው አዝማሚያ ሊቆም ይችላል የሚል ተስፋ አለ:: ( 387 )

በአንትሮፖለጂ፣ የሰው ልጅ ጥቃት ለሌለበት እና ሰላማዊ ለሆነ ህይወት ያለው ችሎታ፣ ከጥቃትና ጠብ ጋር በሚያያዝ አዲስ የጥናት ፍላጐትን እየፈጠረ ሲሆን ፣ ያም መግደል የሌለበት ማህበረሰብ ሊኖር አይችልም የሚለውን አስተሳሰብ በጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጓል:: ሌስሊ ኢ. ስፖንሴል እንደሚያብራሩት “ጥቃት የሌለባቸውና ሰላማዊ ማህበረሰቦች ያሉ አይመስሉም- ያ የሆነው የእውነት ስለሌሉ ሳይሆን ፣ ሰላምና ጥቃት የለሽነት፣ በሚዲያ፣ በጥናቶችና ሌሎች አካባቢዎች በተገቢው መንገድ ስላልታዩ ነው::” በተጨማሪም “ የጥቃት የለሽነት እና የሰላምን ባህሪዎች፣ ሁኔታዎች፣ ምክንያቶች፣ ስራዎች፣ ሂደቶች እና ወጤቶች ማጥናት የጥቃትንና ጦርነትን ሁኔታዎች ከማጥናት እኩል አስፈላጊ ነው::”
( ስፖንሴል: 19949: 18-9 )

የሆቤሲያን አስተሳሰብ የሆነው የጥንት ሰዎች የገዳይነት ስሜት፣ ሳይንሳዊ ጥያቄዎች የቀረቡበት ሲሆን ከነሱም ውስጥ ፒየሮ ጂዎርጂ ( 1999 ) እና ጂ.ም.ጂ ቫን ደኔን ( 1990;1995 ) ይገኙበታል:: በኤትኖግራፊክ ሰነፅሁፍ ውስጥ፣ ባለፈው ክፍለዘመን ላይ በተገኙ 50,000 “ የጥንት” ህዝቦች ጋር በተያያዘ ስለሚደረግ ጦርና የፀብ ጊዜዎች ላይ በተደረገ ጥናት ቫን ዳር ዴኔን ማረጋገጫ ያገኘው 2, 000 ቡድች ላይ ብቻ ነው:: “ ጠብ ወዳድነት” ላይ በተቀሩት ቡድች ውስጥ መረጃ አልተገኘም ማለት፣ ሰላማዊ ነበሩ ማለት እንዳልሆነ፣ ቫን ዳር ዴኔን እያመነ፤ ነገር ግን የሰው ልጅ በሙሉ ጠብ ወዳጅ ነው የሚለው እምነት ተቀባይነት እንዳይረው ያስጠነቅቃል:: ( 1990: 257, 259,264-9 ) ከአቦሪጂናልስ እስከ ዘኒ ድረስ ያሉ 395 “ ጦርነት የሌለባቸው የሚመሰሉ” ማህበረሰቦችን ኤትየግራፊያዊ መረጃ እየጠቀሰ ያሳያል:: ( 1995: 595-619 )

አንትሮፖሎጂያዊ ስነፅሁፎችን በማጥናት ብሩስ ዲ. ቦንታ ( 1993 ) አርባ ሰባት ማህበረሰቦችን ያየ ሲሆን

*ያም የሰው ልጅን "ሰላማዊነት" ችሎታ ያሳያል፡፡*

> *ሰላማዊነት .. ሲተረጎም ሰዎች በተሻለ ደረጃ እርስበርሳቸው ከመስማማት የሚማሩበት ሁኔታ ሲሆን፣ በአዋቂዎች፣ በአዋቂዎችና ልጆች፣ በተለያዩ ፆታዎች መካከል ጥቂት የአካል ጥቃት የሚታይበት ሁኔታ ተደርጎ ይቀመጣል፡፡ በተጨማሪም ሰዎች ግጭትን የመፍቻ እና ጥቃትን የማስቀሪያ ዘዴዎችን ያዳበሩበት ሲሆን፣ ጥቃትን ( ለምሳሌ ጦርነትን) ከሌሎች ሰዎች ጋር ለማስቀረት የቆሙ፣ ልጆቻቸውን ሰላማዊ መንገድ ለማሳደግ የሚጥሩ፣ እና ራሳቸውን እንደ ሰላማዊ የሚቆጥሩ ጠንካራ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው፡፡( 4 )*

*ቦንታ የሰላማዊነትን ማረጋገጫ ካገኙባቸው ማህበረሳቦች ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በአሚሽ፣ አናባፐቲስት፣ ባሊኒዝ፣ ባቴክ፣ ቢርሆር፣ ብሬዳርን፣ ቡዊድ፣ቺዎንግ፣ ዱክሆቦርስ፣ ፌፖ፣ ፎሬ፣ ጅዊ፣ ሁተሪትስ፣ ኢፋሉክ፣ እንዊት፣ ጄንስ፣ ካዳር፣ ኩንግ፣ ላዳኪስ፣ ሌንቻስ፣ ማላፓንዳራም፣ ምቡቲ፣ ሜናይትስ፣ ምንታኜስ-ናስካፒ፣ሞራቪያንስ፣ ናያካ፣ ኑቢያ፣ አንጌ፣ አራንግ አስሊ፣ ፖሊያን፣ ፒያሮአ፣ ኩዌከርስ፣ የሰሜን ገጠር አይሪሾች፣ የገጠሩ ታይ አካባቢ፣ ሳን፣ ሳንፖይል፣ ሳልቶ፣ ፀማይ፣ ታይታንስ፣ ታንካ፣ ተሚያር፣ ቶራጃ፣ ትራይታን አይላንደር፣ ዎራ፣ ያናዲ፣ ዛፖቴክ እና ዙኒ ናቸው፡፡*

*ከነዚህ ውስጥ ሀያአራቱ ውስጥ ያለውን የግጭት መፍቻ ዘዴ ባጠናበት ጊዜ፣ ቦንታ እንደደመደመው* (***1996*** )

> *የነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ ያለውን ውጤታማ እና ሰላማዊ የግጭት ማስወገጃ መንገዶች በሚታዩበት ጊዜ፣ የዌስተርን ምሁሮች ያላቸው የተለመደ የግጭትና የግጭት ማስወገጃ ላይ ያሉ እምነቶች ጥያቄ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሀይል የተሞላበት ጥቃት በሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ ይገኛል የሚለው እምነት፣ ቅጣት እና የትጥቅ ሀይል በውስጥና በውጭ ያሉ የሀይል ጥቃቶችን ያቆማል የሚል አስተሳሰብ፤ ግጭት እንደ ጥሩና አስፈላጊ ነገር መቆጠሩ፡፡ በተቃራኒው የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ከግማሽ በላይ የሆኑት ሰላማዊ ማህበረሰቦች የተመዘገበ የሀይል ጥቃት ሰርተው አያውቁም፡፡ አዋቂዎችን የሚቀጡት በጣም አልፎ አልፎ ነው፡፡ ( ለምሳሌ በማግለል )፡፡ ከውጭ አካባቢዎች ጋር የሚገጥሟቸውን ግጭቶች የሚያስተናግዱት፣ የውስጥ ግጭቶችን እንደሚያደርጉት፣ በሰላማዊ መንገድ ነው፡፡ የውስጥ ግጭት በሚኖራቸው ጊዜ የወጭ መንግስታትን ድጋፍ አይፈልጉም፡፡ እናም ለግጭት ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ አስተያየት አላቸው ፡፡* (403 )

*በተደጋጋሚ የተደረጉ አንትሮፖሎጂያዊ ጥናቶች ያገኙት መረጃ የሚያሳየው፣ የሀይል ጥቃት በብዛት ወይም በትንሹ ያለባቸውን ማህበረሰቦች የሚያለያዩት ፣ በልጆች አስተዳደግና በማህበረሰብ የራስ ማንነት ስሜት ነው፡፡( ፋብሮ: 1978 )፡፡ ደግላስ ፒ ፍላይ ( 1994 ) በሁለት ተመሳሳይ ማህበረሰባዊና ኢኮሚያዊ ሁኔታዎች ባሏቸው የሜክሲኮ ዛፖቴክ መንደሮች ላይ ባደረገው የንፅፅር ጥናት ታይቷል፡፡ እነዚህ ሁለት መንደሮች የተለያየ የጥቃት መጠን የታየባቸው ነበሩ፡፡ ሰላማዊ በሆነው ላፖዝ ውስጥ ግድያ አልፎ አልፎ የሚታይ ሁኔታ ሲሆን ፣ ዜጎች ራሳቸውን "እንደተከበረ፣ ሰላማዊ፣ ቅናት የሌለበት እና ተባባሪ" ያያሉ፡፡* (140 ) *በቅርብ ባለው ጥቃት በበዛበት ያሳን አንድሬ፣ "በስፋት የተያዘ፣ ጥቃትን የሚሻ፣ ተቃራኒ እምነት አለ፡፡" ( 14 )፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ ተያይዞ ሴቶችን አለማክበር፣ የሚስት ድብደባ፣ ልጆች ላይ የሚደርስ የአካል ቅጣት፣የማይታዘዙ ልጆች፣ መሳደብ፣ ስክሮ መጣላት፣ ለፆታዊ ፋክክሮች የሚደረጉ ግድያዎች፣ ጥሎችና በቀል አሉ፡፡ የቁሳቁስና መዋቅራዊ ሁኔታቸው ተመሳሳይ ቢሆንም፣ በሳን አንድሬ ያለው የግድያ መጠን በላፖዝ ካለው 3.4 ጋር ሲወዳደር በ18.1 በ 100, 000 ነው፡፡ ይህ ንፅፅር እንደሚያሳየን፣ ስለሰው ልጆች ባህሪ ያለ አሉታዊ አስተሳሰብና ጥቃትን የሚያበረታቱ የማህበረሰብ እምነቶች፣ ከግድያ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን ፣ አለመግደል ላይ ያተኮሩ እምነቶችና አስተሳሰቦች ወደ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ ይመራሉ፡፡*

*የሰው ልጅ ያለመግደል ችሎታ ላይ ያሉ ዋና ሳይንሳዊ ድጋፍ የሚገኘው ታሪካዊ በሆነው ሴቪል " ስለ ጥቃት ያለ መግለጫ" ላይ ሲሆን ይህ በሜይ 16,* 1986 *በአለም አቀፍ ምሁራን ቡድን የተሰጠ ነው፡፡ እነዚህም ከእንስሳ ባህሪ ጥናት፣ ከሰዎች ስነባህሪ፣ ባዮሎጂያዊ አንትሮፖሎጂ፣ ኢቶሎጂ፣ ኒውሮፊዚዮሎጂ፣ ፊዚካል አንትሮፖሎጂ፣ ፖለቲካዊ ሳይኮሎጂ፣ ሳይኪያትሪ፣ ሳይኮባዩሎጂ፣ ሶሻል ሳይኮሎጂ እና ሶሲዎሎጂ የመጡ ናቸው ያወጁትም፡-*

> *እኛ ጦርነትን የተማርነው ከእንስሳዎቹ ቅደም አያቶቻችን ነው ብሎ መናገር ሳይንሳዊ ስህተት ነው፡፡ ... ጦርነት ወይም ሌላ ጥቃት የተሞላ ባህሪ ፣ በተፈጥሮ*

ባህሪያችን ውስጥ በጂን ኘሮግራም የተደረገ ነው ብሎ መናገር፣ ሳይንሳዊ ስህተት ነው። ... በሰው ልጅ ሂደታዊ ለውጥ ውስጥ ከሌሎች ባህሪያት የበለጠ ፀብ የተሞላ ባህሪ መፋጠር አለ ብሎ መናገር ሳይንሳዊ ስህተት ነው። ... የሰው ልጆች "የሀይል ጥቃት የተሞላ አእምሮ" አላቸው ብሎ መናገር ሳይንሳዊ ስህተት ነው። ... ጦርነት "በደመነፍስ" ወይም በሌላ አንድ ምክንያት ብቻ የተፈጠረ ነው ብሎ መናገር ሳይንሳዊ ስህተት ነው።

የስታንፎርድ ሳይኪያትሪክቶች ያላቸውን ከአለመግደል ጋር የተያያዘ ቀና እና አዎንታዊ አስተያየት ጋር በመመሳሰል፣ የሴቪል ሳይንቲስቶች ያወጁት:-

> "የደመደምነው፣ ተፈጥሮ የሰው ዘርን ለጦርነት የታደለ ነው ብሎ እንደማያስቀምጥ፣ እና የሰው ልጅ ከባዮሎጂ አሉታዊ አስተያየት በመላቀቅ በራስ በመተማመን ስሜት ተሞልቶ በዚህ አለም አቀፍ የሰላም አመትና ወደፊት በሚመጡ አመቶች ውስጥ የለውጥ ስራ መስራት እንደሚችል ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ሰራዎች ድርጅታዊና ጠቅለል ያሉ ቢሆኑም የእያንዳንዱ ግለሰብ ግንዛቤ ላይ የተመረኮዙ በመሆናቸው ቀና እና አዎንታዊ አስተያየትና አለታዊ አስተያየቶች ከፍተኛ ሚና ይራቸዋል። 'ጦርነት በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ እንደሚጀምረው ሁሉ' ሰላምም ጭንቅላትን ውስጥ ይጀምራል። ጦርነትን የፈጠረው ዝርያ ሰላምንም መፍጠር ይችላል። ሀላፊነቱ በሁላችንም ውስጥ ይገኛል። ( አዳምስ 1989:120-1; 1997 )

አገስት 2, 1939 ላይ አልበርት አይነስታይን ለኘሬዚደንት ፍራንክሊን ዲ.ሩዝቬልት በፃፋው ደብዳቤ እንደገለፀው አቶሚክ ፊዚክስ በደረሰበት እድገት "አዲስ አይነት የሆነ በጣም አደገኛ ቦምብ ሊታሰብ እንደሚችል" ነው። ( ኔትን እና ርደን 1968:295 ) ይህም የአማካሪ ኮሚቴ መፈጠርን፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የመጀመሪያ ስድስት ሺህ ዶላር ኢንቨስትመንት ማድረግን፣ የብዙ ቢሊየን ዶላር የሚፈጅ የማንሀታን ኘሮጀክት መደራጀትን፣ እና ከስድስት አመት በኃላም የመጀመሪያውን የአለም ዩራንየም እና ኘሉቶንየም በምቦች መስራትን ፈጠረ። ከሰባ አመታት በኃላ፣ የሰው ልጅን ያለመግደል ችሎታ የሚያረጋግጥ በቂ ሳይንሳዊ መረጃ የኖረው ሲሆን ፣ በዘዴ ከተዋሀደ እና ከተስፋፋ ግድያ የሌለበትን የሰው ልጅ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል። ይህንን ከሚያሳዩት ነገሮች አንዱ "ጥቃት የለሽነት" ላይ ከ1963 ጀምሮ በዩናይትድ ስቴትስ የተፃፈ ከአንድ ሺህ በላይ የተፃፈ የድህረምረቃ ፅሁፎች ናቸው እነዚህም ከአንትሮፖሎጂ፣ ክሪማኖሎጂ፣ ትምህርት፣ ታሪክ፣ ቋንቋና ስነፅሁፍ፣ ፍልስፍና፣ ሳይኮሎጂ፣ ፖለቲካዊ ሳይንስ፣ ሀይማኖት፣ ሶሲዎሎጂ፣ ንግግር እና ቲዎሎጂ ትምህርቶች ናቸው።( ዲዘርቴሽን አብስትራክትስ ኢንተርናሽናል 1963-)

በሌሎች እንደህንድ ባሉ አገሮች የተሰሩ ጥናቶችን በመጨመር፣ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጭ የተፃፋትን፣ በአንዳሚክ ኮንፈረግሶች ውስጥ የቀረቡ ፅሁፎች፣ በመፅሀፍት እና ከተለያየ የትምህርት አይነት የተዘጋጁ ሲሞፖዚየሞችን፣ (ኩል 1990; 1993 ) ፈር ቀዳጅ የሆኑ የዋሀዱ ትንታኔዎችን ( ግሬግ 1966 ) ፣ በአዲስ ጆርናሎች ውስጥ ( ኢንተርናሽናል ጆርናል ኦፍ ካንሻዩለንስ 1993 - ) ተብራርተው በቀረቡ ጥቃት የለሽ ተግባር ላይ የተሰበሰቡ ቢብሊዩግራፊ ሰራዎችን (ማካርቲ እና ሻርኘ 1997 ) ፣ እና ሌሎች ምንጮችን ከማየት የምንረዳው፣ ጥቃት የለሽነት ላይ ያለ እውቀት ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እያደገ መሆኑንና በተጨማሪም "ሰላም" እና "ግጭት መፍቻ መንገዶች" ላይ መረጃዎች እየጨመሩ መምጣታቸውን ነው። አሁን ያለው አለመግደል ላይ ያተኮረ የእውቀት ሀይል በ1939 ከነበረው የአቶሚክ ፊዚክስ ሁኔታ ጋር ተወዳዳሪ ነው።

**የአለመግደል ችሎታ ዋና ገፅታዎች**

ኤሚል ደርካይም ( 1858-1917 ) የዘመናዊ ሶሲዎሎጂ መስራች ሲሆን ፣ ወደ ማህበረሰባዊ ኑሮ መላምታዊ ሁኔታዎች "ዋና ያፈጠጡ ገፅታዎች" ትኩረትን ስቧል። ይህ ሀሳብ በአሜሪካዊው ሶሻል ላይኮሎጂስት ዶናልድ ቲ ካምቤል የቀጠለ ሲሆን፣ እሱም ኖርዝዌስተርን ዩኒቨርስቲ ለሚገኙ ፖለቲካዊ ሳይንስ ተማሪዎች ፣ ንቁ ሆነው "በተፈጥሮ የሚከሰቱ ማህበረሰባዊ ሙከራዎችን" እንዲከታተሉ መክሮ፣ እነዚህም በሙከራ ላብራቶሪ ውስጥ ከሚታቀዱት እኩል ሊሆኑ እንደሚችሉ ገልጿል። ( ፔጅ 1971)። ፖለቲካዊ ሳይንስ መላምትን ተግባሮችን ከመመልከት ሊያወጣ ስለሚችል ከታሪክና ዘመናዊ ልምድ የወጡ የአለመግደል ምሳሌዎች መግደል የሌለበትን ማህበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ:- ማኪያቪሊ «ዘ ኘሪንስ» በሚለው ስራው ላይ ያቀረበው፣

የጨካኙ መሪ ሲዞር ቦርጅያ ቴክኒኮች ላይ የነበረ መላምታዊ ማብራሪያን ማየት ይቻላል::

ያለመግደልን ችሎታ የሚያሳዩት ዋና ገላጮች፤ የህዝብ ፖሊሲዎች፣ ድርጅቶች፣ ባህሎች፣ ግድያ የሌለባቸው የፖለቲካ ትግሎች፣ የታሪክ ምሳሌዎች፣ እና ቁርጠኛ አቋም ያላቸው ግለሰቦች ናቸው::

**የህዝብ ፖሊሲዎች**

ግድያ የሌለበትን ማህበረሰብ እውነታ ለማድረግ፣ የሞት ፍርድን ባሰወገዱ አገሮች፣ የጦር ወታደር በሌላቸው አገሮች፣ በጦር አገልግሎት ውስጥ መግደልን ለመቃወም ህሊናዊ ውሳኔ መስጠት እንደሚቻል የተቀበሉ አገሮች ወስጥ ይታያሉ::

እስከ ጀንዋሪ 2009 ድረስ፣ በአለም ውስጥ ካሉ 195 አገሮችና ክልሎች ውስጥ፣ 93ቱ ለማንኛውም ወንጀል የሚሰጥ የሞት ፍርድን አስወግደዋል:: (73 በ 2002 አንደኛ ህትመት )

**ሰንጠረዥ 2 የሞት ፍርድ የሌለባቸው አገሮችና ክልሎች ( 93)**

አልቤኒያ
አንዶራ
አንጐላ
አርጀንቲና
አርሜኒያ
አውስትራሊያ
አዘርባጃን
ቤልጂየም
ቡታን
ቦስኒያ ሄርዞጐቪና
ቡልጋሪያ
ካምቦዲያ
ካናዳ
ኬፕ ቨርዲ
ቺሊ
ኮሎምቢያ
ኩክ አይላንስ
ኮስታ ሪካ
ኮትዲቯር
ክሮሺያ
ሲፕረስ
ቼክ ሪፐብሊክ
ዴንማርክ
ጅቡቲ
ደማኒካን ሪፐብሊክ
ኢኩዋዶር
ኤስቶኒያ
ፊንላንድ
ፍራንስ
ጆርጂያ
ጀርመኒ
ግሪክ
ጊኒ ቢሶ
ሃይቲ
ሆንዱራስ
ሀንጋሪ
አይስላንድ
አየርላንድ
ጣሊያን
ኪሪባቲ
ሊችተን ታይን
ሊቱኒያ
ሉክሰምበርግ
ሞልዶቫ
ሞናኮ
ሞንቴኔግሮ
ሞዛምቢክ
ናሚቢያ
ኔፖል
ኔዘርላንድስ
ኒውዚላንድ
ኒካራጉዋ
ኒዌ
ኖርዌይ
ፖላው
ፓናማ
ፓራጉዋይ
ፊሊፒንስ
ፖላንድ
ፖርቱጋል
ሮማንያ
ሩዋንዳ
ሳሞዋ
ሳን ማሪኖ
ሳኦ ቶሜ ኤንድ ፕሪንሲፔ
ሴኔጋል
ሰርቢያ
ሲሸልስ
ስሎቫክ ሪፐብሊክ
ስሎቬንያ
ሰለሞን አይላንድስ
ደቡብ አፍሪካ
ስፔይን
ስዊድን
ስዊዘርላንድ
ቲሞር ሎሮሳኤ
ቱርክ
ቱርክሜኒስታን
ቱቫሉ
ዩክሬን
ዩናይትድ ኪንግደም
ኡራጋይ
ኡዝቤኪስታን
ቫኑቱ
ቫቲካን ሲቲ ስቴት
ቬንዙዌላ

ምንጭ: አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ጀንዋሪ 2009

እያንዳንዱ የተቋረጠ የግድያ ቅጣት፣ ከፍተኛ ሳይንሳዊ እና ፖለቲካዊ የማወቅ ፍላጐትን ይቀሰቅሳል:: ለምን? እንዴት? እና መቼ እያንዳንዱ መንግስት አለመግደል ላይ ወሰነ? ለምንድን አንዳንድ ሀገሮች፣ ባህሎችና እምነቶች ይህንን ሲያደርጉ ሌሎቹ አልገቡም? አሁን ላለው አለማቀፋዊ ሁኔታ ምን አይነት የታሪክ የፈጠራ ሂደቶች እና መስፋፋቶች ምክንያት ሆነዋል? እነዚህ ያለመግደል ምሳሌዎችስ ለወደፊቱ አለማቀፋዊ የሆነ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ መፈጠር ምን አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል?

ሙሉ ለሙሉ ካስወገዱት ውስጥ፣ ዘጠኝ አገሮች የግድያ ቅጣትን ለአንዳንድ የጦር ህግ እና ጦርነት

የመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ ብቻ ይጠቀማሉ::/ለምሳሌ ቦሊቪያ፣ ብራዚል፣ ኤል ሳልቫዶር፣ ፊጂ፣ እስራኤል፣ ካዛክስታን፣ ኪርጂክስታን፣ ላቲቪያ እና ፔሩ/:: ስላሳ ስድስት አገሮች የሞት ቅጣት በህጋቸው ውስጥ ቢኖርም፣ ከአስር አመት በላይ ማንንም በሞት ቅጣት አልቀጡም:: /ለምሳሌ አልጀሪያ፣ቤኒን፣ብሩኔ ዳሩ ሰላም፣ ቡርቢና ፋሶ፣ ናሜሩን፣ ሴንትራል አፍሪካን ሪፐብሊክ፣ ኤርትራ፣ ጋቦን ፣ ጋና፣ ግሬናዳ፣ ኬንያ፣ ሳውዝ ኮሪያ ፣ ላኦስ፣ ላይቤሪያ፣ ማዳጋስካር፣ ማላዊ፣ ማልዲቭስ፣ ማሊ ፣ ሞሪታንያ፣ ሞሮኮ፣ ማይናማር፣ ናውሩ፣ ኒጀር፣ ፓፑዋ ኒው ጊኒ ፣ራሻያን ፊደሬሽን ፣ስሪ ላንካ ሱሪናም፣ ስዊዘርላንድ፣ ታጂኪስታን፣ ታንዛኒያ፣ ቶጐ፣ ቶንጋ፣ ቱኒዚያ እና ዛምቢያ/::

ሀምሳ ዘጠኝ [በ2002 ዘጠና አንድ] አገሮች በህጋቸው ውስጥ የግድያ ቅጣትን ያስቀመጡ ሲሆን መግደልም ቀጥለዋል:: ( ለምሳሌ አፍጋኒስታን፣ አንቴጉዋ እና ባርቡዳ፣ ባህማስ፣ ባህሬን፣ ባንግላዲሽ፣ ባርባዳስ፣ ቤላሩስ፣ ቤሊዝ፣ ቦትስዋና፣ ብሩንዲ፣ ቻድ፣ ቻይና፣ ኮሞሮስ፣ ኮንጐ ዴምክራቲክ ሪፐብሊክ፣ኩባ፣ ዶሚኒካ፣ ግብፅ፣ ኢኳቶሪያል ጊኒ፣ ኢትዮጵያ፣ ጉዋቲማላ፣ ጊኒ፣ ጋያና፣ ህንድ፣ ኢንዶኔዢያ፣ አራን፣ ኢራቅ፣ጀማይካ፣ጃፖን፣ጆርዳን ፣ ሰሜን ኮርያ፣ ኩዌት፣ ሊኖባስ፣ ሌሶቶ፣ ሊቢያ፣ ማሌዢያ፣ ሞንጐሊያ፣ ናይጀሪያ፣ ኦማን ፣ ፓኪስታን፣ ፍልስጤም፣ ካታር፣ ሴንት ክሪስቶፈር ኤንድ ኔቪስ፣ ሴንት ሉቺያና ቤንት ቪንሰንት እና ግሬናዳ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ሲራሊዩን ፣ ሲንጋፖር፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን ፣ ሶርያ፣ታይዋን ፣ ታይላንድ፣ ትሪኒዳድ ኤንድ ቶባጐ፣ ኡጋንዳ፣ ዩናይትድ አረብ ኤሚሬትስ፣ ዩናይት ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣ ቪየትናም፣ የመን እና ዚምቧብዌ ናቸው::) ዩናይትድ ስቴትስ በፌደራል ደረጃ ለሚደረጉ ወንጀሎች የሞት ቅጣትን ቢያስቀምጥም ከሀምሳዎቹ ውስጥ አስራአራቱ ክልሎች እና የኮሎምቢያ ግዛት አቁመውታል:: አነሱም አላስካ፣ ሀዋይ፣ አዩዋ፣ ሜይን ፣ ማሳሹሴትስ፣ ሚሺጋን ፣ ሚኔሶታ፣ ኒው ጀርሲ፣ ኒውዩርክ፣ ሰሜን ዳኮታ፣ ሮድ አይላንድ፣ ምዕራብ ቨርጂኒያ እና ዊስኮንሲን ናቸው::

ምንም እንኳን በመተውና መልሶ በማፅደቅ መካከል ያሉ መፈራረቆች ቢኖሩም፣ አለማቀፋዊው ሂደት እንደሚያሳየው ከጥቃታዊ ባህል ተነስተው ግድያን ማቆም ያወጁ መንግስታት መኖር፣ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ እውን ለሆን ይችላል የሚለውን ሀሳብን ያጠናክራል:: የዜጐችን መግደል የሩሶ “ማህበረሰባዊ ኮንትራት” አካል መሆንም ሆነ ማክስ ዌበር እንዳስቀመጠው የፖለቲካ ሊቀየር የማይችል ባህሪ ተደርጐ መወሰድ የለበትም::

በ2002 የነበሩ ሀያሰባት የጦር ሰራዊት ያልነበራቸውን አገሮችንም መውሰድ ይችላል:: ከኩክ አይላንዶችና ከኔው በስተቀር፣ ሁሉም የዩኤን አባላት ናቸው::

**ሰንጠረዥ 3: የጦር ሰራዊት የሌላቸው አገሮች ( 27)**

**የጦር ሰራዊት የሌላቸው ( 19)**

| | | |
|---|---|---|
| ኮስታሪካ | ሞሪሺየስ | ሳን ማሪኖ |
| ደሚኒካ | ናውሩ | የሰለሞን ደሴቶች |
| ግሬናዳ | ፓናማ | ቱቫሉ |
| ሄይቲ | ሳን ኪትስ ዩ ኔቪስ | ቫኑዋቱ |
| አሪባቲ | ሴንት ሉቺያ | ቫቲካን ሲቲ ስቴት |
| ሊችተንስታይን | ሴንትንቪንሰንትና ግሬናዲንስ | |
| ማልዲቭስ | ሳሞዋ | |

**የጦር ሰራዊት የሌለው ( የመከላከያ ስምምነት) ( 8)**

| | |
|---|---|
| አንዶራ ( ፈረንሳይ፣ ስፔን) | ማይክሮኔዥያ ( ዩ.ኤስ.ኤ) |
| ኩክ ደሴቶች ( ኒውዚላንድ) | ሞናኮ(ፈረንሳይ) |
| አይስላንድ ( ኔቶ፣ዩ ኤስ.ኤ) | ኒው ( ኒውዚላንድ) |
| ማርሻል ደሴቶች ( ዩ.ኤስ.ኤ) | ፖሎ ( ዩ.ኤስ.ኤ) |

ምንጭ: ባርቤይ 2001

በተጨማሪም፣ ቢያንስ አስራ ስምንት ጥገኛ ክልሎች በጆግራፊያዊ አቀማመጣቸውም ምክንያት

በስምምነት የጦር ሀይል እንዳይኖራቸው የተደረገ ሲሆን፤ ለምሳሌ:- ኤላንድ አይላንድስ ኦፍ ፊንላድ፣ በአለም አቀፍ ስምምነት ደግሞ አንደ አንታርቲከ እና ጨረቃን ይጨምራል:: ( ባርቤይ 1989:5)

ለሀገር ማንነት፣ ማህበረሰባዊ ቁጥጥር፣ ደህንነትና፣ የጥቃት እርምጃን ለመወሰድ አስፈላጊ የሆነው የጦር ሰራዊት፣ በአንዳንድ አገሮች ውስጥ አለመገኘት ይገርማል:: ምንም እንኳን እነዚህ አገሮች በቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆኑም እና አንዳንዶቹም የሌሎች አገሮች ስራዊቶችን ቢጠቀሙም፣ የጦር ሀይል የሌለው መንግስት ሊኖር እንደሚችል ያሳያሉ:: ግድያ የሌለባቸው ማህበረሰቦች የማይታሰቡ አይደሉም::

የጦር ሰራዊት ባላቸው አገሮች ውስጥ፣ በጦር ሰራዊት አላስፈላጊ እንግልት እንዳይኖር መንግሥት መገንዘቡ፣ መግደል የሌለበት ፖለቲካ ሊኖር እንደሚችል ተጨማሪ መረጃ ይሆናል። በ2005 ዓ.ም፣ አምሳ አራት አገሮች፣ ዜጎቻቸው በጦር ሠራዊት ውስጥ የአገልግሎት አለመስጠት ጥያቄ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ በሕግ ተቀብለዋል።

**ሠንጠረዥ 4፡ የጦር ሠራዊት አገልግሎትን ላለማድረግ የሚላክ ፈቃድን የተቀበሉ አገሮች (54)**

| | | |
|---|---|---|
| አልቤኒያ | ጉዋያና | ስፔን |
| አርጀንቲና | ሀንጋሪ | ሱሪናም |
| አርማኒያ | ጣሊያን | ስዊድን |
| አውስትራሊያ | ካርጂክስታን | ስዊዘርላንድ |
| ኦስትሪያ | ላቲቪያ | ዮክሬን |
| አዘርባጀን | ሊቱኒያ | ዮናይትድ ኪንግደም |
| ቤላሩስ | ማሴዶኒያ | ዮናይትድ ስቴትስ |
| ቤርሙዳ | ማልታ | ኡዝቤኪስታን |
| ቦስኒያ-ሄርዞጎቪና | ሞልዳቫ | ዩጎዝላቪያ |
| ብራዚል | ሞንቴኔግሮ | ዚምቧብዌ |
| ቡልጌሪያ | ኔዘርላንድ | |
| ካናዳ | ኖርዌይ | |
| ክሮሺያ | ፓራጎዋይ | |
| ሲፕረስ (ግሪክ-ሲፕረስ) | ፖላንድ | |
| ቼክ ሪፐብሊክ | ፓርቹጋል | |
| ዴንማርክ | ሮማንያ | |
| ኢስቶኒያ | ሩሲያ | |
| ፊንላንድ | ሰርቢያ | ምንጭ:- ሆርማን እና |
| ፈረንሳይ | ስሎቫኪያ | ስቶልዊ ጆክ (1998 ዓ.ም) |
| ጀርመን | ስሎቬኒያ | እና ዋር ሬዚስተርስ |
| ግሪክ | ደቡብ አፍሪካ | ኢንተርናሽናል (2005 ዓ.ም) |

ሕጋዊ ሁኔታዎችን አገሮቹ የተቀበሉባቸው ምክንያቶቹ ከጠበበ የሃይማኖት መስፈርት እስከ ሰፊ የሆነ መንፈሳዊ፣ ፍልስፍና፣ ኤቲክስ፣ ሞራል፣ ሰብአዊነትና የፖለቲካ ምክንያቶች ይለያያሉ። በተጨማሪም በአገሮቹ ውስጥ ያለው ሌላ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ፣ በአገልግሎት ላይ ያሉ ወታደሮች ተቃውሞአቸውን ሊያቀርቡበት የሚችሉበት መጠን፣ እና ሕጎቹን ማስፈፀም ላይ ያለው አስተማማኝነት መጠን ይለያያል (ምስኮስ እና ቻምበርስ 1993 ዓ.ም)። ከሁሉም በላይ በጣም ነፃነት የሚሰጥ የአለመግደል መብት የተሰጠው በጀርመን ውስጥ ሲሆን፣ እሱም በ1949 ዓ.ም የፌደራል ጀርመን ሪፐብሊክ መሠረታዊ ሕግ አንቀፅ 4 ላይ ይገኛል። “በራሱ ሕሊና ፈቃድ ውጭ ምንም ሰው የጦርነት አገልግሎት እንዲሰጥ አይገደድም።” (ኩልማን እና ሊፐርት 1993፡ 98)። የሞት ፍርድ መቅረት፣ እና የጦር ሰራዊት የሌላቸው አገሮች መገኘት እንደሚያስደንቀው ሁሉ፣ የጦርነት ገዳዮች ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን ምንጩ፣ ሂደቱ፣ ዓለማቀፋዊ ሁኔታው እና በፖለቲካ የመታወቅ እድሉ ከፍተኛ ሳይንሳዊ የማወቅ ፍላጎትን ይፈጥራል።

**ማኅበረሰባዊ ድርጅቶች**

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ወደ ፊት ግድያ የሌለበት ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ሊጠቅሙ፣ ወይም ሊሠሩ የሚችሉትን የሚያመቻቹ ድርጅቶች ተፈጥረዋል፡፡ የሰው ልጅን ያለመግደል ችሎታ ለማሳየት እነዚህ ተጨማሪ መረጃ ያቀረባሉ፡፡ እነዚህ የተበታተኑ ማኅበረሰቦች፣ ለአንድ ማህበረሰብ ፍላጎት በሚሆን መልክ በፈጠራዊ ሁኔታ ቢደባለቁ ኖሮ መግደል የሌለበትን ማኅበረሰብ በሀሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በእውነትም የሰው ልጅ ልምድ ሆኖ ለማየት ይቻል ነበር፡፡ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ እዚህ ተዘርዝረዋል፡፡ ሁሉም ሙሉ ለሙሉ መነገር የሚገባቸው ታሪኮች አሏቸው፡፡

**መንፈሳዊ ድርጅቶች**

ያለመግደል እምነት ያላቸው መንፈሳዊ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ውስጥ በተለያየ ከፍል ይገኛሉ፡፡ ከነሱ ውሰጥ የምስራቆቹ ጄን፣ የምዕራቦቹ ኩዌከሮች፣ በፈረንሳይ የሚገኙት የቡዲስት ፕለም ቪሌጅ ማኅበረሰብ፣ አፍሪካ የሚገኘው ሳይመን ኪምባንጉ ቸርች፣ የሩሲያና ካናዳ ዶክሆቦር (መንፈስ ታጋዮች) እና በዮናትድ ስቴትስ የሚገኘው ጁዊሽ ፒስ ፌሎሺፕ ናቸው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ በ1919 ዓ.ም የተመሰረተው ‹ዓለም አቀፍ የእርቅ ፌሎሺፕ› የሁሉም ሃይማኖት ሴትና ወንዶች አንድ ላይ የሚያመጣ ሲሆን፣ "እነዚህም የፍቅርና የእውነት ኃይልን በማመን በማኅበረሰብ ውስጥ ሰላምና ፍትህን እንደሚያመጣ ተቀብለው፣ ጥቃት ለሌለው ሕይወት ራሳቸውን በማዘጋጀት ለግል፣ ለማህበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ ይጠቀሙበታል፡፡"

**ፖለቲካዊ ድርጅቶች**

ላለመግደል *ሥርዓት* ራሱን የሰጠ የምርጫ ፖርቲ የሆነው የብሪታኒያ ፌሎሺፕ ፖርቲ፣ በሮናልድ ማሎን፣ ጆን ላቭርሲድ እና ሌሎች ክርስቲያን ፖሲፊስቶች (ጦርነትን የሚቃወሙ ግለሰቦች)፣ እና የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ላይ በዘመቱ ሰዎች በ1955 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡[3] ምንም ዓይነት የጦርነት ዝግጅቶች ላይ የተቃውሞ ቅስቀሳ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለኢኮኖሚያዊና ማኅረሰባዊ ፍትህ በመቆም ስነጥበብና ስፖርትን ያበረታታል፡፡ ጀርመን ውስጥ "ጥቃት የለሽነት"፣ በፔትራ ኬ ኬሊ እና ሌሎች ሰላሳ ሰዎች፣ በ1974[4] በተመሰረተው ኢኮሎጂካዊ አረንጓዴ ፓርቲ (*Die Grünen*) ዋና ባህሪ ነው፡፡ ለዚህም እንደምሳሌ የሆኑት፣ በጋንዲ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የተደረጉት ጥቃት የለሽ እንቅስቃሴዎች ናቸው (ኬሊ 1989 ዓ.ም)፡፡ አረንጓዴ ፓርቲ ያቀረበውን ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ጅማሮን ፈጥረዋል፡፡ በ1983 ዓ.ም የተመሰረተው የዩናይትድ ስቴትስ ፓሲፊስት ፓርቲ መንፈሳዊ፣ ሳይንሳዊ እና ሰብዓዊ የሆኑትን የብራድፎርድ ሊትል መርሆዎች የሚከተል ሲሆን፣ እሱንም በ1996 ዓ.ም እና 2000 ዓ.ም ላይ ተመራጭ አድርጎ በማቅረብ በአሜሪካ ማኅበረሰብና አሜሪካ በዓለም ውስጥ ባለው ድርሻ ጥቃትን የሌለው ለውጥን ሸቷል፡፡ በህንድ፣ በቲ.ኬ.ኤን ኡኒታን እና ሌሎች የተመሰረተው ሳርቮዳያ ፓርቲ የሁሉንም እድገት የሚያበረታታውን የጋንዲን ሞዴል በመከተል ወደ ምርጫ ገብቷል፡፡[6] በኋላም ከጋንዲ ባህል እና ከፖለቲካ ራሱን በማራቅ የሳርቮዳያ ፓርቲ ሲያብራራ "ኃይል በተፈጥሮው አያደላም፡፡ ነገር ግን መጥፎ ሰዎች እጅ ውስጥ ሲገባ ጥፋትን ይፈጥራል፡፡" በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ የሆነ ትራንዝናሽናል ራዲካል ፓርቲ፣ የጋንዲ ጥቃት የለሽ እንቅስቃሴን መሠረት አድርጎ፣ ከጣሊያን ፓርቲቶ ራዲካል ውስጥ በ1988 ተነስቷል፡፡[7] አላማውም በዓለም አቀፍ ደረጃ በመስራት ጥቃት የለሽ የሆነ ግፊት በዩናትድ ኔሽንስ ላይ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ዓለም አቀፍ የሆነ የሞት ቅጣትን ማስወገድ፣ ታስቦ የሚደረግን ተቃውሞም መቀበል፣ የጦር ጥፋተኞች የሚዳኙበትን መንገድ... ፓርቲው ሀገር አቀፍ ምርጫዎችን አይቃወመምም:: አባላት ሌላ ፓርቲ ውስጥም አባል መሆን ይችላሉ፡፡ ክፍያዎችም የሚታሰቡት በአባል ሀገሩ አንድ ፐርሰንት ግሮስ ናሽናል ፕሮዳክት ፐር ካፒታ ነው፡፡ ከጋንዲ ምስል ስር ፓርቲው እንደሚለው "ለውጥ የሚያመጣ ሕግ እና ጥቃት የለሽነት የተሻለ ዓለምን ለመገንባት በጣም ውጤታማና ለውጫዊ መንገዶች ናቸው፡፡"

## የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች

የአለመግደልን አቋም የሚገልፁ ዋና የኢኮኖሚ ድርጅቶች ውስጥ ካፒታሊስት የጋራ ሀብት ፈንድን ሲጨምር፤ ያም የጦርነት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ኢንቨስትመንት አያደርግም። (ፓክስ ወርልድ ፈንድ) ሌላው በጋንዲ እና ኪንጊያን ጥቃት የለሽ መርሆች የተመራ የሰራተኞች ኅብረት፣ (ዩናይትድ ፋርም ወርክርስ ኦፍ አሜሪካ ሲሆን፣ በሴዘር ሻቬዝ፣ ዶለረስ ሁሌታ እና ሌሎች የተመሰረተ ነው።) ሌላው በስሪላንካ የሚገኝ አጠቃላይ የማኅበረሰብ እድገት ፕሮግራም ሲሆን፣ በቡዲስት ጥቃት የለሽ መርሆ ላይ የተመረኮዘ ነው (በኤ.ቲ.አሪያራትኔ የሚመራ ሳርቮዳያ ሻርማዳና ሳንጋማያ)። ምንም እንኳን ውጤታማነቱ የተወሰነ ቢሆንም፣ የህንድ ቡድን (የመሬት ስጦታ) እንቅስቃሴ ልምድ እንደሳየው ግድያ የሌለበት የውስጥ ሀብት ክፍፍል እውነት ሊሆን እንደሚችል ነው። ይህ እንቅስቃሴ፣ መሬት ለሌላቸው መሬት ማስተላለፍ ላይ የሚሰራ ሲሆን፣ በጋንዲ "የአደራ" መላምት ተነሳስቶ በቪኖባ ባቬ (1994 ዓ.ም) እና ጃያፕራካሽ ናራያን (1978 ዓ.ም) የተመራ ነው። ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችም ለማኅበረሰብ ግድያ የሌላው አገልግሎትን ይደግፋሉ። ለምሳሌ የጋንዲ ፋውንዴሽን (ለንደን)፣ ሳቮዳያ ኢንተርናሽናል ትረስት (ባንጋሎር) እና ኤ.ጄ. ሙስቴ ኢንስቲቲውት (ኒውዮርክ) ናቸው።

## የትምህርት ድርጅቶች

የጋንዲን መርሆ አስተማሪ የነበረው ዶክተር ጂ. ራማቻንድራን (1903-1995 ዓ.ም)፣ የሰው ልጅ ፍላጎትን ለማሟላት ብሎ ሁሉንም እምነት መሰረት ያደረተ የአለመግደል መንፈስ ላይ የተመሰረተ ሙሉ ዩኒቨርስቲ ጀምሯል። እሱም በህንድ ታሚል ናዱ ጋንዲግራም ሩራል ኢንስቲቲውት (ዩኒቨርስቲ የተባለ) መሰርቷል። የአካባቢውን መንደሮች ያገለግል የነበረው የዚህ ዩኒቨርስቲ መሠረታዊ ባህሪዎች የሆኑት፡- (1) ሥርዓታዊ ትምህርቶችን ከማኅበረሰብ ሁኔታዎች ጋር ማዋሀድ፡- ለምሳሌ ፖለቲካዊ ሳይንስና የመንደር ውስጥ ውሳኔ አሰጣጥን፣ ፊዚክስና ሬዲዮ መጠገንን፣ ባዮሎጂ እና የውሃ ጉድጓድ ፅዳትን፣ ስነጥበብ ፈጠራ የተሞላው የልጆች አስተዳደግን። (2) እንዳንዱ ተመራቂ ተማሪ ችግር የሚፈታ ቴሲስ እንዲያቀርብ መጠየቁ። (3) ሦስት ቋንቋ መማራቸው፡- ለአካባቢ ፍላጎት የታሚል፣ ለሀገር አቀፍ ውህደት ሂንዱ፣ የዓለም መስኮት የሆነውን እንግሊዘኛ እና ፤ (4) ሁሉም የዩኒቨርስቲው እድገትና ጥበቃን ለማረጋገጥ የጉልበት ስራ መስራታቸው። ለምሳሌ ፅዳት ሥራ፣ ጥበቃ እና ምግብ ማብሰል።

የራማቻንድራን ትልቅ አስተዋፅዖ፣ በዚህ ድርጅት ውስጥ የወታደራዊ ስልጠና አማራጭ የሆነ ግድያ የሌለውን መንገድ፣ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ መስጠቱ ነው። እሱም ሻንቲ ሴና (የሰላም ብርጌድ) ሲሆን ዋና አደራጁም የሰብአዊ መብት ፕሮፌሰር የሆኑት ኤን ራድ ሀክሪሽናን ናቸው። (1992, 1997 ዓ.ም) ከ1958-1988 ዓ.ም ሻንቲ ሴና አምስት ሺህ ፈቃደኛ የሆኑ ባለዮኒፎርም ወጣት ወንዶችና ሴቶችን ያሰለጠነ ሲሆን፣ እነሱም ቃል የገቡት "ለሰላም መስራት እና አስፈላጊም ከሆነ ሕይወትን ለሱ ብሎ ለመስጠት ነው።" መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ እውቀታዊና ድርጅታዊ ስልጠናን በማቀላቀል፣ ሻንቲ ሴና ተማሪዎችን ግጭትን ለማስወገድ፣ ለደኅንነት ስራዎች፣ አደጋን ማቅለል እና የማኅበረሰብን ፍላጎት ለማድረስ የትብብር የማኅበረሰብ ስራ ያዘጋጃቸዋል። ዘዴው ያነጣጠረው ሁልጊዜ ከመንደሩ ሰዎች ጋር በመስራት የልጆችን እንክብካቤ፣ የአካባቢ ንፅህና፣ የሴቶች ጉዳይ እና የማኅበረሰቡን ስነጥበብ ባህል የማቆየት ስራን መስራት ላይ ነው። በ1970ዎች አንዳንድ የህንድ ከተማ ውስጥ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች የጭቆና መሳሪያዎች ናቸው ተብለው የተወቀሱ ሲሆን፣ በዚህ ጊዜ ግን በጋንዲ ግራም አካባቢ ያሉ የገጠሩ ነዋሪዎች የገጠሩ ኢንስቲቲውት ወደ ዲምድ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያደገበትን ጊዜ እያከበሩ ነበር። ሻንቲ ሴና ለካምፓስ ደህንነት ኃላፊነቱን ወስዶ ነበር። ማንም የታጠቀ ፖሊስ ወደ ካምፓሱ ለመግባት የማይፈቀድለት ሲሆን፣ ይሄ ሕግ የህንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኔህሩ፣ ኢንድራ ጋንዲና ሌሎች ባለሥልጣኖች በመጡም ጊዜ የተጠበቀ ነበር።

**የሥልጠና ድርጅቶች**

ለማኅበረሰብ ለውጥ አለመግደል ላይ ያተኮረ ስልጠና ፣ የግጭት አካባቢዎች ውስጥ የሚሰሩ ስራዎች፣ የማኅበረሰብ መከላከያ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ስልጠናዎችን የሚሰጡ ድርጅቶች በፍጥነት እየተከሰቱ ነው። በሀገር አቀፍ ዓለማቀፋዊ ድርጅት ስልጠና የሚሠጡ ልምድ ያላቸው አሰልጣኞች እየተፈለጉ ሲሆን፣ የሰው ልጅ ጥቃት የተሞላባቸውን መንገዶች ግድያ በሌለባቸው ችግር መፍቻ ዘዴዎች ሊቀይር እንደሚችል መተማመንን እያሳደጉ ነው። ጥቂት ድርጅቶችንና ታዋቂ አሰልጣኞች ለመጥቀስ ያህል (ቢር 1994 ዓ.ም)፣ የጂ.ራማቻንድራን ‹ስኩል ኦፍ ነን ቫዬለንስ› (ኤል ራድክሪሽናል) ‹ፒስ ብርጌድስ ኢንተርናሽናል› (ፒራያን ዴሳይ)፣ ከፍሎሪዳ የማርቲን ሉተር ኪንግ ‹ጁኒየር ኢንስቲቲውት ፎር ነን ቫዮለንስ›፣ ካላፋዬት እና ተባባሪዎቹ ጋር (በርናንድ ላፋዮት ጁኒየር፣ ቻርልስ ኤል አልፊን፣ ሲኒየር፣ እና ዴቪድ ጀንስን)፣ ‹ኢንተርናሽናል ፌሎሺፕ ኦፍ ሪኮንሲሊየሽን› (ሂልዴጋርድ ጎስ-ማየር እና ሪፓርድ ዲስት)፣ ‹ፓለስቲኒያን ሴንተር ፎር ዘ ስተዲ ኦፍ ነን ቫዮለንስ› (ሙባረክ አዋድ)፣ ‹ቫዮለንስ ኢንተርናሽናል› (ሚካኤል ቢር)፣ ሰርቪቺዮ ፓዝ ይ ጀስቲቺያ (አዮልፎ ፔሬ ኢስዌቪል)፣ ‹ዘ ኢንተርናሽናል ኔትዎርክ ኦፍ ኢንጌጅድ ቡዲስትስ› (የሹዋ ሞሰር-ፑአንግውሳን)፣ እና ትራንሴንድ (ጆሀን ጋልተንግ)።

ራስን ከጥቃት ለመከላከል እና ባህሪን ለማሳደግ ጠቃሚ የሆነ እና ግድያ ወደሌለበት ዘዴያዊ የማህበረሰብ ለውጥ ሊመራ የሚችል መንግድ ሲኖር፣ ይሄም ፈጠራዊ የሆነው ግድያ የሌለበት አይኪዶ የተባለው ከጃፓን የተነሳ የማርሻል አርት ጥበብ ነው። በፈጠረው ግለሰብ፣ ማለትም ሞሪሄይ ኡሺባ እንደተገለፀው "መጨፍለቅ፣ መጉዳት እና ማጥፋት የሰው ልጅ የሚያደርገው ከሁሉም አስከፊ ኃጢያት ነው።" የአይኪዩ አላማ፣ ከዩኒቨርስ የሕይወት ኃይል ጋር ሰላምን መፍጠር ነው። "አይኪዶ የፍቅር ውጤት ነው።" (ስቴቨንስ 1987፡ 94፣ 112፣ ዩደር 1983፡ 28)

**የደኅንነት ድርጅቶች**

በዓለም ውስጥ ያሉ የተለያዩ ድርጅቶች፣ የማህበረሰቡን ደህንነት ግድያ በሌለበት መንገድ የመጠበቅ ችሎታ እንዳላቸው አሳይተዋል። ከነሱም ውስጥ ለምሳሌ፡- መሳሪያ የሌለው ዜጋ ያላቸው አገሮች (ጃፓን)፣ ፖሊሶች የጦር መሳሪያ የማይዙበት አገር (ብሪታኒያ)፣ የታጠቁ ጠባቂዎች የሌሉት እስር ቤት (ፊንላንድ)፣ መሳሪያ የሌለባቸው የሰላም ክልሎች (ሲቲዩ ካንቶማንዮግ፣ ፊሊፒንስ)፣ ትጥቅ ለሌለው የዜጎች ደኅንነት የቆመ ማህበር (ቡንድ ፋር ሶዚያሌ ቬርቴዲጉንግ፣ ሚንደን፣ ጀርመን)፣ እና የጦር ዞኖች ውስጥ ሰላምን ለመፍጠር የሚሰሩ ድርጅቶች (ሞሰር ፑዋንግሱዋን እና ዌበር 2000፣ ማሆኒ እና ኢጉሪን 1997 ዓ.ም)። ከነዚህ ላይ፣ ከጦር መሳሪያ ነፃ የሆነ ዓለምን ለመፍጠር የሚሞክሩ ሀገሮችና ዜጎች ሲገኙ የሚንቀሳቀሱትም ኒኩሊየር፣ ኬሚካል እና ባዮሎጂካል መሳሪዎችን ለማጥፋት፣ የእጅ ሽጉጦችን፣ የጥቃት መሳሪያዎችን እና የሚጠመዱ ቦምቦችን ለማስከልከል ነው። ከድርጅቶቹ ውስጥ በቀድሞው የኮስታሪካ ፕሬዚዳንት እና በ1987 ዓ.ም የኖቤል ሽልማት ተመራጭ በሆነው ኦስካር አሪያስ ሳንጄዝ፣ የጦር ሰራዊት ለማጥፋትና ግጭትን ለመፍታት ብሎ የመሰረተው ‹ሴንተር ፎር ፒስ ኤንድ ሪኮንሲሊየሽን›፣ የፀረ-ባሪያ ንግድን ልምድ የሚመስለው ‹ሙቭመንት ቱ አቦሊሽ አርምስ ትሬድ›፣ እና ፊሊፒንስ ውስጥ በሬይናልዶ ፖቼኮ እና ኃይዲ ዋይ ዩርዳክ የተመሰረተውና የሰው ልጆችን "ሊጠፉ ያሉ ዝርያዎች" ብሎ በማዳን ላይ ያተኮረው ‹ኔቸር/ ጋንለስ ሶሳይቲ› ይገኙበታል። (ቪላቪንቼሲዮ ፓሮም 1995 ዓ.ም)

### የጥናት ድርጅቶች

በምዕራብ፣ የአልበርት አይነስታይን ኢንስቲቲውሽን (በቦስተን ማሳሱሼትስ)፣ በጂን ሻርፕ ተመስርቶ ጥቃት የለሽ የዲሞክራሲ፣ ደኅንነት እና ፍትህ ጥናቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያካሂዳል፡፡ በምስራቅ የጋንዲያን ኢንስቲቲውት ኦፍ ስታዲስ (ቫራንሳይ፣ ህንድ ውስጥ)፣ በጃያፕራካሽ ("ጄ.ፒ.") ናራያን ተመስርቶ፣ ግድያ የሌለበት ማኅበረሰባዊ ለውጥን ለመደግፍ ማኅበረሰባዊ ጥናቶችን ያካሂዳል፡፡ በአገር አቋራጭ ደረጃ በቲዎዶር ኤል ኽርማን የተመሰረተው ‹ነንቫዮለንስ ኮሚሽን ኦፍ ኢንተርናሽናል ፒስ ሪሰርች አሶሲየሽን› በጥናት፣ ትምህርትና፣ ተግባር ዙሪያ የተደረጉ ግኝቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ መጋራት ላይ ያተኩራል፡፡

### ችግር ፈቺ ድርጅቶች

አለመግደል መርሆ ላይ በመመርኮዝ ችግሮችን ለመፍታት ከሚሞክሩ ድርጅቶች ውስጥ አምነስቲ ኢንተርናሽናል (የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶችን መጠበቅና የሞት ቅጣትን ማስወገድ ላይ)፣ ግሪንፒስ ኢንተርናሽናል (የአካባቢ ጥበቃ እና የኒኩሊየር መሳሪያዎች መጥፋት ላይ)፣ ዘ ዋር ሬዚስተርስ ኢንተርናሽናል (በግድ ለጦርነት መመልመልን ማቆም እና ለጦርነት ከሚደረጉ ማንኛውም ዝግጅቶች ራስን ማግለል የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር ላይ)፣ እና ሜዲሳ ሳን ፍሮንቲየር (ለጥቃት ሰለባዎች የሚያደረግ ሰብአዊ የሆነ የሕክምና እንክብካቤ ላይ) የሚሰሩ ይገኙበታል፡፡

### የመገናኛ ብዙሀን

ግድያን ከማይደግፍ እይታ ተነስቶ፣ የአገርና አለም አቀፍ ሁኔታዎችን የሚዘግብና አስተያየት የሚሰጥ የመገናኛ ብዙሀን የመፈጠር ሁኔታ በጋዜጠኛው ኮልማን ማካርቲ( 1994) ስራ እና በአለም ዙሪያ በተሰሩ ብዙ የፅሁፍ ስራዎች ላይ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ዴይ ባይ ዴይ፣ መንዝሊ ኘሬስ፣ የብሪታንያ ፖሲፊስት ፌሎሽፕ ፖርቲ፣ የአርትና ስፖርት ዘገባ ( ለንደን) ፣ የባንኮክ ቡዲስቶች «ሲድስ ኦፍ ፒስ ኢንተርናሽናል»፣ ፒስ ኒውስ ፎር ነን ቫዩለንት ሪቮሉሽን ( ለንደን) ፣ የፈረንሳይ ወርሀዊው «ነን ሻዩለንስ አክቹዋሊቴ» ( ሞንታርጂ)፣ የጣሊያን «አሪዞን ነንቫዩለንታ» ( ቪሮና)፣ የጀርመን «ግራስውርትዜል ሪቮሉሽን» ( አልደንበርግ) ፣ እና የአሜሪን መፅሄቶች ውስጥ ፌሎሽፕ ( ኒውዮርክ)፣ እና ነንቫዩለንስ አክቲቪስት ( ኒው ዮርክ) ፡፡ ከአለማግደል ጋር የተያያዙ በተለያዩ የማህበረሰባዊ ጉዳዬች ላይ ያለ እውቀትን ለማውጣትና ለማስተላለፍ ከጠቀሙ ጆርናሎች ውስጥ፣ «ሶሻል ኦልተርኔቲቭስ» ( ብሪስቤን ኦስትሪሊያ) ፣ ጋንዲ ማርግ ( ኒውዴልሂ)፣ እና «ኢንተርናሽናል ጆርናል ኦፍ ነንቫዩለንስ» ( ዋሽንግተን ዲ.ሲ) ይገኙበታል፡፡ ጥቃት የሌለው ማህበረሰባዊ ለውጥ ላይ ያተኮሩ መፅሀፎችን በማተም እንደ ናቫጂቫን ( አህመዳባድ ህንድ) ፣ ኒው ሶሳይቲ ፐብሊሽርስ ( ብሌን ዋሽንግተን) ፣ ነን ቫዩለንስ አክቹዋሊቴ ( ፖሪስ)፣ እና ኦርቢስ ቡክስ ( ሜሪል ኒውዮርክ) ያሉ ማተሚያ ቤቶች ይገኙበታል፡፡

### ባህላዊ ሀብቶች

አለመግደል ላይ ያተኮሩ የባህል ሀብቶች፣ የስነጥበብና የእውቀት ፈጠራዎች ሲሆኑ፣ የሰውን ልጅ መንፈስ ከፍ ከፍ የማድረግ ባህሪና ፣ ግድያ የሌለበት ማህበረሰብን እውነት የማድረግ ስራዎችን የሚያሳድጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ከሚይዙት ነገር ውስጥ ለምሳሌ፡- የባህል መዝሙሮች ("እናሸንፋለን") ; ኦፔራ ( ፊሊኘ ግላስ፣ "ሳትያግራሀ")፣ መፅሀፎች ( የቤርታ ቮን ሱትነር "መሳሪያህን አስቀምጥ") ፣ ግጥሞች ( የስቲቭ ሜሰን "የጆኒ ዘፈን ")፣ ስዕል ( የካቲ ኮልዊትዝ "የሚተከል ዘር ሊፈገጥ አይገባም ")፣ እና ፊልሞች (ሪቻርድ አቴንቦሮ "ጋንዲ")፡፡ በማሊካ ሳራባይ በ1995 በአህመዳባድ ህንድ የተመሰረተው " ሴንተር ፎር ነንቫዩለንስ ትሩ አርትስ" ያለመግደል ላይ ያተኮረ የፈጠራ ችሎታን በእይታ፣ በቲያትር፣ እና የፅሁፍ አርት ተጠቅሞ ማህበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣት ይሞክራል፡፡

### ያለመግደል ፖለቲካዊ ትግሎች

ምንም እንኳን ለታሪክ አዲስ ባይሆንም፣ ያለመግደል ላይ የነበሩ ፖለቲካዊ ትግሎች ባለፈው ግማሽ ሀያኛ ክፍለ ዘመን ውስጥ የሰው ልጅን ያለመግደል ችሎታ በከፍተኛ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡ ጂን ሻርኘ እንዳሉት " እስከ 1980 ድረስ ጥቃት የሌለው ትግል፣ ወይም የሰዎች ሀይል፣ በአለም ውስጥ ያለውን የፖለቲካ መንገድ በአስርት አመታት ውስጥ ሊቀይር ይችላል

ብሎ ማሰብ አይቻልም ነበር" ( ሻርፕ 1989:4 ):: ከ1970 እስከ 1989 ባለው ጊዜ የነበሩትን ያለመግደል ትግሎችን ሻርፕ ጠቁመዋል:: እነሱም:- በአፍሪካ ( አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ሱዳን) ፣ እስያ ( ባርማ፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ፖኪስታን፣ ፊሊፒንስና ቲቤት) ፣ በአሜሪካዎች ( አርጀንቲና፣ ቦሊቪያ፣ ብራዚል፣ ቺሊ፣ ሀይቲ፣ ሜክሲኮ፣ ኒንራጉዋ፣ ፖናማ እና ዩጉዝላቪያ) በመካከለኛው ምስራቅ (በእስራኤል የተያዘው ፍልስጤም) ፣ በፖሲፊክ ( አውስትራሊያ እና ኒው ካሌዶንያ):: ከ1989 ጀምሮ የሰዎች ያለመግደል ሀይል የቀድሞ ሶቪየት ዩኒየን፣ ምስራቅ አውሮፖ፣ ባልቲክ ሪፐብሊክ እና ሞንጉሊያ የነበሩትን የአንድ ፖርቲ የኮሚውኒስት ዘመን እንዳያልቅ አድርገዋል:: በተጨማሪም ለጀርመን ሰላማዊ ወህደት እና በደቡብ አፍሪን ለነበረው የአፖርታይድ አገዛዝ ማብቃት ረድቷል::

ምንም እንኳን ሁሉም ያለመግደል ትግሎች ከግድያ ነፃ ባይሆኑም፣ አንዳንዶቹ እንደ በርማ ( በ1988) እና ቻይና ( በ1989) በሀይል ጥቃት የታፈኑ ቢሆንም፣ እና አንዳንድ ተመልካቶች ወጤታማነቱን ለመግደል በማስፈራራት የመጣ ነው ቢሉም፣ እነዚህ ትግሎች ሌሎች ደም መፋሰስ ከታየባቸው የአሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ሩሲያ፣ ቻይና ትግሎች እና ሌሎች ጥቃት የተሞላባቸው አብዩቶች ይለያሉ:: በህንድ ከነበረው የጋንዲ የነፃነት እንቅስቃሴ የአለምን የቅኝ አገዛዝ ስርዐት እንዴት እንደጣለ በመማር ሌሎች የታዩ እንቅስቃሴዎች:- የዘር ህዝባዊ መብቶችን በዩናይትድ ስቴትስ ያረጋገጠው የኪንግያን እንቅስቃሴ፣ ለዲሞክራሲ በፊሊፒንስ የነበረው ያለመግደል የዜጐች እንቅስቃሴ፣ የኒኩሊየር ጦርነትን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ፣ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እና ሌሎች ልምዶች ናቸው:: ከነዚህም ጠንካራ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም፣ ያለመግደል ስትራቴጂ ከልምድ ውስጥ እየወጣ ነው:: በተራቸው አንዳንድ ገዢዎች፣ የዜጐችን ለሰላም፣ ነፃነትና ፍትህ ያለ ትግል በማይገድል ሁኔታ እያስተናገዱት ነው::

በመንግስቶችንና የመዋቅራዊ ለውጦችን ለመለወጥ ሀይል እንዳላቸው ካሳዩ ሰፊ ትግሎች በተጨማሪ ብዙ የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ግድያ የሌለበትን ማህበረሰብ ለመፍጠር ልዩ ለውጦችን ፈልገዋል:: ከነሱም ውስጥ:- የሞት ግድያን ለማቅም የተደረገ እንቅስቃሴ፣ ላለማስወረድ አማራጭ ፍላጋን፣ በራስ ፈቃድ በጦር ሰራዊት ውስጥ ላለመስራት ያለ ፍላጐትን መቀበል፣ የጦር ሀይሎችን መተው፣ ግድያ የማይፈፅም የህዝብ መከላከያን መፍጠር፣ በገጠርና ከተማ ግጭቶች ውስጥ ግድያ ሌለበትን ደህንነት መፈለግን፣ የጦርነት ግብርን ማቆም፣ የኒኩሊየር፣ ባዩሎጂካል፣ እና ኬሚካል መሳሪያዎችን ማጥፋት፣ የሚቀበሩ ፈንጂዎች ማጥፋት፣ አወቶማቲክ መሣሪያዎችን እና የእጅ ሽጉጦችን ማጥፋት፣ የግድያን የሚረዳ ኢኮሚያዊ ድጋፍን ማቆም የሰዎችን የጥቂቶተንና የአካባቢ ነዋሪዎችን ሰብአዊ መብት መጠበቅ፣ አካባቢው ከጥፋት አንድድን መጠበቅና፣ ሌለች ፖለቲካዊ፣ ሚሊተሪያዊ፣ ኢኮሚካዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ባህላዊ ለውጦችን እውነት ለማድረግ መሞከር ናቸው::

ከታሪክ አጋጣሚ ላቅ በማለት፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ያለመግደል ትግሎች በፊር ቀዳጅ ጥናት የተደገፋ ሲሆን ፣ የበለጠ በእውቀት የተመሩ፣ ይበልጥ በፈጠራ የተሞሉ፣ በስፋት በአለም አቀፍ መገናኛ መንገዶች የተሰራጩ ናቸው:: ጥናቶቹን ካደረጉት ወስጥ ጂን ሻርፕ ( 1973)፣ ጆሀን ጉልታንግ (1992;1996)፣ ጃክ ሴሚሊን ( 1993) ፣ ማይክል ራንድል (1994) ፣ እና ሌሎች ይገኙበታል:: በግሎባላይዜሽን ዘመን ወስጥ ከቀጠለው ደም መፋሰስ መሀል፣ ፀረጥቃት እንቅስቃሴዎች እየተነሱና በአለም እየተስፋፉ ያለ ሲሆን፤ ይህም በፈጠራዊ መንገድ የህብረተሰቡን ጥቃት ላይ መውደቅና ፍትህ ማጣት ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ነው:: ( ፖወርስ እና ቮጌል 1997; ዘንስ፣ ኩርትዝ እና አሽር 1999፣ አከርማን እና ዱቫል 2000 )

### ታሪካዊ ስሮች

ታሪክ፣ በተለይም በታላቅ የሀይል ጥቃት ጊዜያቶች ውስጥ፣ ዋና ያለመግደል ችሎታ መስረቶችን ያሳያል:: በአለምአቀፍ ደረጃ ያለመግደል ውጤቶች አንድ ላይ ቢሰብሰቡ፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ግድያ የሌለው ጊዜ ሊፈጠር ይችላል:: አንዳንድ ይሄን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በአሁኑ ጊዜ ሊታዩ ይችላሉ::

ያለመግደል እምነትና ቀራጥነት ሊታፈኑ አይችሉም:: ከ2ሺህ አመት በላይ የአይሁድ ክርስቲያን ታሪክ፣ እንደ ስድስተኛው ትዕዛዝ " አትግደል " (Exod 20 :13) በተራራው ላይ ያለው ስርዐት ( ማቲ 5:3: 7:27) ፣ እና በመስቀሉ ላይ የነበው ክርስቶስ ምሳሌ በቃልም በፅሁፍም

ቆይተዋል፡፡ ያመግደል ጥሪት ለግድያ ባለ ደፋር ተቃውምም ይቀጥላል፡፡

መሞትም፣ መሰዋትም ቢኖር፣ ይህ እንቅስቃሴ በአንዳንድ ያልተማሩ ገበሬዎች ጀምሮ እስከ ታላላቅ በተከበሩ ሰዎች ድረስ ቀጥሏል ( ብሮክ 1968; 1970; 1972 ;1990 ; 1991a 1991b 1992)፡፡ በጅን 29 1895 በሩሲያ ውስጥ ሶስት አካባቢዎች ላይ 7, 000 ፖሲፊስት የዱክሆቦር ገበሬዎች በመሰብሰብ "መሳሪያዎችን የማቃጠል ስራ" የሰሩ ሲሆን ፣ ያንንም ተከትሎ 7, 500 ዱክሆቦሮች ለክስ እና በ1899 ወደ ካናዳ ለመሰደድ ተዳርገው፤ በቶልስቶይ እርዳታ ደርሰዋል፡፡ ( ታራሶፍ 1995፡ 8-9) ያለመግደል ችሎታ ታሪካዊ ስሮች፣ በሌሎች ባህሎች ውስጥም ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ቡዲዝም ( ሆሪገን 1996; ፔጅ እና ጊላቅ 1991)፣ በእስልምና( ባነርጂ ፣ 2000; ክሮው 1990 ኢስዋለን 1999፣ ኪሽቴኒ 1990፣ ፒጅ 1993 a ፣ ሳታ አናንድ 1990፣ ታያቡላ 1959) ፣ እና በአይሁድ እምነት ( ሽዋርዝቻይልድ - ቀን የለም; ፖልነር እና ጉድማን 1994፣ ዊልኮክ 1994)

በተጨማሪ ሞስኮስ እና ቻምበርስ /1993/ እንዳሳዩት፣ በፈቃደኝነት ጦርነት ላይ ላለማገልገል የሚደረግ ውሳኔ በዲሞክራሲዎች፣ ሰብአውያን እና ፖለቲካዊ መሰረቶች እየጐሉ መጥተዋል፡፡ መንፈሳዊውና አለማዊው፣ በመርሆ የሚመራውና፣ በተግባር የሚመራው፣ ሁሉም ለመግደል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን እያሳዩ ነው ፡፡

ሌላ ታሪካዊ እይታ ደግሞ፣ የአንዳንድ ጥቃትን ይቀበሉ የነበሩ የፖለቲካ መሪዎች በኃላ ወደ ሀቀኛ፣ እና ሞት የማይሽረው ያለመግደል እምነትን የሚያሳዩ ግለሰቦች፣ መቀየራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፡ በ1713 የኘርሺያው ንጉስ ፍሬድሪክ አንደኛ፣ ጦርነትን የሚቃወሙ ሜኖናይቶችን ለግድያ ማሳደደድ እንዲቆም አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በሩሲያ ለሚገኙ ሜኖናይቶች እንደዛ አይነት ሁኔታ በካተሪን 2ኛ (1763) እና አሌክሳንደር 2ኛ ( 1875) ተሰጥቷል፡፡ ( ብሮክ 1972፡ 230፣ 234፣ 436) በ1959 የቶልስቶይ ጓደኛ የሆነውን ቪ.ጂ. ቼርትኮቭ ልመናና፣ የበልሼቪኩን ቪ.ሲ. ቦንች ብሩቪች ምክር ተከትሎ፣ ሌኒን ቶልስቶይንና ሌሎች ለዘብተኛ የሀይማኖት ማህበረሰቦች «በሬድ አርሚ» ውስጥ ከማገልገል ነፃ አድርጓቸዋል፡፡ ( ጆሴፍስን 1985፡ 162; ኮፒተርስ እና ዝቬሬቭ 1995) ከቦልሼቪክ የመጀመሪያ ውሳኔዎች ውስጥ አንዱ በጦር ሀይሉ ውስጥ የሞት ቅጣትን ማስቀረት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ውሳኔዎች፣ ከፍተኛ የሆነ ያለመግደል ግኝት ላይ ለመድረስ ይረዳሉ፡፡

ጀሮም ዲ. ፍራንክ እንደተመለከተው፣ መሪዎችን የመከተል ሁኔታ በዜጐችን ላይ ስለሚታይ፣ በቅድሚያ የፖለቲካ መሪዎችን ባህሪ መቀየር ለሰላም ከሚደረጉ በጣም ውጤታማ ስራዎች ውስጥ አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን መሪዎች እየመሩም ተከታዬች ወደኃላ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ በምዕራብውያን ዴሞክራሲ ውስጥ የሞት ቅጣትን ማስወገድ ላይ በሰሩት ጥናት ዚምሪንግ እና ሆኪንስ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> በዲሞክራሲዎች ውስጥ የሞት ቅጣት መቆም አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ተቃውሞን ተከትሎ ይደረጋል፡፡ ከዩናይትድ ስቴትስ በስተቀር ሁሉም የምዕራብ ዴሞክራሲ የሞት ቅጣትን አቁሟል፡፡ ነገር ግን የሞት ቅጣት በሚቆምበት ወቅት፣ የህዝብ ዲሞክራሲያዊ ስምምነት በቅጣቱ መነሳት ላይ የታየበት ሀገር አላገኘንም፡፡ የማህበረሰቡ ቅራኔ ቢኖርም ነገር ግን የቅጣቱ መነሳት ለረጅም ጊዜ እንደቆየ ይገኛል (1986:XVI)

ነገር ግን ግድያ ለሌለበት የማህበረሰብ ለውጥ የመሪዎችን ፖለቲካዊ አመራር ማየት ( ፔጅ 1977፣ በፒንስ 1978) ፣ የህዝቦችን እያደገ የሄደ ያለመግደል ሀይል እንዳናይ አያደርግም፡፡

ሌላ ታሪካዊ እይታ የሚያሳየው ደግሞ አለመግደል ላይ ያለ ቁርጠኝነት፣ ብዙውን ጊዜ ስቃይን ከሚያላቅቁ ስራዎችና ህይወቶችን ከሚያከብሩ የማህበረሰብ ለውጦች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ አለመግደል ማለት፣ አለማሰብንም ሆነ አለመስራትን አያሳይም፡፡ ለምሳሌ «ጄን አሂምሳ» ጥሪቱን በማስፋት እንስሳትን ፣ ወፎችንና፣ ሌሎች ህይወት ያላቸውን ነገሮች በማዳን ላይ ያተኩራል፡፡ (ቶቢያስ 1991 ) ሌሎች መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚጥሩ ያለመግደል

እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ በህንድ በጋንዲያውያን እንቅስቃሴ ይታያሉ። ይሄ ፖለቲካዊ ነፃነት ላይ ብቻ ሳይሆን ትኩረቱ ከፍተኛ ኢኮሚያዊ ማህበረሰባዊ እና ባህላዊ ለውጦችን ለድሆች፣ ሴቶች፣ አናሳ ቁጥር ያላቸው ቡድኖች፣ የመደብ ክፍያዎች፣ እና በማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ግንኙነቶች ለማምጣት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በዩናይትድ ስቴትስ ያለው ኪንጊያን እንቅስቃሴ እና ለነፃነትና ለዘር እኩልነት ያለው ጥረት በአሜሪካ መዋቅር እና አሰራር ውስጥ ያሉ የፍትህን መሰናክሎች ለማስወገድ እና ህዝቡን ከድህነት እስከ ጦርነት ለማላቀቅ ሰርቷል።

ዘመናዊ በሆኑ መንግስታት ውስጥ እንኳን ጥቃት የሌለው ችሎታን የሚያሳይ ታሪክ አለ። ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ እንደ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል። በጣም የሀይል ጥቃት ከነበረባቸው ባህሎች ጋር በመነፃፀር ያልተቀመጠ ቢሆንም፣ በአሜሪካ ልምድ ያሉት ያለመግደል ስሮች፣ ለፖለቲካ ሳይንስ ተማሪዎች በብዛት ያልታወቁ ናቸው። ሆም ፊር ቀዳጅ ጥናቶች የማያጠያይቅ መራቸወን ያሳያሉ። (ብሮክ *1968* ; ኩኒ እና ሚካሎውስኪ *1987* ) ; ሆክሌ እና ጁንኬ *1993*; ካፑር *1992*; ኮን *1987*; ሊንድ እና ሊንድ *1995*; የአሜሪካ ሂስቶሪያንስ አሶሲየሽን *1994*; ሺ ልሴል *1968*; ትሩ *1995*; ዚን *1990*)

**በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የአለመግደል ሁኔታ**

በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ አመሰራረት ጊዜ፣ ያለመግደል ሁኔታ ነበር። ይህም በአካባቢው የመጀመሪያ ነዋሪዎችና በፓስፊስት መጤዎች መካከል በነበረ ሰላማዊ ግንኙነት ታይቷዋል። በሰባ አመታት ውስጥ፣ አብዛኛውን ጊዜ (1682-1756) ወታደር ባልነበረበት የፔንስላቫንያ ክልል ውስጥ፣ ፓስፊስት ኩዌከርስ ከዴላዌር ህንዶች ጋር በሰላም የኖሩ ሲሆን፤ ይህም ያደረጉት ለጓደኛዊ ጥየቃዎች በራቸውን ክፍት ለማድረግና፣ የጥቃት ወይም የጠብ ጭምጭምታዎች ሲኖሩ ለመወያየት ቃል ገብተው ነው። (ብሩክ 1990፡ 87-91) ሃይማኖታዊ የሆኑ፣ በጦርነት ውስጥ ላለመሳተፍ የሚቀርቡ ምክንያቶች፣ ከአስራ ሶስቱ ውስጥ በአሰራ ሁለቱ ቅድመ አብዮታዊ ክልሎች ውጥት ተቀባይነት ተሰጥቶአቸው ነበር። በጣም ነፃዊ በሆነው ሮድ አይላንድ (1673) ፣ሃይማኖታቸው "ለመሰልጠን፣ ለትጥቅ፣ ለተቃዋሞ ጥል እና ለመግደል" የማይፈቀድላቸውን ወንዶች መብታቸውን የጠበቀ ሲሆን፤ እነዚህም "ምንም ቅጣት፣ የገንዘብ ክፍያ፣ ማራቅ ወይም መታሰር" ሊያጋጥማቸው እንደማይገባ አስቀምጧል።(ኮን 1987፡ 10,13)

አለመግደል አዲስ እየመጣ በነበረው አስተዳደር የህግ ነጥቦች ውስጥ ነበር ። በኮንቲኔንታል ኮንግረስ በ1775 ከተላለፉት ደንቦች ውስጥ አንዱ፣ ግድያ ለማይደግፍ የሃይማኖት እምነት ላይ "ምንም ጥቃት" እንደማይደረግ ነው (ኮን 1987፡ 10,13)። ለዩኤስ ህገመንግስት በ1989 ቢል ኦፍ ራይትስን በጨመሩት ውይይቶች፣ ተወካዩ ጀምስ ማድሰን ያቀረበው ሃሳብ - በአንቀፅ 2 ውስጥ የማንኛውም ዜጋ ለመግደል ፍቃደኛ ባይሆን እንዲችል የሚያደርገው መብት እንዲሰጠው ነው። "ማንም በሃይማኖቱ የጦር መሳርያ እንዲይዝ የማይፈቀድለት ሰው፣ የሚሊተሪ አገልግሎት ውስጥ እንዲገባ መገደድ የለበትም" (ኮን 1987፡ 11) የማዲሰን ሃሳብ በተወካዮች ምክር ቤት ተቀባይ ያገኘ ቢሆንም፣ ነገር ግን በመንግስቱ የመብት ጥበቃ የሴኔት ኮንፍረንስ ኮሚቴ ውስጥ፣ ይሄ ሃሳብ የፌደራልን ቁጥጥርን በክልሎች ላይ ያስቀምጣል ተብሎ ውድቅ ተደርጓል።

በአሜሪካ አብዮት ጊዜ (1775-83)፣ በተለያዩ ጎኖች ያሉ ብዙ ብሄር እና የሃይማኖት እምነቶች ያሏቸው ቀኝ ገዢዎች ለመግደል ፍቃደኝነታቸውን ነፈጉ። መፅሀፍ ቅዱስ አንባቢ የሆነ የእንግሊዙ ወታደር ቶማስ ዋትሰን፣ መግደልን የተቃወመ ሲሆን፣ በኃላም የማሳቹሴትስ ክዌከር ሽማግሌ ሆነ(ብሮክ፡ 1968፡ 280-81) እንግሊዞች ቦስተንን ከከበቧት በኂላ፣ እና በመቀጠልም አሜ,ሪካኖች ከያዝዋት በኂላ(1774-76)፣ ፀረ ጦርነት እምነት ያላቸው ኩዌከርስ በጊዜው የነበሩትን ዋሽንግተን እና ሀዌ የተባሉ ጀነራሎች፣ ለህዝቡ እና ለስደተኞች የሰብአዊ እርዳታ መስጠት እንዲችሉ አሳመኗቸው። (ብሮክ፡ 1968፡ 193-94) ከብዙ ስቃይ በኂላ የሰዎች ያለመግደል ፍላጎት ሊከበር ችሎ ነበር።

ያለመግደል ትግል ነፃነትን ሊያገኝ ይችላል ብሎ ማሰብ ይቻል ነበር።(ኮንሰር እና ሌሎችም 1986) ቻርልስ ኬ. ዊፕል ‹ኢቮልብስ ኦፍ ሪቮሉሽናሪ ዋር› (1839) ብሎ በፃፈው ፅሑፍ "ወደ የመሳርያ ትጥቅ ባንሄድ ኖሮ ነፃነትን ውጤታማ በሆነ ፈጣን፣ በተከበረ እና በተመቻቸ ሁኔታ ማግኘት እንችል ነበር። መንገዱም "አንደኛ፡- ፍትሃዊ ያልሆነ ጥያቄዎችን በዝምታ መቃወምና ባለመቀበል፤ ሁለተኛ፡- ህዝብ ብሶቱን መግለፅና ለመፍትሄ ጥያቄውን ማቅረብ እንዲችል ማድረግ እና፤ ሶስተኛ፡- የሰውን ታዛዥነት ለማረጋገጥ የሚጠቀሙትን ማንኛውም ጥቃት ችሎ ማለፍ።" (2) የዊፕል ጥቃት የለሽ ትግል ትንተና፣ በኃላ የመጣውን የጋዲንና ጂን ሻርፕ(1973) ዋና ዋና ሃሳቦች የጠበቀ ነበር። የጥቃት የለሽ አብዮትን ጥቅሞች ዊፕል በሚያሰላበት ጊዜ፣ አሁን ከጠፉት ህይወቶች ያነሱ ሰዎች ይጠፉ ነበር ብሎ ገምቷል(ምናልባትም 1000 መሪዎችና 10,000 ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆች። በስምንት አመቱ የትጥቅ ትግል ከሞቱት 100፣000 ሰዎች ጋር ሲነፃፀር) የጦርነት የኢኮኖሚ ዋጋ (135 ሚሊዮን ዶላር) ሊቀር የሚችል ወጪ ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ የአዲሱ ሃገር መንፈሳዊና ስርአታዊ መሰረት ከፍ ባለ ደረጃ ይመሰረት ነበር። በተጨማሪም መግደል ላይ ያላተኮሩ የአሜሪካ አብዮተኞች በባርነት ቀጥለው "ማጭበርበርን ፣ ጥፋትን፣ በማድረግ እየቀጠሉ የሃገሪቷን የመጀመርያ ነዋሪዎች አያጠፋም ነበር።" እና "ለሃገራቸው መንግስት የጥቃትና የመልሶ ማጥቃትን ስርአት ተክለው አይሄዱም ነበር" ይህም የሞት ቅጣትን ጨምሮ ነው።(10)

አለመግደል ከሲቪል ጦርነቱም በፊት ነበር። ስቃይና መስዋእትነትን በመቀበል ጀግኖች ከእንግሊዝ(1812) እና ሜክሲኮ(1845) ጋር በነበሩ ጦርነቶች ጊዜ ለሰላም የሰሩ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ የሴቶችን መብት የማስከበርና፣ ባርነትን የማስወገድ ጥረቶች ይገኙበታል። ከነሱም ውስጥ፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ጥቁርና ነጭ፣ ሃይማኖታዊ እና አለማዊ ሰዎች ይገኙ ነበር። (ኩኒ እና ሚካሎውስኪ 1987፡ 20-33፤ ሊንድ እና ሊንድ 1995፡ 13-41) መግደልን የማቆም ጥረቶች፣ ነፃነትን የሚሰጡ ህጎችን በሰሜናዊ ህጎች ውስጥ ለማካተት በቅተዋል። በዙርያ አካባቢና ደቡባዊ ክልሎች ውስጥ፣ አንዳንድ የባሪያ ባለቤቶች መንፈሳዊና ኢኮኖሚያዊ ማሳመኛዎች በማቅረብ ባርያዎቻቸውን ነፃ ሊያደርጉ ተስማምተው ነበር። ይህም የኩዌከርን ጆን ውልማንን (1720-72) ትንቢታዊ የስራ ውጤቶች ቀጥሏል ። በእንግሊዝ ባርነት የቀረው በ1777፣ የባርያ ንግድ ደግሞ በ1807፣ እና ባርያ መያዝ በ1833 ነበር። እንደ ካናዳ ሁሉ፣ አሜሪካ ከእናት ሃገሩ ጋር ግንኙነቱ ባያቋርጥ ኖሮ ባርነት በሰላም ይጠፋ ነበር።

በሲቪል ጦርነቱ ጊዜ(1861-65) የጦር ተቃዋሚዎች ከተሰቃዩ፣ ከታሰሩ እና ከተገደሉ በኋላ በኮንፌደራንሲ (1862) እና ዩንየን (1864) ህግ ረቂቆች ውስጥ፣ አንድ ሰው በህሊና ጉዳዮች ምክንያት መግደል ባይፈልግ መብቱ ሆኖ ተቀምጦ ነበረ። ምንም እንኳን ህጎች አንዳንዴ ተገቢ ባልሆነ መልኩ በዝቅተኛ ደረጃዎች ላይ እየተፈፀሙ ቢሆንም፣ የግል ጉዳዮችን የማቆም ጥያቄ ለዩኒየኑ ፕሬዝዳንት አብርሀም ሊንከን፣ ለጦር ሴክሬተሪ ኤድዊን ስታንተን እና የኮንፈደሬት ረዳት የጦርነት ሴክረታሪ ጆን ኤ ካምፐቤል ቀርቦ ነበር። (ሞስኮስ እና ቼምበርስ 1993፡ 30-1) በጦርነት ውስጥ ተይዘው የነበሩ ግድያን የሚቃወሙ የቱነሲ ‹ዲሳይፐልስ ኦፍ ክራይስት› በመጀመርያ ውጤታማ በሆነ መልኩ ጥያቄያቸውን ለኮንፈደሬት ፕሬዝዳንት ጄፈርሰን አቅርበው በመቀጠልም የዩንየኑን ጦር መሪ አንድሪው ጆንሰን ከግድያ እንዲያመልጡ አሳመኑ። (ብሩክ 1968፡ 842-3)

በሲቪል ጦርነቱ ጊዜ ከነበረው የወንድማማቾች ደም መፋሰስ መሃል፣ ያለመግደል ፍላጎት በሁለቱም ጎኖች በተለያየ መጠን ተቀባይነት አግኝቶ ነበር።

አለመግደል በኢንደስትሪያዊ እና ኢምፔርያል ዘመን ቀጥሎ ነበር። ወደሃያኛው ክፍለ ዘመንም፣ ሶስት የአለም ጦርነቶችን ይዞ ሄዷል።

ምንም እንኳን በቀጣሪ፣ ፖሊሲ፣ አገር እና አንዳንዴም የሰራተኞች የሃይል ጥቃት የተረበሸ ቢሆንም፤ በአሜሪካ የነበረው የጉልበትን ሁኔታ የማሻሻልና የማደራጀት መብት የትግል

ጉዳይ አልነበረም። የሰራተኛው መደብ የትጥቅ አብዮት አልነበረም። ባለመግደል ትግል የሴቶችን እኩል የመብት እንቅስቃሴ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የመጀመሪያዋ የሴቶች ኮንግረስ በ1916 ተመራጭ የሆነችው ጃኔት ራንክሊን፣ (የሞንታና ሪፐብሊካን) ተመርጣለች (ጆሴፍሰን 1974)። በ1917 ከ49 መንገድ የስራ ባልደረቦች [8] ከስድስት ሴናተሮች [9] ጋር በመሆን፣ የዩናይትድ ስቴትስን ወደ አንደኛ አለም ጦርነት መግባት ተቃውማ መርጣለች። በ1940 ድጋሜ ተመርጣ፣ በ1941 የዩናይትድ ስቴትስ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ውስጥ እንዳትገባ የተቃወመች ብቸኛ ተመራጭ ነበረች። በኃላ በ88አመቷ 5,000 ሴቶችን በጃኔት ራንክሊን ብርጌድ ሰልፍ ዋሽንግተን ውስጥ የመራች ሲሆን፤ አላማውም በቬትናም ጦርነት ውስጥ አሜሪካ የምታደርገውን ግድያ መቃወም ነው።

በመጀመርያው የአለም ጦርነት ወደ 4000 የሚሆኑ የአሜሪካ ሰዎች አንገድልም ብለው ነበር። አንድ ሺህ ሶስት መቶው፣ ውግያ የሌለባቸውን የጦር ሰራዊት የሰራ ድርሻዎች ተቀብለው ሰሩ። ይሄም አብዛኛው የህክምና ነው። ሌሎች 1000፣ ለእርሻ የጉልበት ስራ ተመደቡ። 940 የተገላሉ የሚሊተሪ ማሰልጠኛ ዩኒቶች ውስጥ ተቀመጡ። እና 450 "ፍፁማውያን" በምንም መንግድ ከግድያ ጋር የተያያዙ ነገሮች ላይ አንተባበርም ብለው በጦር ፍርድ ቤቶች ተዳኝተው፣ በጦር እስር ቤቶች ውስጥ የተከተቱ ሲሆን፤ አስራሰባቱ ከመጥፎ አያያዝና ከበሽታ የተነሳ ሞተዋል። (ሞስኮስ እና ቻምበርስ 1993፡ 34-5፤ ኮን 1987፡ 42፤ ሊንድ እና ሊንድ 1995፡ 91-117፤ ሽሊሰል 1968፡128-175)።

በሁለተኛው የአለም ጦርነት የሚሊተሪ አገልግሎት ጊዜ(1940-47)፡ 72,354 ወንዶች ህሊናችን ለመዋጋት አይፈቅድልንም ብለው 25,000 ውጊያ የሌለበት ሚና ሲሰጣቸው፤ 11፣996 ወንዶች ከ 213 የሃይማኖት መደቦች በመምጣት፣ 151 የሲቪል ህዝብ አገልግሎት ካምፖች ውስጥ ለመስራት ተስማምተዋል(ዋቢ ሰነድ 4)። 6,086 ሰዎች ከምንም አይነት ጦርነት ጋር የተያያዘ ነገር ላይ አንተባበርም በማለታቸው ለእስር ተዳርገዋል። ከታሰሩት ውስጥ ሶስት አራተኛው የጂሆቫ ምስክር እምነት ተከታዮች ነበሩ። (አንደርሰን 1994፡ 1-2፣ ሞስኮስ እና ቻምበርስ 1993፡37-8፤ ኩኒ እና ማክሎውስኪ 1987፡ 94-5፤ ጋራ እና ጋራ 1999)

የአሜሪካ ህዝብ ችሎታ በድጋሜ በኒኩሌር ዘመን "ቀዝቃዛ ጦርነት" ጊዜ (ከ1945-91) የታየ ሲሆን፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከአንደኛውና ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኃላ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ አራተኛውንና አምስተኛውን ከፍተኛ የደም መፍሰስ የታየባቸውን ዘመናት ናቸው። እነዚህም የቪየትናም(1964-75) እና ኮርያ(1950-53) ጦርነቶች ናቸው። በአሜሪካ፣ ሶቭየት ዩንየን፣ እና ተባባሪዎቻቸው መካከል በነበረው ቀዝቃዛ ጦርነት ቢያንስ በአለም አቀፍ ደረጃ ወደ 20 ሚልዮን ሰዎች በአብዮታዊ፣ ፀረ አብዮታዊ እና ጂዎፖለቲካዊ የግድያ ምክንያቶች ጠፍተዋል። በኮርያ ጦርነት ጊዜ ወደ 22500 የሚሆኑ ለጦርነት የተመለመሉ አሜሪካዊያኖች፣ ግድያን ለመፈፀም ሳይስማሙ ቀርተዋል። በቪየትናም ጦርነት ጊዜ የነበረውም ታላቅ ተቃውሞ፣ ብዙ ቁጥር ያላቸው ወንዶች ሃይማኖትን መሰረት አድርገው እንዳይዋጉ አድርጓል።(ሞስኮስ እና ቻምበርስ 1993፡ 39-43)። በ1972 ውስጥ፣ ከተመለመሉት ይበልጥ ከተመዘገቡት ውስጥ አብዛኛዎቹ ህሊናቸው ለጦርነት እንደማይፈቅድ ገልፀዋል። ሌሎች የቪየትናም ጦርነትን የሚቃወሙ ሰዎች ከምዝገባ ለማምለጥ ሞክረዋል። ከዚያም ወደ እስር ወይም ስደት በመዳረግ፣ በቀድሞ ጊዜ ጦርነት የሚሸሹ ሰዎች ከአገራቸው ወደ አሜሪካ ያደረጉትን ስደት በተገላቢጦሽ ደግመዋል። በቬትናም ውስጥ ከነበረው ደም መፋሰስ መሃከል፣ ትጥቅ ያልያዙና ቀጥታ ውግያ የሌለበት ስራ (እንደ ህክምና ያለ ድርሻ) የነበራቸው አሜሪካኖች፣ ጦርነቱን ባለመፈለግ ተፈርጀዋል።(ጂዮግሊዮ፡ 1989)

በቀዝቃዛው ጦርነት ማግስት፣ ያለመግደል እምነት በፐርሽያው ኢራቅ ላይ በተደረገ የገልፍ ጦርነት ጊዜ በድጋሚ ተነስቷል። ከቅኝ ግዛት ዘመን ጀምሮ የሞት ቅጣት የሚጠይቁ የወንጀል አይነቶች ቁጥር የቀነሱ ሲሆን፤ አሁን ያለው ሁኔታ እንደሚከተለው ነው። የአገር

ክህደት በሚሽጋን(1846)፤ እና ምንም የግድያ ቅጣት የሚያሰጥ የወንጀል አይነት አለመኖር-በሮድ አይላንድ(1852) እና ዊስኮንሲን(1853)። በአሁኑ ጊዜ በአስራ አራት ክልሎችና፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚኖሩ እና በሲቪል ኑሮ እና በግላቸው ያሉ አሜሪካኖች፣ ‹በአጠቃላይ መግደል አልፈልግም› ብለው መናገር ይችላሉ። ነገር ግን በፌደራል ደረጃ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ‹ዜጎችን መግደል የዩኤስ ህገመንግስትን ይቃረናል› የሚል ህግ ማውጣት ይቀረዋል። (ዚምሪንግ እና ሆኪንስ 1986)

ሌሎች በአሜሪካ ውስጥ ይህንን ለመስራት እድል የሚታባቸው አካባቢዎች የሚከተሉት ናቸው። ከኑክሊየር ነፃ የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት(ሰይፎችን ወደ ማረሻ መሳሪያ የመቀየር እንቅስቃሴ)፣ የድህንነት ጥቃት የሌለበትን ማህበረሰብ መፍጠር(ካቶሊክ ሰራተኞች እንቅስቃሴ)፣ በወንዶች ሴቶች ላይ የሚደረግ የጥቃት ባህልን ማንሳት (የሴቶች እንቅስቃሴ) ፣ እና የአፍሪካዉያን አሜሪካኖችን እኩልነትና የሁሉንም ዘሮች በነፃና ፍትሃዊ ማህበረሰብ ውስጥ መኖር የሚያረጋግጥ እንቅስቃሴ (ኪንጊያን እንቅስቃሴ ጥቃት ለሌለበሰት ማህበረሰባዊ ለውጥ)። በ1936 ጋንዲ ከአፍሪካዊ-አሜሪካዊ መሪዎች ጋር በተገኘበት ጊዜ የተናገረው፣ የሱን የጥቃት የለሽነት መልእክት "ከኔግሮ መንፈሳዊነት" ጋር እንደሚመሳሰልና አፍሪካዊ-አሜሪካዊያኖች ሊቀበሉት ፈቀደኛ እንደሆኑ ነው። ጋንዲ እንደመለሰው "የጥቃት የለሽነት ያልተበረዘ መልእክት ለአለም ሊቀርብ የሚችለው ምናልባትም በአፍሪካን አሜሪካኖቹ ሊሆን ይችላል" (ካፑር 1992፡89-90)። በመሆኑም በጋንዲያዊ፣ ኪንግያዊ እና ሌሎች በአለም ላይ ያሉ ያለመግደል እንቅስቃሴዎች መካከል ያለው ግንኙነት፣ እና የአሜሪካ ጦርነትን የሚቃወም ታሪኩ ጭምር የሚያሳየው፣ የአሜሪካ ጥቃት የለሽነት ከሌላዉ አለም ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነው።

ምንም እንኳን የፖለቲካ ባህሉ ጥቃትን የሚያከብር ቢሆንም፣ ከቀኝ አገዛዝ ዘመን እስከአሁን ያለው የአሜሪካ ህብረሰብ ታሪክ ውስጥ፣ ግድያ የሌለበት፣ ህይወትን የሚያከብር ስርአት ይታያል። ለምሳሌ፦ ጦረነት ውስጥ ለመግደል ፍቃደኛ ባልሆኑ ሰዎች፣ የሞት ቅጣት ላይ ባለው ተቃውሞ፣ ማስወረድ ላይ ባለ ተቃውሞ፣ የጦር ትጥቅን መፍታት ላይ በሚደረጉ ትእዛዞች፣ የሚሊተሪ ሃይል እና የአለም አቀፍ ደረጃ የሃይል ጥቃት ማሳየትን በሚቃወሙት፣ በኢኮኖሚ፣ የዘር ግንኙነቶች፣ የሴቶች መብቶች፣ እና የባህል ማንነት ውስጥ የሚታዩ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጠት የሚደረጉ ያለመግደል ስራዎች፣ እና በሃይማኖት እይታና ስነፅሁፍ አገላለፆች ይህ ይታያል (ትሩ 1995)። በተያያዘም ታሪካዊ ሁኔታዎች የታዩ ሲሆን፣ "ያለመግደል አገር ወዳጅነት" ተብሏል። ይሄም፣ የዌልሽ ጦርነትን የሚቃረን ‹ፕሌድ ሲምሩ› የተባለ ፓርቲን የመሰረተው ግዊንፎር ኢቫንስ፣ ለዌልስ በተከራከረበት ጊዜ ታይቷል።(ኢቫንስ 1972) ብሄራዊ መዝሙሩም "አሜሪካ ቆንጆዋ" ሊሆን ሲችል፣ የማርች መዝሙሩም "እናሸንፋለን" እና ፀሎቱም "እግዚአብሔር ኢ-ጥቃታዊ የሆነችውን አሜሪካ በኢ-ጥቃታዊ አለም ውስጥ ይባርክ" ይሆናል።

**የማይገድሉ ህይወቶች**

የማይገድል ማህበረሰብ መሰረት የሚገኘው የሰው ልጅ የህይወት ታሪክ ውስጥ ነው። ሴቶችና ወንዶች፣ ለብቻቸው ወይም በብዛት፣ የተመሰገኑ ወይም የልታወቁ ፣ የድሮ ወይም ያሁን ያሉት፣ አዎንታዊ የሆነ ማህበረሰባዊ ለውጥን እና ያለመግደል ሁኔታን ደባልቆ የመፍጠር ታልቅ ቆራጥነት ይታይባቸዋል። አንዳንዶች ማድረግ የሚችሉትን ሌሎችም ማድረግ ይችላሉ።

በፓሪስ የሚገኘው ‹ሙውዚ ዳርት ሞደርን ደ ላ ሲቪል ዲ. ሪ.› መግቢያ ላይ አንድ በክብ መልክ በራኦል ዱፊ የተሰራ የስነጥበብ ውጤት አለ። እሱም የሚያሳየው፣ ከኤሌክትሪክ ጀምሮ እስከ የጥንት ፍልስፍና እና ዘመናዊ ተመራማሪዎች ድረስ፣ ፈጠራ ያበረከቱ ሰዎችን ነው። ይህንን እና ወደ ግድያ የሌለው ፖለቲካዊ ሳይንስ የገቡትን ሰዎች አጠቃላይ ገፅታ

በምናቡ ሊያየው የቻለው አለም አቀፋዊ ውርስ የሚታይበት እንድ ነገር፣ "ቢብሎግራፊካል ዲክሽነሪ ኦፍ ሞደርን ፒስ ሊደርስ" (ጆሴፍሰን 1984) ሲሆን እሱም በ39 አገሮች ያሉ ከ1800-1980 የኖሩ ታሪክ ይዘግባል፡፡ ከገፅ እስከ ገፅ ሲነበብ፣ 1134 ገፆቹ ግድያ የሌለበትን አለም ለማግኘት የሚረዱ ሙያዎችን፣ መንገዶችና፣ የሊብራል አርት ትምህርትን ያቀርባል፡፡ አስተሳሰቦች፣ ጊዜያዊ የሆነ ጥቃትን ከመቀበል ጀምሮ፣ ሙሉ በሙሉ ያለመግደል መርሆች ላይ ቆራጥ አቋም መያዝን ይጨምራሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ጥናትን በታሪካዊ፣ ጂኦግራፊያዊ፣ ባህላዊ እና በዘመናዊ ኑሮ ውስጥ ማካሄድ አለም አቀፍ ያለመግደልን ድፍረትና ቆራጥነት ያበረታታል፡፡ ሁሉን ያካተተ ግኝት እና ግድያ ያሌለበትን ህይወት መካፈል አስፈላጊ ነው፡፡

ግድያ የሌለባቸው ህይወቶች በጊዜ፣ ባህልና ቦታ ውስጥ ይገናኛሉ፣ እናም ያስተጋባሉ፡፡ በግብፅ ውስጥ የኑቢያ ተወላጅ የሆነው ፈርኦን ሻባካ(በ760-695 ክ.ል.በፊት) የሞት ቅጣት አቁሟል(ቤኔት 1988፡11)፡፡ በህንድ ውስጥ ቡዲስት የሆነው መሪያቸው አሾካ፣ የካሊንጋን መያዝ ተከትሎ ጦርነትንና የህይወት መጥፋትን ተቃውሟል፡፡

የካሊንጋ ጦርነት 100,000 ሞትን፣ የ150,000 ሰው ስደትን፣ እና ቁጥር የሌለውን የየዋሆች ሞትና ስቃይ አስከትሏል (ቾውድሁሪ 1997፡52)፡፡ ግድያን የማይደግፉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ የፈጠራን ስሜት በተለያዩ ዘመን ሰዎች ውስጥ ይፈጥራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቡዳ፣ ማህቪራ፣ እየሱስ፣ መሀመድ፣ ጆርጅ ፎክስ፣ ጉሩ ናናክ፣ ባህኡላ እና ሌሎችም፡፡ ሰዎች ከገዳይነት ወደ ግድያን ተቃዋሚነት ሲቀየሩ፣ መንፈሳዊና አለማዊ የሆኑ አስገራሚ ለውጦች ይከሰታሉ፡፡ ወታደሮች ጦርነትን የሚያወግዙ ይሆናሉ፡፡ /ክሮዚየር 1938፣ ቴንዱልካር 1967፣ ካን 1997፣ ቡባልት ጎቻርድ እና ሙለር 1986፣ ሩሴል 1997/፡፡ አብዮተኞችም ግድያን ይቃወማሉ፡፡ /ናራያን 1975፣ ቤንዳኛ 1998/፡፡ ጦርነትን የሚቃወሙ፣ የጦርነት ምልመላንም ይቃወማሉ፡፡ /ሞስኮስ እና ቻምበርስ 1993/፡፡ በሰብአዊ ጉዳዮች ዙሪያ የኒውዚላንድ አርኪባልድ ባክስተር፣ የአካል ስቃይንና የአንደኛው የአለም ጦርነት ምልመላን፣ በሚያስገርም ያለመግደል ጀግንነት ተወጥቶታል /ባክስተር 2000/፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ አንባቢ የሆነው የኦስትሪያ ገበሬ ፍራንዝ ጃገርስታተር ለሂትለር ለመዋጋት እምቢ በማለቱ ጭንቅላቱ ተቀልቷል፡፡ /ዛን 1964/፡፡ አለመግደል የሚደግፉ ነፍስ አዳኞች፣ አይሁዶችን ከሂትለር ሆሎኮስት ለማዳን ብለው ህይወታቸውን አደጋ ውስጥ ከተዋል /ፎግልማን 1994፣ ሄሊ 1979/፡፡ ግለሰቦች ጦርነትን ከሚደግፍ ዘመናዊ የኢንዱስትሪያዊ ክልል ለመራቅ፣ የሞራል፣ የቁሳቁስና፣ የጉልበት ድጋፍ ከማድረግ ተቆጥበዋል፡፡ /ኤቨሬት 1989/ ሌሎች ደግሞ ብዙሀንን የሚያጠፉ መሳሪዎችን በቀጥታ ስራ እንዲያቆሙ ይሻሉ፡፡ /ኖርማን 1989፣ ፓልነር እና ኦግሬዲ 1997/

ትንሽና፣ አምስት ጫማ ከአራት ኢንች ለሆነው ለህንዳዊው ሞህንድራስ ኬ.ጋንዲ ያለመግደል ላይ ያተኮረ አመራር፣ ብዙ ሚሊዮኖች ፍላጎታቸውን ያሳያሉ፡፡ በባህላቸው ጥቃት አለ ተብለው ከሚታሰቡት ፓታኖች፣ ለጥቃት የለሹ ሙስሊም መሪ አብዱል ጃፋር ካን ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ /ባነርጂ 2000፣ ኢስዋራን 1999/ ታላቁ፣ የጋንዲያዊ ትምህርት አስተማሪ የሆነው ዶክተር ጂ.ራማቻንድራን እንዳለው «ያልታወቁት የኢ-ጥቃታዊ ወንድና ሴት ጀግናዎች፣ ከሚታወቁት ይበልጥ ጠቃሚ ናቸው፡፡» /ራማቻንድራን 1983/ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በጋንዲ መንገድ የተማሩ ጥቂት አፍሪካ አሜሪካውያን ወጣት የኮሌጅ ተማሪ ቡድኖች፣ የተከበሩት ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርን ወደ መሪነት ቦታ ያመጣውን የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ ጀምረዋል፡፡ /ሀልበርስታም 1998/ አለመግደል ላይ ያተኮሩ አዲን ባሉ እና ሄንሪ ዴቪድ ትሩ የተባሉ አሜሪካውያን ቶልስቶይን ምሳሌ ሆነውታል፡፡ /ክርስቲያን 1978፡588/ ቶልስቶይ ለጋንዲ ፣ ጋንዲ ለኪንግ ምሳሌ ሆነዋል፡፡ ሁሉም የጀርመኑ ግሪን ፓርቲ አግኚ የሆኑትን ፔትራ ኬሊ አነሳስተዋል፡፡ /ኬሊ 1989/ እና ለሌሎችም ብዙዎች በአለም አቀፍ የፈጠራና የማስመሰል ስራን በማስፋፋት ሂደት ረድተዋል፡፡ በ1997 እና 1998 ጋንዲ ለሁሉም በጣም ተደናቂ የሆነ መሪ ተብሎ ከስልሳ ሀገሮች በላይ በመጡ ሁለት መቶ ወጣት መሪዎች ተመርጧል፡፡ እነዚህ፣ በዩናይትድ ኔሽን ዩኒቨርስቲ «ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ አካዳሚ» በአማን ጆርዳን ከሚሰጡ ሁለት ስልጠናዎች ውስጥ የመጀመሪያው ላይ የተሳተፉ ናቸው፡፡ የነሱ አድናቆት፣ ሌሎችንም ከ1945 የአለም ቅኝ ግዛት ዘመን በፊት የነበሩ የነጻነት እንቅስቃሴ መሪዎችን አድናቆት ያንጸባርቃል፡፡

አለመግደል ላይ የሚሰሩ መሪዎች በአለም ውስጥ መነሳት ቀጥለዋል፡፡ ከነሱም ውስጥ፣ ማህ

ጎሳናንዳ ከካምቦዲያ፣ ሁም ሱን ሆን ከኮሪያ፣ ኬን ሳሮ ዊዋ ከናይጄሪያ፣ ኤ.ቲ.አሪያራትኔ ከስሪላንካ፣ ሱላክ ሲቫራክሳ ከታይላንድ፣ ላንዛ ዴል ቫስቶ እና ጀነራል ጃክ.ደ.ቦላርዲዮ ከፈረንሳይ፣ ሮናልድ ማሎን ከእንግሊዝ፣ አልዶ ካፒቲኒ ክጣልያን፣ ኤን.ራዳክሪሽህን ከህንድ፣ ዶም ሄልደር ካማላ ከብራዚል፣ ኤ.ጄ.ሙስቴ ከዩናይት ስቴትስ ይገኙበታል። በታሪክ የጋንዲን መረሳት በመገልበጥ፣ የኖቤል ሽልማቶች አለመግደል ላይ ዋና አቋም ያላቸውን መሪዎች መለየት ጀምረዋል። አልበርት ጄ.ሉቲሊ እና ዴዝሞን ቱቱ ከደቡብ አፍሪካ፣ ማይሬድ ኮሪጋን ማጉዋየር ከሰሜን አየርላንድ፣ አዶልፎ ፔሬ ኢስኩቬል ከአርጀንቲና፣ ኦንግ ሳንግ ሱ ኪ ከበርማ፣ እና ዳላይ ላማ ከቲቤት ይገኛሉ።

ሴቶች የራሳቸውን ታሪክ ይዘው፣ በማህበረሰብ የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ጥቃቶችን፣ በአለመግደል ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ተነስተዋል። ለምሳሌ፦ ቤርታ ቮን ሳትነር ከኦስትሪያ፣ ጊዮንግ ቤጎስ ኦካ ከባሊ፣ ማዳ ፓትካር ከህንድ፣ ዶሮቲ ዴይ፣ ባርባራ ዴሚንግ እና ጂን ቱመር /ስታንፊልድ 1993፡ 49/ ከዩናይትድ ስቴትስ ናቸው። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጊዜ በእንግሊዝ 1704 ሴቶች ስለጦር ምልመላ ተቃውሞአቸውን ያሰሙ ሲሆን፣ 214 ለጦር ሜዳ ውጊያም ሆነ ለሲቪሊያን ስራ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ታስረዋል። /ሀሪስ ጄንኪንስ 1993፡ 77/ በአጠቃላይ ሴቶች በሚሊተሪ በሚደረጉ የሰብአዊ መብት መጣሶች ላይ ጠንካራ የሆነ ተቃውሞ አሳይተዋል። ለምሳሌ፦ /የፕላዛ ደ ሜዮ እናት፣ ቦነስ አይረስ/፣ የዘር ማጥፋት ግድያን /ዉሜን ኢን ብላክ፣ ሰርቢያ/፣ ለኒኩሊየር ጦር ዝግጅትን /ግሪንሀም ኮመን ውሜንስ ፒስ ካምፕ፣ ብሪታንያ/፣ የአካባቢ ጥፋት /ቺፕኮ ሀግ ዘ ትሪስ እንቅስቃሴ፣ በህንድ/፣ እና ሌሎች የፍትህ መጓደሎችን /ማክአሊስተር 1982፣ 1988፣ ሞርጋን 1984፣ ፎስተር 1989/። እንደ ጆአን ቪ ቦንድራንት /1969/ ያሉ ምሁራን፣ ኤሊሴ ቦልዲንግ /1980፣ 1992/፣ እና ቤርኒስ ኤ. ካሮል /1998/፣ ግድያ ለሌለበት የማህበረሰብ ለውጥ የሚረዳ እውቀትን አሳድገዋል።

የኮሌጅ ጥንዶች፣ ተጋብተውም ሆነ ሳይጋቡ፣ ግድያ ለሌለባቸው የለውጥ ትግሎች በህብረት ድጋፍ ሰጥተዋል። ለምሳሌ፦ ካስቱርባ እና ሞሀንድራስ ጋንዲ፣ ኮሬታ ስኮት፣ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ ዶሎረስ ሁሬታ እና ሲዛር ሻቬዝ፣ ዶሬቲ ዴይ እና ፒተር ሞሪን፣ ፍራንስስ ሜይ ዊዘርስፑን እና ቻርልስ ሬችት፣ ኤልሳቤጥ ማካሊስተር እና ፊሊፕ ቤሪጋን ይገኛሉ።

ሁሉንም ጾታ ያካተተ የህዝብ ሀይል በሰፊው በፊሊፒንስ የ1986 ዴሞክራሲያዊ ያለመግደል ስራ ላይ የታየ ሲሆን፤ የሴቶች መነኮሳት፣ ቄሶች፣ ተራ ሴቶች እና ተራ ወንዶች ተባብረው አምባገነንነትና ፀረ አብዮታዊ ደም መፋሰስን ተቃውመዋል። /ሳንቲያጎ. ኤ.ኤስ 1995/። በአለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ፣ የማይገድል ማህበረሰብ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ብዛትና ታሪክ፣ ሌሎች ሴቶችና ወንዶች ከግድያ ነፃ የሆነ የሁሉንም ፍላጎት ያከበረ ፍትሀዊ ማህበረሰብን መፍጠር እንደሚችሉ አሳይቷል።

## ግድያ የሌለበትን ማህበረሰብ ለመፍጠር ያሉ ብቃቶች

ግድያ የሌለበት ማህበረሰብ መኖር በሰው ልጅ ልምድና ፈጠራዊን ችሎታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። አብዛኛዎቹ የሰው ልጆች ገድለው አያውቁም። እናም አይገድሉም። ምንም እንኳን መግደል ብንችልም በተፈጥሮአችን የመግደል ፍላጎት የለንም። ሁሉም በትክክል ባይከተሉትም፣ የትልቁ መንፈሳዊ ባህል ትምህርት የሆነው «ህይወትን አክብሩ፣ አትግደሉ» ነው። ከዚህ ትምህርት ጋር ተያይዞ እንደታየው የሰው ልጆች በጣም ጥቃት ባለበት ሁኔታ እንኳን አእምሮአቸውን ማሰራትና በሙሉ ታማኝነት መስራታቸውን አሳይተዋል። ሳይንስ የግድያን ምክንያት ለማጥናት ቃል ሲገባ፣ እንዴት እንደሚያስወግዳቸውና ራስንና ማህበረሰብን እንዴት ከግድያ እንደሚያላቅቅ ያጠናል።

የተለመዱ የማይገድል ማህበረሰብ ሁኔታዎች፣ በድሮና አሁን ባሉ አለማቀፋዊ ልምዶች ይታያሉ። እነዚህ የመላመታዊ ምናብ ውጤቶች አይደሉም። መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ እና ባህላዊ ድርጅቶች እና ተግባሮች ባለመግደል መርሆ ላይ ተመርኩዘው በሰው ልጅ ልምድ ውስጥ ይገኛሉ። ሰራዊት የሌላቸው፣ ግድያ የሌለባቸው፣ መሳሪያ የሌላቸው ማህበረሰቦች አሉ። የሰው ልጅን ደህንነት የሚፈትኑ ችግሮችን መፍታት ላይ ያተኮሩ፣ ፀረ ግድያ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች አሉ። ግድያ የሌለው የታሪክ ልምድ የአሁኑንና የወደፊቱን የለውጥ ስራ ለመስራት የሚረዳ መረጃን ይሰጣል። በጣም ትልቅ የሆነ ግድያ የሌለባቸው የህይወት ታሪኮች፣ በአሁንና በድሮው ጊዜ ሲኖሩ የእነሱንም ድፍረትና ስራ ማንኛውም ግለሰብ አሁን ካሉት የአለም አቀፍ የሰዎች ልምድ ላይ ለመጨመር፣ ለማሻሻል እና ለማደባለቅ ቢያስቡ ምናልባትም ወደ ግድያ

የሌለበት ማህበረሰብ በቅርብ መድረስ ይቻላል፡፡ ይሆናል ማለት እርግጠኛ ነን ማለት ባይሆንም፤ ግን በፊት የማይታሰብ የሚመስለውን ነገር እንዲታይና፣ እኛ ሰዎች ግድያ የሌለበት አለማቀፋዊ ለውጥን ማምጣት እንደምንችል በራስ መተማመናችን እንዲጨምር አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ 3

## ፒለቲካ ሳይንስን የሚያመላክቱ ነገሮች

*ብጥብጥ አልባነት የኃይማኖት ብቻ ጉዳይ አይደለም፡፡*

*ብጥብጥ አልባነት የማህበረሰብ ብቻ ጉዳይ አይደለም*

*ብጥብጥ አልባነት የስልጣን ሳይንስ ነው፡፡*

*/ጂ. ራማቻንድራን/*

ለፖለቲካ ሣይንስ አካዳሚያዊ ስርአት ሲባል የማይገድል ማህበረሰብን መፍጠር ምንን ያስከትላል? እንበልና ያለመግደል እመርታን ከሚገድሉ ነገሮች ማምለጥ ባለመቻል ብንለውጠው ፖለቲካ ሣይንቲስቶች ምን አይነት ሣይንስ ለመፍጠር ይጥራሉ? ምን አይነት እሴቶች ስራችንን ይቀሰቅሳሉ ይመራሉስ? የትኛዎቹን እውነታዎች እንፈልጋለን? የትኞቹን የሚያብራሩና የሚተነብዩ ፅንሥ-ሀሳቦች እንመረምራለን? የትኞቹን የእውቀት አጠቃቀም እናሳልጣን? እራሣችንንና ሌሎችን እንዴት እናስተምራለን እናሠለጥናለንስ? ምን አይነት ተቋማት እንገነባለን? እንዲሁም እንዴት አሌሎች ጋር የግኙነት፣ የፈጠራን፣ የመካፈልን እና የማይገድሉ ማህበረሠቦችን ለማይገድል አለም ለመፍጠር እውቀትን የመጠቀም ሂደቶችን እንዴት እናያለን?

የማይገድል ማህበረሰብን መፍጠር ይቻላል ብሎ መገመት የሚያመለክተው ወደ አለመግደል ፈጠራ መጠጋትን ነው፡፡ የፖለቲካ ሣይንስን ለመተግበር ብጥብጥን (ግድያን) መቀበል ግድ ይላል፡፡ እንዲሁም ያለመግደል ሥነ-ምግባር ከእነሱ ጋር አይገጥምም የሚለውን የዌበርያዊያንን ቀኖና ጥርጣሬ ውስጥ ይጥላል፡፡ ቀድሞ የማይታሠብ የነበረውን በትንሹም ቢሆን እንደ ችግር እንዲታይ ያደርጋሰል፡፡

## የአለመግደል ፖለቲካዊ ትንታኔ ስነ አመክንዮ (logic)

የአለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ የአስተሣሠብ ለውጥ የሚያመላክተው አራት ክፍል ያለው የፖለቲካ ሣይንስ ትንታኔ ስነአመክንዮን ነው፡፡ የግድያን ምክንያቶች፣ ያለመግደልን ምክንያቶች፣ በመግደልና አለመግደል መሃል የሚደረጉ ሽግግሮችን ምክኒያቶች እንዲሁም ከመግደል ፍፁም ነፃ የሆኑ ማህበረሠቦችን መለያ ባህሪዎች ማወቅ አለብን፡፡ የሚጋጭ በሚመስል ሁኔታ ለአለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ ከተለመደው ብጥብጥን ከሚቀበሉ ስርዓቶች ይልቅ መግደልን መረዳት ይበልጥ ይጠቅመዋል፡፡ ይህም ጉልቶ የወጣው ሞትና ተከታዮቹ በሌሉበት ቦታ ላይ በአለመግደል መንገድ አስተዋፅኦ ለማድረግ ባለ ግብ (ፍላጐት) ነው፡፡ ግድያ አይቀሬ ሆኖ በግላዊ ወይንም በማህበረሰባዊ ምክንያቶች ተቀባይነት ባገኘበት ቦታ ሞትን የሚያስከትሉን ነገሮች (የራስን፣የሌሎችንና የሚመለከታቸውን) መረዳትና ማስወገድ አስቸኳይነቱ ይቀንሣል። የደህንነት ስሜት ይኖረዋል፡፡ ችግር ያለውም ቢሆን በመጨረሻው ትንታኔ "እኔ/እኛ እንገድላችኋለን" በሚል አስተሳሰብ ውስጥ ነው፡፡ ይህ አስተሣሠብ ሲቀር የግድያን ምክንያቶች መረዳትና ማስወገድ ለኑሮና ለደህንነት ፍፁም አስፈላጊ ነው፡፡

የምክኒያታዊነት ፅንሠ-ሀሣብ ለአለመግደል ትንታኔ ምሰሶው ነው፡፡ ግድያ በሚፈፀምበት ጊዜ (ከግድያ ወንጀል እስከ ዘር ማጥፋት እንዲሁም በአውቶሚክ ቦንብ የሚደረግ ማጥፋት) የመንስኤና ክትለቱን ሂደት ምንም የተወሣሠበና የተሣሠረ ቢሆንም ልንረዳው ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ግድያ ምክኒያታዊ ማብራሪያ ያስፈልገዋል፡፡ ማን ማንን እንደሚገል፣ እንዴት፣ የት፣ መቼ፣ ለምንና (ምንን በመከተል)፣ ይዘታዊ ሁኔታዎች፣ ግላዊና ህብረተሠባዊ ትርጉሞች እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማወቅ አለብን፡፡ የየጉዳዩን

የመግደል ምክኒያታዊ ተደጋጋሚነት (ቅጥ) ማግኘት ጥልቅ ለሆነና ገንዘብ ለማያስወጣ ማብራሪያ ይረዳል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ ያለመግደልን ምክኒያቶች መረዳት አለብን፡፡ የሰው ልጆች የማይገድሉት ለምንድን ነው? ያለመግደል ሃሳብ በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ የተነሳው ለምንድን ነው? የሠው ልጆች ላለመግደል መርሆዎች ለምን ቁርጠኝነት አሳዩ? በታሪክ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች መሳለቅን፣ መገለልን፣ መሰደድን፣ ማጣትን፣ መታሰርን፣ መሠቃየትን፣ መቆራረጥን እና የሞት አደጋን እስከ መገደል፣ መረሸን፣ እና በጅምላ መጥፋት ድረስ ቢገጥማቸውም ሞትን ከሚያመጡ ነገሮች ይልቅ የመኖርን መርህ ሙጥኝ ማለትን ለምን ይመርጣሉ? ያለመግደልን ውጤቶች ባለመግደል መንገዶች ለማምጣት ለምን ፖሊሲዎችን፣ አተገባበሮችን እንዲሁም ተቋሞችን ፈጠሩ?

አልፎ ተርፎም በግለሠብም በቡድንም ደረጃ ከመግደል ወደ አለመግደል እና ከአለመግደል ወደ መግደል የመሸጋገር ምክኒያቶች ምንድናቸው? ገዳዮች የሠውን ልጅ ህይወት ማጥፋትን ከመቀበል ወደ አለመቀበል ለምን ተሸጋገሩ? ለምን ወታደሮች የሠላም ጠባቂዎች ሆኑ፣ አብዮተኞች ሞት የሚያመጡ ነገሮችን አወገዙ እንዲሁም ነፍሰ-ገዳዮች ያለመግደል ቁርጠኝነትን ያዙ? አስተሣሠቦች፣ ግለሰቦች፣ መሪዎች፣ ድርጅቶች፣ ተቋሞች እና ፖሊሲዎች ለምን ወደ አለመግደል ተሸጋገሩ? እንዲሁም ከዚህ ቀደም ያለመግደል ቁርጠኝነት የነበራቸው ደም መፋሠስን ወደ መደገፍና መሣተፍ ለምን ተሸጋገሩ? (ለምሣሌ አንዳንድ ሀገሮች የሞት ቅጣትን ካስወገዱ በኋላ እንደገና መልሠው ማምጣታቸው፣ አንዳንድ ሠላምን የሚደግፉ አልፎ አልፎ የተወሠኑ ጦርነቶችን መደገፋቸው) ያለመግደል ማብራሪያ ሁልጊዜ የማይመለስ ቀጥተኛ እድገት ይኖራል ብሎ አይገምትም፡፡ ሁኔታውን መረዳት፣ ስፋቱን እና ወደ አለመግደል ለመሸጋገር ያለውን መዋለል ምክንያት ማወቅ ወደ አለመግደል ለሚደረግ ለውጥ መሣለጥ አስፈላጊ ነው፡፡ አትኩሮቱ ከግለሠቦች ወደ መላው ማህበረሰብ የሚሸጋገረው በመሠረታዊ ፈርጆች አማካኝነት ነው፡፡

ለአለመግደል ፖለቲካዊ ትንተና 4ኛ መስፈርት ደግሞ ከመግደል ፍፁም ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦችን ባህሪ መረዳት (ስፍር ቁጥር የሌለው ልዩነት በመሀከላቸው ይኖራል የሚል አስተሣሠብ በመያዝ)። የሠውን ልጅ የፈጠራ ችሎታ ስንመለከት የግዴታ አንድ አይነት የመሆን ነገር አለ ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ይህ 4ኛ መስፈርት እጅግ ከፍተኛ የፈጠራ ስራን ይፈልጋል፡፡ በርግጥ ሁሉም ከፍተኛ የሆነ ፈጠራን ይሻሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስት መስፈርቶች ግኝቶችን ከታሪክና ከዘመናዊ አተረጓጎም ጋር ማጣቀስን ይፈልጋሉ፡፡ 4ኛው ደግሞ ከነዚህ ስነምግባርን በተከተለ መልኩ ከተደረጉ ምርምሮች፣ ለመተግበር እመርታን ካሣዩ እና አንዳንዴ በግለሠብ፣ በማህበረሠብና በአለማቀፋዊ ህይወት ውስጥ መላምታዊ የራዕይ ሁኔታዎች የተገኙ እውቀቶችን ያሠባስባል፡፡ ይህ ለኛ ፈተና ይሆናል። ገጣሚው ዋልት ዊትማን እንዳለው “አልፎ መዝለል ቀረብ ያደርጋል” (ዊትማን 1977 [1855]:71)

እስካሁን ድረስ በመግደል እዝማሚያ ባህሪዎች የታጠረ የትኛውም ማህበረሠብ የሠው ልጅ ማድረግ የሚችለውን ያህል ያለመግደል ሙሉ ባህሪያትን ገና አላሣዩም። ነገር ግን ከአለማቀፋዊ ታሪክና ዘመናዊ ተሞክሮ እንዲሁም በመላምት የታዩ ብቃቶችን በማጣመር ለየትኛውም ማህበረሠብ የሚሆን አዲስ አይነት ያለመግደል እመርታዎች ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ከዚህም አልፎ እንዲህ በጥናት የተደገፉ እውቀቶች "ፅንሰ-ሀሳቦችን" ለመመርመር የድጋፍ እጅ መዘርጋት አለባቸው፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ከመግደል ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦችን ተወዳጅ ባህሪዎች ለይቶ በማውጣትና አሁን ላለ ነባራዊ ሁኔታ እዲተገበር ተጨባጭ ሂደቶችን በመንደፍ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ፖለቲካ ሣይንስ ለመላምታዊ የፅንሰ-ሀሣብ ምናቦች ተቀባይነት አይሠጥም። አንዳንድ ሣይንሶች ግን ይህን አይነት የፅንሰ-ሃሣቦች መዳበር ጠቃሚነት ላለው ትግበራ አስተዋፅኦ ያደርጋል ይላሉ (ለምሣሌ ሂሣብ፣ ፊዚክስ እና ኢኮኖሚክስ)፡፡ የፖለቲካ ሣይንስ አስተሣሠብ ብጥብጥም ላይ እንደተጠቀሠው ነው፡፡ ብጥብጥን የሚቀበል

ፖለቲካ ሣይንስ ያለመግደል ፈጠራን የማዋደቅ ዝንባሌ አለው፡፡ የፖለቲካ ሣይንስ እውቀት በባለሙያዎች ስልጠና ውስጥ በተለየ ሁኔታ "ዩቶፒያዊ"፣ "ተጨባጭነት የሌለው"፣ "ሊተገበር የማይችል" እንዲሁም ማለቂያ በሌለው ሞት ውስጥ ተገድቧል በመባል ይኮነናል፡፡ ያለመግደል ፈጠራ የነፃነትን ቃልኪዳን ይገባል ፡፡

ከአለመግደል ትንታኔ ዋነኛው እውቀት ሊተገበር የሚገባው አማራጮችን ለመፍጠር በአምስት ዞኖች ውስጥ በሚደረግ የለውጥ እንቅስቃሴ ነው፡፡ እነዚህ አምስት ዞኖች /Funnel of killing/ የመግደል ማንቆርቆርያ ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ፡፡

**ምስል 1. የመግደል ማንቆርቆርያ** /The funnel of killing/




የግድያ ዞን የተባለው የደም መፋሰስ ቦታ ነው፡፡ ከግድያ ወንጀል አንስቶ እስከ ጅምላ መደምሰስ። የመላመጃ ዞን ደግሞ ሠዎች መግደል የሚማሩበት ቦታ ነው - ቀጥታ በመሠልጠን ወይንም ደግሞ በተዘዋዋሪ ሞዴሎችንና የተሠሩ ማሥመሰያዎችን በመመልከት፡፡ በባህል የማነፅ ዞን ውስጥ ግድያን ልናመልጠው የማንችል እና እውነተኛ የሆነ ነገር እንደሆነ አምነን እንድንቀበል እንደረጋለን፡፡ የማነፅ ምንጮች ከምንላቸው መሀል ሀይማኖቶች፣ የፖለቲካ "እምነቶች"፣ ማሸነፍና አሠቃቂ ሁኔታዎችን ማወደስ፣ የቤተሠብ ባህሎች፣ ሕግ፣ የብዙሀን መገናኛ እና ስነ-ጥበብ ይገኙበታል፡፡ የመሠረታዊ መልሶ ግንባታ ዞን መግደልን ለመደገፍና ለመቀበል ህብረተሠባዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን፣ ተቋሞችን እና የቁሣዊ መንገዶችን ያመቻቻል፡፡ የኒውሮ ባዩኬሚካል ብቃት ዞን የሚያካትተው አካላዊ፣ ነርቮችን የሚመለከት፣ እንዲሁም የአእምሮ ስራ ሁኔታዎችንና ሂደቶች የሠውን ልጅ የማደን ወይም በህይወት ለመኖር ሲባል የመግደል እንዲሁም ላለመግደል ባህርይ ብቃት ላይ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ (ሎፔዝ ሬይስ 1998፣ ሞርተን 1999)

ያለመግደል ለውጥ ለማድረግ የሚሠራው ስራ በፊት የነበረውን የመግደል ማንቆርቆርያ ( Funnel of killing) ወደ ማይታጠፍ ያለመግደል ማራገቢያ (Fan of nonkilling ) አማራጮች በያንዳንዱ ዞን ውስጥና በዞኖቹ መካከል አላማ ባለው ጥረቶች ይታያል (ምስል 2)፡፡ እንዲህ ያሉ ለውጦች በግድያ ዞን ውስጥ ከመንፈሣዊና የማይገድሉ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ጣልቃ ገብነት ጀምሮ እስከ አለመግደልን መላመድና በባህል መታነፅ እንዲሁም የህብረተሠብና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚገድሉ ነገሮችን እንዳያመርቱ ለለውጥም እንዳያስፈልጋቸው እና በህክምና፣ በፋርማሲ ጥናት፣ በአካላዊ እና ራስን በሚቀይር ጥልቅ ሀሣብና ባዮ ፊድባክ ጣልቃ ገብነት አማካኝነት ለመግደል ካለ አዝማሚያ ውስጥ ነፃ ያወጣል፡፡

## ምስል 2. የማይታጠፍ ያለመግደል ማራገቢያ አማራጮች

/Unfolding fan of nonkilling alternatives/




## ያለመግደል እርምጃ መርሆዎች

ባለመግደል ፖቲካ ሣይንስ ትንታኔ ስነ-አመክንዮ ያለመግደል አማራጮችን ግድያ ላይ የሚስማሙ ዞኖችን ከመፍጠር ጋር በተገናኘ መልኩ የሚጠበቀውን እውቀት ለማግኘት ከሞሞከርም በተጨማሪ ያለመግደል አስተሣሠብ ለውጥ ለማድረግ መርሆዎችን የግለሠብንና የህብረተሠብ ውሣኔን ከቀን በቀን ህይወት እስከ አለም አቀፍ ፖለቲካ ድረስ እንዲያግዝ ማስተካከል፡፡ ይህም ሊጐለብት የሚችለው ተግባራዊ ተሞክሮንና ምርምራዊ ሙከራዎችን በማጣመር ሙከራዊ የሆነ ማረጋገጥን በመጠቀም ነው፡፡ በኮምፒውተር የሚታገዝና "እውነት በሚመስል" ጦርነትና ውጊያን የማስመሰያ መሣሪያዎች በመጠቀም ሠዎች በቴክኖሎጂው መጥቀው ሄደዋል፡፡

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ተግባሮች ውስጥ ጐልተው የወጡና ሊታዩ የሚገባቸው ያለመግደል መርሆች እንደሚከተለው ናቸው፡፡ (ጋዲያዊና ኪንግያን ንቅናቄዎች ውስጥ እንደነበረው)

- ሕይወትን ከሚያከብር አረቦን ጥንካሬን መውሠድ - ኃይማኖታዊም ሆነ ሠብአዊ። የራስንም የሌሎችንም ሕይወት ማክበር።
- የሁሉንም ደህንነት መፈለግ። መግደል ይከፋፍላል፣ አለመግደል አንድ ያደርጋል።
- በግጭት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እርቅን እንጂ ማዋረድን፣ ዘርፋን ወይም ማጥፋትን አለመምረጥ።
- በእጦት ላይ ያሉትን ስቃይ ለመቅረፍ የሚደረግ ገንቢ ስራ ላይ መሣተፍ።
- ፈጠራን መጠቀም። አሁን ያለንበትን የቴክኖሎጂያዊና መሠረታዊ ብጥብጥ ደረጃ ላይ ለመድረስ ታላቅ ፈጠራ ተጠቅመናል፡፡ ወደ አለመግደል ለመሸጋገር ደግሞ ከዚያ የበለጠ ፈጠራ ያስፈልጋል፡፡
- ለመለወጥ የሙከራ መንገድን መከተል፡፡ ያለመግደልን የተጠጉ ማህበረሠቦችን በማየት ከስኬታቸውና ከገጠማቸው ችግሮች ለመማር መሞከር።
- የግለሠባዊና ሠፊ የማህበረሠብ እርምጃዎችን ማክበር፤ ከሞራላዊ ምሣሌ ተፅእኖ እስከ የህዝብ በጅምላ ያለመግደል ስልጣን ድረስ።
- ገንቢ በሆነ መልኩ መጐበዝ። ለብጥብጥ የሚደረግን ድጋፍ በመተው ያለመግደል አማራጮችን ለማጠናከር መደገፍ፡፡

❖ ምድራችን ላይ በዝግታ መራመድ፣ በተፈጥሮ ላይና ለግድያ አስተዋፅኦ በሚያደርጉ ሠዎች ላይ የምናደርገውን ጫና መቀነስ፡፡

እያንዳንዱ ያለመግደልን በማግኘትና በመተግበር ሂደቶች ላይ የሚሣተፍ ሠው አለማቀፋዊ ለሆነ ያለመግደል ህይወት መረጋገጥ እና ጠንካራ የሆኑ መርሆዎችንና ችሎታዎችን ወደፊት ለማስኬድ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በዘመናዊ ፖለቲካ ሣይንስ አተረጓጐም የማይገድል ማህበረሠብ ሊተገበር እንደሚችል ማወቅ ለስርአቱ ጥያቄዎችን ያስነሣል፡፡ ባጠቃላይ የብጥብጥን አይቀሬነት እና እውነተኛነት ወደ መቀበል በማዘንበል እኛ የፖለቲካ ሣይንቲስቶች እንደሌላው የማህበረሠብ አባል ራሣችንን ወደሚከተሉት አመለካከቶች አዘንብለን እናገኛዋለን። *ግድያን ደጋፊ፦ ግድያ ለራስም ሆነ ለስልጣኔ በአዎንታዊ መልኩ ጠቃሚ እንደሆነ ያምናሉ፤ የመግደል ዝንባሌ ያላቸው ፦* ጠቀሜታ የሚያገኙበት ከሆነ ለመግደል ይነሣሣሉ ወይም ግድያን ይደግፋሉ፤ *ግድያን በሁለቱም መልኩ የሚቀበሉ፦* መግደልንም አለመግደልንም በእኩል ሁኔታ ይቀበላሉ ወይ ይቃወማሉ፤ *መግደልን የሚሸሹ፦* ላለመግደል የተዘጋጁና የሚደግፉ ነገር ግን ካስፈለገ ለመግደል ዝግጁ የሆኑ፤ *የማይገድሉ፦* ላለመግደል ቁርጠኛ የሆኑ እንዲሁም ሞትን የሚያመጡ ሁኔታዎችን ለመቀየር የሚጥሩ። በአጠቃላይ ስናየው የመጀመሪያዎቹ አራት አዝማሚያዎች ግድያን የሚቀበሉ ፖለቲካንና ፖለቲካ ሣይንስን ባህሪያት ይመስላሉ ማለት ይቻላል፡፡ የመጨረሻው አስተሣሠብ ደግሞ ጥሪ የሚያደርገው ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ እንዲፈጠር ነው፡፡ የርሱም ስራ በሣይንስና በማህበረሠብ ላይ ወደ አለመግደል ለሚደረግ ሽግግር አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

የዘመናዊ ፖለቲካ ሣይንስ አመለካከት በአብዛኛው በግልፅም ሆነ በድብቅ አስተሣሠብ "ብጥብጥን የሚቀበሉ" ነው ብሎ ሲፈረጅ ሁሉም ፖለቲካ ሣይንቲስቶች ተማሪዎቻቸውን በክፍል ውስጥ ጦር አዛዥ የበታቾቹን "ግደል! ግደል! ግደል!" እንደሚላቸው ያደርጋሉ ማለት አይደለም፡፡ እንዲሁም ብጥብጥ መሸሽ ላይ ፖለቲካ ሣይንቲስቶች ያደርጉትን አስተዋፅኦም ወደጐን ለመተው ሣይሆን ይህን ለማድረግ ያደረጉት ጥቂት የእርስበርስ እና አለማቀፍ ጦርነቶችን በዲሞክራሲያዊ ተቋማት (ለምሣሌ የፖርቲ ውድድር ምርጫዎች፣ ህግ አውጪዎችና ህግጋት) መተካትን ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ያለውን የሙያውን ብጥብጥ ተቀባይነት አመለካከትና ያለመግደል አማራጮች ቃል የሚገቡት የስነምግባራዊ-ብጥናት የተደገፈ እንዲሁም በጥናት የተደገፈ-ስነምግባርን ለማጐልበት ነው፡፡ የሚያመላክተውም ያለመግደልን ከነፃነት ጥያቄዎች፣ እኩልነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ጋር በተለምዶ-በጥናት የተደገፈ እና በጥናት የተደገፈ-ተለምዶ አማካኝነት የስርአቱን ዋና ሀሣብ አንድ ላይ ማስቀመጥን ነው፡፡

## ያለመግደል የሣይንሣዊ አብዮት

የማይገድሉ ማህበረሠቦችን የማፍራትን አስፈላጊነት ማወቅ የሚያመላክተው ፖለቲካ ሣይንስ ውስጥ ያለመግደል ሣይንሣዊ አብዮትን ነው፡፡ ሰባት ተያያዥነት ያላቸው ንዑስ-አብዮቶች አስፈላጊ ናቸው፡- *የተለምዶ አብዮት፦* ግድያን ከመቀበል ወደ አለመቀበል፣ *ተጨባጭ አብዮት፦* ማህበረሰብን ወደ አለመግደል ለማሸጋገር የሚያመቻቹ ሁኔታዎችን ለይቶ ማወቅ፣ *ፅንሰ-ሀሣባዊ አብዮት፦* ያለመግደል ለውጥን ምክኒያቶችና ሂደቶች ለመረዳት፣ *ትምህርታዊና የስልጠና አብዮት፦* ለአለመግደል ለውጥ እውቀትና ችሎታን ለመስጠት፣ *የሚተገበር አብዮት፦* ያለመግደልን እውቀት መተግበር፣ *ተቋማዊ አብዮት፦* ድርጅቶች ያለመግደል ለውጥን እንዲያሣልጡ መለወጥና መመስረት፤ *ስልታዊ አብዮት፦* ለአለመግደል ለውጥ ስራዎች የሚጠቅሙ እርምጃዎችን፣ ትንታኔዎችንና የመጠየቂያ ስልቶችን መፍጠርና መቀበል፡፡

*የተለምዶ አብዮት*

*የተባለው የልምድ (የተለምዶ) ሽግግር ከመግደል አስተሣሠብ ወደ አለመግደል አስተሣሠብ ነው፡፡ ይህ ሊከሠትበት የሚችለው አንዱ መንገድ ተጠራቅሞ በመጣና እሴት በሚጨምር ሂደት ስነምግባራዊና በጥናት የተደገፉ ግኝቶችን አጣቅሶ በማየት ነው፡፡ ስነምግባራዊ የሆነው አካሄድ መግደል በስነምግባርም አስፈላጊ ነው ከሚለው ወደ መግደል አስፈላጊነቱ ያጠያይቃል ከዚያም ያለመግደል በመላምት ሊመረመር ይችላል ወደሚል ከዚያም ያለመግደል በተለምዶ እንዲሆን ቁርጠኝነት ይሻል ወደሚል ነው። ትይዩ የሆነና በጥናት የተደገፈው አካሄድ ደግሞ፡- የማይገድሉ ማህበረሰቦች ሊኖሩ አይችሉም ከሚለው የማይገድሉ ማህበረሰቦች ይኖራሉ ማለት አስቸጋሪ ነው ወደሚለው ከዚያም የማይገድሉ ማህበረሰቦችን ባህሪ በአካልና በመላምት መመርመር ወደሚለው በመጨረሻም የማይገድሉ ማህበረሰቦችን በማይገድል አለም ውስጥ ለመፍጠርና ለማቆየት የሚያስፈልገውን እውቀት ለማግኘት ሣይንሳዊ ቁርጠኝነት መውሠድ ነው፡፡*

*እንዲህ ባሉ በተሳሰሩ የስነምግባራዊ ፈተና እና በጥናት የተደገፉ ምላሽ (በጥናት የተደገፉ ፈተናዎችና ስነምግባራዊ ምላሽ) ሂደቶች በዌበር የተቀመጠው በአለመግደል መርሆዎችና በሚገድል ፖለቲካ መሀል ያሉ የማይገፉ እንቅፋቶች ሊታለፉ ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ለህይወት ያለን አክብሮት ሣይቀር "ለመረጃና ማረጋገጫ ደንቦች ያለንን ቁርጠኝነት ሣንለውጥ" የሚለው ላይ (አልመንድ* 1996፡89) *እንደተራ ስነምግባራዊ መሰረት ዘመናዊ ፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ላይ ልንጨምር እንችላለን፡፡*

**ምስል 3.የተለምዶ-በጥናት የተደገፈ ያለመግደል አስተሣሠብ ለውጥ ሂደት**

| ***የተለምዶ ሽግግር*** | ***የመገናኘት ሂደት*** | ***በጥናት የተደገፈ ሽግግር*** |
|---|---|---|
| *መግደል አስፈላጊ ነው* | | *አለመግደል የማይቻል ነው* |
| *መግደል ያጠያይቃል* | | *አለመግደል ይቻላል ማለት አስቸጋሪ ነው* |
| *መግደል ተቀባይነት የለውም* | | *አለመግደል ሊመረመር ይችላል* |
| *አለመግደል አስፈላጊ ነው* | | *አለመግደል ይቻላል* |

*ተጨባጭ አብዮት*

*እውነታው ያለመግደል ሽግግር የሚያመላክተው ለሠው ልጅ ያለመግደል ብቃት አላማ ያለው የማስረጃ ትውስታና ግኝት እንደሚያስፈልግ ነው ነገር ግን ብዙ ጊዜ የመረሳትና አትኩሮት ያለማግኘት አዝማሚያ ብጥብጥን በሚቀበሉ አስተሣሠቦች ይደርስበታል፡፡ እንዲህ ያሉ እውነታዎች ከኒውሮ ሣይንስ እስከ የማይገድሉ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎች ድረስ ያለውን ያካትታል፡፡ በተለየ ሁኔታ የሚስበው ደግሞ ብጥብጥ የሚበዛባቸው ታሪካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ ያለመግደል ባህሪዎች ጐልተው ሲወጡ ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል በግሪክ በ*399 *አመተ አለም ከ*500 *የአቴንስ ሴናተሮች ወደ* 140 *የሚጠጉት ሶቅራጥስ በሞት እንዳይቀጣ ድምፃቸውን ሠጥተዋል (ስቶን* 1989፡187)። *ጃፖን ውስጥ በቡዲስቱ ሄያን ዘመን* (794-1192) *"የሞት ፍርድ ለሦስት መቶ ሃምሣ አመታት ገደማ አልተተገበረም ነበር" (ናካሙራ* 1967፡145)። *በአሜሪካ በአፕሪል* 4 *እና* 6, 1917 *ስድስት ሴናተሮችና*[8]

ህምሣ ተወካዮች[9] ጀርመን ላይ ጦርነት መክፈትን በመቃወም ድምፅ ሠጥተዋል፡፡ ራሺያ ውስጥ በአክቶበር 23, 1917 በትንሹ ሁለት ምናልባትም አምስት ወይም ስድስት የሚደርሱ የቦልሼቪኮች ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሌኒንን የታጣቂ አብዮት ፖሊሲ ተቃውመው ነበር (ሽብ 1976፡271)፡፡ በአሜሪካ በ1945 ጁላይ ወር መጨረሻ በሂሮሺማና ናጋሳኪ ላይ አውቶሚክ ቦንብ ጥቃት ከመደረጉ ዋዜማ ከ150 የማንሃተን ፕሮጀክት ሣይንቲስቶች መሀል አስራዘጠኙ የሠራነው መሣሪያ ምንም አይነት ጦርነት ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውል በማለት ድምፅ ሠጥተዋል (ጂዮቫኒቲና ፍሬድ 1965፡168 አልፔሮቪትዝ 1995)፡፡ በ1996 የአሜሪካ ማሪን ኮር የአጠቃላይ የመከላከያና የሌሎች የመንግስት  የምርምርና ስርፀት እንዲሁም የማይገድሉ መሳርያዎችን የመግዛት ስራዎችን የማቀናበር ሃላፊነት ተሠጥቶት ነበር (ሊወር እና ሾፊልድ 1997፡45)፡፡ የኋለኛው ወደ አለመግደል ደህንነት አስተሣሠብ መሸጋገርን ያካትታል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያሉ መሣሪያዎች በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት የሚገድሉ መሣሪያዎች ላይ በመደረብ ሲሆን ከባድ ጉዳት ማድረስም ሆነ መግደል ይችላሉ፡፡

ወደ አለመግደል የሚደረግ ተጨባጭ ሽግግር ባለፉና በአሁን ጊዜ ያሉ በእለት ከእለት ማህበረሰብ ውስጥ የሚታዩ ያለመግደል አዝማሚያ ጠቋሚዎችን ለማግኘት ይጥራል፡፡

*ፅንሠ-ሀሣባዊ አብዮት*

ፅንሠ-ሀሣባዊ አብዮት የሚያመላክተው የተለመዱ፣ በጥናት የተደገፉና በአለመግደል ትንታኔ ስነአመክንዮ አስፈላጊ ነው የሚባልን እውቀት ለማጐልበት እንዲሁም ለግላዊ ውሣኔ ለሲቪል ማህበረሠብ እርምጃዎች እና ለህዝብ ፖሊሚዎች አስተዋፅኦ ለማድረግ ፅንሰ-ሀሣቦችን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ለምሣሌ ሶስት ፈር ቀዳጅ የሆኑ የፅንሠ-ሀሣብ አከመለካከቶች ምንጭ (ወግ አጥባቂ፣ በተግባር የሚመራና በሂደት የሚመራ) ስለ አለመግደል ፖለቲካዊ ስልጣን የመለወጥ እመርታ ጥልቅ የሆነ እውቀት ለማስጨበጥ ቃል ይገባል፡፡ የመጀመሪያው በተለምዶ የሚረሣውና የጋንዲ ደጋፊዎች አበክረው የሚናገሩት ህይወትን የሚያከብር መንፈሣዊ ሀይል እውነትን የመፈለግ (ፍትህን የመፈለግ) አስፈላጊነት፣ ግላዊና የጋራ እርምጃዎች  እንደተቀመጡ ለምሣሌ ጋንዲ በ "The science of Satyagraha" (1970) ላይ እንዳስቀመጠው ለጋንዲ በእግዚአብሔር ያለ ዘላለማዊ እምነት በእውነት፣ በፍቅርና ብጥብጥ ባለመኖር ይገለፃል፡፡ ሁሉንም ሀይማኖቶች በማቀፍ የማይበገር ያለመግደል የኃይል ምንጭ ይገኛል፡፡ ያለመግደል መንፈስና እውነታ የሠው ልጅ ህይወት መሠረታዊ ህግ ነው መግደል ደግሞ ይህን ይጥሣል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የብጥብጥ አልባነት ኃይል ፅንሠ-ሀሣብ ነው። ይህም በጂን ሻርፕ “The politics of Nonviolent action” (1973) ላይ ቀርቧል፡፡ የፖለቲካዊ ስልጣንን ተፈጥሮ በመታዘዝ ላይ ጥገኛ ስለመሆኑ በተደረገ ጥልቅ ትንታኔ ብዙ ስራዎችን ሠብስቦ አቅርቧል፡፡ በታሪክ ሲሠሩ የታዩ የብጥብጥ አልባ ትግሎችን መንገድ በማየት ስለብጥብጥ አልባ ፖለቲካዊ ለውጥ ስልታዊ የሆነ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ የሻርፕ ፅሁፍ የሚለው ብጥብጥ አልባ ፖለቲካዊ እርምጃ በቀላሉ በተግባር በሚመራ መልኩ ጠንካራ ነው፡- ለመንፈሣዊ፣ ኃይማኖታዊና ሠላማዊ መርሆች መሳምታዊ እምነት አያስፈልግም፡፡

ለአለመግደል ፅንሠ-ሀሣባዊ አስተሳሰብ ፈተና የሚሆነው ሶስተኛ የእውቀት ምንጭ የጆን በርተን ፍላጐትን መንፈግ ትንታኔ ነው፡፡ የሚያብራራውም ያለመግደል ለውጥ ላይ ለመሣተፍ የብጥብጥን መነሾ ለፍላጎት ማሟላት ሂደት ስለማወቅ ነው። የበርተን ጽንሰ ሃሳብ የቀረበው  “ Deviance Terrorism & War: The Process of Solving Unsolved Social and Political Problems (1979)” እና ሌሎችም ስራዎቹ ላይ ነበር (1984፣ 1996፣ 1997)። የበርተን ሃሳብ የትኛውም ሞት የሚያስከትል ነገር ከግድያ ወንጀል አንስቶ እስከ ጦርነት የሚነሱት የሰውን ልጅ ፍላጎት በመጣስ ነው፡፡ ከነዚህም ግንባር ቀደሙ ማንነትንና ክብርን መቀበል ነው፡፡ ጣሺውም የተጣሰበትም ተመሣሳይ ፍላጎት አላቸው፡፡ መጣስ

በተከሰተበት ሁኔታ በእሴቶች መማፀንም ሆነ በማስፈራራት መቆጣጠር ግድያን ሊያፍን አይችልም። ችግርን የመፍታት ሂደቶች ሲፈጠሩ ግን ፍላጎታቸው የተጣሱትን በሚያካትትና በሚያረካ መልኩ ሲሆን የማይገድሉ ማህበረሰቦችን ከመግደል ነፃ በሆነ አለም ውስጥ ለመፍጠር ተስፋ ይሰጣል፡፡

እነኚህ የመንፈሳዊ ሀይል፣ በተግባር የሚመራ ስሉጥነት እና ተሳትፎአዊ ችግር መፍታት አመለካከቶች የሚያሳዩት ያለመግደል ፅንሠ-ሃሣብን መሰረቶች ነው፡፡ እነዚህም በታሪክ ፣ በመደብ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በተቋማት ፣ በፆታ ፣ በዘር፣ በጎሣ ፣ በኃይማኖት፣ በባህል ፣ በአካባቢ፣ በወደፊት ትልም ፣ እንዲሁም በሌሎች በሀገር ውሰጥና በአለም አቀፍ ሁኔታዎችን ምክንያት ባደረገ አከፋፋል ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ያለመግደል ፅንሠ-ሀሣብን መመደብና ፈጠራን ማጎልበት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካደረጉ መሀል ሮበርት ጄ ቡሮውስ (1996)፣ በርኒስ ኤ ካሮል (1998)፣ ጆሀን ጋልቱንግ (1996)፣ ብራየን ማርቲን (1989) እና ኬት ማክጊነስ (1993) ይገኙበታል፡፡

*የሚተገበር አብዮት*

የተለምዶ፣ ተጨባጭ እና ፅን-ሀሣባዊ ሽግግሮች ሲጣመሩ የሚያመላክቱት ለአለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ አዲስ የሚተገበር ቁርጠኝነትን ነው፡፡ የተለምዶው ሽግግር ለአለመግደል ሃሳብ ፣ ግለሰቦች ፣ ድርጅቶች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ፖሊሲዎች እና ተቋሞች የሚያመለክተው አዲስ ተመስጦ እና ገንቢ (ነገር ግን ሂስ የሌለው የማይባል) ድጋፍ ነው፡፡ የሻርፕ ፅንሠ-ሀሣብ የሚጠቁመው በኃይለኛ ሁኔታ ጨቋኝ የሆኑ መንግስታትን ለአለመግደል ለውጥ ለማገዝ ግልፅ የሆነ አቋም መያዝ እንዱሁም ምላሽ የማይሰጡ ዲሞክራሲያዊ ስርአቶችን ለመለወጥ እጅን ሊዘረጋ ይችላል፡፡ የበርተን ፅንስ ሃሳብ የሚለው ደግሞ የፖለቲካ ሳይንስ መዐከላዊና የሚተገበር ሚና ለሰው ልጅ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጡ ብጥብጥ አልባ ህብረተሰባዊና ፖለቲካዊ ችግር የመፍታት ሂደቶችን በሚያሳትፍ መልኩ እንዲሆን መርዳት ላይ ነው፡፡ የጋንዲ ደጋፊዎች ፅንሠ-ሀሣብ፣ ስነምግባሮችን ማዋሀድ፣ ስልቶች እንዲሁም ለፍላጎቶች መነፈግ በቀላሉ መሰማት በግልፅ የሚያመላክተው የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ህብረተሰባዊ እና የግድያና ለመግደል የማስፋራራት ውጤት የሆነ መሰረታዊ የባህል ብጥብጥ ሁኔታዎችን ለመለወጥ መታገዝ እንዳለበት ነው፡፡ ሊታወስ የሚገባው ደግሞ ባለመግደል መንፈሳዊ መርሆዎች የተነሣሱ እንደ ጋንዲና ኪንግ ያሉ መሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ላለመግደል መሰረታዊ ለውጥ ቁርጠኝነት ያሳዩ እንደነበር ነው፡፡

ያለመግደል ትንታኔ ስነ-አመክንዮ ከሚሻው እውቀት በመነሳት እና የመግደል ማንቆርቆርያን ሰፋ ወዳለው ያለመግደል ማራገቢያ አማራጮች ለመቀየር በሚሰራው ስራ መረጃን በማግኘት ሊተገበር የሚችል ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የሚገጥመው ፈተና የአካባቢና የአለምአቀፍ ለውጥን ማገዝ ነው። በዘመናዊ “ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ” እና “ነፃ ገበያ” ሁኔታ ውስጥ ግላዊና የህብረት ግድያ አልጠፋ ማለት የሚያሳስበው እነዚህ ሁኔታዎች አሁን በሚተገበሩበት መልኩ ለሰው ልጅ ደህንነት መረጋገጥ ይረዳሉ ለማለት ያስቸግራል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከ “ኢ-ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ” እና “ነፃ ያልሆነ ገበያ” ጋር ሲጣመሩ ለሚተገብር ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ፈጠራ ፈተናን ይፈጥራሉ፡፡

*ትምህርታዊ አብዮት*

ወደ ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ለመምጣት በፖለቲካ ሳይንቲስቶች ሙያዊ ስልጠና እና ለሌላ የህብረተሰቡ አባላት የሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ያመላክታል፡፡ የመግደል ባህልንና ሁኔታን በግልፅም ሆነ በውስጠ ታዋቂነት ከማንፀባረቅና ከማበረታታት ይልቅ የፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ለአለምአቀፋዊ ያለመግደል ለውጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡ ግልጽ የሆነው ግብም ለማይገድሉ ማህበረሰቦች አመራርና ዜግነት ለማነፅ የሚረዳ ይሆናል፡፡ ፈታኝ ስራ የሚሆነው ለምርምር፣ ለማስተማር፣ ለማማከር ፣ ለአመራር፣ ለሲቪክ እርምጃ እና ለጥልቅ አስተሳሰብ በቂ

ሁኔታዎችን ለማጎልበት ግኝቶችን እንዲሁም ያለመግደል እውቀት በመጋራት መጠቀም ነው፡፡

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ስልጠና በተሳታፊዎች ከስነ-አእምሮ ባለሙያዎችና ከመንፈሳዊ አማካሪዎች የሚጠበቀውን ያህል ከፍተኛ የግል እውቀትን ይጠይቃል፡፡ የራሳችንን ስለ መግደልና አለመግደል ያለንን እምነት፣ አመለካከትና ስሜት ምንጭና የሚያመላክታቸውን ነገሮች ልንረዳ ይገባል። እራስን መረዳት ለህብረተሰባዊ ያለመግደል ለውጥ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ሳይንሳዊ በሆነና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አቀራረቦችን በሚቀበል ጥልቅ ሀሳብ (ሜዲቴሽን) መሰልጠን ተገቢ ነው፡፡ የግልና የሙያዊ እድገት ተሞክሮን የመጋራት እድል ለጋራ ጥቅምና መደጋገፍ ሲባል ሊኖር ይገባል፡፡ ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንቲስቶች በሌላ ጉዳዮች ምንም ያህል የተለያየን ብንሆንም ለህይወት ያለንን ጥልቅ አክብሮት ለማሳየት እርሰ በርሱ የሚደጋገፍ ዘለቄታያለው እድገትን (በግልም ሆነ ከስራ ባልደረቦች ጋር) ለማምጣት መጣር አለብን፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ከሚሻው አይለይም፡፡

ለማማከርና ተግባራዊ ስራዎችን ለመሰራት በሚደረግ ዝግጅት ላይ ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንቲስቶች ከህክምና ተመራማሪዎች፣ ከህክምና ባለሙያዎችና ከህክምና ባለሙያ አስተማሪዎች እንዲሁም ከሌላ የሞት ሽረት ሙያዎች ያልተናነሰ ብቃት ላይ ለመድረስ ሊሹ ይገባል። ፖለቲካ ሳይንቲስቶች ለማይገድሉ ማህበረሰቦች የሚያደርጉት አስተዋፅኦ የጤና ባለሙያዎች ለግላዊና ለህዝብ ጤንነት ከሚያደርጉት አስተዋፅአ አንሶ ሊታይ አይገባም። ሁለቱም የሚጋሩትና የሚጨነቁበት የሞት የሽረት ጉዳይ አለ በተባለው አዲስ እውቀት ላይ በመመርኮዝ መመርመር፣ ማዘዝ እና ማከም ነው፡፡

ይህ በንዲህ እነዳለ ማናኛውም የማህበረሰብ አባል ላለመግደል አለማቀፋዊ ለውጥ አስተዋፅኦ ሊያደረግ ይችላል፡፡ ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ትምህርታዊ ስራ በየትኛውም ደረጃ ላለ ለያንዳንዱ ተካፋይ የስራ ባልደረባ እራሱን ለማሳደግ (ለማጎልበት ) እንዲሁም ለዘለቄታው ያለመግደል አመራርና ዜግነትን የሚያጎላ እውቀትና ችሎታን እንዲያካብት እድል መስጠት ነው፡፡ ሁሉም ያስተምራል፤ ሁሉም ይማራል፡፡

የትምህርት መርሀ ግብር ሲነደፍ ያለመግደል ትንታኔ በሚያስቀምጠው የእውቀት መስፈርት በመመራት ለመግደል ያለን አዝማሚያ ወደ አለመግደል አማራጮች ለመለወጥ ተግባራዊ ችሎታዎች ማስፈለግ እና የግለሰብና የህብረተሰብ እርምጃን ሊመራ የሚችል መርህን የመንደፍ ማስፈለግ ነው፡፡ የመክፈቻ ትምህርተ ክፍል ወይንም ሴሚናር ላይ የሰው ልጅን የመግደል ብቃት የሚያሳይ እጅግ አሰቃቂ ከሆኑት ታሪካዊ ወይም ዘመናዊ ማስረጃዎች ውስጥ ለተካፋዮች ማሳየት ይገባል፡፡ ከዚያም በአንድ ላይ ዘላቂነት ያለውን ፈተና እንጋፈጣለን፡- የሙያችን ስራ የሰውን ልጅ ግድያ መግታት ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው የትምህርታዊ ተሞክሮ ግልፅ በሆነ መልኩ የሰው ልጅን ያለመግደል እመርታ በአለም አቀፋዊ ማስረጃ ደግፎ ማሳየት። ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የግለሰቦችንና ህብረተሰቦችን ለውጥና መዋቅር ያስተዋውቃል። አራተኛው ዋና ተሞክሮ የሰው ልጅ የፖለቲካ ተቋምን ለሚያስፈልግ ማህበረሰቦች የመፍጠር ችሎታን ይለካል እንዲሁም ከግድያ ነፃ ስለሆኑ ማህበረሰቦች ባህሪ እና ፖለቲካ ሳይንስ አስተዋፅኦ ሊያደርግላቸው የሚችልበትን መንገዶች ላይ የሚደረግን ፈጠራ ይፈትናል፡፡ በያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ከሀገር ውስጥ ወደ አለም አቀፍ ያለ እውቀትና ፍላጎት እንዲሁም በአለም አቀፍ እና ሀገር ውስጥ ያሉ ግንኙነቶችን ያስተዋውቃል፡፡

እንዲህ ያሉ መሰረቶች ላይ ያለመግደል ትምህርታዊ ፈጠራዎች ሊገነቡ ይችላሉ፡፡ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል የቅድመ-ምረቃ ትምህርተ ክፍል ስለ አለመግደል ፖለቲካዊ አማራጭ ነበር። በዚህ ላይም ሁሉም ተካፋዮች በግል የሚያሳስባቸውን የብጥብጥ ሁኔታ እንዲመርጡ መጋበዛቸው ትርጉም ያለው ጥረትን እና የጋራ ፈጠራን ቀስቅሶ ነበር። እንዲሁም ስለተፈጥሮውና ስለሚከሰትበት ምክንያት ቀድሞ የተሰሩ ስራዎችን ማየት፣

እንዲህ አይነት ብጥብጦች ላይ የሚሰሩ ሰዎችን ማማከርና ስለሁኔታው፣ ስለአዝማሚያው፣ ስለመንስኤው እና አማራጮች ያላቸውን ሃሳብ መቀበል፤ ሊኖሩ ስለሚችሉ አማራጮች ፈጠራን በመጠቀም ማሰብ፤ ትንተናዎችንና ችግር መፍቻ ረቂቅ ሀሳቦችን እርስ በርስ መጋራት፤ ስለህብረተሰባዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ረቂቅ ሀሳብ ላይ መስማማት፡፡

*ስልታዊ አብዮት*

ያለመግደል ለውጥ በስልት ደረጃ የምርምር፣ የትምህርት፣ የሚተገበር ፖለቲካ እና ተቋምን የመገንባት መንገዶችን አዲስ አስተሳሰብ ይፈትናል፡፡ ፈታኝ የሚሆነው አሁን ያሉ መንገዶችን ለአለመግደል ግኝቶችና አተገባበራቸው ለመጠቀም መሞከር፣ እንደአስፈላጊነቱ አዲስ ስልቶችን መንደፍ እና እንደ ኒውሮሳይንስ ያሉ ሙያዎች የነርሱን ስልት ያለመግደል ለውጥ ችግር መፍታት ላይ እንዲያውሉት ማበረታታት፡፡ በተለይ ከባድ ፈተና ይኖረዋል የሚባለው በግድያ ዞን ውስጥ የምርምርና ጣልቃ ገብነት ስልት ማስፈለጉ እንዲሁም በሚገኙ የግድያ ዞኖች ውስጥ የሚስማማ ትንታኔ ማስፈለጉ ነው፡፡

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ እጅግ ሰፊ ከሆነው የእውቀትና የስልት ስብስብ ብዙ ሊያገኝ ይችላል፡፡ እነዚህም ስብስቦች ከሚያካትቱት ጥቂቶቹ ፍልስፍናን፣ ታሪክን፣ ተቋማዊና የህግ ትንታኔዎችን፣ ቃለመጠይቅን፣ ተካፋይን ማጤን፣ ጥናቶች፣ ውድድራዊ ትንታኔ፣ የይዞታ ትንታኔ፣ የፅሁፍ አተረጓጎም፣ የውድድር ፅንሰ ሃሳብ፣ የህዝብ ምርጫ ትንታኔ፣ በቁጥር በተመረኮዘ ምክንያት አሰጣጥ፣ የዳሰሳ ጥናት፣ የላብራቶሪና መስክ ሙከራዎች፣ የሰውና የኮምፒውተር አስመስሎ መስራት፣ እንዲሁም የነዚህ በተለያየ መንገድ አላማውን የተከተለ መጣመር ናቸው፡፡ የትምህርት ስልቶች ደግሞ ከባህላዊ ማስተማር ጀምሮ በማንበብና በመቃኘት እና በልምምድ መልኩ በመወያየትና በመመራመር እንዲሁም ኮምፒውተር በመጠቀምና ራስን በመምራት የትምህርትን አለም እስከመዳሰስ ይደርሳል፡፡ የፖለቲካዊ አፈፃፀም የሚያካትተው የህገመንግስት ቀረፃ፣ ግጭት መፍታት፣ ድርጅታዊ ማማከር፣ የምርጫ ምክር፣ የሚዲያ ሂስ ፣ የደህንነት ፖሊሲ ምክር፣ በህብረተሰብ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የመሪ-ዜጋ ቀጥተኛ ተሳትፎን ነው፡፡ ለዚህ ሰፊና የተጠናቀረ እውቀትና ችሎታ ሊቀርብ የሚገባ ስልታዊ ጥያቄ “ከሰው ልጅ ሁኔታ ላይ ግድያን ለመቅረፍ አሮጌና አዲስ ስልቶች እንዴት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ?”

*ተቋማዊ አብዮት*

ያለመግደል አስተሳሰብ ለውጥ በተቋም ላይ የሚያመላክተው የፖለቲካ ሳይንስ ሙያ እንዴት ሊዋቀር ይገባዋል፣ ንዑስ ስርአቶቹ ምን ሊሆኑ ይገባል፣ እንዲሁም ከሊሎች ሙያዎችና የማህበረሰብ ተቋሞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንዴት ሊሆን ይገባል የሚሉትን ጥያቄዎች ነው። ካለመግደል አመለካከት አሁን ባሉ የስርአቱ መሰረቶች ውስጥ ሆኖ በአለምአቀፍ፣ ሀገር አቀፍና በአካባቢ ደረጃ ጥያቄ ማንሳትን ያመላክታል፡፡ አዲስ በተከፈቱ ተቋማት ውስጥም አዲስ ያለመግደል ፖለቲካ ሰይንስ ክፍልን የመፍጠርን ሀሳብ ያመለክታል ወይም ደግሞ አዲስ የተዳቀለ ሙያን በመፍጠር ያለመግደል ህብረተሰባዊ ፍላጎቶችን እንዲያገለግል ማድረግ፡፡

አሁን አለማቀፋዊው የፖለቲካ ሳይንስ ሙያ የሚወከለው በአለም አቀፋዊ የፖለቲካ ሳይንስ ማህበር (IPSA) በሚባል በ1996 በተቋቋመ ማህበር ነው፡፡ አርባ ሁለት ብሄራዊ የፖለቲካ ሳይንስ ማህበራት በትንሹ 34,900 አባሎችን በዋና አባልነት በመያዝ በተቋም ደረጃ IPSA ዋና ኮሚቴው ውስጥ ይወከላሉ (አባሪ A)። የተለያዩ የአባላት ፍላጎት በ18 ዋና መስኮች መሰረታዊ በሆነ መልኩ ይገለፃሉ በ38 የምርምር ኮሚቴዎች እና በ12 የጥናት ቡድኖችም ጭምር (አባሪ B)። እዚህ ላይ ሊጨመሩ የሚችሉት ደግሞ በብሄራዊ ማህበሩ ያልተወከሉ ሀገራት ውስጥ ያሉ ፖለቲካ ሳይንቲስቶች እና በአለም ፖለቲካ ሳይንቲስቶች የሚማሩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተማሪዎች ናቸው፡፡

A New Handbook of Political Science (ጉዲንና ክሊንግማን 1996) ከIPSA ፕሮጀክት ውስጥ አድገው የወጡ 42 ደራሲያን የስርአቱን ነባራዊ ሁኔታ ለማየት ዳሰሳዊ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በሁለት አስርት አመታት ውስጥ በተደረጉት እድገቶች ስምንት ዋና ንዑስ-ስርአቶች ተለይተው ወጥተው ታይተዋል፡- ፖለቲካዊ ተቋማት (በምክንያት የተደገፈ ምርጫ፣ ከህግ አኳያ)፣ ፖለቲካዊ ባህሪ (ምክንያታዊ ድምፅ ሠጪዎች እና የብዙ ፓርቲዎች ስርአት ፣ ተቋማዊና ተሞክሮአዊ አቀራረብ)፣ የማወዳደር ፖለቲካ (ሰፊ ባህሪ አስተያየት፣ ዲሞክራታይዜሽን ጥናቶች) ፣ አለምአቀፋዊ ግንኙነት (ኒዮ-ሪሊዝም እና ኒዮ-ሊበራሊዝም፣ ድህረ-አዎንታዊ እና የሴቶችን እኩልነት የሚደግፍ አስተያየት)፣ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ (የሶሊዮሎጂና ዳውንሲያን አመለካከት) እና ፖለቲካዊ ስልት (qualitative methods፣ የምርምር እቅድ እና ሙከራዊ እቅድ)። የIPSA ፕሬዝዳንት እንደተናገረው "ፖለቲካ ሳይንስን ወደ አዲሱ ክፍለ ዘመን ሊወስድ የሚችል የተሻለ ነገር የለም" (12)

ሆነም ቀረ የተሠሩ ነገሮች ቢኖሩም A New Handbook ወደ አለመግደል ስርአታዊ ለውጥ የመምጣትን አስፈላጊነት ያሳያል። ለምሳሌ የቃላት ማውጫው ውስጥ ስለ "ብጥብጥ" ወይም "ብጥብጥ አልባ" እንዲሁም "የግድያ ወንጀል"፣ "ዘር ማጥፋት"፣ "የሞት ቅጣት"፣ "ጦር ሀይል"፣ "ሽብር" ወይንም "ፖሊስ" አይጠቅስም። "ጦርነት" ስልሳ ጊዜ ተጠቅሷል ስለ "ሰላም" ስምንት ጊዜ። የስም ማውጫው ላይ ደግሞ "ሂትለር" እና "ሌኒን" ሲጠቀሱ "ጋንዲ" እና "ኪንግ" ግን አልተነሱም። በአለም አለ የተባለው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ጂን ሻርፕ ስምም ሆነ እንደ "The Politics of Nonviolent action" (1973) ያሉ ስራዎቹ እንዲሁም ስለ ብጥብጥ አልባ ፖለቲካዊ ትግል ለዲሞክራሲ ብሄራዊ መከላከያ እና የወታደራዊ መፈንቅለ መንግስትን ማስወገድ ላይ ያሉ ፅንሠ-ሀሳቦች አልተነሱም። እንዲሁም ስለብጥብጥ አልባ ግጭት መፍታት ፅንሠ-ሀሳብ ያቀረበው እና አስተዋፅኦ ያደረገው የጆን በርተን (1979፣ 1984) ስምም አልተጠራም፡፡ ስለ ጆሀን ጋልተንግ (1996) የአለማቀፍ ሠላም ጥናት ላይ ታላቅ ድርሻ የነበረው ሰው በጥቂቱ ስሙ ተነስቶ ነበር፡፡

IPSA ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየና አንጋፋ የሆነው ክፍል የአሜሪካ ፖለቲካ ሳይንስ ማህበር ሲሆን ወደ 13,300 የሚጠጋ አባላት አሉት፡፡ የተመሰተረውም በ1903 ዓ.ም. ነበር፡፡ አባላቱ የሚፈልጓቸው ዋና ጥናቶች በስምንት ይከፈላሉ፣ እነኚህም በዘጠና ስድስት ንዑስ ጥናቶች እና ሰላሳ አንድ ልዩ ጥናቶች ይከፈላሉ፡፡ የ APSA እና IPSA የፍላጐት መሠረት በአጠቃላይ ይመሳሰላል፡፡ የአሜሪካ ፖለቲካ ሳይንስ ዋና መስኮች፡- የአሜሪካ መንግሥትና ፖለቲካ፣ ውድድራዊ ፖለቲካ፣ አለም አቀፍ ፖለቲካ፣ ስልት፣ የፖለቲካ ፍልስፍና እና ፅንሠ- ሃሣብ፣ የህዝብ ሕግና ፍርድቤቶች፣ የሕዝብ ፖሊሲ እና የህዝብ አስተዳደር ናቸው፡፡ በ "ግጭት ሂደቶች" እና "አለማቀፍ ደህንነት እና መሣሪያ ቁጥጥር" ላይ ልዩ ንዑሶች ቢኖሩም የትኛውም የተቋም መሠረት ግልፅ በሆነ ሁኔታ ያለመግደል ፖለቲካዊ ትንታኔና እርምጃ ስነአመክንዩ እውቀትና ችግር የመፍታት መስፈርት ላይ ትኩረት አያደርግም፡፡ ለምሳሌ ያህል ስለ "ብጥብጥ"፣ "ብጥብጥ-አልባ" ወይም "ሠላም" ልዩ ክፍል የለውም (ከአለምአቀፍ የሠላም ምርምር ማህበር ጋር ይነፃፀር) በአስጊ ሁኔታ ስር የሰደደና ጥበቃ የሚደረግለት ዲሞክራሲ ለስልጣኔ እድገት ያለው ዋነኛ ተስፋ ነው የሚል ባህላዊ አስተሳሰብ አለ፡፡ ይህም አስተሣሠብ ያለመግደል ሥልጣኔ አማራጮች ላይ ዳሰሳ እንዳይደረግ የተቋሞችን ትኩረት ወደኋላ አድርጓል፡፡

ያለመግደል ሽግግር የሚያመላክተው አሁን ባሉ መስኮችና ንዑስ መስኮች መሀል ጥያቄዎችን ማንሳት በስርአቱ ውስጥ አሜሪካንና አለማቀፍ የፖለቲካ ሳይንስ ማህበር ውስጥ በርእሱ ቅርፅ ውስጥ እንደታየው ማለት ነው፡፡ "ስለማይገደሉ ማህበረሰቦች እና ያለመግደል መንገዶች እንዲሁም እንዴት መተግበር እንደምንችል ምን ልትነግሩን ትችላላችሁ?" ይህ ማለት አሁን ከተተገበሩ ሥራዎች መውሰድና አዲስ ነገሮችንም ማስተዋወቅ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ይህ ሊታይ የሚችለው በአራቱ "ባህላዊ" የአሜሪካ ፖለቲካ ሳይንስ መስኮች - በፍጥነት እያደገ ከመጣው ዘመናዊ ልዩነት ውስጥ ጥያቄዎችን በማንሳት ነው፣ ፖለቲካዊ

ፍልስፍና እና ፅነሠ-ሀሳብ የአሜሪካ መንግሥትና ፖለቲካ፣ ውድድራዊ ፖለቲካ እና አለማቀፋዊ ግንኙነት፡፡

## የፖለቲካ ፍልስፍናና ፅንሠ-ሃሳብ

በፖለቲካዊ ፍልስፍናና ፅንሠ-ሀሳብ ያለመግደል ሽግግር ማለት በሁሉም ባህል ያለውን የፖለቲካ አስተሳሰብ ቅርስ በማየት ያለመግደል አስተሳሰብን ማግኘት እንዲሁም አዲስ ያለመግደል ፈጠራን ማስተዋወቅ ነው። ለምሳሌ፡- የኘሌቶ "ዘሪፑብሊክ" የተሰኘው መፅሀፍ ውስጥ ዴኒስ ዳልተን የ "ጉዳት-አልባ"ን አይነተኛ ስነምግባር ተፈላጊፊዎችንና የፖለቲካ አመራሮች ሊተገብሩ መፈለግ ያለባቸውን ሁኔታ አግኝቷል ምንም እንኳን ኘሌቶ ጦርነትን፣ የሞት ቅጣትንና የጦር ባህልን የሚቀበል ቢሆንም ይህ ዓይነት አመለካከት በኘሉታርክ ተንፀባርቋል፡- "ወደ ቢላው መሄድ የጥሩ ጤና ባለሙያም ሆነ የመሪ መለያ አይደለም፣ ነገር ግን በሁለቱም ሁኔታ የችሎታ ማነስን ያሳያል፡፡ በመሪው ደረጃ ግን ኢ-ፍትሐዊነትና ጭካኔ ይጨመርበታል፡፡” (ኘሉታርክ 10፡249) በቻይናዎቹ ባህል የሜንሲየስን (C.371 - C.289 አ.አ.) አመለካከትን አነፃፉ፡- "ሀይልን በመጠቀም ምግባረ-ሠናይነትን ለማስመሰል የሚሞክር አምባገነን ነው... ምግባረ-ሠናይነትን ተጠቅሞ የሰው ልጅን ቅንነት የሚተገብር ንጉስ ነው (ዋንግ)" (ፋንግ 1952፡112) አሁንም በቻይናዎች ባህል የሞ ዙ አስተሳሰብ (ሞ ቲ, C.468-C.376 አ.አ.) የቻይናን ጦርነትና ጭቆና የሚቃውምና የ”አለም አቀፍ ፍቅር” ፋላስፋ በአለማቀፍ ደረጃ እንደገና ማግኘትን ይጋብዛል (ፋንግ፡ 1952፡ 76-105)፡፡

ረጅም ጊዜ የቆዩ ብጥብጥን የሚደግፉ ፅሁፎች ግድያን አውጥተው ነገር ግን ያለመግደል እውቀትን በመያዝና በማጐልበት እንደገና ሊተረጐሙ ይችላሉ፡፡ እንደምሳሌ ልንወስዳቸው የምንችለው ቻይዋት ሳታ-አናንድ የማኪያቬሊን “The Nonviolent Prince” (1981) እንደገና እንደተረጐመው እንዲሁም ቡሮው የክሎውዝዊትዝን “On War to Drive Principles for Nonviolent Strategic Defense” (1996) እንደገና ተርጉሞታል፡፡ ሁለቱም የሚያስታውሱት ጋንዲ የብጥብጥ አልባ እርምጃዎች መርሆዎችን ከሂንዱው ታሪክ "ባክሀቫድ ጊታ" ሎርድ ክሪሽና ለጦረኛ ጀግናው አርጁና የመከረውን እንደወሰደ ነው፡፡ (ጋንዲ 1971)

የቆዩ ብጥብጥን የሚቀበሉ ሥራዎች የአሁንና የወደፊት ያለመግደል ፈጠራን ይፈታተናሉ፡፡ ኘሌቶ የጦር ምግባሮችን በሚያሳዩ መሪዎች የሚመራ ሪፑብሊክን ካረቀቀ አሁን ደግሞ በጐበዝ መሪዎች የሚመራና ለአለመግደል መርህዎች ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ዜጐች ያሉበት የማይገድል ሪፖብሊክን ልናልም እንችላለን፡፡

አሪስቶትል ለጦርነት ትግል ቡድኖች ህገመንግሥትን ማብራራት ከቻለ እኛ ደግሞ ለማይገድል ማህበረሰብ አመቺ የሆኑ ህገመንግስቶችን ልናስብ እንችላለን፡፡ ማካቬሊ ብጥብጥን ለሚቀበል የበላይነት ችሎታን ካቀረበ አሁን ደግሞ ለማይገድል ፖለቲካዊ ሥልጣን ስትራቴጂና ታክቲክ መሥራት ይቻላል፡፡ ሆብስ በብጥብጥ የበላይነት የሕብረተሰብን ሠላም በማስገደድ የሚያስከብር ጭራቃዊ ሀገርን ማርቀቅ ከቻለ ለሰው ልጅ ፍላጐት ምላሽ የሚሰጥና ግድያ የማያስፈልግበት አዲስ የአመራር መንገድ ሊዳሰስ ይችላል፡፡ ሎክ ጨቋኝ አመራርን በብጥብጥ የተሞላ አብዬትን በመጠቀም ለማስወገድ ካለመ እኛ ደግሞ የማይገድል ዲሞክራሲያዊ ነፃ መውጣትን ስትራቴጂና ታክቲክን ልናስብ እንችላለን ማርክስና ኤንግልስ የመደብ ትግልን ሊያልሙ የቻሉት ብጥብጥ ብቸኛው ዳኛ ነው ብለው ከሆነ እኛ ደግሞ ያለመግደል ትግል ሂደቶችን የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚያዊ ፍትህ ትልምን ለመተግበር ማለም እንችላለን፡፡ ሩሶ የሚጥሱን ግድያ ላይ የተመረኮዘ ህብረተሰባዊ ውል ያስፈልጋቸዋል ካለ እንዲሁም አሁን ያሉ መሪዎች ብጥብጥን ስለተመረኮዙ "ውሎች" እና "ቃል-ኪዳኖች" መናገራቸውን ከቀጠሉ እኛ ደግሞ የማይገድሉ

ማህበረሰቦች ውስጥ ስለሚኖር ደህንነት መወሰድ ያለበትን የእርስ በእርስ ቁርጠኝነት መመርመር መጀመር እንችላለን፡፡ ካንት (1795/1959) "ዘላቂነት ያለው ሠላም" የሚመጣው ጦርነት የሌለበት ጐራ ውስጥ የሙጥኝ ብሎ መከተል የሚለውን ማለም ከቻለ እኛ ደግሞ ያለመግደል መርሆን ወደ አለማቀፍ እውነታ ለመቀየር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ልናውቅ እንችላለን። የአሜሪካ ፖለቲካ ባህል የሚያስቀምጠው የቆየ አዋጅ በብጥብጥ የተሞላ ልእልና እና ብጥብጥን የሚደግፍ ህገመንግሥትን ከሆነ ያለመግደልን የልእልና አዋጅ ከአሜሪካ ሕብረተሰባዊ ብጥብጥ ማግኘት ይቻላል ብሎ ማለም እንዲሁም አዲስ የማይገድል ህገመንግሥትም ሊመጣ ይችላል፡፡ ዌበር ፖለቲካ እንደ ሥራ ግድያ የማይቀር መሆኑን መቀበል አለበት ካለ እኛ ደግሞ ፖለቲካን እና ፖለቲካ ሳይንስን ልናስባቸው የምንችለው ከብጥብጥ ነፃ ሊወጡ የሚችሉ ዘርፎች እንደሆኑ ነው፡፡ (አረንድት 1970፣ ሙለር እና ሴመሊን 1995፣ ስቴገርና ሊንድ 1999)

ያለመግደል ሽግግር የሚያመላክተው ጥብቅ በሆነ መልኩ የጋንዲያዊያንን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወደ ፍልስፍና እና ፅንሠ-ሀሳብ መስክ ማስገባትን ነው፡፡ ያለመኖሩ የሚመሳሰለው በዚህ ብጥብጥን በሚቀበል አለም ውስጥ ጋንዲ ለኖቤል የሠላም ሽልማት ባለመታጨቱ ከተደረገው ያለፈ ስህተት ጋር ነው፡፡ ሥራውን ለመስራት ሀብቱ ብዙ ነው፣ በተለይ በተለያየ አስተሳሰባዊ እና ስርአታዊ አመለካከት ውስጥ ያሉ የህንድ ተርጓሚዎች ከሌሎች ህንድ ካልሆኑ ፈር ቀዳጆች ጋር በመሆን (ዳዋን 1957፣ ዳንጅ 1977፣ ኢየር 1973፣ ፖርከህ 1989a, 1989b፣ ቦንዱራንት 1969፣ ዳልተን 1993፣ ጋልተንግ 1992፣ ሻርፕ 1979፣ ስቴጀር 2000)። ያለመግደልን ፅንሠ-ሀሳብ በፈጠራ ለማጐልበት ያሉ እድሎች ያለመግደል አማራጮችን በሚደግፉት ሀሳብ ይቀርባል ካለፈም ካሁንም በአለም ላይ ካሉ ባህሎች በሙሉ በአርተር እና ላይላ ዊንበርግ (1963) የቀረበ በ550 አ.አ. የተሰራ የዳሰሳ ጥናት ነበር፡፡ የብዙ ሀይማኖቶች መሠረት የተጣለው በኡኒታን እና ዬጀንድራ ሲንግ (1973) ውስጥ ነበር። በግሪክ-ሮማ፣ ዩሮ-አሜሪካ ባህል ዊል ሞሪሲ (1996) እጅግ እውቀት የተሞላበት ሂስ ከጥንት ጀምሮ ሠላማዊነት (Pacifism) ላይ አቅርቧል፡፡

ያለመግደል ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ላይ አለማቀፍ ጥናት በተደረገ ጊዜ አንዳንድ አስደናቂ ግኝቶች ሊጠበቁ ይገባል፡፡ የኮርያዊው የፖለቲካ ፈላስፋ ህዋንግ ጃንግ ዩፕ በፒዮንግያንግ ዲሴንበር 3, 1987 የሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ "ፖለቲካ" ን ባለመግደል መልኩ ያብራራው እንዲህ ነበር፡- "ፖለቲካ ማለት የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ፍላጐት ፍቅርንና እኩልነትን መሠረት በማድረግ ማስማማት ነው"፡፡ በዚያን ጊዜ እርሱም ቃለ መጠይቅ የሚያደርገውም ሶሮኪን /1948፣1954/ የተሰኘ ሶሺዩሎጂስት ስለ "ፍቅር" እና "ፈጠራ ያለው ስለሌሎች መቆርቆር" (Ceative alutrism) የተደረጉትን ልዩ ጥናቶች አያውቁም ነበር:: ይህ ጥናት ሊጣመር የሚችለው ከአረንድት (1970) መነጋገር፣ መወሰን እና አንድ ላይ መተግበር ላይ ያለ ትኩረት፣ የበርተን (1979) የሰው ልጅን ፍላጎት የማርካት ሂደቶች ለአዲስ ያለመግደል ፖለቲካዊ ፅንሠ-ሃሳብ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ላይ ከሚደረግ ትኩረት ጋር ነው፡፡

## የአገዛዝ /Polity/ ጥናት

በፖለቲካ የተደራጁ ማህበረሰቦችና ክፍልፋዮቻቸው ላይ በሚደረግ ጠቅላላ ጥናት፣ ከመንደሮች አንስቶ እስከ ህዝባዊ ሀገሮችና የሽግግር አካሎች (እንደ አሜሪካ መንግስትና ፖለቲካ መስክ) ያለመግደል ትንታኔ ስነአመክንዬ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች በድፍረት መነሳት ያለባቸው ሃሮልድ ሊንስቶን "በመሰለኝ ወደኋላ መቅረት" (Assumption drag) የሚለውን አባባል ለመወጣት ነው፡፡ ፖለቲካዊ ግድያ ጥያቄ ሳይነሳበትና ለፅድቅ የተሰራ ነው በሚል ከለላ ውስጥ መቆየት ይፈልጋል፡፡ ጥያቄዎች በአገዛዝ ውስጥ መነሳት ካልቻሉ ውጪ ያሉ ፖለቲካ ሳይንቲስቶች ሊያነሷቸው ይገባል፡፡

ያለመግደል አቀራረብ የሚያመላክተው ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን አይነት ጥያቄዎች መመለስ እንዳለባቸው ነው፡፡ በመጀመሪያ ግድያ ለእያንዳንዱ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ

መፈጠርና መኖር ምን ዓይነት አስተዋፅኦ አድርጓል? አገዛዙ አራሱን የሚያይበትን መንገድ የሚለካው በታሪክ ውስጥ የሚመሰገን የግድያ ተግባር የሚፈፅመው እስከምን ድረስ ነው? በአብዛኛው የሚታየው መንግስታዊ የሆነ ነው ወይስ መንግስታዊ ያልሆነ ግድያ? የወደፊት ቀጣይነቱስ እንዴት ነው? ዜጎች ግድያ ላይ እንዲሳተፉና እንዲደግፉ እንዴት ሊደረጉ ቻሉ? ሕጋዊ ወይስ ከህግ ውጭ፣ መንግሥስትን በሚደግፉ ወይስ በሚቃወሙ፣ በሀገር ውስጥ ወይስ ውጭ? ፖለቲካዊ፣ ኢካኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ባህላዊ አስተሳሰቦች ተግባሮችና መሠረቶች እንዴት ነው ለግድያ አስተዋፅኦ የሚያደርጉት? አገዛዙ ሌሎች እሴቶችን ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ (እንደ ነፃነትና እኩልነት ያሉ) ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት ላይ ግድያ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሣድራል?

ሁለተኛው ደግሞ ያለመግደል አስተሳሰብ፣ ተግባር፣ ፖሊሲ እና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ተቋማት ታሪካዊ መሠረታቸው ምንድን ነው? በአሁኑ ጊዜ እንዴት ነው የሚታዩት የወደፊትስ ተስፋቸው ምንድን ነው? ያለመግደል ተቃውሞ የግድያ አዝማሚያ ካለው ፖለቲካዊ ሥልጣን ጋር ያስመዘገበው ሁኔታ እንዴት ነው? ፈጠራና የማይገድል ማህበረሰብን እውን ለማድረግ የሚወሰድ እርምጃ ያስመዘገቡት ሁኔታ እንዴት ነው?

በአገዛዝ ጥናት ውስጥ ሶስተኛው መስፈርት በመግደልና አለመግደል መካከል ያለውን መሸጋገርና መመላለስ ብዛት ላይ ጥያቄ ማንሳት ነው፡፡ ምን ዓይነት የታወቁ አካሎች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች እንደዚህ ያለ ሽግግር ላይ ተጠምደዋልን? ወታደሮች የሠላም አስፋኞች ሆነዋልን? ገዳዮች ለወደፊት ህይወታቸው ወደ ማክበር ተቀይረዋልን? ብጥብጥን የሚደግፉ አብዬተኞች ወደ አለመግደል ማህበረሰባዊ ለውጥ ቁርጠኝነት አሳይተዋልን? የህይማኖት መሪዎች ግድያን መባረክን ትተዋልን? የባህል መሪዎች ብጥብጥን በመቀበልና በማውገዝ መሐል ተሸጋግረዋልን?

የሞት ቅጣት የሚያስጥባቸው ወንጀሎች ገደብ ላይ ምን ለውጥ ታይቷል? (ተጥሏል፣ ተወግዷል፣ ወይስ እንደገና ተቀምጧል) የጦር ኃይሎች ከተነሱ በኋላ እንደገና ተዋቅረዋልን? ሠራዊቶች ተወግደዋልን? ፖሊሶችና ዜጎች መሣሪያ ከተወሰደባቸው በኃላ እንደገና ታጥቀዋልን? ከባድ ጥለኞች በሚባሉ መሐል እውነተኛ የሆነ ሠላማዊ እርቅ ከተካሄደ በኋላ ግድያ ተመልሶ የተጧጧፈበት ሁኔታ ኖሮ ያውቃልን? ግድያን ይደግፉ የነበሩ ኢኮኖሚዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማይገድል ግላዊና ማህበረሰባዊ ፍላጐት ወደመመለስ ተሸጋግረው ያውቃሉን?

አራተኛ የትኞቹ ታሪካዊ ወይም ዘመናዊ በአገዛዝ መሐከል ያሉ ንጥረ ነገሮች (ፖለቲካዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ ኢካኖሚያዊ እና ባህላዊ) ቢጣመሩና በአለመግደል ለውጥ ሂደት ቢገለፁ ለዚያ ማህበረሰብ አስፈላጊ የሆኑ ያለመግደል የህይወት ሁኔታዎችን ለማምጣት ተስፋ ይሆናሉ? በኃይማኖት፣ በአስተሳሰብ፣ በህግ፣ በተቋማት፣ በፖሊሲዎች፣ በህብረተሰብና ኢክኖሚያዊ መሰረቶች፣ በትምህርት፣ በግንኙነት፣ በጥበብ፣ እና በአገዛዝ መኃል ያሉ ግንኙነቶች ላይ የሚደረጉ ለውጦች የማይገድል ማህበረሰብን እውን ለማድረግ በዚያ ይዘት ውስጥ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ እንደ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ቁሳዊ ደህንነት እንዲሁም ወደ ግድያ ወይም በግድያ ማስፈራራት ሳንመለስ ደህንነትን ማምጣት ያሉ እሴቶችን እድገት በጥሩ መልኩ ሊያሣልጡ የሚችሉ ሁኔታዎች ምንድንናቸው?

## አንፃራዊ ፖለቲካ

ያለመግደል ሽግግር የሚያመላክተው የሰውን ልጅ ያለመግደል ብቃት ጥያቄ በአንፃራዊ የፖለቲካ ጥናት መሀል ማስቀመጥን ነው፡፡ ስጋትን ወይም ደግሞ ለሞት የሚያደርስን ሀይል በመንግሥት ወይም በዜጐች አማካኝነት በማህበረሰብ ውስጥ መጠቀምን ማስወገድ የሚለውን በሀሳብ፣ በተቋም፣ በመሠረት፣ በሂደት እንዲሁም በፖሊሲ የሚስማሙትን በአለማቀፍ ደረጃ ከማነፃፀር ምን ዓይነት እውቀት ሊገኝ ይችላል? በአለመግደል ትንታኔ ስነአመክንዬ በመመራት እና ተግባራዊ ለውጥን የሚያመጡ

አሰራሮችን በመፈለግ አንፃራዊ ጥናት ከአንድ አገዛዝ ወሰን ያለፈ አማራጭ እውቀትን ይፈልጋል፡፡

ማህበረሰቦች ለመግደል ወይም ላለመግደል ባላቸው አዝማሚያ ሊነፃፀሩና ደረጃ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ልክ ለዲሞክራሲያዊ ተቋማት፣ ለሰብአዊ መብቶች፣ ለሴቶች መብት፣ ለህፃናት ደህንነት እና ለኢኮኖሚያዊ እድገት ደረጃ እንደተደረገው። ከግድያ መለኪያ ጥቂቶቹ በወኪሎችና በተቃዋሚዎች የሚደረግ ግድያ፣ ወንጀላዊ ማጥፋት፣ የዜጋ ህይወት ማጥፋትና ራስን ማጥፋት፣ ከሀገር ሀገር የሚደረግ የሌላ ማህበረሰብን አባላት መግደል፣ ለመግደል ከፍተኛ ስልጠና፣ የቴክኖሎጂያዊ ብቃት እና የግድያ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ቁሳዊ ጠቋሚዎች፡፡ ከነጣላ አገዛዝ ትንታኔ በመነሳት ያለመግደል ባህሪዎች ትይዩ በሆነ መልኩ ደረጃ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ለሚገድሉና ለማይገድሉ ሀገራት በየጊዜው የሚደረግ ደረጃ አሰጣጥ አለማቀፍ የፖለቲካ ሳይንስ ለህዝብ ሊያደርገው የሚገባ አስተዋፅኦ ነው፡፡ የግድያ ደረጃ ከፍና ዝቅ ማለት እንዲሁም ያለመግደል የለውጥ ብቃት ማደግ ወይም መታፈን ሪፖርት ከቀን የቀን የአለም የገበያ ሁኔታ ወይም የስፖርት ውጤት ሁኔታን ከመከታተል የሚተናነስ አይደለም፡፡

በአገዛዝ መሀከል እንዲሁም በአገዛዝ ውስጥ የሚደረግ የማህበረሰባዊ ክፍሎች ንፅፅር በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥም ሆነ ተመሳሳይ ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ለምክንያታዊና ለለውጣዊ መግባባት እገዛ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህም የሚያካትቱት የሀይማኖቶች፣ የርዕዮተ አለሞች፣ የጥበቦች፣ የፓርቲዎች፣ የፆታ፣ የእድሜ እኩዮች፣ የትምህርት ደረጃ፣ የመደቦች፣ የጎሳ ቡድኖች፣ የኢኮኖሚያዊ ኢንተርፕራይዞች፣ የዩኒቨርስቲዎችና የሙያዎች መግደል እና ያለመግደል አዝማሚያን ነው፡፡

ያለመግደል አንፃራዊ ጥናቶች ዘመናዊውን የፖለቲካ ሳይንስ አስተሳሰብ ወደፊት ለማስኬድ ይረዳል፡፡ ይህም አስተሳሰብ የሚለው ዲሞክራሲያዊ ሀገሮች ከአምባገነን አገዛዝ ጋር ሲነፃፀሩ ዲሞክራሲያዊዎቹ እርስ በርሳቸው ጦርነት ውስጥ አይገቡም እንዲሁም የራሳቸውን ዜጎች በብዛት አይገድሉም፡፡ በሊበራል ዲሞክራሲ ውስጥ መግደል በቀጣይነት ሲኖር (ፕሬዝዳንታዊም ሆነ ፓርላሜንታዊ አወቃቀር ቢኖረውም) እና የብጥብጥ ባህል ሲታይ ያለመግደል አወቃቀርና ባህላዊ አማራጮችን ላይ ያለ እውቀትን ለማዳበር የአንፃራዊ ጥናቶችን አስፈላጊነት ያጎላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በምዕራፍ 2 ውስጥ እንደታየው ቅርብ ለቅርብ በሆኑ ሁለት የሜክሲኮ መንደሮች ላይ በተደረገው አንፃራዊ ጥናት በብጥብጥ ደረጃቸው የተለያየ ሆኖ በህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ግን ተመሳሳይ የሆኑት እራሳቸውን በሚያዩበት ባህላዊ መንገድ የሚለያቸው ባህሪ መሆኑ ታይቷል፡፡ ሀይለኛ (በጥባጭ) የሆኑት መንደርተኞች እራሳቸውን የሚያዩት ኃይለኛ እንደሆኑ ነው፡፡ ሀይለኛነታቸውንም ተቀብለውታል፡፡ በጥባጭ ያልሆኑት መንደርተኞች እራሳቸውን የሚያዩት ሰላማዊ እንደሆኑ ነው፡፡ በዚያም ይኮሩበታል፡፡ (ፍራይ 1994)

በሁለት የኢንዶኔዥያ መንደሮች ውስጥ (አንደኛው ከፍተኛ የብጥብጥ ደረጃ ያለው ሌላኛው ደግሞ ዝቅተኛ የብጥብጥ ደረጃ ያለው) በህፃናት ጨዋታ ዙሪያ የተሰራ አንፃራዊ ጥናት ያገኘው በይበልጥ የብጥብጥ ባህል ያለው መንደር የሚመርጠው ጨዋታ በሰውና በእንስሳት መካከል የሚደረግን ትግል እንደሆነ ነው፡፡ ዝቅተኛ የብጥብጥ ባህል ያለው መንደር የሚመርጡት የጨዋታ አይነት ደግሞ የወይን ዛፍ ላይ መንጠላጠል እና በሰዎችና በእንስሳት ያሉ ሰላማዊ ባህሪዎችን ማስመሰል ነው፡፡ (ሮይስ 1980) እንዲህ ያሉ ግኝቶች በብጥብጥ የተሞሉ ባህሎች ውድድር ካለባቸው እንደ ቦክስ፣ የገና ጨዋታ፣ ነፃ ትግል እና የአሜሪካ እግር ኳስ ያሉ የንክኪ ስፖርቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥልቅ ለማየት ይረዳል፡፡

## አለማቀፋዊ ፖለቲካ

አለማቀፋዊ ፖለቲካ፣ አለማቀፋዊ ግንኙነት ወይም የአለም ፖለቲካ እየተባለ በተለያየ ስም የሚታወቀው መስክ ከአለመግደል ሽግግር ጋር በአንድ ላይ የሚያስተዋውቀው ለግለሰብ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሁሉም መጠንቀቅን ነው፡፡ በስፋትም ሆነ በትንሹ የሚደረጉ ጥናቶችን ጣልቃ ለሚገቡ ተቋማት ከሚደረግ ተገቢ ጥንቃቄ ጋር ያጣምራል፡፡ በአንድ በኩል የአለም አቀፍ አገዛዝ ክፍሎች (ሀገራዊ እና ሀገራዊ ያልሆኑ)፣ በመሀከላቸው ያሉ ግንኙነቶች አወቃቀር እና ችግር የመፍታት ሂደቶች እንደ አንድ ይታያሉ፡፡ ይህ ግን ታሪክን ያልተከተለ ወይም ከይዘት የወጣ ነው ማለት አይደለም ታሪኩ የሰው ልጅ ነው፡፡ ይዘቱ ደግሞ በአለማቀፋዊና በአካባቢ ያሉ የተሳሰሩ የግንኙነት ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ያለመግደል አለማቀፋዊ ማህበረሰብ ይተገበራል የሚለው አስተሳሰብ እያንዳንዱ በዚህች ምድር ላይ ከልጅነት እስከ እውቀት ለሚኖር ሰው ደህንነት አትኩሮት መስጠትን ይሻል (ትውልዶች መጥተው እስከሚያልፉ ድረስ ጭምር)። ለአለመግደል ፖለቲካዊ ትንታኔ መነሻ የሚሆነው አንድ የሰው ልጅ ነው፡፡ ድርጅቶች፣ መዋቅሮችና ሂደቶች የሰው ልጆች ባህሪ ስብስብ ውጤት ነው፡፡ የአለም ፖለቲካ የአለም ግለሰቦች ፖለቲካ ነው፡፡ የማይገድል አለማቀፋዊ ማህበረሰብ የሚመረኮዘው ከግድያ ነፃ በሆኑ ግለሰቦች ነው፡፡ ማንም ሰው የማይገድልም ሆነ የሚገደል ከሆነ የሁሉም የሰው ልጆች ፍላጎት ሊታይ ይገባዋል፡፡

ይህ የሚያመላክተው ያለመግደል ትንታኔ ስነአመክንዬ እርምጃን በአለማቀፍ ደረጃ የሰው ልጆች ላይ መተግበር አስፈላጊነትን ነው፡፡ ለመግደል የፖለቲካ ሳይንስን በሀገራዊ ግድያ፣ ሀገርን በመቃወም የሚደረግ ግድያ እንዲሁም ሁሉም አይነት በማህበረሰቦች መሀልና ውስጥ ያሉ ግድያን በማካተት የሚደረግ የምርምር ባህልን ማስፋት እና አጠቃሎ በአለማቀፍ ደረጃ ምክኒያታዊ ማብራሪያ መስጠት ማለት ነው፡፡ ለአለመግደል ደግሞ በአለማቀፍ ደረጃ ባሉ የፖለቲካ አካሎች ውስጥና መሀል ያሉ የማይገድሉ ሀይሎችን ለይቶ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ለአለመግደል ለውጥ አለማቀፍ በሆነ አጠቃላይ የሲስተም ይዘት ውስጥ በሚገድሉና በማይገድሉ ሀይሎች ውስጥና መካከል ያለን የግንኙነት ሂደት መረዳት ማለት ነው፡፡

የማይገድል አለማቀፍ ማህበረሰብን ተግባራዊ፣ የሚቻልና የሚፈለግ ባህሪዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ ለመረዳት ባለፉና አሁን በሚገኙ ህብረተሰባዊ ትግበራዎችና ፍላጎቶች ውስጥ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲደረግ በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ በአለመግደል ሙሉነት ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌለው ልዩነት እንደሚገኝ በመገመት ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ የግለሰቦች ወደ መግደልና ያለመግደል ማመዘንን፣ ወደአለመግደል የመለወጣቸው አካሄድ እና ህይወትን ሙሉ የግለሰብን ያለመግደል እመርታ ማሳየትን የሚደግፉ የህብረተሰባዊ ይዘቶች ባህሪ ማለት ነው፡፡

የግድያን መስመሮች ወደማይገድሉ የማራገቢያ አማራጮች ለመለወጥ በሚደረጉ ተግባራዊ አዝማሚያዎች አለማቀፋዊ አመለካከት ማለት ጨቋኝ የግድያ ተግባሮችን በመጣስ የግድያ ዞኖች ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ጣልቃ ለመግባት መፈለግ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ለአለመግደል ችግር መፍታት አለማቀፍ በሆነ መልኩ አመራርና ዜግነትን ልምምድ እና ስልጠና ላይ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ማለት ለአለመግደል ለውጥ የሚደረጉ አለማቀፍ ባህላዊ አስተዋፅኦዎችን ለይቶ ማወቅና ማበረታት ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ማለት በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰባዊ እና ባህላዊ ግድያን የሚደግፉ መዋቅሮችን ወደማይገድል አለማቀፋዊ ለውጥ ማምጣትን መረዳትና ማገዝ ማለት ነው፡፡

የሰው ልጆች ከግድያ ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦችን የመፍጠር ብቃቱ አላቸው ከሚለው አስተሳሰብ በመነሳት ለእያንዳንዱ መስክ ንዑስ መስክ እና ለዘመናዊ ፖለቲካ ሳይንስ አመለካከት ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ፖለቲካ ሳይንስ ከእሴት ነፃ አይሆንም እንበልና ያለመግደል

*ተቀባይነት ያለው ሙያዊ እሴት ነው? ያለመግደል ፖለቲካዊ ስልጣን ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበር በተሳካ ሁኔታ ከብጥብጥ ሀሳቦችና ትግባሮች ጋር ሊወዳደር ወይንም ሊለውጠው ይችላል? ከአካባቢ ጀምሮ እስከ አለምአቀፍ ድረስ ከግድያ ነፃ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት እውን መሆን ይችላሉ? ወደ ግድያ ከሚያዘነብል ብሄራዊ ደህንነት ተነስቶ ወደ ማይገድል ብሄራዊና አለማቀፋዊ ደህንነት መሸጋገር ይቻላል? ወደግድያ ከሚያዘነብል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተነስቶ ወደማይገድል አለማቀፍ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚስ? የሴቶች መብት ተቆርቋሪነት፣ የዘር፣ የመደብ፣ የጎሳ፣ የቋንቋና የሃይማኖት አመለካከቶች ላለመግደል ፅንሰ-ሀሳብና ትግበራ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉን? ምን አይነት ስልቶች ናቸው? ጠቅለል ባለ ሁኔታ የማህበረሰባዊ ብጥብጥን፣ ያለመግደል እመርታን፣ የለውጥ ሂደቶችን እንዲሁም ልዩ ልዩ ያለመግደል ውጤቶችን ፈጠራን ተጠቅሞ መዘርጋትና መከታተል ለመረዳት የሚጠቅሙት?*

*ይህ ሲባል ፖለቲካ ሳይንስ በሁሉም መስክ እነኝህን ጥያቄዎች ለመመለስ አስተዋፅኦ አላደረገም ለማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን የፖለቲካ ሳይንስ ከግድያ ነፃ የሆኑ ማህበረሰቦች በማይገድል አለም ውስጥ የመተግበርን እድል ከበድ አድርጎ ቢያየው ምን ይመስል ነበር የሚለውን ሀሳብ ለመጋበዝ ነው፡፡ እንዲህ ያለ እድልን መቀበል የሚያመላክተው የፖለቲካ ሳይንስ በአለመግደል አለማቀፋዊ ችግር መፍታት ላይ መጠመዱን ነው፡፡*

# ምዕራፍ 4

## ችግርን መፍታት የሚያመላክታቸው ነገሮች

የሰው ልጆችን እልቂት (በሚሊዮኖች
የሚቆጠሩ በረሃብና በኢኮኖሚያዊ ድህነት
ምክኒያት የሚያልቁትን) የሚያወግዙና
የሚዋጉ በሙሉ በአንድ ድምፅ
የሚስማሙበት ነገር ቢኖር የዚህ አሳዛኝ
ክስተት ምክኒያት ፖለቲካዊ ጉዳይ እንደሆነ
ነው።

የ53 የኖቤል ሎሬቶች ማኒፌስቶ 1981

*ከግድያ ነፃ ፖለቲካ ሳይንስ ችግርን በመፍታት ላይ የሚያመላክታቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?*

በአጠቃላይ ዋና አላማው በአለማችን ላይ ሞትን የሚያመጡትን ማጥፋት ነው። ይህም ማለት የሰው ልጅ አጥቂም ተጠቂም ሊሆን ስለሚችል ለደህንነቱ ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ትኩረት መስጠት ይገባል። ይህ ነገር በአንድ በኩል የፖለቲካ ሳይንስን ዝንባሌ ወደ ግለሰብና አላማ ወዳለው ፈጠራ ይመልሰዋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ችግርን የመፍታት አቅጣጫ ይዞ ነገር ግን የመንፈስ፣ የጾታ፣ የእድሜ፣ የዘር፣ የመደብ፣ የሙያ፣ የብሄራዊ እንዲሁም የፖለቲካዊ ማንነት የማይገድበው ነው። ይህ የሚያመለክተው ያለመግደል "ብዙ ተከታዮች" እና (ጉትዝኮው 1955) ችግርን የመፍታት ሂደት በላቀ ሁኔታ ማሳለጥ አንድ ላይ ተጣምረው የሰዎችን ፍላጎት ያለ ማስፈራራት ወይም ሀይል ሳይጠቀሙ ማስተናገድ ነው።

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ በአንድ ላይ ያለው ቁርጠኝነት ለግድያ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን መቀነስና አለመግደልን የሚያጠነክሩ ብሎም የሚያበረታቱ ሁኔታዎችን ደግሞ መጨመር ነው። የሚጥረውም በምስሉ ላይ በሚታዩት አምስት ዞኖች ውስጥና መካከል ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ነው(ምስል 1 እና ምስል 2)። ይህም ማለት ፖለቲካ ሳይንስ በአጠቃላይ ችግር የመፍታትን ሃላፊነት እንዲሁም በተዘዋዋሪ የሌሎችንም ጥረት መደገፍ እንደሙያው አንድ ክፍል አድርጎ መቀበል ማለት ነው። ይህም የሚያካትተው ጥናቶችን ማሳለጥ እንዲሁም የግልና የህዝብን ችግር የመፍታት እርምጃ ለማገዝ ስልጠና መስጠት። ማለትም ፍላጎትን በማሳካት ሂደት በኩል በግልና በህብረተሰብ የሚደረግ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሁሉንም ሰው ተሳትፎ ማሳለጥ ነው።

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስን የችግር መፍታት ተሳትፎ መቀበል ሁሉን አዋቂነትን፣ ሁሉን ቻይነትን ወይም ከፍተኛ ስልጣንን አያመላክትም። የሚያመላክተው ግን በአጠቃላይ ከማህበረሰባዊ ህይወት - ማለትም መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ቁሳዊ እና ባህላዊ - ጋር ሊኖረው የሚችለውን ተያያዥነት ነው። ይህ ግን አጠቃላይ የሆነ ቁጥጥር ማድረግ ሳይሆን ይልቁንም የፖለቲካ አካላት፣ ተቋማት፣ መንግስታት እንዲሁም እነርሱን የሚደግፉ ሰዎች የሚያደርጓቸው ወይም ሳያደርጓቸው የሚቀሩ ነገሮች የማህበረሰቡን የመኖር፣ የኢኮኖሚያዊ ደህንነት ብሎም እስከ ከፍተኛው የሰው ልጅ ትልም ድረስ ሰፋ ያሉ የሚያስከትሏቸው ነገሮች እንዳሉ ማወቅ ነው። ያለመግደል ማህበረሰቦችን ለማገልገል በሚያደርገው ጥረት

የፖለቲካ ሳይንስ በስፋት የሚሸፍናቸውንና የሚያበረክታቸውን ነገሮች ከህክምና ወይም ከማህበረሰብ ጤንነት (Public Health) ሙያዎች በተለየ ሁኔታ መገደብ የለበትም።

ችግርን በተፈለገውና በነባራዊው ሁኔታ መካከል ያለ አለመጣጣም ብለን ልናብራራው እንችላለን። እያንዳንዱ ችግር የራሱ የሆነ የተወሳሰበ ግልጽ ያለመሆን ንዑስ ችግር ይዞ ይመጣል፦ የተለምዶ (መሆን ያለበት)፣ በጥናት የተደገፈ (አሁን የሆነው)፣ እመርታን የሚያሳይ (መሆን የሚችለው)። እያንዳንዱ ችግር ደግሞ ስልታዊ ውስብስብነቶች፣ እርስ በርሱ የተሳሰረ የምላሽ ሂደት እንዲሁም የድሮ-ዘንድሮ-ወደፊት የጊዜ ክፍሎችን ይዞ ይመጣል። ነገር ግን ችግሮች ምንም ያህል በሞራልም ሆነ በፊሎዞፊ ረገድ ከባድና ውስብስብ ቢሆኑም ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የሰው ልጅን ደህንነትና የመኖር ፍላጎትን የሚፈታተኑት ለመግታት የሚያደርገውን የማያወላዳ ጥረት አይክድም። ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የጸባይ መረበሽ ፣ መሰረታዊ የብጥብጥ ሁኔታዎችን መቀየር እንዲሁም የሁለቱንም ሁኔታዎች ችግር በውይይት ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ውስጥ ይሳተፋል። የሚጥረውም ሞትን ለማምጣት የሚሹትን መቅረፍ፣ በስራ ላይ ያሉ ተቋመማትን ወደ አለመግደል እንዲያዘነብሉ መርዳት እንዲሁም አዳዲስ ያለመግደል ፖሊሲዎች እና ተቋሞችን ለመፍጠር ነው።

ተግባራዊ ሳይንስና ተግባራዊ ሰብአዊነት ላይ የተመረኮዘ ችግርን የመፍታት ሚና ለፖለቲካ ሳይንስ ሰጥተን ስናበቃ መፍትሄዎች በቅድሚያ መታወቅ አለባቸው ማለት በፍፁም ሳይንሳዊ አይሆንም። በተመሳሳይ ሁኔታ በሽታ ሊድን አይችልም፣ መዳኛው ከምርመራው አስቀድሞ መታወቅ አለበት ወይንም መድሃኒት ማዘዝ እንዲሁም ማከም ከመዳን ያስቀራል የሚለው አባባል በተግባራዊ ህክምና ሳይንስ አያስኬድም። ፖለቲካ ሳይንስም ስር መሰረቱ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለሆነ ከዚህ ሊለይ አይገባውም።

ብጥብጥን የሚቀበል ፖለቲካና ፖለቲካ ሳይንስ ሊፈታቸው ያልቻላቸውን ችግሮች ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ በአንድ ጊዜ ይፈታዋል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይሆናል። ብጥብጥን በብጥብጥ አፍኖ ለማስቀረት በሳይንሳዊ፣ በቁሳዊና በሰው ሃይል የተደረጉ ሰፊ ጥረቶች በከባድ ደም መፋሰስ ታጀቡ እንጂ በአለም ዙሪያ፣ በኒኩሌር መሳሪያ ዋና ከተሞች የሚደረጉ ከጦርነት፣ ዘር ማጥፋትና ነፍስ ማጥፋት የሚመጡ ግድያዎችን ለማቆም አልቻለም። እጅግ ብዙ የፈጠራ ስራ ለግድያ ማሳለጫ ውሏል። ልንጠቀምበት የሚቻል ያለመግደል ምርጫ ለማስቀመጥ ደግሞ ከዚያ ያላነሰ ፈጠራ ያስፈልገናል።

ይህንን የሰዎች የመገዳደል ዘመን ለመግታት መስራት ያለበት ፖለቲካ ሳይንስ ብቻ አይደለም። ይህንን ጉዳይ ሁሉም ሳይንሶች፣ ስብእናዎች፣ ሙያዎች እንዲሁም ሰዎች ሊካፈሉት ይገባል። ነገር ግን ፖለቲካ ሳይንስ ተነሳሽነቱን መውሰድና የሌሎችንም ተነሳሽነት ድጋፍ መስጠት አለበት። ተቀዳሚ ስራ የሚሆነው በተለምዶ እጅግ ጠንካራ የሚባትን ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የማይገድል አለምን መፍጠሩን የሚቃረኑትን ችግር መፍታት ነው። ሶስቱ በተለምዶ የሚታወቁት፦ "ሂትለርና ያደረሰው እልቂት(the holocaust)" ያስከተለው ችግር፣ መሰረታዊ የአብዮት ለውጥ እና ከግለሰብ አንስቶ እስከ ህዝብና አገር ያለ ደህንነት ነው።

## አለመግደል፣ ሂትለርና ሆሎኮስቱ

የፖለቲካዊ አመራርና ለሞት የሚዳርጉ ነገሮች ችግር (ሂትለርና ሆሎኮስቱን እንደ አንድ ምሳሌነት ማየት ይቻላል) በቀጥታ መታየት እና በመሰረታዊና በተግባራዊ ሳይንስ የችግር መፍቻ መንገዶች ላይ ማለፍ አለበት። የዘር ማጥፋት ወረራ፣ በጅምላ የህብረተሰብ ክፍልን ማጥፋት እንዲሁም ህዝብን የማውደም አሰቃቂ ምሳሌዎች ያለመግደልን ሳይንሳዊ የፈጠራ ችሎታዎች ሊያኮላሸው አይገባም። አለዚያ ግን ፖለቲካ ሳይንስ ለዘለዐለም መዘጋጀት የሚኖርበት የትኛውም ዘር አጥፊ አምባገነን መሪ፣ አብዮታዊ የህብረተሰብ ክፍል

አጥፊ ወይም የከተሞችና መንደሮች ደምሳሽ ሊያደርሰው ከሚችለው በላይ ግድያና ብጥብጥን ለመከላከል መሞከር ይሆናል።

አንድ ተጨባጭ መንገድ ብናይ ከተለያዩ ሙያዎች የተውጣጡ ስራዎችን በደንብ ያልጎለበተው የፖለቲካ ሳይንስ ጥናቶች ላይ አጠናክሮ ማካተት ነው። ይህም ማለት የግድያ ዝንባሌ ፀባይ እና ስልታዊ ሁኔታዎችን መለየትና ለአለመግደል አመራርና ተከታይነት አመቺ የሆኑ ለውጦችን መፈለግ ነው። አንዳንድ ቀደም ብለው አላማን ማዕከል በማድረግ የታወቁ ሁኔታዎች፣ ያለመግደልን ለውጥ አምጪ ጣልቃ ገብነት ብጥብጥ የሚያመጡ የአመራር ሃሳቦች፣ የባህሪ ቅድመዝግጅቶች፣ የሚና ስልጣን፣ የድርጅታዊ ድጋፍ፣ ከስራ የሚጠበቅ፣ ቴክኖሎጂያዊ አቅም እና ኢኮኖሚያዊ፣ ህብረተሰባዊ እንዲሁም ባህላዊ ግድያን ሊያጠናክሩ ይችላሉ። (Paige 1977)

የ20ኛው ክፍለዘመን ተሞክሮ ደግሞ አንዳንድ ነጥቦች ላይ የተለየ ሃሳብ ያቀርባል። የመግደል ዝንባሌ ያላቸው መሪዎችና የመግደል ዝንባሌ ባላቸው ተከታዮቻቸውን ድጋፍ፣ በታሪክ የሆነ ነጥብ ላይ ሰዎችን መግደልም ሆነ በመግደል በሚያምን ስርአት መተባበር ማቆም አለባቸው፡፡ አለበለዚያ በተበቃይ ጠፊዎችና በተጎዱ አሸናፊዎች መሃል የሚኖረው የግድያ ዑደት ይቀጥላል ማለት ነው። ይህ ቀላል ይመስላል፣ ነገር ግን የ20ኛውን ክፍለዘመን አሰቃቂ ሁኔታዎች አይተን ከ19ኛው ክፍለዘመን ጋር ስናነጻጽር፣ በ19ኛው ክፍለዘመን ጦርነትን ለማስወገድ ሲጥሩ የነበሩ የሰላም ተሟጋቾች እጅግ ትክክል እንደነበሩ ያሳያል። ከመጀመርያው የአለም ጦርነት እስከ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ብሎም እስከ ቀዝቃዛው ጦርነት ድረስ ብናይ ከጦርነቶቹ በመጡት አሰቃቂ ሁኔታዎች መሃል ግልፅ የሆነ ግንኙነት ይታያል። የፖለቲካ ሳይንስ የመከላከል ሚና የሚጠቅመው በበቀል የተሞላ ጥላቻን - የቆየም ሆነ የቅርብ - ወደ አሰቃቂ ሁኔታ ከመቀየሩ በፊት ለማስታረቅ መሞከር ነው። በበቀል የተሞላ እልቂት በጠላቶቻቸው ላይ ማድረስ የሚወዱ መሪዎችና ተከታዮቻቸውን እድገት ለመቅጨት ፖለቲካ ሳይንስ በትኩረት መስራት ያለበት ግድያን መከላከል፣ በቀለኞችን ማግባባት እና ያለመግደል ህይወትን ለመኖር የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ነው።

የወደፊት ሂትለሮችን፣ ስታሊኖችን፣ ማዖዎችን፣ አሚኖችን፣ ፖል ፖቶችን ወይም ደግሞ አውቶሚክ ቦንብ የሚጥሉ ትሩማኖችን እድገት ለመቅጨት የፖለቲካ አመራርን መሰረተ ሀሳብ ከሚገል አዛዥ ወደ ያለመግደል ማህበረሰባዊ ችግር መፍታትን የሚያሳልጥ መለወጥ፤ ሀይለኛና የብጥብጥ ባህሪ ያላቸው፣ መምራት የሚሹ ሰዎችን ቀደም ብሎ ለይቶ ማወቅና ድጋፍ መንፈግ ፤ የአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች ከሌሎች የሚጠብቁትን ለመግደል ፍቃደኝነት ማስወገድ፤ በግድያ ላይ ሰልጥነው መሳርያ ታጥቀው ለመታዘዝ ዝግጁ የሆኑ ድርጅቶችን ለመሪዎች አለማዘጋጀት፤ የግድያ ዝንባሌ ያላቸውን ድርጅቶች የሃይማኖታዊ፣ የንግድ፣ የስራ፣ የሳይንስ እንዲሁም የጥበብ ድጋፎችን ነፍጎ ወደ አለመግደል አማራጮች እንዲመጡ ማድረግ፤ ፍላጎትን ያማከለ ግጭትን የመፍታት መንገዶችን ማሳደግ የፖለቲካ መሪዎችና የህዝብ ዋነኛ ስራ እንዲሆን ማድረግ፤ ያለመግደልን ጠቀሜታ ዋነኛ የብሄራዊ ኩራትና ማንነት መገለጫ አድርጎ ማስቀመጥ፤ የትኛውንም አይነት ቡድን ከሰብአዊነት ያነሰ ወይንም እጅግ እርኩስ ከመሆኑ የተነሳ መጥፋት ይገባዋል የሚለውን አስተሳሰብ አለመቀበል፤ በተለያዩ ቡድኖች መካከል ለሁሉም ደህንነት ሲባል ውይይት ማዳበር፤ ሰዎችን በግልም ሆነ በቡድን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በብጥብጥ እርካታን እንዲያገኙ የሚገፋፋቸውን የህብረተሰባዊ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች መሰረታዊ ሁኔታዎችን መቀየር፤ ለግድያ የሚውሉትን ወጪዎች ህይወትን ወደሚደግፉ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ማሸጋሸግ፣ ያለመግደል ባህሎችን ፈጠራ በጥበብና ሳይንስ መደገፍ።

የሂትለር መሰል አሰቃቂ ስራዎችን ለመግታት ያለመግደል ሳይንሳዊ ፈጠራ ከፍተኛ የሆነ ፈተና ይገጥመዋል። ነገር ግን በዚህ የቴክኖሎጂያዊ ፈጠራ ታይቶ በማይታወቅበት ደረጃ በደረሰበት ጊዜ የማይታሰብ አይሆንም። አንዳንድ መታሰብ ያለባቸውና በችግር

መፍታት ተመሳሳይ ሁኔታዎች ላይ መሞከር ያለባቸው እርምጃዎች በትንሽም ሆነ በጅምላ የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ መሪ - ተከታይ፣ መንፈሳዊ - ሳይኮሎጂያዊ፣ ያለመግደል መቻል - አለመቻል፤ አለማቀፍ ወገዛ፣ ድጋፍን መንፈግ፣ ግድያን አለመቀበል (የተጎጂዎች ብቻ ሸክም ሊሆን አይገባም)፣ ከአስከፊ ሁኔታ ተሰደው ለሚሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ እንዲሁም ግድያ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ለማኮላሸት የተወሳሰበ አሰራር ያላቸው ሀይሎች በሀዋ-አየር-ውሃና-የብስ ጣልቃ ቢገቡ። በአጠቃላይ መተኮር ያለበት ድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ጣልቃ የመግባትን ግፊት በአዎንታዊም ሆነ አሉታዊ፤ በቀጥታም ሆነ በብዙ መንገዶች የመግደል ምንጮች ላይ ማዋል።

ከሂትለር መሰል ጉዳቶች ማግስት በተረፉት ሰዎች መካከል -ገዳዮች፣ ተጎጂዎች እና ቤተሰቦቻቸው -የሰውን ልጅ ያለመግደል ችሎታ በመፈለግ ለውጥን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ፖለቲካ ሳይንስ መስራት ያለበት አሰቃቂ ሁኔታ ላይ ያለ ሀላፊነትን የማወቅ፣ መልሶ የመገንበባት፣ የማግባባት ሂደትን መፍጠር በይበልጥ ደግሞ የማይገድል ማህበረሰብ በማይገድል አለም ውስጥ የሚለውን እውን ለማድረግ የሚጠቅሙ የሚከላከሉ መሰረታዊ ለውጦችን ማሳለጥ። ከመንፈስ፣ ከሳይንስና ከባህል ምንጮች በመነሳት አለመግደል ወደፊት ለሚኖሩ ማህበረሰቦች የባህል መገለጫና መኩሪያ ሆኖ ሊወደስ ይገባዋል። እንዲህ ያሉ አሰቃቂ ሁኔታዎች እንደገና እንዳይከሰቱ ተጨባጭ የሆነ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል።

በአሰቃቂ ሁኔታዎች በዘር ማጥፋትና በጦርነት የተሞላውን ዘመን ለመግታት ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የሚከተሉትን ሶስት የተግባር ሳይንስ ስራዎች መስራት ይጠበቅበታል፦ መከላከል፣ ጣልቃ መግባት እና ከጉዳት በኋላ የሚደረግ ያለመግደል ትራንስፎርሜሽን። እንዲህ አይነት አሰቃቂ ሁኔታዎች ከአለመግደል መመሪያዎች መወገድ አይችሉም ከሚል ዘወትር ከተለመደና ፈጠራን ከሚገታ አስተሳሰብ እራሱን ነጻ ማውጣት አለበት።

## አለመግደል እና በግጭት የተሞላ አብዮት

በሁለተኛ ደረጃ ትልቅ ችግር የሚባለው እና የችግር መፍታት ጥረት የሚያስፈልጋቸው ደግሞ በግጭት የተሞላ አብዮትና ፀረ-አብዮት ናቸው። ከዚህም ጋር የሚገናኙት ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስቶች፣ ፀረ-መፈንቅለ መንግስቶች፣ ሽብርተኝነት፣ ፀረ-ሽብርተኝነት፣ ሽምቅ ውጊያ እና በሰፊው የሚካሄድ የርስ በርስ ጦርነት። የተለመደው ፖለቲካ ሳይንስ እንዲህ አይነት አብዮቶችንና የሚደርስባቸውን ጭቆና የሚያየው ግጭትን በሚቀበል ግልጽ ያልሆነ አመለካከት ነው። መጥፎ መንግስታት ላይ ግጭት ማንሳት ተቀባይነት ሲኖረው ጥሩ መንግስታት ላይ ግን ተቀባይነት የለውም። መጥፎ አብዮተኞች ላይ ፀረ-ግጭት እንቅስቃሴ ተቀባይነት አለው ጥሩ አብዮተኞች ላይ ግን ተቀባይነት የለውም። ያም ሆነ ይህ ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣትም ሆነ መቃወም እጅግ ከባድ የሚመስል እና አብዛኛውን ጊዜ የሚያሽልም የፖለቲካዊ ህይወት እውነታ ነው። በአንዳንድ አሜሪካዊ ምሁሮች መሃል የሚነሱ የተለመዱ ክርክሮችን እንደምሳሌ ብናነሳ፦ በኢኮኖሚ የላቀ ደረጃ ላይ ያሉ በሰላም ሀብትና ስልጣንን ስለማይተዉ አብዮታዊ ግጭት ተገቢ ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ለግል ሀብት ብዝበዛ ሲሉ አመራርን ለመቀየር የሚፈልጉት ላይ ፀረ-ግጭት እርምጃ መውሰድን ይደግፋሉ። ሁልጊዜ ለአብዮት ገዳይነት መዘጋጀት የሚለው አስተሳሰብ በአሜሪካ ምርጫ ላይ የተመረኮዘ ዲሞክራሲ ባላት አገር እንኳን መኖሩን ቀጥሏል፤ አንዳንዶች ለግለሰቦች የጦር መሳሪያ እንዲይዙ መፍቀድ ነፃነትን በሀይል ከማጣት ለመከላከል ይጠቅማል ብለው ይከራከራሉ።

ነገር ግን ጨቋኝ የፖለቲካ አገዛዝን ማስወገድና መቋቋም የማይቻል የማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረታዊ ብጥብጥን መቀየር አስፈላጊ ነው ብንል ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ያለመግደል አብዮታዊ አማራጮችን ለይቶ በማውጣትና በማገዝ ይረዳናል። ይህም የሚፈልገው አብዮቶች የግድ በብጥብጥ የተሞሉ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ መፈተሽና

የሚሰሩ ያለመግደል አማራጮች ላይ እውቀት መስጠት ነው፦ መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ታክቲኮች፣ ድርጅታዊ ዘዴዎች እና ሞያዎችን መተግበር።

በቀዝቃዛው ጦርነት የመጨረሻ ክፍል ስለ አለመግደል አብዮት ተግባራዊነት ሶስት ተጠቃሽ የሆኑ እውነታዎች በፖለቲካ ምሁሮች የተነሱት ከሶስት በአለም ላይ ተሰሚነት ካላቸው አገሮች በብጥብጥ የተሞላ አብዮታዊ ባህል የላቸው፦ አሜሪካ፣ የሶቪየት ህብረት እና ቻይና ናቸው። ጂን ሻርፕ (1973) በአሜሪካ ያቀረበው ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበር ስለ ብጥብጥ አልባ ፖለቲካዊ አብዮቶች ሆኖ መሰረቱን በፖለቲካዊ አገዛዝና በብጥብጥ አልባ ትግል ውስጥ ሰፋ ያለ ታሪካዊ ዳሰሳ በተግባራዊ ብጥብጥ-አልባ ትግል ዙርያ ነበር። ሻርፕ በትንሹ 198 የብጥብጥ አልባ መተግበሪያ መንገዶችን ለይቶ አውጥቷል፦ ከተቃውሞና ማግባባት፣ ማህበረሰብ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ አለመተባበር እስከ ቀጥተኛ የሆነ ብጥብጥ አልባ ጣልቃ ገብነት። በመቀጠልም ሁሉንም በአንድ ላይ በማጣመር የብጥብጥ አልባ ትራንስፎርሜሽን ፅንሰ ሀሳብ “የመለወጥ፣ መቀበልና ማስገደድን” ሂደት በመጨመር ፈጠረ። ቆየት ብሎ ደግሞ “መፍረስ” የሚለውን ጨመረበት። በሶቭየት ህብረት ደግሞ ፒልማክ እና ካርያኪን (1979) አብዮትን ሲተነትኑ አገዛዝ ከአንደኛው የህብረተሰብ ክፍል ወደሌላኛው ሲሄድ “በሰፊው ህዝብ ህይወት ላይ ከፍተኛ ለውጥ” ሲያስከትል ነው። በመቀጠልም የተከራከሩት የማርክሲስት ሌኒኒስትን ፅንሰ-ሀሳብ በመመርኮዝና ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ ቅኝ አገዛዝን በማስቀረትና የዲሞክራሲ ልምድ በማዳበር ሰላማዊ ህብረተሰባዊ አብዮትን ማካሄድ ይቻላል። ሰላማዊ ህብረተሰባዊ አብዮትን ያብራሩት ደግሞ “መሳሪያ አልባ ትግል፣ ያለ እርስ በርስ ጦርነት እና በመሳርያ ያልተደገፈ ፀረ-አብዮት ጣልቃ ገብነት” ብለው ነው። ያለፉት ግድፈቶች በአዲስ ታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሰላማዊ አብዮትን ፍለጋ ላይ ማነቆ ሊሆኑ አይገባም ብለው ይከራከራሉ፤ አበክረው የሚናገሩትም “ሰላማዊ አብዮታዊ ልማት… ጥንቃቄ በተሞላበትና ወገናዊ ባልሆነ መንገድ በሁሉም መልኩ ሊጠና ይገባል” [የደራሲው ትርጉም]. በቻይና ዛንግ ዪ-ፒንግ (1981:79) ሃሳቡን በማርክሲስት ፅንሰ-ሀሳብና ስኬታማ በሆኑ በእሲያ፣ አፍሪካ እንዲሁም በላቲን አሜሪካ (በተለይም ህንድ ውስጥ በተካሄደ በጋንዲ ተከታዮች ህዝብን የማንቀሳቀስ ችሎታ) ስለ ብሄራዊ ነፃነት በተካሄዱ ብጥብጥ አልባ ትግሎች ላይ በመመርኮዝ የሚከራከረው፦ “ወገናዊ በሆነ መንገድ በብጥብጥ የተሞላ አብዮትን የሚደግፍ አመለካከት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን ሳያመዛዝንና ብጥብጥ አልባ አብዮትን የሚያወግዝ *በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ ስህተት ነው አተገባበር ላይ ደግሞ ጎጂ ነው”* [የደራሲው ትርጉም]።

ስለዚህ በዚህ በተወሳሰበ አለም አቀፍ አብዮታዊና ፀረ-አብዮታዊ ደም ማፍሰስ ከሶስት በብጥብጥ የተሞሉ ባህሎች የወጡ የፖለቲካ አዋቂዎች - እራሳቸውን የቻሉና እርስ በርስ የሚተዋወቁ የማይመስሉ - ያለመግደል አብዮትን ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበር በሳይንሳዊ መንገድ የማዳበርን ስራ ጀምረዋል። በአትኩሮት ሊታይ የሚገባው በጋራ ያነሱት ነጥብ ደግሞ በህንድ የጋንዲ ተከታዮች ያደረጉት ያለመግደል ንቅናቄ ፖለቲካዊ ነፃነትን ብቻ ሳይሆን የህብረተሰብ-ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ለውጥንም ያካተተ ነበር።

እስካሁን ድረስ ያለመግደል አብዮት ፅንሰ-ሀሳብ “ከካፒታሊስት” ወይም “ከሶሻሊስት” አመለካከት በሰፊው የሚታየው ከተጨቆኑት በኩል ነው። ባለመግደል የላቀ ደረጃ ላይ ያሉ ተነፃፃሪ ፅንሰ-ሀሳቦች ያለመግደል አብዮት እርምጃን ከብጥብጥ ጭቆና ውጭ ሌላ አማራጭ መንገድ አልተነደፈም። የሻርፒያንን ጥናት ተቃራኒ የጠቁማል። ሀብታም ባለንብረቶች፣ በዘር አብላጫነት ያላቸው፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ ፖሊሶች እና ወታደሮች ደሃውን፣ መሬት አልባውን፣ የተጨቆነ አናሳ ወይም አብላጫነት ያለውን ያለብጥብጥ ሰብአዊ መብትና ፍትህን የሚጠይቀውን ያለጭካኔና ያለመሳሪያ ለመጋፈጥ ወኔው አላቸው? የበላይነትን የተቀዳጁት ደግሞ ስለተነሳው የሰው ልጅ አክብሮትና እውቅና ጥያቄ ያላቸውን ቅራኔና የነሱን ሀሳብ ተቀባይነት ለማግኘትና ለማስገደድ ደም ሳይፈስ ማስፈፀም ይችላሉ?

ከዚህም አልፎ ተርፎ ስለ "ያለመግደል ትግል" እንደውም "ያለመግደል የመደብ ትግል" ሊተገበር የሚችል ፅንሰ-ሀሳብ ሆኖ በጨቋኝ/የበላይነት ያለው እና በተጨቋኝ/በየታች በሆነው ክፍሎች መካከል አዋጋቢ በሆነ ግንኙነት ላይ የሚንፀባረቅ የህብረተሰብ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ይህም በሰው ልጅ ውስጥ ያለመግደል ንዋረነገሮች በተፈጥሮ ተገኝተው ሊቀሰቀሱ የሚችሉና ሰላማዊ ለውጥ የሚፈልጉ ላይ የተነጣጠረ የታፈነ ጥላቻ ብጥብጥን ከሚደግፉ ክፍሎችና ከተቃዋሚዎቻቸው ይታያል። አያንዳንዱ ታጋይ ያለመግደል እርምጃዎችን የሚያፍነው እንዲህ ያሉ አመለካከቶች ለውጊያና ለመግደል ዝግጁነትን በራሳቸው የድጋፍ መደብ ያዳክማሉ በሚል አስተሳሰብ ነው። ለምሳሌ ያክል በቀዝቃዛው ጦርነት ፍጥጫ የአሜሪካና የሶቭየት የላቀ ደረጃ ላይ የሚገኙ ክፍሎችና እንዲሁም ሚዲያው ስለሰላም የሚያወሩ ድምፆችን በፍጥነት አፍነው ያለመግደል ሀሳብ የመቀበልን ምላሾችን ይቀሰቅስና ለራሳቸው ወታደራዊ ሀይል የሚሰጠውን ድጋፍ ያሳንሳል የሚል አመለካከት ስለያዙ - ተቃዋሚዎቻቸውን የሚያደክሙ ስላልመሰላቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሩትና የታጣቂ ንቅናቄዎች ደጋፊ ያለመግደል አብዮታዊ አማራጮችን መፈተሽን ለማውገዝ ይቸኩላሉ ምክኒያቱም የተጨቆኑት ያለመግደል አማራጮችን ይቀበላሉ ብለው ስለሚፈሩ ነው። ስለዚህ ያለመግደል መርሆዎችን መቀበልና መተግበር በጨቋኝም በተጨቋኝም በኩል ከኖረ ያለመግደል መንገድን የያዘ የመደብ ሽኩቻ የሚታሰብ ይሆናል። ይህም የሚያመላክተው ፖለቲካ ሳይንስ ያለመግደል አብዮታዊ ችግር መፍቻ ሂደቶችን ማሳለጥን መተግበሩን ነው። ውጤታማነቱ የታየ እርቅ ላይ ያተኮረና የመጨረሻ ግቡን እርቅ ያደረገ ነገር ግን ለሚደረገው ያለመግደል ትግል የጋንዲንና የኪንግያንን መሰል መንገዶች በመጠቀም ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት በየደረጃው ተቃውሞ ገጥሞታል። ማኪያቬሊም የተከራከረው በፖለቲካዊ አገዛዝ ይህ ነው የሚባሉ ለውጦች "ከአምባገነን ወደ ነፃነት" እንዲሁም ተገላቢጦሹ "ያለ ደም መፋሰስ" ሊገኝ የሚችለው " ሀገሪቷን ትልቅ ደረጃ ባደረሷት ህዝቦች አጠቃላይ ስምምነት" ከተፈፀመ ነው። (ዘ ዲሰኮርስስ መጽሀፍ 3 ምዕራፍ 7)

### ያለመግደልና ደህንነት

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ሊፈታው የሚገባ ችግር በግድያ የተሞላን ወረራ በግለሰብ፣ በሀገር ውስጥ፣ በብሄራዊና በአለማቀፍ ደረጃ ተአማኒነት ያላቸው የደህንነት አማራጮችን መፈለግ ነው። የተለመደ የደህንነት ፅንሰ-ሀሳብና ትግባር በስተመጨረሻ የሚነሳው ሞትን ከሚያስከትሉ ነገሮች በሚመጣ አደጋ ነው፦ "እኔ/እኛ በእርግጠኝነት እንድታምኑት የምንፈልገው እኔ/እኛ እገድላችኃለሁ/እንገድላችኋለን።" ያለመግደል ደህንነት ግን ይህንን መርህ ይፃረራል ፦ "እኔ/እኛ በእርግጠኝነት እንድታምኑት የምንፈልገው እኔ/እኛ አልገድላችሁም/አንገድላችሁም። እናንተም ለኛ በእርግጠኝነት ልታሳምኑን የሚገባው እኔን/እኛን እንደማትገድሉኝ/እንደማትገድሉን ነው።" ባጭሩ "እኛ በእርግጠኝነት እርስ በርሳችን ልንተማመን የሚገባው እንደማንገድል ነው።"

ማንም ሰው ሌላ ሰው ሊገድለው እየፈለገ ደህንነት ሊሰማው አይችልም። የመግደል ጉብዝና ማንኛውንም መከላከያ ከጋሻ፣ እቃጦር፣ ምሽግ፣ ግድግዳና ግንብ እስከ አውቶሚክ ቦንብ መጠለያ ድረስ ያሸንፋል። ጥቃታዊ ግድያ የትኛውንም አይነት የግድያ መከላከያ ያሸንፋል፦ ፍላፃ ጦርን፣ አውቶማቲክ መሳርያ ጠብመንጃን፣ ታጣቂ ክፍለጦር እግረኛ ክፍለጦርን፣ ታንኮች ፈረሰኞችን፣ ሮኬቶች ታንኮችን፣ ባህር ሰርጓጆች የጦር መርከቦችን፣ የአየርና የሚሳኤል ሀይሎች አሉ የተባሉ ነገሮችን፣ የኒውክሊር ባዮሎጂካል እና ኬሚካል መሳርያዎች ደግሞ ሁሉንም መሳርያዎች። በመሳርያ የተሞላ ቤት ውስጥ መኖር ደህንነትን አያረጋግጥም፦ ሰርጎ ገቡ እቃጦርን የሚቀድ ሚሳኤል፣ ከባድ መሣርያዎችና የተሻለ የትግል ችሎታ ሊኖረው ይችላል ወይም ደግሞ አየርን፣ ምግብንና የውሃ ማከፋፈያውን መመረዝ ይችል የሆናል። ብቸኛውና እርግጠኛ ደህንነት የመግደል ፍላጎት አለመኖር ነው።

ግድያ ወደሌለበት ደህንነት ለመሸጋገር የፖለቲካ ሳይንስ ሚና አደጋን ወይም የሚገድል ሀይልን ለመፃረር የሚረዳ ተአማኒ አማራጭ ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበርን ማዳበር ነው። ይህም የሚያጠቃልለው በተቃራኒዎች መሃል የመገዳደል ፍላጎትን ግድያ ወደሌለበት ማሸጋገር ነው። ይሁን እንጂ በተለመደው ፖለቲካ ሳይንስ ውስጥ ጎልቶ ባይታይም የተለያዩ መጣጥፍት እንዲሁም ተሞክሮዎች ከየት መጀመር እንዳለበት መነሻውን ያመላክቱናል። ጥናቶቹም ከሚያጠቃልሏቸው መሀል የናዚ ዘር ማጥፋት ላይ የተደረገው የህዝብ ተቃውሞ ላይ የነበረው ምርመራ (ሄሊ 1979፣ ፎግልማን 1994፣ ሴሜሊን 1994)፣ የዳኒሎ ዶልቺ የማፍያ ወንጀል ላይ የተደረገ ያለመግደል ማህበረሰባዊ ተቃውሞ (አማቶ 1979፣ ቾውዱሪ 1998)፣ ያልታጠቁ ጠባቂዎች ለሰብአዊ መብት ሰራተኞች (ማሆኒ እና ኢጉረን 1997)፣ ለወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ያለመግደል ተቃውሞ (ሮበርትስ 1975፣ ሻርፕ 1990፣ 1993)፣ ያለመግደል ብሄራዊ ሲቪላዊና ህብረተሰባዊ መከላከል (ቦሰርአፕ እና ማክ 1974፣ ሻርፕ 1990፣ ማርቲን 1991፣ ራንድል 1993፣ ቡሮውስ 1996)፣ የተለመዱ ወታደራዊ ሀይሎችን በማይገድል መልኩ መጠቀም (ኪይስ 1982)፣ አማራጭ ያለመግደል ሀይሎች (ባነርጂ 2000፣ ቄበር 1996፣ ሞሰር ፑዋንግሱዋን እና ቄበር 2000) እና ሞትን የማያስከትሉ መሳርያዎች መፈጠር (ሊወር እና ሺፎልድ 1997)።

የተወሰኑ መንግስታት የማይገድል ሲቪላዊ መከላከያ አዋጪነት አለው ወይ በሚል ጥናት አካሂደው ነበር ነገር ግን የተለመደውን የወታደራዊ መንገድ እንዲያግዝ ብቻ ነበር። እነዚህም ስዊድን፣ ኖርዌይ፣ ዴንማርክ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፈረንሳይ፣ ላቲቪያ፣ ሊትዌኒያ፣ ኢስቶኒያ፣ ኦስትሪያ፣ ስዊዘርላንድና ፊንላንድ ናቸው። (ሽሚድ 1985፣ ሻርፕ 1990፣ ራንድል 1994: 121-37) በታይላንድ ደግሞ ለየት ያለ ቀድሞ የወጣ ደንብ በአዲሱ የ1997 የታይ ህገመንግስት ውስጥ አንቀፅ 65 ላይ ተቀባይነት ስላለው ያለመግደል ተቃውሞ ወደፊት ሊደረጉ የሚችሉን ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስቶች ተቀባይነት ባለው አለመግደል ስለመቃወም "ህዝቦች ምንም አይነት አስተዳደራዊ ስልጣንን ህገመንግስቱ ላይ ባልተጠቀሰ መንገድ ሊይዙ የሚሞክሩ ሀይሎችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመቃወም መብት አላቸው።

የማይገድሉ መሣርያዎች ለፖሊስና ለጦር ሀይል ጥቅም እንዲውሉ በአሜሪካ ውስጥ ከ1965 ጀምሮ ጥናት ተደርጎ በ1990ዎቹ ደግሞ ይህ ጥናት ተጠናክሮ ነበር። ሰፋ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ተጠንተው ነበር፦ ጨረር፣ ኦፕቲክ፣ አኮውስቲክ፣ ኤሌክትሮማግኔቲክ ፐልስ፣ ኬሚካል፣ ባዮሎጂካልና በብዙዎች የሚቆጠሩ ሌላ መሣርያዎችም ነበሩ። አንዳንዶቹ በፖሊስና በውጭ ሀገር የጦር ዘመቻ ላይ ጠቀሜታ ላይ ውለዋል (ሊወር እና ሾፌልድ 1997)። የህብረተሰብ መከላከል ላይ መንግስት እንዳለው አመለካከት የማይገድሉ መሣርያዎችም በአሁኑ ጊዜ የሚታዩት የተለመደ የመግደል አቅምን እንዲደግፉ ነው። ነገር ግን ያለመግደል አማራጮች በብጥብጥ ደህንነት ውስጥ ባሉ ባህላዊ ባለሙያዎች በጥሞና በመታየታቸው ፖለቲካ ሳይንስ ከዚህ ያላነሰ ጥሞናና በይበልጥ የላቀ አጠቃላይ ጥረት ሊያደርግ ይገባል። ፈተና የሚሆነውም ፍፁም ወደማይገድል ደህንነት መሸጋገርያ ላይ ያሉ ችግሮችን መፍታት ነው። ሌላ ወደማይገድል ደህንነት ያለውን እንቅስቃሴ የሚጠቁም ምልክት በካርኔዥ ኮሚሽን በግድያ የተሞላ ግጭትን መገደብ (1997) የመጨረሻ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃሏል። ይህም የሚለው "መሰረታዊ የሆነ መገደብ፦ በግድያ የተሞላ ግጭትን ምክኒያት ከመሰረቱ ለመፍታት ስልት መንደፍ" እንዲሁም "የመገደብን ባህል" መፍጠር። ወደ አለመግደል እርምጃ መውሰድና ግለሰብና አለምአቀፍ ደህንነት በውስጠ-ታዋቂነት ይኖራል።

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ እስካሁን የማይገድል ማህበረሰብን ለመፍጠር ሊታለፉ የማይቻሉ የተባሉ እንቅፋቶችን ለማለፍ ችግሮችን ለመፍታት መሞከር አለበት። በኃይል የመጥፋትን ቀጥተኛ አደጋ ማሸነፍ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ምክኒያቱም በመጀመርያ ደረጃ መኖር ከሌለ ምንም አይነት ችግር ሊፈታ አይችልም። ሁለተኛ ደግሞ

ለመግደል ዘላቂነት ያለው ቁርጠኝነት የግለሰብ፣ የህብረተሰብና የአለማችንን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መሰረታዊና ኢኮሎጂያዊ ሁኔታዎችን ያግዛል።

ያለመግደል እንደ ህብረተሰባዊ ችግር መፍቻ ትኩረት ተደርጎበት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይጋፈጣል፦ ለምን ያለመግደል ላይ አትኩሮት እናደርጋለን በአሁን ጊዜ ስነልቦናዊ ጥቃት፣ ስቃይ፣ ዘረኝነት፣ ፆታዊ አድልዎ፣ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና አምባገነንነት ሞትን የሚያስከትሉ ቁሰ-አካሎች ይበልጥ ስቃይና ሞት እያስከተሉ ነውና። እነዚህ ጥያቄዎች የሚያመላክቱት እንዲህ ያሉ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት የመግደል አማራጭን እንደ አማራጭ ይዘን ከቀጠልን ነው። አንድ መልስ ሊሆን የሚችለው የመግደል ፍላጎት፣ ችሎታና፣ ባህል የህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረታዊ በደሎች ዋነኛ ምክኒያት መሆኑ ነው። ታድያ ጥቃት፣ ማሰቃየት፣ ዘረኝነት፣ የሴቶች ጭቆና፣ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና አምባገነንነት በፍርሀትና በሞት ማስፈራርያነት ላይ ካልተመሰረቱ እንዴት ማቆየት ይቻላል? መግደልን ከግድያ ወንጀል በመቅረፍ ወደ ጦርነት ውስጥ መክተት ለሰው ልጅ ተሞክሮ በከፍተኛ ደረጃ አስተዋፅኦ አለው፦ መንፈሳዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ቁሳዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም አካባቢያዊ በሆነ መልኩ የሰው ልጅን በሌላ በኩል የሚገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳል።

ላለመግደል ቁርጠኛ መሆን የሚያመላክተው ፖለቲካ ሳይንስ በየዘመኑ የሚፈጠረውን የሰው ልጅ ደህንነትና መኖር አደጋ ላይ የሚጥሉ ችግሮችን ለመፍታት እገዛ በማድረግ መጠመዱን ነው። ጋንዲ በየመንደሮቹ ሲያናግራቸው ዋነኛ የችግር መፍቻ ተግባሮችን የግራ እጅ ጣቶቹን እያጠፈ፦ ለማይነኩት እኩልነት፣ ለኢኮኖሚያዊ ነፃነት ራስን የቻለ ጥጥ ፈተላ፣ ከአደንዛዥ ዕፅና አልኮል መታቀብ፣ የሂንዱና የሙስሊሞች ጓደኝነት እና የሴቶች እኩልነት ብሎ ይዘረዝርላቸውና “እጁ ደግሞ ብጥብጥ አልባነትን ያሳያል” ይላል (አሽ 1969: 243)። በተመሳሳይ መንገድ አሁን በአለማችን እየጎሉ የመጡ አምስት ችግሮችን ማየት እንችላለን፦ ቀጣይነት ያለው ግድያና የመሳርያ ቅነሳ ማስፈለግ፣ ድህነት የሚያደርሰው እልቂትና የኢኮኖሚያዊ እኩልነት ማስፈለግ፣ የሰው ልጅ ክብር መዋረድና እርስ በርስ የሰብአዊ መብት ማክበር ማስ ፈለግ፣ አለማችንን መጉዳትና ለአለማችን የህይወት ድጋፍ ማስፈለግ እንዲሁም ሌላ የችግር መፍታት ትብብሩን ወደኋላ የሚያስቀሩ ለእጦት የሚደርጉ መከፋፈሎች ናቸው፡፡

እነዚህ አምስት ችግሮች ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ ፣ለማህበረሰብ ፣ለህዝብ እና በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ሁሉ የተለመዱ ናቸው። ሁላችንም ከመግደል ነፃ መውጣት እንፈልጋለን፣ እንዲሁም ከኦኮኖሚያዊ እጦት፣ ክብርን ከመነፈግ፣ ከተመረዘ አካባቢ እና እነኝህንና ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት ካለመተባበር፡፡ እነኝህ ችግሮች የተያያዙ ሲሆኑ ግድያን እንደዋነኛ ችግር ፈቺ አድርገን ለረዥም ጊዜ መጠቀማችን ደግሞ ችግሩ እንዲባባስ አድርጎታል፡፡ ደህንነትን ለማግኘት የምንሞክረው በመግደልና ለመግደል በማስታጠቅ፣ ፀረ-ግዲያ ስጋቶችን በመፍጠር፣ ለመግደል ማስታጠቅ ለኢኮኖሚያዊ እጦት ከመዳረጉም በላይ መሰረታዊ በደልን ያጠናክራል፣ ሰብአዊ መብትን ለመንፈግ የሚደረግ ግዲያ ለረዥም ጊዜ የታፈነ በበቀል የተሞላ ጥላቻ አስተዋፅኦ ያደርጋል፣ ግዲያ የተሞላበት ውጊያና የጦር ኢንዱስትሪያላይዜሽን አካባቢያችንን ይጎዳል፣ በፍርሃት የተሞላ የጥላቻ ክፍፍል ለሁሉም ጠቃሚ የሆነ የችግር መፍታት ትብብርን ወደ ኋላ ያስቀራል፡፡

ያለመግደል ችግር የሚያመላክተው ግድያን መቃረንን ብቻ ሳይሆን ፍላጎትን የማሟላት ለወጥ ላይ ገንቢ የሆነ ተሳትፎንም ያካትታል፡፡ ይህም ማለት ግልፅ በሆነ ሁኔታ ጦርነትና ማሳሪያዎቹን ማጥፋት፣ ድህነትን ማጥፋት፣ መብትና ግዴታዎችን ባለመግደል መግለፅና የችግር መፍታት ሂደቶች ላይ አስተዋፅኦ በማድረግ ለሰዎች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥና ግለሰቦችና በአጠቃላይ የሰው ልጆችን ማለቂያ የሌለው የፈጠራ ችሎታን መቀስቀስ ነው፡፡

እንደዚህ አይነት አጀንዳ የማይታሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ብዙ ተሞክሮ ባላቸው ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም የዚህ ዘመን

የሲቪል ማህበረሰብ መሪዎች የተተውልን ናቸው (የጥንት ሰዎች ስለ አዲሱ ዘመን የነበራቸውን ጭንቀት በማስተጋባት)። ፖለቲካ ሳይንቲስቶች ሊያዩት የሚገባ በጣም ጠቃሚ ነገር ቢኖር እያንዳንዱ ትልቅ በተባበሩት መንግስታት ወይንም ሌላ አካል የተዘጋጀ ችግር የመፍታት ኮንፈረንስ የሚያደርገው የአለምን ህዝብ በሙሉ አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን ለማምጣት "የፖለቲካ ፍላጎት" ለመፍጠር እንዲያግዙ ጥሪ ማድረግ ነው። ጥሪውም ለመንግሥታት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ችግር የመፍታት ስራ ምንጮች፦ ፓርቲዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኮርፖሬሽኖች ህብረቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሚዲያዎች፣ ሃይማኖቶች እና ጥበቦች ነው። ለህይወት አስጊ አለም አቀፍ ችግሮች እየተጠናከሩ ሲመጡና አሁን እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት ወደፊት ስለሚመጣው አስጊ ሁኔታ ያለ ንቃት እየጨመረ ሲመጣ በአፋጣኝ የማስፈፀም ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል። ይህም የሚያካትተው የመሳሪያዎች መብዛት፣ በፍጥነት የሚያድግ የህዝብ ቁጥር እየሰፋ ከመጣ የኢኮኖሚያዊ ልዩነት ጋር ተደርቦ በህዝቦች ውስጥና መሃል ቁሳዊና ስነ–ልቦናዊ መቻቻልን የማፍረስ አደጋ፣ ተፈጥሮ የሰጠችውን ፀጋ ገደብ የለሽ በሆነ መልኩ በኢንዱስትሪና በእርሻ በመበዝበዝ ለህይወት አስጊ ሁኔታ ማስከተል፣ ስለ እኩል ተሳትፎ የሚደረጉ ጥያቄዎችን ለማክበር እራስን ማሸነፍ አለመቻልና ጥራት ያለው ህይወት ለሁሉም የሚለውን በመቀበል ለሴቶች፣ ለህገር ተወላጅ፣ ለተጨቆኑ አናሳ ክፍሎች እና ብዛት ያለው ባህላዊ መገለጫዎች ላሏቸው መተግበር። ስለ አለማችን ሁኔታ እውቀት ላላቸው ይህ ዘመን "ሁሌ እንደተለመደው ያለሆነበት" (No business as usual) ነው። እንደ ፍሬድኮ ሜየር የ UNESCO ዳይሬክተር) አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ደግሞ ለየት ያለ አንድ ሀገርና ግዛት የሚል አቋም አላችዉ ስለዚህ ለፖለቲካ ሳይንስ ብዙ አስቸኳይ ያልሆነ ሊሆን ይገባልን?

## አለመግደልና መሣሪያ ቅነሳ

ሊፈቱ የሚፈለጉት ችግሮችም ሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተነሱት ያለመግደል ንቅናቄዎች የትምህርታዊ ፖለቲካ ሳይንስ ፈጠራዎች አይደሉም። የቀረቡት በዘመናዊ አለም አቀፍ ፖለቲካዊ ህይወት ነው። ፖለቲካ ሳይንስ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ቁርጠኛ አቋም መውሰድ አለበት። ግልፅ የሆነ የችግር መፍቻን መቋቋሚያ ተግባር የመጀመሪያው የተባበሩት መንግሥታት አጠቃላይ ጉባኤ በመሣሪያ ቅነሳ ላይ ባካሄደው ልዩ ስብሰባ (UN General Assembly 1978) ተጠናክሮ የወጣው ሪፖርት ውስጥ እንደተካተተው "አጠቃላይና ፍፁም የሆነ የመሣሪያ ቅነሳ ውጤታማ በሆነ አለም አቀፍ ተቆጣጣሪ" አስፈላጊ ነው ብሏል። በ159 ሀገሮች ስምምነትና በአልባንያ ድምፀ ታቅቦ የፀደቀው ሁሉም አይነት የነውክለር መሣሪያ መወገድ እንዳለበት፤ ሁሉም ባዮኬሚካል መሣሪያ መወገድ እንዳለበት፤ እንዲሁም ሁሉም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያም መወገድ እንዳለበት፤ በውጪ ሀገር ከሚገኙ ወታደራዊ ካምፖች መውጣት፤ ታጣቂ ሀይሎችን ለወሰን መከላከያ ብቻ እንዲበቃ አድርጎ መቀነስ፤ የተለመዱ መሣሪያዎችን መቀነስ፤ አለም አቀፍ የጦር ወጪዎችን በማቆም የሰው ሃይልና ማቴሪያልን ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰባዊ ፍላጎቶችና ወደ ማሟላት ማሸጋሸግ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ተያያዥነት ያላቸው ረቂቅ ሃሳቦችም ፀድቀዋል። ይህ በሰፊው ብጥብጥን የሚያራምዱ ሀገራት ወደ አለመግደል ለመሸጋገር የሚያደርጉት ጥሪ ቢሆንም በአብዛኛው የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪዎች አይታወቅም።

ያለመግደል ፖለተካ ሳይንስ ግን መሳሪያ አልባ ህብረተሰቦችን ለመመስረት ቃል በሚገቡ መንግስታዊና ሲቪል ማህበራት ከሚደረጉበት ጥረቶች መራቅ የለበትም፡፡ ከእነዚህም መኃል ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉትን ለማገድ የሚደረግ ዘመቻ፦ ሽጉጦች፣ የማጥቂያ መሳሪያዎች፣ ፈንጂዎች እና የመሳሪ ሽያጭ። እንዲሁም መሳሪያ አልባ የሰላም ቀጠና በየመንደሩና በየከተሞች መመስረትና የኒውክለር መሳሪያ አልባ ክፍለ አለም መፍጠር፡፡

## ያለመግደልና ኢኮኖሚያዊ እጦት

ደግሞ ሌላ ችግርን ለመፍታት የሚደረግ መፍጨርጭር በ53 ከኬምስትሪ እስከ ፊዚክስ የተወጣጡ የኖቤል ሽልማት ሎሬቶች ያወጡት "ማኒፌስቶ" ነው፡፡ ይህም አለም አቀፋዊ የሆነ እልቂት ያሉት ሊገታ በሚችል ኢኮኖሚያዊ እጦት ምክኒያት የሚያልቁትን ሰዎች ለመታደግ ጥሪ አቅርበዋል (Nobel Prize Winners 1981: 61-3)፡፡ የገለፁትም "የሰው ልጆችን እልቂት የሚያወግዙና የሚዋጉ በሙሉ በአንድ ድምፅ የሚስማሙበት ነገር ቢኖር የዚህ አሳዛኝ ክስተት ምክኒያት ፖለቲካዊ ጉዳይ እንደሆነ ነው፡፡"

> በጣም አስፈላጊው ነገር ማንኛውም ዜጋና ፖለቲከኛ ያደራጃቸው በምርጫ ላይ፣ ፓርላማ ውስጥ፣ አዲስ በጀት ላይ፣ አዲስ ፕሮጀክት ላይ እንዲሁም በቢሊዎኖች የሚቆጠሩ ህዝቦችን ከምግብ እጥረትና አለማደግ እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በየትውልዱ በርሃብ የሚያልቁትን ለመታደግ የሚነደፉ አዳዲስ እርምጃዎች ላይ መምረጥና ድምፅ መስጠት አለባቸው፡፡ (62)

"በህይወት ያሉትን ለመኖር መፈለግ፣ ግድያ አለመፈፀምና አለመጥፋት፣ እርምጃ አለመውሰድ ወይም ግድ አለመስጠት" በማለት ለውጥን የሚያስከትል ያለመግደል ኢኮኖሚያዊ አብዮት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፦

> የዚህ አለም ኃያላን ከሁሉም የለቀ ሀላፊነት ቢኖርባቸውም በነሱ ላይ ብቻ አይጣልም። ደካሞች የራሳቸውን እድል በእጃቸው ቢይዙ፣ በዛ ያለ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ከዋነኛ የሰብአዊ መብት ጋር የተያያዘ ህግ ካልሆነ በቀር አልታዘዝ ቢሉ የሁሉም መሰረት የሆነው ህግ ደግሞ የመኖር መብት ነው፣ ደካሞች እራሳቸውን አደራጅተው ጥቂት ነገር ግን ኃይለኛ መሳሪያዎችን ቢጠቀሙ፦ በጋንዲ የተፈፀመው አይነት ብጥብጥ አልባ ተግባሮች፣ የተወሰኑና ተገቢ የሆኑ ግቦችን ተቀብሎ ማስፈፀም፦ እነዚህ ነገሮች ቢተገበሩ በዘመናችን ያለውን አስጊ ሁኔታ መግታት ይቻላል፡፡(63)

> የሚያጠናቅቁትም "አሁን ጊዜው የመስሪያ ነው፣ አሁን ጊዜው የፈጠራ ነው፣ አሁን ጊዜው የኛ አኗኗር ለሌሎች ህይወትን በሚሰጥ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡"

የእኩልነት አለመኖር፣ ህዝብ ቁጥር ማደግ እና ጦርን ማዘጋጀት አንድ ላይ ለኢኮኖሚ መሞት፣ ለብጥብጥና ለአካባቢ መጥፋት መባበስ ያግዛል፡፡ በ1999 የአለም ባንክ የገመተው እስከ 1.5 ቢሊየን ሰዎች "በፍፁም ድህነት" ውስጥ እየኖሩ ነው ተብለው የተፈረጁት በቀን ከአንድ የአሜሪካ ዶላር በታች የሚያገኙትን ሲሆን፤ ሶስት ቢሊዮኖች ደግሞ በቀን ከሁለት የአሜሪካ ዶላር በታች የሚያገኙትን ነው፡፡ በህንድ ውስጥ ብቻ ፍፁም ድሀ የሚባሉት በ1980ዎቹ መጨረሻ ከ300 ሚሊዮን በ40 ሚሊዮን በመጨመር 340 ሚሊዮን እንደደረሱ ይገመታል (World Bank 1999)። አብሮ ደግሞ የገቢ እኩልነት አለመኖር ይጨምራል፡፡ የወርልድ ባንኩ ታሪክ ሁሴን በሰኔ 1997 በመጀመሪያው የተባበሩት መንግስታት ዩኒቨርሲቲ አለም አቀፍ የአመራር አካዳሚ ውስጥ ለነበሩ 160 ወጣት መሪዎች እንደሚከተለው አጠቃሎታል፦

> አለማች በመካከለኛው 1990ዎች ….. በይበልጥ ከ1980ዎቹ ልዩነቶች የሰፉ ነበሩ …. እጅግ የደኸዩት 20% የአለም ህዝቦች ባለፊት 30 ዓመታት ገቢያቸው እያዩት ከ2.3% ወደ 1.4% አሽቆልቁሏል። ይህ በእንዲህ እዳለ እጅግ ኃብታም ለሆኑት ደግሞ ከ70% ወደ 85% አድጓል። ስለዚህ የኃብታምና የድሀ ድርሻ ከ30:1 ወደ 61:1 በእጥፍ አድጓል። የአለም 360 ቢሊየነሮች ኃብት አንድ ላይ ተጣምሮ ቢታይ 45% የአለም ህዝብ ከሚኖርባቸው ሀገሮች ጥምር አመታዊ ገቢ ይበልጣል (Hussain 1997: 13)

የአለም ባንክ ፕሬዝዳንት ጀምስ ዲ. ውልፈንሰን እና ማህታማ ጋንዲ የእኩልነት አለመኖር ለብጥብጥ እንደሚዳርግ ይስማማሉ። ፕሬዝዳንቱ ሚለውም “የእኩልነት አለመኖር ለአለመረጋጋት ይዳርጋል። ድህነት ጦርነትን ይወልዳል።” (Hussain 1997:6) ማህተማ እዳስጠነቀቀው “ብጥብጥ አልባ መንግስተ-ስርአት የማሆይን ነገር እደሆነ ግልፅ ነው ስዚህ በኃበታምና በሚሊዬኖች በሚቆጠሩ ረሀብተኞች መሀል ያለው ሰፊ ባህረ-ሰላጤ እስከቀጠለ ድረስ …… በውዴታቸው ሀብታቸውንና በኃብት የሚመጣን ስልጣን አሳልፈው ካልሰጡና ለሁሉም ጥቅም እዲውል ካላደረጉ ሀይለኛ ደም መፋሰስ የበዛበት አብዮት የማይቀር ይሆናል።” (Collected Works 75 (1941):158) የፕሬዝዳንቱንና የማህተማውን ሃሳብ በማጣመር ወጣት አሜሪካዊት የሰላም ሠራተኛ ቤትሲ ዱረን ከወረሰችው ሀብት አብዛኛውን አሣልፋ ሰጥታለች። እሷም የምትለው “ዘላቂነት ያለው ሰላም ልናገኝ የምንችው ሀብትን መልሰን በማከፋፈል ብቻ ነው። ድህነት፣ ጦርነትና ስቃይ የሚመጣው ከሚገባቸው በላይ ያላቸው ሰዎች ያላቸው እዳያመልጣቸው በሚያደርጉት ጥረት ነው።” (Mogil and Slepian 1992: 100) የፕሬዝዳቱ፣ የማህተማውና የወጣትዋ አሜሪካዊት አመለካት የሚያስተጋባው አሪስቶትል ከ2,300 አመታት በፊት በእልነት አለመኖርና ለሞት በሚዳርጉ ነገሮች መካከል ያለውን ግኙነት በተመለከተ ያደረገውን ትንታኔ ነው።

> ዋናው ሊታወስ የሚገባው ነገር ስልጣንን የመስጠት ሃላፊነት ያለባቸው ገለሰቦችም ይሁኑ የመንግስት ወይም የጎሣ አባላት ወይም የመሳሰሉት ትልቅም ይሁን ትንሽ፤ ወደ አብዮት የሚያመራውን ረብሻ ሊያስነሱ የሚችሉ እነርሱ ናቸው። መነሾ ሊሆኑ የሚችሉት በተዘዋዋሪ ሊሆን ይችላል፤ ይም የሚሆነው ሌሎች እነሱ ባላቸው ስልጣን ቀንተው አብዮት ሲያስነሱ ሲሆን፤ በቀጥታ ደግሞ መንስኤ የሚሆኑት እነርሱ ራሳቸው ከፍተኛ የሆነ የበላይት ተሰምቷቸው ከሌሎች ጋር በእኩልነት መኖራቸው አላረካ ሲላቸው ነው። (Aristotle 1962፡ 199)

የአለም የህዝብ ቁጥር በ1950 2.5 ቢሊዮን የነበረው በ2000 6.1 ቢሊዮን ተብሎ ተገምቷል በ2050 ደግሞ 8.9 ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ይህ የአለም የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር የአለመግደል ችግር መፍታት ላይ የሚደረገውን ጥረት ፈተና ውስጥ ይከታል። በ2050 ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር የኖራቸዋል ተብለው የሚጠበቁት ሀገሮች ህንድ (1,529,000,000)፣ ቻይና (1,478,000,000)፣ አሜሪካ (349,000,000)፣ ፓኪስታን (345,000,000) እና ኢንዶኔዥያ (321,000,000) ናቸው። በሌስተር አር ብራውንና በወርልድዎች ኢንስትቲውት የስራ ባልደረቦቹ ተጠንቶ እንደተተነተነው እንዲህ ያለ ያልተጠበቀ በየዓመቱ 80 ሚሊዮን ያክል የህዝብ ጭማሪ የአለማችንን ህይወት የማኖር አቅም አስጊ ሁኔታ ላይ ይጥላል። ከአስራ ዘጠኝ ሊያሰጉን ከሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፦ የውሀ አቅርቦት፣ የሰብል ምርት፣ ኃይል፣ የሚታረስ መሬት፣ ደን፣ የተለያዩ እፅዋትና እንስሳት፣ የአየር ለውጥ፣ በሽታ፣ መከተም፣ ቤት መስራት፣ ትምህርት፣ ስራ እና በሀገር ውስጥና በሀገራት መካከል የሚነሳ ጠብ። (Brown, Gardner and Haliweil 1999)

የተለመዱ የህዝብ ቅነሳ የሚያስከትሉ የግድያ መንገዶች ለምሳሌ ያክል ጦርነት፣ ዘር ማጥፋት፣ ህፃናትን መግደል፣ ማስወረድ እዲሁም ረሀብና ወረርሺኝ የሚፈለጉ ስላልሆኑ ያለመግደል ፓለቲካ ሳይንስ የሚገጥመው ፈተና ያመግደል አማራጮችን ግኝትና አፈፃፀም መደገፍ ይሆናል። ይህም ማለት በፖለቲካዊ ፅንሠ-ሀሳብና በኢኮኖሚያዊ ችግር መፍታት ትግበራ መሀል ለሰው ልጅ ህይወት ጥራትና ህይወትን ለሚደግፈው አካባቢያችን ያለንን ከበሬታ ማስቀመጥ ነው።

አንዳንድ እጅግ የታወቁ የአለማችን የጦር መሪዎችና በመግደል ባለሙያ የሆኑ ሰዎች ኢኮኖሚያዊ የጦር ማስወገድ ማስፈለጉን በተመለከተ ከፍተኛ የሆነ ማስተዋል አሳይተዋል። ከነዚህም ተጠቃሽ የሚባለው የሁለተኛው የአለም ጦርነት ላይ ጀነራል የነበረውና የአሜሪካ ፕሬዝዳት የሆነው ድዋይት ዲ አይዘንሀወር ነው (1953—1961)። ማንኛውም የሰላም ደጋፊ እርሱ ለመግደል ባለ ቁርጠኝነትና በኢኮኖሚያዊ መሰረታዊ ብጥብጥ መሃል ያለውን ግኙነት

በተመለከተ ያቀረበውን ያልተንዛዛ ነገር ግን ኃይለኛ ትንተና የትኛውም የሰላም ደጋፊ እስካሁን አልበለጠውም፦

> እያንዳዱ የሚሰራ ሽጉጥ፣ እያንዳዱ የሚላክ የጦር መርከብ፣ እያንዳንዱ የሚተኮስ ሮኬት ባጠቃላይ ሲታይ እየተራቡ ካልተመገቡ እየታረዙ ካልለበሱት ላይ እንደማስረቅ ነው። ይህ የታጠቀው አለም እያባከነ ያለው ገንዘብ ብቻ አይደለም። እያባከነ ያለው የጉልበት የሰራተኞቹን ላብ ነው፣ የሳይንቲስቶቹን እውቀት ነው፣ እንዲሁም የህፃናቶቹን ተስፋ ነው። … ይህ በምንም መልኩ የአኗኗር ዘዮ አይደለም። በአስጊ ጦርነት ደመና ስር ስብእና በብረት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ነው ያለው። (Address to the American Society of Newspaper Editors, April 16, 1953)

ለስብእና "በብረት መስቀል ላይ መሰቀል" አንዱ ምክኒያት የተደረገው ስርቆት በአሜሪካ የኒውክር መሳሪያ ፕሮግራም ከ1940—1996 በገንዘብ ሲተመን 5,821 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነበር (Schwartz 1998)። ይህ የሚሳየው በአለም አቀፍ የጦር ወጪዎች "ወደርየለሽ ብክነት" እንዳለና በ1990ዎቹ በአማካኝ "በአመት ከ500 ቢሊዮን ዶላር ያለፈ" ወጪ ነበር (Sivard 1996:7)። ያለመግደል ፓለቲካ ሳይንስ በአለም አቀፍ የጦር ዝጁነት ምክኒያት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚያዊ እጦትን አሻፈረኝ ብሎ አለመቀበል ማለት ነው። የሚቀበለው ግን የሰው ልጅን ከ "ብረት መስቀል" ነፃ ለማውጣትና የድህነትን "እልቂት" ለመግታት የሚደረጉ ገንቢ የሆኑ ጥረቶች ነው።

## ያለመግደል ሰብኣዊ መብቶች ግዴታዎች

ለችግር መፍታቱ ጥረት ፈተና የሆነው በዩኒቨርሳል ዲክላሬሽን አፍ ሂውማን ራይትስ (1948) እና የተከተሉት የማስፈፀሚያ ትእዛዞች ሲቪልና ፖለቲካዊ፣ ህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ነበር። ዋናው ፅሁፍ በሁሉም ፖለቲካ ሳይንቲስትና የአለም ህዝብ ሊታወቅ ይገባዋል።

ነገር ግን ሰብአዊ መብቶች የሚተነተኑት ሁሉን አቀፍ በሆነና በባህላዊ ልዩነት መሀል ባለ አወዛጋቢ ሁኔታ ነው። ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ ያለው ቁርጠኝነት በማይገድል መንገድ መከላከል ነው። አለፎ ተርፎም አበክሮ የሚናገረው ሁሉን አቀፍ በሆነ ሁኔታ ያመገደልን መብትና ሌሎች ያለመግደል ግዴታ ተቀባይነት አግኝቶ እንደ አላማ መያዝና ማስፈፀም ነው አንድ መንገድ የሚሆነው ዩኒቨርሳል ዲክላሬሽኑ ውስጥ እዲካተት መጣርና በአለማቀፍ ትግበራ ላይ የሚከተለውን ማየት:-

> አንቀፅ 3(2) ሁሉም ያለመገደል መብት አለው እንዲሁም ሌሎችን ያለመግደል ግዴታ አለበት።

ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ ያለውን ሀብት ወደ ጥናት፣ ስልጠና፣ ማማከርና ከለላ ለሚሹ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን በሁሉም ደረጃ ለማሳደግ የሚጥሩ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶችን ድጋፍ መስጠት ላይ የማዋል ፈተና አለበት። ለምሳሌ በ1995ቱ የቤጂንግ የሴቶች ኮንፈረንስ ላይ የተላለፈው ሴቶች ላይ የተነጣጠረ የትኛውንም አይነት ጥቃት መግታት የሚለው ፕሮግራም የሚያነሳው አጀንዳ አፈፃፀም ላይ ቁርጠኝነትን የሚገፋፋ ነበር (United Nations 1996)። ሌላኛው የፖለቲካ ሣይንስን ሙሉ ጥረት የሚፈልግ ፈታኝ ነገር 1961 በኢምኔስቲ እተርናሽናል የተመሰረተው በብጥብጥ አልባ መንገድ ሰብአዊ መብት መጠበቅ ነው። ስራው መሰረት ያደረገው የዩኒቨርሳል ዲክላሬሽን መርሆዎች ነው። ለምሳሌ "ማንም ሰው ለስቃይ ወይም ጭካኔ፣ ኢሰብአዊ ወይ አዋራጅ ለሆነ ድርጊት፣ እንዲሁም ለቅጣት መጋለጥ የለበትም።" (አንቀፅ 5)፤ "ማንም ሰው አላግባብ ለእስር ወይም ስደት መጋጥ የለበት" (አንቀፅ 9)፤ እንዲሁም "ሁሉም ሰው ነፃ አስተሳሰብና ራስን የመግለፅ መብት አለው። ይህ መብት የሚያጠቃልለው ያለጣልቃገብ የራስን አስተሳሰብ መያዝ እና በየትኛውም ሚዲያ ስለወሰነ ሳይጨነቅ መረጃንና ሀሳብን እንደፈለገ መቀበልና መስጠት። (አንቀፅ 18) አምኔስቲ እተርናሽል የሚፈልገው የሞት ቅጣት በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲወገድ፣ ማሰቃየት እንዲወገድ፣ ወገንተኝነት የሌለበት ፍትህ ለሁሉም፣ እና ብጥብጥን የሚያስፋፋም ሆነ በብጥብጥ ውስጥ ተሣትፈው

የማያውቁ የህሊና እስረኞች በአፋጣኝ እንዲለቀቁ:: ማስፈፀሚያ መንገዶች ደግሞ ሁሉም ዓይነት ያለመግደል ፖለቲካዊ እርምጃን ያካትታል።

ያለመግደል የፖለቲካ ሣይንስን በማገዝ ሊሠሩ ከሚገቡ የሰብዓዊ መብት ስራዎች አንዱ ተወካይ የሌላቸው ህዝቦችና ሀገሮች ድርጅቶች (Unrepresented Nations & Peoples' Organization - UNPO) ሲሆን የተመሰረተውም በ1991 ዓ.ም ነበር። UNPO የሚሰራው ከ50 ለሚበልጡና አህጉራት ላይ የሚገኙ የሀገር ተወላጆችን አጠቃላይ ሠብአዊ መብት ተቀባይነት አግኝቶ እንዲከበር ነው። አባላቱ ለUNPO ስምምነት ሲጽፉ ያደረጉት ቁርጠኝነት "የጥበብ አለመኖርን ማበረታታትና አሸባሪነት የፖሊሲ መሣሪያ መሆኑን መቃወም" ን በተመለከ ነበር። UNPO ጥሪ የሚያደርገው "ለመንግስታት፣ ለአለምአቀፍ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ኃይል መጠቀምን ስለመቀነስ በተመለከተ ግልጽና መርህን የሚከተል ፖሊሲን መቀበል" እንዳለባቸው ነው። ይህም የሚያካትተው፡-

> የሁሉም ህዝቦችና የአናሣዎችን መብት እኩልነት መቀበልና ማክበር፤ ብዛታቸውን፣ የባህልና የሀየማኖት ልዩናቸውን ሳንመለከት ነገር ግን ተጠሪ የሌላቸውን ህዝቦችና የአናሳዎች ፍላጎትና አመለካከት አጢኖ በማት፤ሳይነኩ ብጥብጥ የሚያስነሱና በአጠቃላይ ተጠሪ የሌላቸውን ህዝቦችና አናሳዎች ሰብዓዊ መብት የሚጥሱትን መቃወምና ማውገዝ፤ አላማቸውን ለማስፈፀም ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚጠቀሙ እንቅስቃሴዎችም ሆኑ መንግስታትን እውነተኝነት መቀበል፤ እንዲህ ካሉ እንቅስቃሴዎችና መንግስታት ጋር ውይይት ማድረግና ብጥብጥ አልባነትን በመከተላቸው ሽልማት መስጠት፤ (እና) በሀገር መንግስታትና ህዝቦች መሐል፣ በህዝቦችና በተጨቆኑ አናሳዎች መሐል ያሉ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታትን ማበረታታትና ማገዝ (UNPO 1998:8)

ከዚህም አልፎ ተርፎ UNPO ጥሪ የሚያደርገው "የህዝቦች የመኖር መሠረት የሆኑ ሀብቶችን አላግባብ የሆነ ብዝበዛ ተቋሞችና የንግድ ተቋሞች እንዲያቆሙ፤ በግድየለሽነት የተሞላ የመሣርያ ንግድን በማካሄድ ብጥብጥን ከማበረታታት እንዲቆጠቡ እንዲሁም በሚዲያና በምርቶቻቸው ብጥብጥን ከማስተዋወቅ እንዲቆጠቡ" (9) ይህን የመሠለ ያለመግደል ፖለቲካ ላይ ቁርጠኝነትን የሚያሣዩ በዘር ማጥፋት፣ ጎሣ ማጥፋት እና አካባቢ ማጥፋት ውስጥ ያለፉ ሠዎች ለድጋፍ ሰጪ ያለምግደል ፖለቲካ ሳይንስ ግልጽ የሆነ ፈተና ያቀርባሉ። በዓለም ላይ ያሉ የሀገር ተወላጆችና አናሳዎችን ብዛትና የማንነት ጥያቄ ስናይ የUNPO አባላት ቁጥር ቀስ በቀስ የተባበሩት መንግስታት ሀገር አባላትን ሊበልጥ ይችላል።

## ያለመግደልና ያካባቢ ጤንነት

ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ የሠውን ልጅ ከአካባቢው ከሚወጣ ሞት ነፃ ለማውጣት እርዳታ ያደርጋል። እኛ አካባቢያችንን እንገድላለን አካባቢያችን ደግሞ እኛን ይገድላል። የማይገድል ማህበረሠብ የማይገድል አካባቢ ያስፈልገዋል።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የሠው ልጅ የአለማችንን ህይወት የማኖር አቅም አጥፍቶታል በሚል ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ወድቆ ነበር። የጦር ኃይች በኢንዱስት መደገፍና በጦርነት ምክኒያት አለማችን ላይ የሚደረግ ጥቃት ለጥፋቱ አስዋጽኦ ያደርጋል። በተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ጉባኤ ኦክቶበር 28, 1982 ላይ በ111 አባላት ተቀባይነት ያገኘውና ስለተፈጥሮ የተደረገው የአለም ቻርት (The World Chater for Nature) ያሉት "ተፈጥሮ በጦርነት እና በሌሎች ግጭች ምክኒያት ከሚደርስባት መጎሳቆል ልትጠበቅ ይገባታል" (አንቀጽ 1፣ ክፍል 5) አሣዛኝ ከሆኑ ጥፋቶች ጥቂቶቹ አሜሪካ በቪየትናም ጦርነት ላይ በኬሚካል አማካኝነት ያደረሰችው የደኖች መድረቅ፣ በገልፍ ጦርነት ጊዜ ኢራቅ ያደረሰችው የነዳጅ ማውጫዎችን ማቃጠል ነበሩ። ቤሪ ኮመነር ያቀረበውን ሃሣብ ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ ይጋፈጠዋል። "ከአለማችን ጋር ሠላም ፈጥሮ ለመኖር በውስጧ በሚኖሩ ሠዎች መካከል ሠላም ልናሰፍን ይገባል።" (ኮመነር 1990፡ 243)

በአካባቢና ልማት ዙርያ የተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ኮንፈረንስ ሴክሬተሪ ጀነራል ሞሪስ ኤፍ ስትሮንግ የተነሣው ሌላ ሃሣብ "የአካባቢ አብዮት (eco revolution) አስፈላጊ የሆነው

አለማችንን ወደ አዲስ መንገድ ለማሸጋርና ወደፊት የሚጠብቀን ቀጣይነት ያለውና በእኩልነት የተሞላ አለም እንዲሆን ነው፡፡ (United Nations: 1993-1) አጀንዳ 21 በኮንፈረንሱ ላይ እርምጃ እንዲወሠድ ጥሪ የሚያደርገው የተገነዘብው ነገር "ጦርነት ቀጣይነት ያለውን ልማት እንዳይኖር አፍራሽ ነው፡፡" (መርህ 24) እና "ሠላም፣ ልማትና የአካባቢ ጥበቃ የተሣሠሩ ግን የማይታዩ ናቸው፡፡" (መርህ 25) ችግር የመፍታት እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ የሚቀርበው ለሀገራት፣ ለመንግስታት፣ ለህዝቦች፣ ለሤቶች፣ ለወጣቶችና ለሀገር ተወላጆች ነው፡፡ እዚህም ላይ ሊታከሉ የሚችሉ ደግሞ የጦር ሀይሎች፣ የጦር ኢንዱስሪዎች፣ ኮርፐሮሽኖች፣ የሠራተኛና ህብረቶችና የፖለቲካ ሳይንቲቶስች ናቸው፡፡

ለመኖርና ለደህንነት እንደሚያሰጉ ሌሎች ችግሮችና የአካባቢ ችግሮችም የተወሳሰቡ፣ ብዙ ችግሮች የአካባቢ ችግሮችም የተወሳሰቡ ብዙ ስርአቶችን የሚነኩና አለም አቀፍ ናቸው፡፡ የህዝባዊ ፖሊሢ ቀረጻና አፈፃፀም ላይ ፖለቲካ ሳይንስ የሚያደርገው ሀብታዊ እገዛ መተግበር የሚገባው ከአለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ የሚያደርገው ሀብታዊ እገዛ መተግበር የሚገባው ከአለመግደል አመለካከት ነው፡፡ ሣይንሣዊ ስራ የሚሆነው የትኞቹ አስጊ የአካባቢ ሁኔታዎች በይበልጥ ተጢነው አፋጣኝ እርምጃ እንደሚያስፈልጋቸው ለይቶ ማወቅ፣ የትኞቹ ችግሮች አፋጣኝ ጥናት ያስፈልጋቸዋል፣ የትኛው ከየትኛው መቅደም አለበት እና በምን አይነት መልኩ ሣይንሳዊ እውቀትን ለፍላጎት ምላሽ ሰጭ እንደሆነ ህብረተሠባዊ ውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ማምጣት እንደሚቻል ማየት የሮያል ስዋዲሽ አካዳሚ ኦፍ ሳይንስ የአቀራረብ ተምሣሌት አሣይቶ ነበር፡፡ (1983; Sebek, 1983)

ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ ማለት ለግለሠቦች፣ ለድርጅቶችና የማይገድል አካባቢያዊ ችግር መፍቻ እርምጃዎች ላይ ለሚሠሩ ህብረተሰባዊ እንቅስቃሴዎች በተለየ ሁኔታ ትኩረትና ድጋፍ ይሠጣል፡፡ ዘመናዊና አትኩሮትን የሚስብ ያለመግደል አካባቢያዊ እንቅስቃሴዎች በመንደር ከሚገኙ የሤቶች "ዛፎችን እናድን" የተሠኘ ህንድ ውስጥ የነበረ ቺፕኮ እንቅስቃሴ (Weber 1989; Nautiyal 1996) አንስቶ በግሪን ፒስ ህዝባዊና የግል ፖሊሲዎችን ለመቀየር የተደረገው ቀጥተኛ ጥረትን ጨምሮ እና በጀርመን ውስጥ የተፈጠው አረንጓዴዎቹ (Die Grunen) የተሰኙ አካባቢያዊ እንቅስቃሴ እና ተመራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ድረስ ይካሄዳል፡፡

ፔትራ ካሪን ኬሊ (1947-1992) የአረንጓዴዎቹ ተመራጭ ፓርቲ መስራች የነበራት ታሪካዊ አመለካከት የሚያቀርበው ለ21ኛው ክፍለዘመን ችግር የመፍታት አጀንዳ ያለው ፖለቲካ ሣይንስ ነበር፡፡ ለእርምጃ ያደረገቸው ጥሪ ከመሣርያ ቅነሳ እስከ ኢኮኖሚና ሠብዓዊ መብቶች እንዲሁም አለማችንን ለማዳን አለማቀፍ የሆነ ትብብር ያሉ ጉዳዮችን ያጠቃልል ነበር፡፡ በተጨማሪም "ለአካባቢ ተጠያቂ የመሆንን ባህል አለም አቀፋዊ ማድረግ" እና በአስቸኳይ "አካባቢያዊ ግንኙነቶችን የሚመሩና የሚያስተሣስሩ መርሆዎችን ለሁሉም ሀገሮች" እንዲነደፍ ማድረግ (ኬሊ 1992፡76)፡፡ ፔትራ ኬሊ ከነቶልስቶይ፣ ጋንዲ፣ አብዱል ጋፋር ካን እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ጋር አሁን አሁን አብራ መታየት ይገባታል፤ ወደፊትም በ20ኛው ክፍለዘመንና መጨ ዘመናት ለአለመግደል አለማቀፋዊ ለውጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገች ሊታይት ይገባል፡፡ (ኬሊ 1989፣ 1992፣ 1994፣ ፓርኪን 1994)

## አለመግደልና ችግር የመፍታት ትብብር

የሠላማዊ ችግር መፍታትን ሂደት ከግለሠብ ደረጃ አንስቶ እስከ አለማቀፍ ድረስ ለማገዝ የሚደረግ ስራ የተለመደ ነው፡፡ ደህንነትም ሆነ የኢኮኖሚያዊ ደህንነት፣ ለሠብአዊ መብት ያለከበሬም ሆነ የአካባቢ ደህንነት እንዲሁም ሌሎች የሚፈለጉ የአኗኗር ሁኔታዎች በሙሉ ሊሟሉ የሚችሉት ለህይወት ከበሬታ በሚሰጥ መልኩ እርዳታቸው በሚፈልጉ ሁሉ መኃል ትብብር ሲኖር ነው፡፡ ይህም ፖለቲካ ሣይንስ ሁሉንም ችግሮች ይፈታል ማለት ሣይሆን የችግር መፍቻ የትብብር ሂደትን ለማገዝ ጠያቂነቱን ይቀበላል ማለት ነው፡፡ አምባገነንነትን አያመለክትም፣ ስርዓት አልባዎች እንኳን ለነፃነታቸው ሲሉ ከሌሎች ስርዓት አልበኞች ጋር የመተባበር ክብርን ይሻሉ፡፡ ያለመግደል አመለካከት እየጠቆመ ያለው በግጭትና ውድድር ምክንያት ከፖለቲካ ይልቅ ግልፅ ወይም ድብቅ ብጥብጥ የመጨረሻ አማራጭ መሆኑን ነው፡፡ ያለመግደል ፖለቲካ የሚያመላክተው እየሰፋ የመጣውን በትብብር ችግር የመፍታት ክብር

የሚያስከትለው ሕይወትን የሚያበስር የእርስ በርስ መከባበርን ነው፡፡ መግደል ሲገዛና ሲከፋፍል ያለመግደል ደግሞ ያስተባብራል እንዲሁም አንድ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ የሚፈልገው በወንዶችና በሴቶች፣ በኃይማኖቶች፣ በስልጣኔዎች፣ በዘር፣ በጎሣ፣ በመደብ፣ በማህበሰብ፣ በኃገር፣ በብሄራዊና ብዙ ሀገር ባሉ ድርጅቶች እና በአለምአቀፍ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የጋራ እርምጃ ነው፡፡ አላማው ለሁሉም ደህንነት ሲባል ሣይገድሉ ወይም ለመግደል ሳያስፋራሩ ችግርን መፍታት ነው፡፡ ግጭትን በመፍታት ዙርያ በፅንሰ-ሀሣብ ደረጃና በአተገባበር ብዙ ስርአቶችና ሙያዎች የሚያሳዩት interest በድንገት ጨምሯል የሚፈልጉትም ሁሉም የሚያሸንፍበት የግጭት አፈታትን በውይይት ማድረግ ዋና የማሣለጥ ሀብትን ይሰጣል፡፡ (ፊሸር and Ury 1981; Burton 1996)

እየላቁ የመጡ ጥቶናች እንደሚያሳዩት ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ በብጥብጥ የሚታወቁ ማህበረሰቦችንና ሲቪል ማህበረሰቦችን ወደ አለመግደል እንዲቀየሩ የማገዝ ስራን ይሰራል፡፡ በአንዳንድ ዘመናዊ የፖለቲካዊ ስርዓቶች የሚታየውን ዲሞክሲያዊ እድገት ባለፉት ዘመናት ምን ያህል እንዳደገ ያስታውሳል፡፡ ነገር ግን ነፃ ፖለቲካና ነፃ ገበያ ለብቻቸው መፍታት የማይችሏቸውን ፀባያዊና መሠታዊ መበጥበጥን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል:: ያለመግደል ፖለቲካ ሣይንስ ህዝብ ያጸደቀውን መጠን የሌለውን ስልጣን ለመገደብ ያወጣውን ህገ-መንግስት ክደት ያውቃል፤ የህዝቦችን ነፃነት ለማጋገጥ ያወጣውን የመብት ህግ፣ የህግ አስፈፃሚ፣ የህግ አውጪና የህግ ጠባቂ ተብሎ የተከፋፈለውን ተቋማዊ ሚዛን የመጠበቅ አሰራርን ጥቅም እርስ በርስ ጦርነትን በምርጫ ፓርቲዎች መለወጡን፤ የሙያዊ ቢሮክራሲን ስራዎች፤ ሀይማኖታዊ ነጻነት፤ እና ድምጽ የመስጠት መብትን አለማቀፋዊ የሆነ ተሣትፎ ማስፋት (Finer 1997; Gold man 1990) ሀይለኛ ጦርና የፖሊስ ስልጣን መኖራቸውን ከማወቅም አልፎ እንዲህ ያሉ ስርዓቶችን ለሚሸፍኑ አማራጭ ይፈልጋል፡፡

ያለመግደል አቀራረብ የስርአቶችን መሰናክል ምልክቶች የሚያየው ለሠው ልጅ ፍላጎት ምላሽ መስጠት ባለመቻሉ በዚህም ምክኒያት እጅግ የመጠቀ ዲሞክራሲ አለበት የተባለው እንኳን አካላዊና መሰረታዊ ብጥብጥ በመከተሉ ነው፡፡ ጥቂት የቅርብ ጊዜ ሁኔታዎችን ብናስታውስ (አሜሪካን እንደ ምሳሌ ብንወስድ)፡- ብጥብጥና የግድያ ወንጀሎች በቤተሠብና በትምሀርት ቤቶች ውስጥ፤ የወጣቶች ተስፋ መቁረጥ ተንጸባርቆ የሚታየው በወንበዴዎች መበጥበጥ፣ አደንዛዥ እፅ መጠቀምና ራስን በመግደል መሆኑ እየሰፋ የመጣ ፖለቲካና ማግለል፣ ፖለቲካና በመንግስት እምነት ማጣት፣ ይህም በከፊል የሚንጸባረቀው በዝቅተኛ የምርጫ ተሣትፎ ነው፤ ውጤት አልባ በሆነ የጦር ወጪ ምክኒያት የሚመጣ የሀብት ብኩንነት በትንሹ 20% የሚሆነው ህዝብ በዝቅተኛ የኑሮ መደብ ውስጥ የሚገኝና ስር በሰደደ ሁኔታ እጦት ያጠቃቸው ጥሩ ባልሆነ የአመጋገብ ስርአት ፣ ጤንነት፣ መጠለያ (መጠለያ ላይኖረቸውም ይችላል)፣ ትምህርትና የቤተሰብ መፈረካከስ የሚታይባቸው መሆናቸው፤ ታጥቆ መዝረፍ የጥላቻ ወንጀሎች፤ የዘርና ጾታዊ አድልዎ በከፍተኛ ሁኔታ የበለጸጉ በከፍተኛ የኑሮ መደብ ላይ የሚገኙ ምናልባትም ሌላ 20% የሚሆኑ ሀብታቸው እየጨመረ የመጣና ከሚቀርቧቸው በመካከለኛ ኑሮ መደብ ላይ ከሚገኙት ጋር በመተባበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ቁጥራቸው የበዛ ፖሊሶችን፣ እስር ቤቶችን፣ ከባድ ቅጣቶችን እና የጦር ኃይልን በሙሉ ከከፍተኛ ባህላዊ ኃይል ጋር መጣመራቸው ነው፡፡

የዘመናዊ ዲሞክሲያዊ ሀገራትና ሲቪል ማህበሰብ ባህሪያት የማይንጸባረቅባቸው ሀገሮች በይበልጥ የተጧጧፈ የብጥብጥ አይነቶች ይገጥሟቸዋል፡፡ እነዚህም የሚያያዙት ያልተገደበ ሞትን የሚያመጣ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እና የኢኮኖሚያዊ እጦት የሚያስከትሉት ለመናገር የሚያግዳግት አካላዊና መሠረታዊ የሆነ አሠቃቂ ሁኔታን ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ከሚጠቁሙ ጥቂቶቹ አጣዳፊ የሆኑ መረሸን፣ ማሰቃየት፣ ለምርጫ መግደል፣ ዘር ማጥፋት፣ ጎሳ ማጥፋት፣ በመሳሪያ መበዝበዝ፣ አሸባሪነት፣ የታጣቂ አብዮት፣ በሀገሩ የተደገፈ ኢኮኖሚያዊ እጦት ምክንያት የሚመጣ ጅምላ ሞት ናቸው፡፡

ብጥብጥ ለሁሉም ነገር መጀመሪያውም መጨረሻውም ነው የሚለውን አስተሳሰብ ከመቀበል ራሱን ነፃ አውጥቶ ያለመግደል ፖለቲካ ሳይንስ የችግር መፍታት ስራ ሊሆን የሚገባው በተወሰነ ደረጃ እንኳን ዲሞክራሲያዊ ናቸው በሚባሉ ህብረተሰቦች ውስጥ እንዲሁም

መካከል ለሰው ልጅ ፍላጎት ምላሽ የመስጠት ሂደቱ እንዲሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ ሳይንሣዊና ሠብአዊ ፈጠራ ላይ ያለው ፈተና ሰፊ ነው፡፡ ነገር ግን አሁንም ግልፅ የሆነው ጉዳይ ገንቢ የሆኑ የሂደት ለውጦች ላይ አስዋጽኦ ማድረግ የሚቻለው ስለአለመግደል እሴቶች በይፋ በማስተዋወቅ፣ ስለሠው ልጅ ያለመግደል ችሎታ አዳዲስ መረጃዎችን በማቅረብ፣ አዳዲስ የዲሞክራሲያዊ አመራርና ህዝባዊነት ያለመግደል ችሎታዎችን በማሳደግ፣ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ ሊኖር የሚችል ተሣትፎን በማሣለጥ፣ እንዲሁም አዳዲስ ለሞት የማይዳርጉ ችግር ፈቺ ተቋማትን በመፍጠር ነው፡፡ እንዲህ አይነት ለውጦችን ለማገዝ፣ ፖለቲካ ሣይንስ ራሱ አለመግደል ለማህበሰብ ጥቅም የመጨረሻ ነጥብ ስለመሆኑ ያለውን ቁጠኝነት ግልጽ ማድረግ አለበት፡፡ እንደተቋምም ምላሽ ያላገኙ የሠውን ልጅ ፍላጎቶች ከግለሰብና ቤተሰብ አንስቶ አለም ውስጥ እስካሉ የፖለቲካ ቡድኖች ድረስ ሊያስተናግድ ይገባል፡፡

# ምእራፍ 5
# ተቋማዊ ምልከታዎች

> አስፈላጊ ብለን የምንጠራቸው ተቋሞች ብዙውን ጊዜ የለመድናቸው ተቋሞች ናቸው……እንዲሁም የማህበረሰብ መተዳደሪያ ህገ መንግስትን ብናይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ማሰብ ከሚችሉት በላይ ነው።
>
> አሌክሲስ ደ ቶክቪል

> በምድራችን ላይ ያለውን ህይወት ለማጥፋት እያሳበቡ ያሉ ችግሮች የተፈጠሩት በህብረት ነው፤ ተፅእኖ እያሳደሩብን ያሉትም በህብረት ነው፤ እኛም እነሱን ለመቀየር በህብረት መዝመት አለብን፡፡
>
> ፔትራ ኬ.ኬሊ

የግድያ አልባ ለውጥ በፖለቲካ ሳይንስ ላይ ያለው ተቋማዊ ምልከታ ምንድን ነው? በሚተገብሩት ላይስ ምን እንደሆነ ያመለክታል? አወቃቀሩ ከሌሎች የእውቀት መስኮች ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? ለሌሎች የተለያዩ ተቋማት ግድያ አልባ ህበረተሰቦችን ከማህበረሰቡ እስከ የሰው ፍጥረት ባጠቃላይ ተቋማት ተደርገው የሚወሰዱት፣ አላማ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነቶች ሆነው፣ በሰዉ ልጆች ፍላጐት እና ምኞት ላይ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

የስልጣኔን ታሪክ ያየን እንደሆነ በዋናነት የተቋማት ፈጠራ ታሪክ ነው፡፡ እምነት ላይ ተመስርተው የቤተመቅደስ፣ የሴናኖግ፣ የቤተክርስቲያን እና የመስጊድ ማህበረሰቦች ተቋቁመዋል፤ የፓለቲካ ተሳትፎ ፍላጐት ላይ ተመስርተው ፓርቲዎች፣ ምርጫ እና ፖርላማ ተጀመርዋል፤ ማህበረሰብ የመጠበቅ ፍላጐት ላይ ተመስርተው ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት እና ወህኒ ቤቶች ተቋቁመዋል፤ ጦርነትን ማሸነፍ በሚል አላማ መሬት፣ ባህርና አየር ላይ የሚዋጉ የቴክኖሎጂ ኃይሎች ተፈጥረዋል፤ግብርን ለመሰብሰብ የጦር ኃይልን ለመደገፍና የመንግስትን አላማ ለማስፈፀም ሲባል ቢሮክራሲ ተፈጥረዋል(ፋነር 1997:16-17፣20-21) በማንሃተኑ ፕሮጀክት አቶሚክ ቦምብ ለመፍጠር የተፈጥሮ ኃብቶችን ተጠቅመዋል። የ15ኛው ክፍለ ዘመን የልዑል ሔንሪ እና የ20ኛው ክፍለ ዘመን አፖሎ ሰውን ጨረቃ ላይ የማውጣት የማይጨበጡ የሚመስሉ ህልሞችን እውን ለማድረግ የመንፈስ፣ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂን፣ የሙያን እና እምቅ ኃብትን አቀናብሮ መጠቀም አስፈልጓል፡፡

ግድያ አልባ አለም አቀፍ ህብረተሰብ ለመሆን ለሚደረገው ለውጥ ምን አይነት ተቋማዊ ለውጦች በፖለቲካ ሳይንስ ያስፈልጋሉ? የግድያ አልባ አለም አቀፍ ሁኔታዎች የተቋም ለውጥን ከዘመናዊ መረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂ አንጻር ሲያያቸው የተለያዩ አድርጎ ነው፡፡ የግድያ አልባ አመለካከት በድሮው አይነት አሰተሳሰብ መዋቅር ውስጥ ለምሳሌ አሳታፊ ዴሞክራሲ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በኑሮ ደረጃ እና በአካባቢ ተቆርቋሪ መሰል የፖለቲካ ሳይንስ ዘርፎች ሊካተት ይችላል። ወይንም ደግሞ የድሮውን መዋቅር አስተካክሎ የመገንባት፣ ተመሳሳይ የሽግግር ደረጅቶችን ማቋቋም፣ አለበለዚያም ጭርሱንም የማይገናኝ አዲስ ወይንም ቅይጥ ተቋሞችን በመፍጠር ያላቸውን ጥንካሬ ምንጭ በማቀናበር የግድያ ነፃ ለውጥ ማስፈፀም ይቻላል፡፡

ከግድያ ነፃ የሆነ ማህበረሰብን እውን ይሆናል ተብሎ ሲታሰብ በተያያዥነት ከግድያ ነፃ የሆነ ሳይንሳዊ እና ስብአዊ ግኝቶችን የሚያበረታቱ ከግድያ ነፃ የሆነ ትምህረት እና ስልጠና የሚሰጡ፣ ህይወት ሳይጠፋ ችግሮች የሚፈታበትን መንገድ የሚያስቡ፣ ከግድያ ነፃ የሆነ ጥበቃ የሚሰጡ እንዲሁም ከግድያ ነፃ የሆነየማህበረሰብ ደህንነትን የሚያረጋጥ ባህልን የሚፈጥሩ ተቋማት ያሰፈልጋሉ፡፡

ዲሞክራሲ የተፈጠረው፣ የሚያደርጉትን በሚያውቁ፣ እንዴት ስራ ላይ እንደሚያውሉ በሚያውቁ እና ስራ ላይ ለማዋል ፍላጐቱ ባላቸው ዲሞክራቶች እንደሆነ ሁሉ፣ ከግድያ ነፃ ማህበረሰብ እና ተቋሞችም እንዲሁም ከግድያ-ነፃ በሆነ የፖለቲካ ሳይንስ፤ እና ከግድያ-ነፃ

በሆኑ ግለሰቦች ነው የሚፈጠሩት ፡፡ ከግድያ-ነፃ የሆነ የአስተሳሰብ መነቃቃት ለመፍጠር የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ አንዳቸውም ግን ብቻቸውን ለሁሉም ሁኔታ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ውልደት፣ እምነት፣ የእውቀት ደረጃ፣ ፍራቻ፣ አዘኔታ፣ ትርፍና ኪሳራ በማመዛዘን፣ ማስመሰል እና መንፈስ መረጋጋት የመሳሰሉት ሁሉም ወደ ግድያ አልባ ኃሳብ መገኘት እና ስራ ላይ መዋል መንገዶች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ከግድያ ነፃ ለመሆን ቁርጠኝነት ማሳየት እንደሚችል ብዙ ታሪካዊ እና የቅርብ ጊዜ የሆኑ ማረጋገጫዎች መኖራቸው ለእያንዳንዳችን የራሳችንን የመለወጥ ብቃት እንድናውቅ ሊያበረታቱን ይገባል፡፡

## ከግድያ ነፃ የሆነ የፖለቲካ ሳይንስ ዲፓርትመንት

ከግድያ ነፃ የሚለውን መንፈስ አሁን ባለው የፖለቲካ ሳይንስ ዲፓርትመንት ወይም ማህበር ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ፣ አዲስ ራሱን የቻለ የተለየ ዲፓርትመንት- አሁን ባለው አደረጃጀት ውስጥ እና የዩኒቨርስቲ ተቋሞች ውስጥ ቢፈጠርለትም ጥሩ ነው፡፡

ይሄ ክፍል ሌሎች ክፍሎች ከተቋቋሙበት አላማ ይለያል፡፡ አላማውም ግድያን፣ ለመግደል የሚደረገውን ማስፈራራት እና የተገናኙ ችግሮችን ማስወገድ ነው።ይኸውም ከሌሎች ጭካኔ ከሚደግፉ የሊብራል ዶሞክራሲ ዲፓርትመንቶች፣ ጭካኔ የሚያበረታቱ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ክፍሎች፣ ወይም ጭካኔ ላይ ከተመሰረተ አምባገነናዊ ስርዓት ይለያል፡፡ ከግድያ ነፃ የሆነው ዲፓርትመንት በዋጋ ተመኩዞ የተመሰረተ አይደለም። የተለየ የራሱ እሴት ያለው ነው እንጂ፡፡

አሁን ያለውን የትምህርት ሒደት ታሳቢ በማድረግ፣ ማለትም ከመግቢያ ኮርሶች እስከ ዶክተሬት ያሉ ጥናቶች፣ ይህ የትምህረት ክፍል የግድያ ነፃ ማህበረሰብን ለመገንዘብና ይዞ ለመቆየት የሚያስፈልገቸው ባህርያት እና ልምዶችን በሚገባ ማግኘት አለበት። ለዚህም አራት ነገሮች ወሳኝ ናቸው፡- ለምርምር ፣ለትምህርትና ስልጠና ፣ለመተግበር እና በእለት ተእለት ህይወት ወስጥ ኃሳብን ለማሰተላለፍ ናቸው፡፡

ጀማሪ ተማሪዎች፣ በግልፅ ሁኔታ ግድያን የሰው ልጅ ከሚያገጥው ሁኔታዎች ውስጥ እንዳይኖር የማድረግ ፈተና እንደ የፖለቲካ ሳይንስ ባለሙያ፣ እንደ ዜጋና፣ ህዝብ አገልጋይ መሪዎች ሆነው መፈለግ አለባቸው።ከዚያም የሰውን ልጅ ችሎታና ፈጠራ እንዲረዱ (ቡርስቱን 1983፣1992፣1998) ፣የፖለቲካን ፈጠራ እንዲረዱ (ፊነር 1997) ሰላማዊ ለሆነ የሰው ልጅ ክብር በተለያየ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን አገለግሎት (ጆሴፍሰን 1985) እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

የሚቀጥለው፣ ዋና የሚባሉ ችግርን በመፍታት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች (ጭካኔ፣የኢኮኖሚ ችግር፣ የሰው ልጅ መብት፣ የአካባቢ ችግር፣ የማህበራትችግር) የፖለቱካ ተቋማት እና ችግር መፍቻ ሂደቶች (አካባቢ፣ አገራዊ፣ አለም አቀፋዊ፣ ምድራዊ)፣ እንዲሁም የቅርብ ጊዜ እውቀቶች ከግድያ ነፃ የሆነ አመለካከቶች እና አፈፃፀሞችን በማጤን ለወደፊቱ ግድያ ነፃ አስተሳሰብ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡

ከዚያም በመቀጠል፣ ለተማሪዎች የሚቀርብላቸው እድል የተለያዩ አማራጮችን በማፈላለግ ከችግር መፍታት እና ለህብረሰተብ ግለጋሎት የመስጠት ፍላጐትነና ችሎታቸው ይፈተንበታል። ለዚህም የምርመር ሙያን ማስተዋወቅ፣ ትምህርትና ስልጠና፣ የመሪና ማህበረሰብ እንቅስቃሴ እናም ወሳኝ የፖለቲካ ምዘና ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲባል ግን የተለያዩ ፍላጐቶችን እና ውድድሮችን ለመከልከል አይደለም። ነገር ግን ሁሉም አራት አይነት የማስፈፀሚያ መንገዶች በብቃት ስራ ላይ እንዲውሉና ከግድያ ነፃ የሆነ የማህበረሰብ ለውጥ እንዲመጣ ለማበረታታት ነው። አንዱ ሌላውን ማክበር እና መተባበር፣ እርስ በርስ በሚወዳደሩ እና የሚደጋግፉ ቡድኖች ውስጥ መኖር አለበት። ልክ በሙያተኞች እና የስፖርት ቡድኖች ጋር እንደሚታየው ማለት ነው፡፡

እነዚህ ዝግጅቶች ከተደረጉ የሚቀጥለው እርምጃ የሚሆነው፣ የግል ወይም የህብረት ፕሮጀክቶችን በየአስፈላጊው ሙያ፡- በምርምር፣ በትምህርት፣ በመተግባር እና ወሳኝ አማራጮችን መፍጠር ነው። ይህም በአካላዊ ጭካኔ፣ በመሰረታዊ ጭካኔ፣ የሰውን መብት

በመጣስ፣ የተፈጥሮ ብክለት እና ጭካኔ የሚያነሳሱ ፣ጥላቻቸውን በማነሳሳት ችግር እንዳይፈታ የሚያረጉት ማህበራትን ይከለክላል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ወደ አካባቢያዊ፣አገራዊ፣አለምአቀፋዊ ወይም ምድራዊ ሁኔታዎች ሊያመሩ ይችላሉ። የነዚህ ጥናቶች ውጤትም እንደመመረቂያ ፅሁፍ ቀርበው ለዲፓርትመንቱ ማስታወሻ መዝገብ ውስጥ ሊቀመጡ ይችላሉ፣ እንዲሁም የአለም አቀፍ መረጃ መረብ ላይ ታትመው ለግለሰቦችና ማህበረሰቦች ውሳኔ ለመስጠት ያግዛሉ፡፡

በዚህ ትምህርት የተመረቁት፣ በህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ማህበራት ውስጥ ስራ ይኖራቸዋል (ተመሳሳይ ተቋማትን ከታች ይመልከቱ)። ከዚያም ከፍ ያለ የማስተርስ እና ዶክተሬት ስልጠና በግድያ አልባ ፖለቲካ ሳይንስ መውሰድ ይችላሉ። እንደ አስፈላጊነቱም አሁን ባሉ ወይም አዲስ የፖለቲካ ሳይንስ መስኮችን በመፍጠር (ዋቢ ሰነድ 2፤3) ወይም ለሌሎች የትምህርት ስርአቶችና ሙያዎች እንደ ፍላጎታቸው መቀጠል ይችላሉ፡፡

የግድያ - ነፃ ዲፓርትመንት፣ በተለይ አገለግሎት ሰጪ እና ሙያ ተኮር ነው።የተጠራቀመው እውቀትና ሙያ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ የላቀ ዶክትሬይት ድረስ ይሄዳል፡፡ የፋኩቲ እና ዲግሪ ምሩቅ እጩዎች፣ ለእያንዳንዱ ችግር የመፍታት ፍላጎቶች የሚሆን የፈጠራ ደሴቶች ለተመሳሳይ ፍላጐቶች ያመነጫሉ። ይህ ክፍል፣ አዲስ እውቀት ትምህርትና ስልጠና በማግኘትና ስራ ላይ በማዋል መካከል እርስ በርሱ የሚደረግ ግንኙነት ይፈልጋል። በእራሱ ፀብን የመፍታትን ሒደትም፣ የግድያ-ነፃ ማህበረሰብን ባህሪዎች አጉልቶ ያወጣል፡፡በሁለቱ ፆታዎች፣ ወንዶችና ሴቶች መካከል ያለ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ጣምራ ግንኙነት፣ የግድያ-ነጻ ማህበረሰብ ዋናው መገለጫ ነው፡፡ ተመራቂዎች በስራ ዘመናቸው በሚሰጡት መረጃ አዳዲስ ፍላጐቶችንና ያልታዩ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ እየታየ ተማሪዎችን ማዘጋጀት ይቻላል። ልምድ ያላቸው የማህበረሰብ መሪዎችና በሌላ የስራ መሰክ ለተሰማሩ ጥምር ሹመትን በመሰጠት አንዳንድ ጊዜ ለጋራ ፈጠራ አሰተዋፅኦ ማድረግ ይቻላል፡፡ የግድያ ነፃ እውቀትና ሙያ አለምአቀፋዊ እንደመሆናቸው መጠን፣ የዲፓርትመቱ የጋራ ችሎታ በቀጥታ ተሳትፎም ሆነ በኮምፒውተር የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም አለም ላይ እንዲዳረስ ማድረግ ይችላል። በአካባቢ ያሉ ማህበራት ችግርን በመፍታት አኳያ፣ በአለም አቀፍ ደህንነትን የሚያሰጉ ችግሮችን በመፍታት ተመጣጣኝ አገለግሎት አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡

## ሻንቱ ሴና ዩኒቨርሲቲ (የሰላም ጓድ)

ወደ ግድያ ነፃ ማህበረሰብ የመቀየር ሒደት የተለመደውን የውትድርና ስልጠና ከሚሰጡ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ምትክ ከግድያ ነፃ የሆኑ ፤የአካባቢ አገለግሎት የሚሰጡ ጓዶችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የመሪነቱ ኃላፊነት ለፖለቲካ ሳይንስ ዲፖርትመንት መስጠት ይቻላል፥ ነገር ግን አባላቱ ከተለያየ ጥናት አይነት ሊመረቁ ይችላሉ፡፡

የሽንቲ ሴና- (ስሙ እንዴትም ቢሰየም) አባላቶቹ ስርአት ያላቸው ተለይተው የሚታወቁ ኃይሎች ሆነው፥ ከግድያ ነፃ በሆነ ግጭት አስወጋጅነት እና አስታራቂነት፣ የአካባቢ ፀጥታና ሲቪሎችን መጠበቅ ፣ነፍስ አድን ችግር እና ከአደጋ መከላከል፣ የመልሶ ግንባታ አገልግሎት በመሳሰሉት የማህበረሰቡን ፍላጐት ለማሟላት ይሰለጥናሉ። ተሳትፎው በአመራር ችሎታ ሙያ ላይ ጐንለጐን እና ተጨማሪ ሆኖ፣ ግብአት ይሰጣል፡፡እንዲሁም ተሳትፎ ማድረጉ ከትምህርት ጋር ለተያያዘ ስራ የአመራር ሙያ ድጋፍ ይሆናል።

ንቃት ላላቸው እምነቶች ሁሉ፣ መንፈስን ለሚያነሳሱ ሙዚቃና ጥበቦች፣ የስፓርት አስፈላጊነት እንዲሁም ትክክለኛ አገለግሎት ለሌሎች በመስጠት የሚገኝ እርካታ የሻንቲ ሴና በካምፓስ ውስጥም ሆነ ውጭ ለሚፈጠሩ ችግሮች እንዲያገለግል እንዲሁም ለሌሎች ማህበራዊ ተቋማት የአመራር ችሎታን ለማስንዘብ መጠቀም ይቻላል። ለሌሎች የጦር ስልጠና አገለግሎት ከሚሰጡት ባላነሰም በገንዘብ መደገፍ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ቅድመ ኮሌጅ መሰናዶ ትምህርት ተደርጐ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ የሻንቲ ሴናን የትምህርት ተቋም

ለማዘጋጀት የፕሮፌሰር ኤን ራድሃክሪሽናን ህንድ ካለው ከጋንዲ ሩራል ዩኒቨርስቲ ተጨባጭ ልመድ ተወስዷል (ራድሃክሪሽናን 1997ኤ፥1997ቢ) እነዚህ ላይ የስልጠና መርሆች እና ልምዶችን በመጨመር ከኩዳይ ኪደማትጋር(ሰርቫንትስ ኦፍ ጎድ) የ80,000 ጠንካራ ብጥብጥ አልባ የሙስሊም ነጻ አውጪ ጦር በህንድ ከ1930-47(ባንረጂ 2000፥73-102 )እና የኪንግያን የግድያ አልባ ንቅናቄ ለ ማህበራዊ ለውጥ (ላፋየተ ኤንድ ጄንሰን 1995፥199) እንዲሁም ሌሎች የግድያ አልባ ስልጠና ልምዶች(ዋር ሬዚስተረስ ሊግ 1989)

## ከግድያ ነፃ ዩኒቨርስቲዎች

የግድያ ነፃ ማህበረሰበን ተጨባጭ እውነታ ላይ ለማድረስ ከአንድ የትምህረት ስርአት ወይም ዩኒቨርስቲ ዲፓርትመንት በላይ እውቀትና ችሎታ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም የግድያ ነፃ የለውጥ ፖለቲካ ሳይንስ ለሌሎች የማህበረሰበ ሳይንሳት፣ አስተዋፅኦ ለማድረግ አቅም ያላቸውን የተፈጥሮ ሳይንሶች፣ ሰብአዊ ፍጡሮች እና የስራ ልምዶች ሁሉ ጥሪ ያደርጋል፡፡ የሚያሳየውም፣ ባጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በአካባቢ፣ በአገር፣ በምድራችን እንዲሁም በአለም ያሉ ማህበረሰባት ለመርዳት ከግድያ ነፃ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸው ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ከዚህ ቀደም የተማረውንም ሆነ ሌላውን የሰው ኃይል ለጦረነት ማስተባበር እንደሚችሉ አሳይተዋል፡፡ የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ጀምስ ቢ ኮናንት በጁን 18.1942 እንዳሉት ‹የአክሲስ ፖወሮች ያለቅድመሁኔታ እጅ የሰጡበትን ሁኔታ ለማፋጠን እንዳደረግን ሁሉ አሁን ደግሞ የጥንት ታሪክ ምሁሮችን እናበረክታለን'፡፡ ሐርቫርድ 'የኮናንት አርሴናል' በመባል ሲታወቅ፣ ጦርነት ለማስቀረት ራሱን ቅርፁን በመቀየር ተገዢ ሆኗል። የሐርቫርድ ወጣት ፊዚስቶች በሎስ አልሞስ ኒው ሜክሲኮ ሚስጥራዊ የአውቶሚክ ቦምብ ጥናቶች ላይ እንዲሰሩ ተመልምለዋል፡፡ በአንድ ወቀት እንደሚታወሰው ‹የሳይንትፊክ ዩቶፒያ እንደማለት ነበረ-----የምርጥ ጭንቀላቶች ስብስብ ሆኖ፣ በነፃነት ሐሳቦች የሚንሸራሸሩበት እድሜን፣ የትምህረት ደረጃን፣ ወይም ቀድሞ የደረሱበትን ድል ከግንዛቤ የማያስገባ› (ሐርቫርድ መፅሔት 1999 ገፅ 32.43)

ዩኒቨርስቲዎች የድሮም የሆነ አዲስ በስፋት የጦርነትንና እና ህይወትን ወይም ደህንነትን የሚጐዱ አደገኛ ሁኔታዎችን በማጥፋት ኃላፊነት መወጣት የለባቸውምን? አሁን ያሉ ዩኒቨርስቲዎች ‹የሰላም ጥናቶች› ላይ ያተኮሩ ኮርሶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ እና ዲፓርትመንቶችን ለመጀመር ፍላጎት አያሳዩም፡፡ በተጨማሪ ‹ያለመግደል› ወይም ‹ጥቃት የለሽነት›፣ በእነዚህ ባለ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ እንደ ዋና መሰረታዊ ‹ኤቲክስ› እና ‹አስተሳሰቦች› እየተወሰዱ አይደለም፡፡ ይህን መሰረት አድርገን፣ በትልልቅ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ወደፊት ‹አለመግደል; ምን ገፅታ ሊኖረው እንደሚችል መለካት እንችላለን፡፡

## ከግድያ ነፃ ፖለቲካ ፓርቲዎች

የግድያ ነፃ ፓለቲካ ሳይንስ የሚያመለክተው በፍላጐት ላይ የተመሰረተ ምላሽ እና ተሳትፎ በማካሔድ የማህበረሰብን ችግር መፍታትና የሁሉንም ደህንነት የሚያስፈጽሙ የግድያ ነፃ አልባ ፓለቲካ ፓርቲዎችን መፍጠር ነው ።ለነዚህ ፓርቲዎች የሚስማማው ስም አሂምሳ-ሳርቮዳያ ፖርቲ( አህምሳ - ብጥብጥ አልባ፣ ሳርቮዳያ- የሁሉም ደህንነት)፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች በስም፣ በአደረጃጀት ፣እና እንቀስቃሴ በተለየ ማህበራዊ ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ ይመነጫሉ፡፡

የግድያ አልባ ፖርቲዎች አላማ ለግድያ አልባ ማህበረሰብ እውን መሆን በአካባቢም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ አስተዋፅኦ ማድረግ ነው ፡፡ በፊት ከነበሩ ፖርቲዎች የሚለዩትም፣ በመደብ የተመሰረተ ሁኔታ ሳይሆን ነገር ግን የሁሉንም ፍላጐት እየለዩ በመግለፃቸው ነው፡፡ ይህም፣ ግድያን አደገኛነትን (ወንጀልን) በማስቀረት የሚገኘውን ጥቅም እና የግድያ አልባ ሁኔታዎች ሲኖሩ ያለውን ነፃነት፣ ፍትህ፣ እና የንብረትን ደህንነት በማሰጠበቅ

ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ ያለመግደልን መርሆ መነሻ አድርገው የሚወዳደሩ ብዙ ፓርቲዎች እንደሚኖሩ ይጠበቃል፡፡

ከግድያ አልባ ፖርቲዎች የሚጠበቁት ገንቢ አስተዋጽኦዎች፡- ማለትም በምርጫ መወዳደር ፣ፖሊሲ መቅረፅ እና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች፣ ‹ቀጥታ ፖለቲካ ላይ መሳተፍ አያስፈልግም› ከሚለው የጋንዲ አስተሳሰብ ጋር ይለያያል፡፡ ጋንዲ ለግድያ አልባ ገንቢ ሰራተኞች በዲሴምበር 1947 መጨረሻ ላይ የመከራቸው ከፖለቲካ ተሳትፎ እንዲርቁ ነበር። ምክንያቱም ፖለቲካ መጨረሻ ላይ ሙሰኝነትን ያመጣል በማለት (ኮሌክትድ ዎርክስ 90፡223-4)፡፡ በተቃራኒው፣ ለግድያ አልባ ማህበረሰብ የሚያገለገሉ ሰራተኞች በሲቪሊያኑ ማህበረሰብ ውስጥ ሆነው በበለጠ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እየሰሩ፣ ፖለቲከኞች እና ፖሊሲውን ከውጪ ሆነው ተፅእኖ እንዲያሳድሩ ያስተምር ነበር። ይህ ማለት ግን ሌሎች ሙሰኛ ሆነው ውሳኔ እየወሰኑ፣ በብዙ ሚሉዩን ብር የሚቆጠር ግብር እየሰበሰቡ፣ የሚሊዩኖችን ህይወት የሚነካ ዉሳኔዎች፦ እንደ ጦርነት፣ የአገር ደህንነት፣ ምግብ ፣ልብስ፣ መጠለያ ፣ጤና ፣ትምህርት፣ ኢኮኖሚ፣ ባህል እና የመሳሰሉትን እየወሰኑ ፤በሌላ በኩል በግሞ የግድያ አልባ ተከራካሪዎች እነዚህ ሙሰኞች እና ደጋፊዎቻቸውን ጥሩ ስራ እንዲሰሩ ለማሳመን መሞከር ማለት ነው፡፡ ይሁንና የጋንዲን ምልከታ ማመስገን ያስፈልጋል። ወደፊት ተሳትፎ ሊኖር እንደሚችል በመጠርጠር የተናገረው እንደሚከተለው ነው፡- 'ነገር ግን የሆነ ደረጃ ላይ፣ ሰዎች እራሳቸው ተሰምቷቸው እኛ ብቻ ስልጣን እንድንይዝ የሚፈልጉበት ጊዜ ሲመጣ ፤ያኔ ጥያቄው ይታሰብ ይሆናል' (223)።

የግድያ አልባ ፖለቲካ ፖርቲዎች ከግድያ ነፃ የሆነ ማህበራዊ ለውጥን ለማምጣት የሚረዱ ምክንያታዊ ተቋሞች ናቸው። ለነእርሱ መፈጠር እንዲመች የሚያደርጉ ሁኔታዎች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፡፡ ፖርቲዎች፣ ምርጫና፣ ተወካይ አካላት በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ቢኖራቸውም እንኳን ሁኔታዎቹ የትም ቦታ ቀላል አይሆኑም፡፡ ከግድያ ነፃ ፖለቲካ ፖርቲዎች መስዋእትነት የሚከፍሉበት ትግል መክፈል ይችላሉ። አንዳንድ የቅርብ ሁኔታዎችን በምናይበት ጊዜ አዲስ እውቀት፣ ክህሎት፣ የድርጅት አይነቶች፣ እና አዲስ ችግር ፈቺ ፓሊሲዎችን ማደባለቅ አስቸጋሪ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ለምሳሌ፡- ውርጃ ፣የሞት ቅጣት ፣ጦርነት፣ የትጥቅ አብዮት፣ ሽብርተኝነት፣ ጅምላ ጭፍጭፋ፣ ወንጀለኝነት፣ ማህበራዊ ነውጥ፣ ባህላዊ ረብሻ፣ ትጥቅ ማስፈታት እና የኢኮኖሚ ትጥቅ ማስፈታት። ነገር ግን ለውጥ በፈጠራ ችሎታ ፣የአለም አንድነት እና ማህበራዊ የመማር ሒደት በኩል ሊመጣ ይችላል፡፡

## የህዝብ አገልግሎት ሰጪ የግድያ እልባ ዲፓርትመንት

በየትኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኝ አመራር፣ የህዝብ አገለግሎት ሰጪ የካቢኔ ኃላፊነት ያላቸው ግድያ አልባ ዲፖርትመንቶች ያስፈልጋሉ፡፡ የነሱም ኃላፊነት የሚሆነው ከግድያ አልባ ፖለቲካ ትንተና ስነ አመክኖ ጋር የተገናኙ ሁኔታዎችን መቆጣጠር፣ ለቅድመ እና ድህረ የለውጥ ማገገሚያ ጋር የተያያዙ ስልጠና ድጋፍ ማድረግ፣ እና የግድያ አልባ ማህበረሰብን ደህንነት የሚያመቻቹ የህዝብ ፖሊሲዎች ላይ ምክር መስጠት ናቸው፡፡ ብጥብጥ የማህበረሰብን ኑሮ ማወኩ ስለማይቀር፤ ለህዝብ አገለግሎት የሚሰጠው ቦታ፤ ቆሻሻን ለመጣል ወይም ንፁህ ውሃን ለመሰጠት ከሚሰጠው አትኩሮት ያላነሰ ነው፡፡

የግድያ አልባ ዲፖርትመንት በግድያና ብጥብጥ ላይ ያለውን ቆጠራ ለያይቶ ከግድያን የሚያስወግድ እርምጃን በህዝብና በግለሰብ ምንጮች ላይ ያመላክታል፡፡ በተለያየ ጊዜያቶችም ለመንግስት ውሳኔ ሰጪ አካሎችና የሲቭል ማህበር አባሎች ሪፖርቶች ያቀርባል። ከግድያ ነፃ ፖሊሲዎችና የገለልተኛ ተቆጣጣሪ አካልን ሚና ይጫወታል። አርቆ ማሰብ ከሚያስፈልጋቸው ቦታዎች፦ ግድያ እና ራስን ማጥፋት፣ የቤተሰብ ብጥብጥ (ልጆች ፣ሴቶች፣ የትዳር ጓደኞች፣ አዛውንቶች) የትምህርት ቤት ብጥብጥ፣ የስራ ቦታ ብጥብጥ፣ የኢኮኖሚ ብጥብጥ፣ የሚሊታሪና የፖርላማ ብጥብጥ፣ እና ድህረ ጭካኔ ድንጋጤ በገዳዮች እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ያለው ተፅእኖ፣ በተጎጂ ቤተሰቦች ላይ ያለው ተፅእኖ፣ እና እንዲሁም በጠቅላላ በማህበረሰቡ ህሊና ላይ የሚፈጥረው ተፅእኖ ናቸው፡፡ ሪፖርቶች ማተኮር ያለባቸው በግድያ  አልባ የመቀየር ችሎታ ጥንካሬና ድክመት ላይ፣ እንዲሁም

በይበልጥ ችግር ፈቺ የሆኑ ስልቶችን መጠቀም ላይ ነው። በሒደቱ ለይ ያለው ለውጥ መዘገብ ያለበት የስቶክ ገበያ ዋጋ ፣የስፖርት ውጤቶች ወይም የአየር ሁኔታ ከሚዘገብበት አጽኖ ባላነሰ መሆን አለበት።

## የግድያ አልባ የጋራ ደህንነት ተቋማት

ወደ ግድያ ነፃ ማህበረሰብ የመለወጥ ሒደቱ፣ የግድያ አልባ ደህንነት ኃይሎች አስፈላጊነትን ያመላክታል። እነዚህ ከተለመደው ጦር ሰራዊትና ፖሊስ ጋር ሲመሳሰሉ ድርሻቸውም ሰብአዊ አገልግሎቶችን በመሬት፣ በባህርና፣ በአየር መጠበቅ ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች መሰልጠን ያለባቸው ለመከላከል፣ ድንገተኛ አደጋዎችን ለመወጣትና የመልሶ ግንባታን ለማድረግ እንዲሁም ውጤታማነት ለመገምገም ነው። የስልጠናውን አመራር አሁን ካለው የጦር ሰራዊትና ፖሊስ በመለወጥ፣ ወይም አዲስ የግድያ ነፃ አገለግሎት አካዳሚ በማቋቋም፣ ስልጠናው ለሁሉም እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡ በመከተልም፣ ለእያንዳንዱ ኃላፊነት ማድረግ ነው። የሻንቲ ሴና ዩኒቨርሲቲዎችም ሌላው የአመራር ምንጭ ይሆናሉ፡፡

አሁን ባለው የጦር ስራዊትና ፖሊስ ተቋሞች አይን ታይቶ ግድያ አልባ የጋራ ደህንነት ኃይሎችን ማሳደግ እንደቀላል መተው የለበትም። እንደውም ብጥብጥን ለመከላከል በቀላሉ የታጠቁ ሰላም አስከባሪ ኃይሎችን በማስማራት እና የበጐ አድራጐት እርዳታ መስጠት፣ የማይገሉ መሳሪያዎች የመጠቀም አማራጭ እና የግድያ አልባ መንገዶች ስልጠናን መቀበል ሊታሰብባቸው ይገባል፡፡

የግድያ አልባ በደህንነትን ጥበቃ የሚያመለክተው የሁሉንም ህዝብ በመንደር፣ በአገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ደረጃ ተሳትፎን ነው። ይንን ለማመቻቸት የግድያ አልባ የጥናት መድረኮችና ሲቪክ ሻንቲ ሴና ላይ የተመሰረተ መኖሪያዎች፣ ትምህርት ቤት፣ የአምልኮ ቦታዎች የስራ ቦታዎችን እና የኤሌክትሮኒክ መረብ ላይ ያሉ ግድያ አልባ ማህበራት ማደራጀት ይቻላል፡፡በቀላሉ የሚለመድ ሞዴሎች በአገር በቀል ድርጅት በብዙ መልኩ ይገኛል፡፡

የግድያ አልባ ጥበቃ፣ የግድያ አልባ የጋራ የደህንነት፣ እና የግድያ አልባ የስለላ ኤጀንሲዎችን ያመላክታል። ይህም በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲሁም በዲፕሎማቲክ ተቋሞችና ህዝባዊ አታሼዎችን ይጨምራል፡፡ የግድያ አልባ የጋራ የደህንነት ካውንስሎች የሚፈለጉት ከብጥብጥ የሚደግፉ እና አጋሮቻቸው የተለየ አማራጭ ፖሊሲዎችን እንዲያመጡ ነው፡፡ (የግድያ አልባ የጋራ ደህንነት ካውንስል በአለም አቀፍ ደረጃ ለምሳሌ፡- እንደ ዩናይትድ ኔሽንስ ባለ ሊሆን ይችላል) ከግድያ ነፃ በሆኑ ኒኩለየር መሳሪያ በሌላቸው የጦር መሳሪያ መላዋወጥ በሌለባቸው እና የመሳሰለው አገሮች መቋቋም፡፡ የግድያ አልባ የመረጃ ኤጃንሲዎች የሚያስፈልጉት፣ በጋራ ከመርማሪ መገናኛ ብዙሀንና የዜጐችን ንቃት ከሚፈጥሩ ጋር በመሆን፣ ሁሉንም የግድያን አደገኛነትና አይነት ለመግለፅ እንዲሁም የህዝብንና የግለሰብን ችሎታ ከመለወጥ በላይ ለማወቅ ነው። በዲፕሎማቲክ ተቋማት ውስጥ የግድያ አልባ ባለሙያዎች አስፈላጊነት ከየጦር አታቼዎች ወይም ከኢኮኖሚ ጉዳዩች ያላነሰ ነው፡፡ የግድያ አልባ ባህላዊ አታሼዎች የሚፈለጉት በሁሉም የግድያ አልባ ምንጮች መካከል ድልድይ ለመገንባት የጋራ መማማር እና መተባበርን ደህንነት ለማምጣት ነው፡፡ አለም አቀፍ የመረጃ መረብ፣ አለም ላይ የዜጐች የጋራ የደህንነት መረጃ የመቀያየር፣ እና በመንግስት በድረጅት ወይም በመገኛኛ ብዙሀን ላይ ያልሆነ ግድያ አልባ ውሳኔዎችን መወሰን ይጠቅማል፡፡

በመንግስትእና በግል ድርጅቶች የግድያ አልባ የአገልግሎት አሰጣጥን ችሎታ ለማሻሻል የግድያ አልባ ስልጠናን የሚሰጡ አግባብ ያላቸው ተቋማትን ግድ ይላሉ፡፡ ምናልባትም እንደ ጀማሪ እና በኃላም በአገልግሎት አቻ የሚተኩ የሚሆኑ የግድያ አልባ ስልጠና ተቋሞች እንደ አማራጭ የጦር ኮሌጆች፣ የአገር መከላከያ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የጦር ስራዊት ማሰልጠኛዎች ፣የፖሊስ ተቋሞች እና የህዝብ አስተዳደር ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ

ሌሎች ብጥብጥ የሚቃወሙ የሰለጠኑ በሲቪል ማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ማሰለጠኛ ተቋሞች ያስፈልጋሉ፡፡

## ከግድያ ነፃ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት

የግድያ አልባ ሲቪል ማህበረሰብ ለግድያ አልባ ማህበረሰብ መገኘት መስተካከል እና መፈጠር የሚያስገኙት እድሎች መጨረሻ የሌለው ነው፡፡ብዙ የሚባሉ የግድያ አልባ ማእከል ያረጉ ተቋማት እስከ አሁን ኖረዋል፡፡ እንዱሁም ሌሎች የተለያዩ አሰተዋፅኦ የሚያርጉ ማሰብ ይቻላል፡፡

## የግድያ አልባ መንፈሳዊ ካውንስል

በየትኛውም ደረጃ ወይም ከእያንዳንዱ የማህበረሰብ ቀለበት ውስጥ ያሉ የግድያ አልባ መንፈሳዊ ካውንስሎች፣ ከውልደት እስከ ህልፈት ላለ የማያጠራጥር የሰው ህይወት አክብሮት፣ በየትኛውም መልኩ እንዲሰጥ ማረጋገጥ አለባቸው ፡፡እነዚህ የኃይማኖት ካውንስሎች ከአማኞች እና ከሰብአዊ በጐ አድራጊዎች ተወካዩች፣ እንደ አካባቢው ባሉ አሰፈላጊ እምነቶች እና ፍልስፍናዎች የተውጣጡ ሆነው፣ በሙሉ ልብ እና ብቃት የግድያ አልባ እውነትን ወደ ባህላቸው ለማምጣት ማቀናጀት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ ካውንስሎች ለምቹ ኃይማኖታዊ ወይም ኃይማኖት የለሾች፣ ከጭካኔ ይልቅ እንደ አማራጭ የማነቃቃት እርዳታ ለሁሉም ጥረቶች በማድረግ የህዝብ እና የግል አገር በቀል እና አለም አቀፍ ሁኔታዎች ላይ ግድያን ከሰብአዊ ሁኔታዎች ማስወገድ ይችላሉ፡፡ የተለያዩ የማነቃቃት አማራጮችን በማምጣት የግድያ አልባ መንፈሳዊ ካውንስሎች የሰብአዊ ያለመግደል ችሎታ በእያንዳንዱ ግለሰብ እና ተቋማት ውስጥ ያለውን ችሎታ ለማነቃቃት ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ግድያ አልባ አማካሪ ቡድኖች

የአለም አቀፍ የጋራ ኃብትን በሚመለከት የግድያ አልባ አማካሪ እና ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች፣ የችግሩን መፍቻ በማህበረሰብና በግል ያሉ አማራጮችን ለመለየት ይረዳል፡፡ ስራ ላይ የሚያተኩር መንፈሳዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ሙያዊ፣ ድርጅታዊ፣ እና ሌሎች ጥሬ ኃብቶችን በማስተባበር፣ እነዚህ ቡደኖች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከደም መፋሰስ፣ ከማያቆም ግድያ ለመከላከል የሚፈለጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ እንዲሁም የተረጋጋ የመልሶ መገንባትና መታረቅ ለሁኔታዎችን መፍጠር ይችላሉ፡፡ የእንደዚህ አይነት ግድያ አልባ አማካሪ ቡድን አስፈፃሚዎች፣ ከሌሎች አማራጭ ሃይሎች የሚለዩበት እነዚያኛዎች በኃይል መጠቀም፣ ማስፈራራት፣ ወይም የኢኮኖሚ ማእቀብ ማድረግ ወይም አንዳንዴ ደም ማፍሰስ ያለው ሲሆን እነዚኛዎቹ ፣ ከግድያ ነፃ ውል መግባት፣ ብጥብጥ ከተሞሉ አገራት፣ ግድያ፣ ሰቆቃ ራስን ነፃ ማውጣት፣ በግል የተመሰረቱ ተቋማት ይህንን የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ አቅም ያላቸው ልምዳቻውን በማካፈልና መጪታማነትን ለማሻሻል ይፈልጋሉ፡፡ቅሬታ ፈቺ እና የበጐ አድራጉት አገልግሎት ሰጪዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የኃይማኖትና ሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች፣ በከፊል የመጀመሪያ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

## አገር አቋራጭ ችግር ፈቺ ማህበር

ከላይ ወደታች ከሚለው አካሔድ በተጨማሪ፣ የግድያ አልባ ፖለቲካ ተቋማት (ለምሳሌ ፖርቲዎች፣ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ዲፖርትመንቶች እና የጋራ የደህንነት ተቋማት) ከታች ወደላይ የሚል ኃይል የተሞላ ግድያ አልባ የለውጥ ኃይሎች ያስፈልጋሉ፡፡ እንደምሳሌ፡- ያልተወከሉ አገራት እና መንግስታት ድርጅት (ዩኒፒኦ) ለፀረ ግድያ አቋም ቁርጠኛ የሆኑ እና ዩናይትድ ኔሽንስን ላይ ተፅእኖ ለማድረግ የሚሰሩ ግለሰቦች፣ መንግስታት እና (የጋራ የሰብአዊ መብቶች እውቅና የሚሰጡ) የተለያዩ አቋማት ናቸው፡፡ አምነስቲ አለም አቀፍ ድርጅት፣ ግሪን ፒስ እና የኢንተርናሽናል ፌሎሽፕ ኦፍ

ሪኮንሲሊየሽን ደግሞ ሌሎች ምሳሌዎች ይሆናሉ፡፡ የግድያ አልባ ማህበራት ተሳታፊዎች በሁሉም አባላት በሚነሱ አቋሞች ላይ መስማማት አይጠበቅባቸውም ፤ነገር ግን ግድያን ከአለም አቀፍ ሁኔታዎች ማስወገድ ላይ ብቻ ይኖርባቸዋል፡፡ እንደዚህ አይነት ማህበር ውስጣቸው አድገው እና እየጠበበ በሚሄደው ግድያ ቀጠናዎች ውስጥና ዙሪያ እና ዋና ችግር ፈቺ ቦታዎች፣ ኢኮኖሚ፣ ሰብአዊ መብት፣ አካባቢ እና ማህበራት ውስጥ ማደግ አለባቸው፡፡ በመጨረሻም አቅም ያለው አለም አቀፍ ዜጎች ማህበር፣ ለግድያ አልባ አለም፣ የወንዶች እና ሴቶች የጋራ አንድ አለም አቀፍ የደህንነት ኃይል ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

## ግድያ አልባ የማስልጠኛ ተቋማት

ኃይል መጠቀም ስለሚያመጣው ችግር ንቃት እያደገ ሲሄድና፣ ለገንቢ ግድያ አልባ አማራጮች ያለው ፍላጎት ሲጠነክር፣ ለግድያ አልባ አመራር ሙያ የፀብ ፈቺው እና ግድያ አልባ ማህበራዊ ለውጦች የስልጠና ፍላጎት አብሮ ያድጋል፡፡ የሙያው አስልጣኞች ከኪንግያን፣ ጋንዲያን፣ቡዲስት፣ ክርስቲያን እና እምነት አልባ ግድያ አልባ ባህሎች በተሻለ ተፈላጊነታቸው ጨምሯል፡፡ ፍላጎቶች፣ ከዜጎች የማህበራዊ ፍትህ ንቅናቄዎች እስከ የትምህርት ተቋማት፤ የስራ ቦታዎች፣ ፖሊስ እና እስር ቤቶች ድረስ ይደርሳል፡፡የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ለግድያ አልባ ዜጋ ሥልጠና ጋር የተያያዙ ልምድ እና የአሰልጣኞች ሥልጠና ለመስጠት ያስፈልጋሉ፡፡

## የግድያ አልባ አመራር ጥናት እና  ማገገምያ ማዕከላት

ተቋማት የሚያስፈልጉት የግድያ አልባ ድርጅቶች፣ መሪዎች እና ንቅናቄዎች ወደ ማገገምያ ነፀብራቅ ጽሑፎች እና የልምድ ልውውጦች ያሉበት ዘመን እንዲመጡ ነው፡፡ ብዙ ጊዜያት የእስር ሁኔታ ወይም ታሞ ሆስፒታል መግባት ሲኖርባቸው ብቻ ነው፡፡ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል እና የሚያስጨንቅ ግዴታ ውስጥ ያሉ መሪዎች፣ የግድያ አልባ ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት ቆም ብለው ማሰብ የሚጀምሩበት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ግድያ አልባ ተመጣጣኝ ሥራ ያስፈልጋል፡፡ መሪዎች ታስረው የአካል ጥቃት በሚደርስባቸው ከድብደባ ሰለባዎች የሚያገግሙበት ማዕከላት ጋር በትብብር መሥራት ያስፈልጋል፡፡ በዓለም ላይ ተሰራጭተው ስለሚገኙ የግድያ አልባ አመራር ማእከላት የመንፈስ እና የአካል መታደስ እድልን ይፈጥራሉ፡፡ የአውቶ-ባዮግራፊ ነፀብራቆች፣ እና የባዮግራፊ ጥናቶች፣ ልምዱ ካላቸውና ተመሳሳይ ኃላፊነት ውስጥ ካሉ የተለያየ አገር ሰዎች ጋር የሚደረጉ ንግግሮች፣ እንዲሁም የወደፊቱን የሚገመት እድሎችን ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ማእከላት ገለልተኛ ሆነው የሚሠሩ ተቋማት መሆን ይችላሉ ወይም በአሰናጋጅ ተቋሞች ሥር ሆነው ለግድያ አልባ ማህበራዊ ለውጥ ይተጋሉ፡፡

## የግድያ አልባ ፈጠራ ላይ ያተኮሩ ማዕከላት፣

የግድያ አልባ ፈጠራን በሥነ-ጥበብ ውስጥ ለማበረታታት ተቋሞች ያስፈልጋሉ፡፡ የስዊስ ፀሐፊው ሮማን ሮናልድ ከቶልስቶይ እንደሚጠቅሰው “ኪነ ጥበብ ብጥብጥን ማስቀረት አለበት፣ ምክንያቱም ጥበብ ብቻ ስለሆነ ይህን ማድረግ የሚችለው(ሮናልድ 1911፡203) የሼሊን ግጥም ውስጥ ብጥብጥ አልባነትን አርት ያንግ በሚያጠናበት ጊዜ የተናገረው ነገር አለ፡፡ ‹ብጥብጥ አልባነት ከፓለቲካ አመለካከት በላይ ነው፡፡ የግጥምና የህይወት አካል ነው፡፡› (1975፡165)

ሙዚቃን ለጦር መንፈስ መነቃቃት አስፈላጊነት እንደመሆኑ ሁሉ፣ የኪንግያን ባህል ደግሞ ሙዚቃ ከሌለ ንቅናቄ አይኖርም ይላል፡፡ (ያንግ 1996፡161-184) አንድ ተቋም ለሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች መፍጠር ከሚገባው እድሎች መካከል አንዱ፣ ሁሉንም የሥነ-ጥበብ ባለሞያዎች (አርቲስቶች) በአንድ ላይ ተሠባስበው ለውጥ ለማምማጣት የሚችልን ግድያ አልባ የሆነ ፈጠራን እንዲያወድሱ ማድረግ ነው፡፡ ግድያ አልባ ፈጠራ መሰናክሎቻቸውን ለመፍታት ከሚያነሳቸው  የጥበብ ዘርፎች መካከል የሥነ-ጽሑፍ፣ ሥነ ግጥም፣ ሥነ-ሥዕል፣ ቅርፃቅርፅ፣ ሙዚቃ፡ ውዝዋዜ፡ ቲያትር፣ ፊልም፣ ቴሌቪዥን፣

ፎቶግራፍ፣ ሥነ-ህንፃ፣ የአልባሳት ንድፍ ሙያ እና በተለያዬ የመገናኛ ብዙኀን የሚቀርቡ ንግድ ነክ የጥበብ ውጤቶች ይገኙበታል፡፡

ለሁሉም የሥነጥበብ ዘርፎች አካላዊም ሆነ ከመንፈሣዊ የኃይል ጥቃት የፀዳ መውጫ መንገድ ማግኘት አዳጋች ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- በሚገባ የሰለጠኑ እና፣ የግድያ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የታነፁ፣ ግድያ አልባ የግድያ ወንጀል ተከታታይ ባለሙያዎችን መፍጠር፣ እስከ አሁን ድረስ እየተሠራበት ያለውን ግድያ ከተፈፀመ በኋላ የሚደረግ የግድያ ወንጀልን የመከታተል ሂደት በመተካት ዋነኛው አማራጭ መንገድ ነው፡፡ በሥነ ጥበብ ዘርፎች ውስጥ የሚደረግ የተቀናጀ ግድያ አልባ ፈጠራ የሰው ልጆችን ተነሳሽነት እና አስተሳሰብ ከፍ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

ዓለም ዓቀፍ እውቅናን ከማግኘት አንፃርም፣ በሥነ ጥበብ ዘርፍ የግድያ አልባ ደጋፊዎች በዘርፍ አስተዋፅዖ ባበረከቱት ሁሉ፣ ከኖቤል ሽልማት ባልተናነሰ መልኩ ማበረታቻና ሽልማት ማዘጋጀትና ማበርከት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ግድያ አልባ ምርምር እና የፖሊሲ ትንተና ተቋማት፣

የግል ተቋማት መንግሥትን እና አጠቃላይ ማህበረሰቡን ከዓለም ዓቀፍ የደህንነት ፖሊሲ አንስቶ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በባህል ጉዳዮች ላይ ምክርን ለመስጠት እንደመቋቋማቸው ሁሉ የግድያ አልባ የፖሊሲ ተቋማትም በመረጃና በትንተና የታገዘ ድጋፍ በመስጠት ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ውሳኔዎች ለማስተላለፍ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነኚህ ተቋማት በግድያ አልባ የፓለቲካ ሳይንስ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙትን የግጭት፣ የኢኮኖሚ፡ የሰብአዊ መብቶች፡ የትብብር እና ሌሎች ንዑስ ዘርፎችን በማገዝ የግድያ አልባ የፖለቲካ ሳይንስ ዘርፍን የችግር ፈቺነት ኃላፊነትን በአግባቡ እንዲወጣ
ያግዛል፡፡

## የግድያ አለባ የግንኙት ሚያዎች፣

የግድያ አልባ የግንኙት ሚዲያዎች መረጃዎችን፣ ዜናዎችን፣ እና ዘገባዎችን በማስተላለፍ ማኅበረሰባዊና ግለሰባዊ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እገዛ ከማድረግ አንፃር እጅጉን አስፈላጊ ናቸው፡፡

ይህም ሲባል ግን ሚዲያው የሰው ልጅን ግድያን ለመፈፀም የሚኖረውን አቅም ከግምት ሳያስገባ የሚያልፍ አይነት ብቻ ሳይሆን፣ በተለምዶ ከምናያቸው ግድያን የማይቀር እና አስደሳች አስመስለው መልዕክት ከሚያስተላልፉ ሚዲያዎች በተለየ መልኩ የሚያይ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡ የግድያ አልባ ሚዲያ፣ የኤዲቶሪያል ውሳኔዎች፣ የግድያ አልባ የፖለቲካ ትንተና መሠረት ያደረጋቸውን ምክንያቶች በግልፅ ማሳየት መቻል ይኖርበታል፡፡ ይህም ሲባል፣ መልእክቶቹ የኃይል ጥቃትን፣ እውነታዎች በጥልቀት በመርመር፣ የግድያ አልባ እውነታዎችን ከግድያ እውነታዎች በተፃራሪ መልኩ የቆሙ መሆኑን ፍንትው አድርጐ በማሰየት፣ የለውጥ ሂደት ውጤቶችን እና ያጋጠሙ እንቅፋቶችን በመዘገብ፣ እንዲሁም ሁሉንም ግድያ አልባ የፈጠራ አሰተሳሰቦችን የሚያስተጋቡ የሥነ ጥበብ ዘርፎችን፣ ሳይንስን፣ በሰብአዊና ሙያዊ የቀን ተቀን ሂደቶችን ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚያሰይ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህ አቀራረብ በጥቅም ላይ ተመሥርቶ ከሚመራና አዕምሮን ነፃ ባልሆነ አስተሳሰብ ቀፍድዶ ከሚይዝ ሚዲያ የተለየ ነው፡፡ በጋዜጣና መፅሔቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ፣ በፊልሞች እነዲሁም በዓለም አቀፍ የኮምፒዩተር መረቦች ውስጥ የሚዲያ አማራጮች እንዲኖሩ ያስፈልጋል፡፡

## የግድያ አልባ መታሰቢያዎች (መዘከሪያዎች)

ግድያ አልባ የሆነ የሥልጣኔ ቅርስን ለማቆየት እንዲቻል ግለሰቦችን፣ ድርጅቶችን፣ ቡድኖችን፣ ያልታወቁ ጀግኖችን እና ታሪኮችን የሚዘክር መታሰቢያ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ መገንባት አለበት፡፡ መታሰቢያነቱም ግድያን እምቢ ብለው በፅናት በመቆም፣

ግድያ አልባ የሆነን መንገድ ተከትለው በመራመድ፣ ግድያ አልባ ለሆነ ዓለም አቀፋዊ ሥልጣኔ ታላቅ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ሁሉ ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ግን በአሁኑ ጊዜ ቆመው የሚገኙ ለጀግኖችና ለገዳዮች መታሰቢያነት የቆሙ ሀውልቶች እና መታሰቢያዎች ይወገዱ ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ነገር ግን ግድያ አልባ ሀውልቶች እና መታሰቢያዎች ግድያ አልባ አሰተሳሰብ አቀንቃኝ ለሆኑና እና፣ ግድያ አማራጮችን ለሰው ልጆች ደህንነት እና ቀጣይነት ያለው የኑሮ ሂደት እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ያሳዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወይም ግለሰቦች እንዳሉ ዘወትር እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡ በመታሰቢያዎቹ ልንዘክራቸው ከሚገባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል፣ የሃይማኖች ሰዎች፣ በኃይል ጥቃት ውስጥ ሆነው ስለዕውነት እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰማዕታት፣ የፀረ-ጦርነት አቋም አራማጆች፣ የሞት ቅጣት ተቃዋሚዎች፣ የሰላም ገጣሚዎችና ፀሐፊዎች፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው ተቃዋሚዎች፣ እራሳቸውን ለእስር ለእንግልትና ለሞት አሳልፈው በመስጠት አመፅን በአስወገደ መልኩ የፍትሕ እጦትን (ኢ-ፍትሐዊነትን) በጽናት የታገሉ ወንዶችና ሴቶች ይገኙበታል፡፡

## ግዳያ አልባ የሠላም ቀጠናዎች

የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት የግድያ አልባ የሠላም ቀጠናዎች ሲሆኑ፣ ከገጠርና ከተማ አቀፍ ማኅበረሰበአዊ ድርጅቶች አንስቶ፣ ሀገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ስምምነቶችን ጭምር ያጠቃልላል፡፡ ግንባርቀደም ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ፣ የሃይማኖት አምልኮ ሥፍራዎች፣ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሀብረተሰቦች፣ የሠላም ቀጠና እንዲሆኑ የታወጁ መንደሮች፣ የተኩስ አቁም ስምምነት የተደረገባቸው አካባቢዎች፣ ከጦር መሣሪያ ነፃ የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ማኅበረሰቦች፣ ዜጎች የመኖሪያ መንደራቸውን ከወንጀልና ከቡድን አመፅ ነፃ ለማድረግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ከኒኩሊየር መሣሪያዎች ነፃ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር የተደረጉ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ይገኙበታል፡፡ በነዚህ የተለያዩ የግድያ አልባ የሠላም ቀጠናዎች ውስጥ አጋዥ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ተቋማትን ማግኘት አለማቻል፣ ግድያ አልባ የሆኑ ተቋማትን ለመፍጠርና ለማሳደግ ለሚደረገው ጥረት ዋና መሰናክል ሆኖ ይጠቀሳል፡፡

## ግድያ አልባ የምጣኔ ሀብት (የኢኮኖሚ) ተቋማት

የጦርነትና የአመፅ አራማጅ ተቋማት ለአብዛኞቹ እጅግ ውድ ዋጋ የሚያስከፍል እንደሆነ ቢታወቅም፣ ለአንዳንዶች ግን ትርፍን ማጋበሻ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ግድያና አመፅን የሚያራምዱ ተቋማት ለአንዳንዶች ትርፋማ እንደሆኑ ከታወቀ ዘንዳ፣ ለሰው ልጅ ደህንነት የሚሠሩ ግድያ አልባ ተቋማት ደግሞ ሁሉም የበለጠ ትርፍን ማስገኘት ይችላሉ፡፡ ግድያ አልባ ከሚለው አመለካከት እና የግድያ አልባ የሆኑ የቁስ፣ የባህል፣ የአገልግሎትና የመዝናኛ ፍላጎቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መምጣት አኳያ፣ ለግድያ አልባ የንግድ ተቋማት የሚፈጠረው እድል ገደብ የሌለው ይሆናል፡፡ አማራጮችን ለይቶ ለማውጣት ያለው የመጀመሪያ መንገድን ለአመፅ ሥራ አገልግሎት በሚሠጡት ተቋማት ላይ ቆጠራ በማድረግ ለግድያ አልባ ሥራ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች ነቅሶ ማውጣት ይሆናል፡፡ እንደምሳሌ ለመዋቀስ ያህል የጦርነት አሻንጉሊቶች የሰላም አሸንጉሊቶችን ሊተኩ ይችላሉ፣ የጦርነት የጊዜው ጨዋታዎች አዝናኚና አስደሳች የሆኑ ፀረ ግድያ የቪዲዮ ጨዋታዎችን ሊተኩ ይችላሉ፣ የጦር ማምረቻ መሣሪያ ኢንዱስትሪዎች ሰላማዊ የቁሳቁስ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ሊተኩ እንደሚችሉ ሁሉ ግድያ አልባ የሆኑ ሚዲያዎች አስገራሚ ወደሆኑ የግድያ አልባ የሥነ ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች ያበረታታሉ፡፡ ጦርነትን በማስወገድና ጦርነት አልባ ቀጠናዎችን በመፍጠር፣ ግድያ አልባ የሆነ የኢኮኖሚ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ምሳሌ የሆኑ ተሞክሮዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ቀላል የኢኮኖሚ ለውጥን ከማምጣት በላይ ግን የሕብረተሰቡን እውነተኛ ፍላጐቶች ምን እንደሆኑ ጠንቅቆ ማወቅና ፍላጐታቸውንም ግድያን ባስወገደ መልኩ ለማርካት የሚያስችል አገልግሎት መፍጠር የግድያ አልባ አስተሳሰብ ዋና ዓላማ ሊሆን ይገባል፡፡

## ዓለም ዓቀፍ የግድያ አልባ ማዕከላት፣

ተቋማት ነገሮችን በጥቅሉ የማየት ምልከታን ለመቀየር ያላቸውን ብቃት የግድያ አልባ ዓለም እንደዋንኛ ራእይ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡ እነዚህ ተቋማት ግድያ አልባ የሆኑ ዓለም ዓቀፍ አስተሳሰቦችና ባህሎች ውስጥ ሥር ሰደው በመግባት በዓለም ዓቀፋዊ የሳይንስ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የክህሎትና ተቋማዊ ሀብቶች ውስጥ የሚደረጉትን የፈጠራ ሂደቶች የማፋጠን ብቃት ኖሯቸው የሰው ልጆችን አደገኛ ከሆነው አካሄድና ከመጥፎ ውጤቶቹ በማራቅ ወደግድያ አልባ መንገድ ሊወስዱት ይገባል፡፡

በዘመናዊ የኮምፒዩተር ሳይንስ አባባል፣ እነዚህን መሰል ማዕከላት ፈጠራን የሚያበረታቱ ግድያ አልባ ሶፍትዌሮች ሲባሉ፣ በመንግሥትና በሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት ለመታገዝም የኅብረተሰቡን ፍላጐት ያረካሉ፡፡ ውጤታማና ስኬታማ ለመሆንም እነዚህ ማዕከላት ከመንግሥትም ሆነ ከግለሰብ ተፅዓኖዎች በተቻለ መጠን ነፃ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ራዕይ ባላቸው በጎአድራጊዎች፣ በብዙኀኑ ተጠቃሚዎችና፣ በሌሎች ኃይሎች በመታገዝም ቀጣይነታቸው በበቂ ሁኔታ የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

አንድ ዓለም አቀፋዊ የግድያ አልባ መዕከል እንደዋና ግብ ሊወስደው የሚገባው ዋና ጉዳይ ፈጠራን ማበረታታት ይሆናል፡፡ ፈጠራን ከሚያበረታታባቸው ዘርፎች መካከልም ግድያ አልባነትና፣ የፍልስፍና ባህል፣ ሥነተፈጥሮና ግድያ አልባነት፣ ሥነፆታና ግድያ አልባነት፣ ምጣኔ ሀብትና ግድያ አልባነት፣ አካባቢ እና ግድያ አልባነት፣ ቴክኖሎጂና ግድያ አልባነት፣ ትምህርትና ግድያ አልባነት፣ ሥነጥበብና ግድያ አልባነት የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በሁሉም ሃሮችና አካባቢዎች የሚገኙትን ግድያ አልባ እምቅ የባህል ሃብቶች ላይ ቆጠራ ማድረግ ዋነኛው የግድያ አልባ አስተሳሰብ ታሪካዊ ሃላፊነት ነው፡፡ ይህም ሲባል ሃገር ተኮር በሆነ መልኩ፣ ግድያ አልባ እምቅ ሃብቶችን ፍለጋ በሁሉም ሃገራትና አካባቢዎች መደረግ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ የፍለጋው ሂደት ግድያ አልባ የሆኑ ታሪካዊ ልማዶችን፤ ወቅታዊ የሆኑ ክስተቶችንና፣ የወደፊት እይታዎችንና ግኝቶችን ከግምት ያስገባ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ሲመዘኑም ግኝቶቹ የሰው ልጆች የግድያ አልባነት አሰተሳሰብን ለማራመድ ፍላጎትና ብቃት እንዳላቸው ሊገልጹልን ይገባል ፡፡

አለም አቀፍ የግድያአልባ ተቋማት በአሁኑ ጊዜ በገሃዱ አለም የሚታዩትንና አለምአቀፋዊ ክስተት የሆኑትን ግድያዎች፤ የግድያ ማስፋራሪያዎችንና ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን የሚያሳይ በቂ የሆነ ጊዜ እና ቦታ ኖሮት፤ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ከግድያ አልባ ምልከታ በተጻራሪ የቆሙ መሆኑን በግልጽ ማሳየት አለባቸው፡፡የሰው ልጅን ደህንነት እና ቀጣይ ህይወት ከማስረገጥ አንጻርም፣ እነኚህ ማዕከላት የአደገኛ አካሄድን ያልተቋረጡ መሰናክሎችን በመጋፈጥ ሳይንሳዊ፤መንፈሳዊ፤ክህሎታዊ እና ተቁዋማዊ እምቅ ሃብቶችን አቀናጅቶ መጓዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አስፈላጊ የሆኑ ግድያ አልባ ተቋማት

ግድያ አልባ የሆነ ማህበረሰብን ለማየት ዋና ግቡ አድርጎ የተነሳ የፖለቲካ ሳይንስ፣ ተገቢ በሆኑ ተቁዋማት በመታገዝ ትምህርትና ፈጠራን ለማበርከት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ ተቋማት የሰው ልጅን ህይወት ክብር ከማረጋገጥ አንጻር እጅጉን ተፈላጊ ናቸው፡፡ አዳዲስ ነገሮችን ፈልጎ ለማግኘት ፤ለትብብር፤ቅንጅትን ለመፍጠር፤በእውቀት ልውውጥ፤ በፖሊሲ ውሳኔ ሰጪነት፤ ግድያ አልባ ለሆነ የጋራ ደህንነት፤ለኢኮኖሚ ደህንነት እና ህይወትን በሁሉም የሙያ እና የጥበብ ዘርፎች አስደሳች ለማድረግ ተቋማት አስፈላጊ ይሆናሉ፡፡

አለምአቀፋዊ ግድያአልባነትን የሚበረታቱ የተቀናጁ ተቋማትን ለመፍጠር የሚደረገው የሽግግር ጥሪ የሰው ልጆችን የግድያ አልባ ፍላጎት ከግምት ያስገባና ለፍላጎታቸውና ለግንዛቤያቸውም መልስ የሚሰጥ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡የግድያአልባ ተቋማት ጥንካሬ በውስጣቸው ካሉ እና ለጋራ ጥቅም ድጋፍ ከሚያደርጉ ግለሰቦች

ይመነጫል፡፡እያንዳንዱ ግለሰብና የፖለቲካ ሳይንቲስት እንደ አንድ የግድያአልባ ማዕከል በመሆን ግድያአልባ አለምን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረትና የሽግግር ሂደት ሊያመቻች እና ብሎም ሊያፋጥን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 6

## ያለመግደል ዓለም አቀፍ የስነ ፖለቲካ ሳይንስ

አዲስ ዘመን ላይ ነው ያለነው:: ስለዚህም አዳዲስ አስተሳሰቦች፣ አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች፣ አዳዲስ ጭብጦች ያስፈልጉናል... የቀደመው ዘመን መፍትሔዎች እና ብልሃቶች በቂ አይደሉም፡፡ ካለፈው ዘመን የአስተሳሰብ ጠፍር መላቀቅ አለብን::
ጄነራል ዳግላስ ማክአርተር

አንድ ሰው በታሪክ ውስጥ ያለውን የጥላቻ እና የጥፋት ሠንሠለት ለመበጠስ ይበቃል የሚል ስሜት እና ስልት (ስትራቴጂ) ሊኖረው ግድ ይላል::
ማረቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር

በተደጋጋሚ (በየጊዜው) ከማይቻለው በላይ ባይደርስ ኖሮ፣ የሰውልጅ የሚቻለው ላይ መድረስ ባልቻለ ነበር:: ታሪክ በተጨባጭ ይህንን እውነት ያረጋግጥልናል::
ማክስ ዌበር

በየቀኑ የትላንትና የማይቻሉ ክስተቶችን ዛሬ የሚቻሉ ሲሆኑ እየመሰከርን ነው::

ሞሀንዳስ ኬ ጋንዲ

### ከገዳይነት ነጻ ወደመውጣት

በመግደል ባርነት ስር ወድቀን ለዘላለም የምንኖርበት ጊዜ አብቅቶ፣ እንደ ችግር ተወስዶ መፍትሄ የሚበጅበት ጊዜ መጥቶአል:: ሆን ብሎ ሰውን አንድ በአንድ፣ ብዛት በብዛት እናም አብዛኛውን በመሳሪያ መግደል የሰው ዘርን የሚያጠፋበት ደረጃ ላይ ደርሶአል:: ነፃ ያወጣል፣ ይከላከላል፣ እንዲሁም ያበለጽጋል ተብሎ የሚጠበቀው ግድያ፣ የድህነት እናም የሰው ልጆች እና የፕላኔት ህልውና ስጋት ምንጭ ሆኑአል:: ክሬይግ ኮምስቶክ እንደሚለው የሰው ልጅ «ከመከላከል ፓቶሎጂ» ማለትም ለመከላከል የታሰበበት የራስ መጥፍያ ምንጭ በመሆኑ እየተሰቃየ ነው:: ለመከላከያ ተብለው በቤት ውስጥ ያሉ መሳሪያዎች (ጠመንጃዎች) የቤተሰብን አባል ይገድላሉ፣ ጠባቂዎች መሪዎቻቸውን ይገድላሉ፣ የስራዊት አባላት ያምጻሉ:: ህዝባቸውንም ያደሀያሉ:: የኒኩሊየር መሳሪዎች ፈጣሪያቸውንና ባለቤቶቻቸውን ስጋት ላይ ይጥላሉ:: ያለመግደል የነጻነት አዋጅ ውስጣችን እና በህብረተሰብ ውስጥ ከሚገኘው ጥፋት ያሰፈልጋል::

ፍላጎትን በጥቃት ለማሟላት የሚደረግ ሩጫ፣ ለስሌት የሚያስቸግሩትን የሰው ልጅ ትውልዶች ለደም መፋሰስ፣ የንብረት ግፈት፣ የስነልቦና ችግሮች ዳርጓል:: ባለፉት ሁለት ምዕተ አመታት የሰው ልጆች ተስፋ የፈረንሳይ አብዮት በተወላቸው -- ነጻነት እኩልነት እና ሰላም --- መርሆች ላይ የተቀረጸ ነበር:: ለነጻነት መግደል በአሜሪካን አብዩት ታሪክ ውስጥ ያለ ነው:: ለእኩልነት መግደልም በራሺያና በ ቻይና ታሪክ ውስጥ የሚገኝ ነገር ነው:: ለሰላምም መግደል፣ የሁለቱ ምዕተ አመታት የጦርነት የአብዮት እንዲሁም የጸረ ሽብር ዘመቻ ውርስ/ቅርስ ነው:: ከዚህ የምንማረው እውነተኛ ነፃነት፡ እኩልነት እና ሰላም መስፈንን ፣ የመግደል ታሪክን ካላስወገድን ማረጋገጥ አይቻልም:: በግፍ የተገደሉ (የተሰዉ) ሰዎች አስከሬኖች ክም ይህንን እንድንማር ድምፃቻን ያሰማሉ::

ይህም ማለት የዘመናችንን የዓለም የፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ፣ መግደል የማየቀር እናም ለሰው ልጆች ደህንነትም መልካም ነው የሚለውን አስተሳሰብ ወይም ይሁንታ፣ መፈተን ይሆናል:: በተጨማሪም፣ አንዱን እና ዋናውን ጥንታዊ አስተሳሰብ እና ጥበብን ፣ እነዲሁም ዘመናዊውን የፖለቲካ እምነት መጠየቅ እና መቀየር ማለት ነው:: ይህንንም በህክምና ሳይንስ ታሪክ ውስጥ ካለው ድንቅ «የመግል ቲዎሪ» ጋር ማመሳሰል ይቻላል:: ለአስራ ሰባት ምዕተ አመቶች በዘርፉ እጅግ በጣም ታዋቂ በነበረው የግሪክ ሀኪም ጋለን (130 ዓ.ም-200 ዓ.ም) በቁስል ዙሪያ የሚፈጠረው መግል ተፈጥሮዋዊ የጤንነት (የቁስሉ መዳን) መንገድ ነው የሚለው አስተምህሮ በስፋት ተቀባይነት ነበረው::ነገር ግን ፣ አንድ በ 1867 የሊስተር «የላንሴት ወረቀት» ወይም «በቀዶ ጥገና ትግበራ የአንቲሴፕቲክ መርሆች» የሚባለው ታዋቂ ስራ ለአንቲሴፕቲክ

መፈጠር እና ተቀባይነት መስፋፋት ምክንያት ሆናል:: ይህም ሲሆን ግን ያለምንም ውዝግብ አልነበረም:: ( አክርንሽት 1982: 77፤ጋሪሶን 1929 : 116፤589-90). መግደልም በተፈጥሮ እናም በፖለቲካ ተግባርም ውስጥ ጤናማ ነው የሚለው አስተሳሰብ የፖለቲካ ሳይንስ «ድንቅ የመግል ቲዎሪ» ነው::

የፖለቲካ ኃይልን ከነብዙሃን መገለጫዎቹ፣ ከቤተሰብ ህይወት እስከ ዓለም ጦርነት ለማጥናት፣ ህይወታቸውን በሙሉ የሰጡ የፖለቲካ ሳይንቲሰቶች ምሁራን፣ ስለመግደል ያለውን ይሁንታ በከፍተኛ ሁኔታ ካልተገዳደሩት ለምንድን ነው የዓለም የፖለቲካ መሪዎች እና ዜጎች ይህንን እንዲያደርጉ የምንጠብቀው? ነገር ግን በታሪክ ውስጥ በይበልጥም ባለንበት ዘመን ነፃነትን፣ እኩልነትን፣ እና ሰላምን ባለመገደል መርሆ ለማረጋገጥ በግልጽ የሚፈልጉ መሪዎች እና ዜጎች በፖለቲካ ሳይንቲስቶች ሳይረዱ ብቅ ብለዋል:: አንድ ምሳሌ የሚሆነው በ1895 ውስጥ 7000 ሰላማዊ የዶከሆቦርስ አርሶአደሮች የራሺያን የሰራዊት ምልመላን በመቃወም የጦር መሳሪያዎችን አቃጥለዋል:: (ታራሶፍ 1995: 8-10) መግደልን በሚቀበል የፖለቲካ ሳይንስ እና መግደልን በማይቀበል የፖለቲካ ሳይንስ ጀማሪዎች መካከል በግልጽ የሚታይ ክፍተት አለ:: በሀያኛው ክፍለ ዘመን የነ ቶልስቶይ: ጋንዲ:አብዱል ጃፋር ካን: ማረቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር እና ፔትራ ኬሊይ ታሪክ በድፍረት ወደፊት ያራመዱ መሪዎች እንደነ ዳላይ ላማ:ኡነግ ሳን ሱ ኪዩ እና ዴስሞንድ ቱቱ ያሉ መሪዎች- ባልተዘመረላቸው ሴቶች እና ወንድ ጀግኖች በመነሳሳት እና በመደገፍ ያለመግደል የመምራት አገልግሎትን የሚቻል አድርገዋል- የወደፊቱን ጠንካራ ያለመግደል ፖለቲካ ፋናወጊ ሆነዋል::

የፖለቲካ ሳይንቲሰቶች ቀስበቀስ ብዙ በግለሰቦች፣ በህባዝባዊ እንቅስቃሴዎች መስዋትነት የተከፈለበትን ያለመግደልን ውጤት ጥቃትን ተቀብለው ከነበሩበት የይርጋ ሁኔታ -እንደ ጠንቃቃ የአምባገነን አገዛዝ ተጠቃሚዎች አመጽ እስኪያስወግዳቸው ድረስ ይከተላሉን? እናም የፖለቲካዊ ሳይንቲስቶች ያለመግደል ዴሞክራሲ ክብረ ባዕሎች ይቀላቀላሉን? ወይስ የፖለቲን ሳይንስ በህክምናው ሳይንስ እንደሚደረገው እራሱን ለመግደል ፓቶሎጂ ምርመራ ያቀርባል፣ እናም ለመድሃኒት ግኝት እና ህክምና ይህም ደግሞ መገደልን ከዓለም ህይወት ለማስወገድ ለሚፈልጉ ሁሉ ማጋራት ይቻላል::

## ያለመግደል ብቃቶች ህሳቤ

እዚህ የሚቀርበው ሀሳብ፣ የማይግደል ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ መፍጠር ይቻላል፣ እናም በፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ውስጥ እና የሳይንሱ የማህበረሰብ ሚና ላይ የሚደረጉ ለውጦች ይህንን መህበረሰብ ለመፍጠር ይረዳሉ ብዬ ነው:: እነዚህን ማህበረሰቦች ለመፍጠር እና አውን ለማድረግ በጥቂቱ ወደ ሰባት ምክንያቶች አሉ:: አብዛኛው የሰው ልጅ አይገልም፤ ጠንካራ የሆነ ያለመግደል እምቅ አቅም በሰው ልጆች መንፈሳዊ ውርስ ውስጥ አለ፤ ሳይንስ የሰው ልጆችን ያለመግደል ብቃትን ያሳያል እናም ይተነብያል፤የመሽጋገሪያ ያለመግደል ፖሊሲዎች ለምሳሌ የሞት ፍርድ መደምሰስ እና የውትድርና አገልግሎት ተቃውሞ፣ እውቅና በኃይል በተመሰረቱ ሀገራት እንኳን ሳይቀር ተቀባይነትን አግኝቶአል፤ባለመግደል መርሆ ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት አሉ:: በቅንጅት እነዚህም የማይገድል ማህበረሰብ የሚኖረውን ተግባር እኩሌታ ይዘት አላቸው፤ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት ያለመግደል ህዝባዊ ትግሎች ከመገደል አብዮታዊ ትግሎች በይበልጥ ጠንካራ አማራጭ መሆኑን ያሳያል:: ያለመግደል መነሳሳት እና ልምድ ስር፣ በዓለም ሁሉ በሚገኙ ታሪካዊ ባሕሎች ውስጥ ማግኘት ይቻላል:: በስተመጨረሻም ያለመግደል የሽግግር ቃል ኪዳን የሚያርፈው በማይገድሉ ግለሰቦች፣ ወንዶች እና ሴቶች፤ የሚታወቁ እና የማይታወቁ ምሳሌነት ነው: የነዚህ ግለሰቦች የጀግንነት ህይወት ያለመግደል እንደሚቻል ይመሰክራል::

## ለፖለቲካዊ ሳይንስ አስተያየቶች (ምልክታዎች)

በስነ ህይወትም ሆነ በሁኔታዎች፣ ሰዎች መግደልም አለመግደልም እንደሚችሉ የታወቀ ነው:: ነገር ግን አብዛኛው የሰው ልጆች ገዳዮች አይደሉም:: በተጨማሪም ባለመግደል መርሆ ላይ የተመሰረቱ ብዙ ማህበራዊ ተቋማት ተፈጥረዋል:: እነዚህም ተቍማት የማይገድል ማህበረሰብ ናሙናዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ከዚህ በላይ በዚህ ወቅት ያለውና ወደፊት ይመጣል ተብሎ ሊጠበቅ የሚችለው የሳይንስ እውቀት ልቀት (መላቅ) የመግደል መንስኤዎችን

የሚያስወግድ፤ ያለመግደል መንስኤዎችንና ምክንያቶችን የሚያጠናክር፣ እናም የማይገድሉ ማህበረሰቦችን ለመፍጠር የሚያስችል ሁኔታዎችን የሚፈጥር እውቀት እንደሚያመነጭ ተስፋ ሰጭ ነው። እነዚህን ነባራዊ ሁኔታዎች እየተመለከትን መግደልን ማምለጥ አይቻልም ብሎ መቀበል፣ ብሎም ለትምህርት ዘርፍ እና ለፖለቲካል ሳይንስ ማህበራዊ ሚና መሰረት አድርጎ መውሰድ፣ በትንሹም ቢሆን ችግር ያስከትላል። ስለዚህም «አደገኛው የፖለቲካ ሳይንስ ዘርፍ» ተብሎ ሊጠራ የሚችለውን የመገደልን ሁኔታዎች እና የሚኖረውንም ምልክታ ወይም ፋይዳ መፈተሽ ወይም መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። የፖለቲካ ሳይንስ ከሌሎች የትምህርት እና የሙያ ዘርፎች ጋር በመሆን ያለፈውን ያለመግደል ታሪክ ማደስ፤በአሁኑ ወቅትም ያለውን ያለመግደል ብቃት (ችሎታ) ማወቅ፣ ወደፊትም ሊኖር የሚችለውን ያለመግደል የታመቀ አቅም መገመት እናም ይህንን እውቀት በምርምር፤ በማስተማር ለማገልበት ከሌሎች ጋር መተባበር እናም ላለመግደል ማህበራዊ ለውጥ ህዝባዊ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።

